# ኤማሁስ

ቅጽ አንድ | ቁጥር ፩



“ ክርስቲያኖች ዛሬም
በኤማሁስ መንገድ ላይ ነን።

በኤማሁስ ፕሬስ

የክረምት እትም

፳፻፲፯ ዓ.ም

# ኤማሁስ

“ክርስቲያኖች ዛሬም በኤማሁስ መንገድ ላይ ነን ።”

ጆን ቤህር

ቅጽ 1 ፣ ቁጥር 1

የክረምት እትም

ኤማሁስ ፕሬስ

ሐምሌ ፣ 2017 ዓ.ም.

**© ኤማሁስ ፕሬስ**

**ሐምሌ ፣ 2017 ዓ.ም.**

**ኤማሁስ መጽሔት (ዲጂታል እትም)**

**ኤዲቶሪያል ዳይሬክተር**

ቀሲስ አባተ አሰፋ

**ዋና አዘጋጅ**

በርናባስ ሽፈራው

**የሽፋን ገጽ እና ግራፊክስ**

ኤፌሶን አድማሱ

**ቋንቋ እና ፊደል እርማት**

ኢዮብ ወንድወሰን

**የሥርጭት እና የማስታወቂያ ሥራ**

ብንያም ፈቃዱ

# ማውጫ


**1. የኤማሁስ መንገድ (እንደ መግቢያ)** **1**

ቀሲስ አሰፋ አባተ

**2. ሐሳቦች መዘዝ አላቸው** **9**

ኤርምያስ ከንዴ

**3. "ከፋትን እፈጥራለሁ"** **25**

ብንያም ፈቃዱ

**4. ባለጸግነትና እጦት** **36**

ፋኑኤል ተረፈ

**5. ስለ ሕይወት ትርጉም መታጣት** **48**

ዮሐንስ ሙሉጌታ

**6. እስኪ እንነጋገር** **59**

በርናባስ ሽፈራው

# ምስጋና

የኤማሁስን ገጽ (website) ለሠራልን ለሱራፌል ተፈሪ እና በራሳቸው ተነሣሽነት ገጹን የበለጠ አስውበው እና አሻሽለው ላዘጋጁልን ለአቅሌስያ ቴዎድሮስ እና ለሮቤል ሲሳይ ።

# የኤማሁስ መንገድ

## (እንደ መግቢያ)

**ቀሲስ አባተ አሰፋ**

† † †

ኤማሁስ ጌታ በተነሣባት ዕለት ከኢየሩሳሌም የተነሡ የሁለት መንገደኞች መዳረሻ መንደር ናት ። ሁለቱ መንገደኞች የጌታ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ። ከሁለቱ ደቀ መዛሙርት መሀከል ስሙ የተጠቀሰው የአንዱ ፣ የቀለዮጳ ብቻ ነው ። የሁለተኛው ስም አልተጠቀሰም ። በዚህም ምክንያት ስለ ሁለተኛው ደቀ መዝሙር ማንነት ሁለት የተለያዩ አስተያየቶች አሉ ። የመጀመሪያው ወንጌላውያን ራሳቸው ተሳታፊ የሆኑበትን ታሪክ ሲጽፉ ፥ የራሳቸውን ስም ያለመጥቀስ ልማድ ያላቸው መሆኑን መሠረት በማድረግ[1] ፥ ሁለተኛው ደቀ መዝሙር ራሱ ቅዱስ ሉቃስ ነው ይላል ። የእኛ ትርጓሜ ከዚህ ወገን ነው ። ሁለተኛው አስተያየት ደግሞ ፥ ከሰባዎቹ ደቀ መዛሙርት መሀከል አንዱ የሆነ ፥ ስምዖን የሚባል ሰው ነው የሚል ነው ። ቅዱስ ቄርሎስ በሉቃስ ወንጌል ትርጓሜው ይህን አስተያየት ገልጧል ።[2]

ወደ ይዘቱ ስንመጣ ፥ ታሪኩን ያነበበ ማንኛውም ሰው እንደሚገነዘበው ፥ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ወደ ኤማሁስ ያደረጉት ጉዞ ትኩረት የሚስቡ ብዙ ነገሮችን በውስጡ ይዟል ። ገና መንገድ እንደ ጀመሩ በስሜት የሚያወሩት አንድ የሚያስጨንቅ ጉዳይ ነበራቸው ። ወንጌላዊው “ስለሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ፣ ይመራመሩም ነበር” (ሉቃ. 24:14-15) ብሎ እንደሚነግረን ፥ እርስ በርሳቸው የሚያወሩት ይሆናል ብለው ፈጽመው ስላልጠበቁት ፥ ነገር ግን በዚያ ሰሞን ስለ ሆነው ነገር ነው ። የሚወዱትን መምህራቸውን የካህናት አለቆች ለሞት ፍርድ አሳልፈው ሲሰጡት ፥ የሞት ፍርድም ሲፈረድበት ፥ በፍርዱም መሠረት መስቀል ላይ ሲሞት ቆመው ተመለከቱ ። መምህራቸውን በእንደዚያ ዓይነት መልኩ እናጣዋለን ብለው ፈጽመው አላሰቡም ነበር ። ይህ ያዩት ነገር ሀዘን እና ድንጋጤ ላይ ጣላቸው ፥ ተስፋ የመቁረጥ እና ግራ የመጋባት ስሜትም ወረሳቸው ።

ይህን ስሜታቸውን በመንገድ የተቀላቀላቸው ሰው ለጠየቃቸው ጥያቄ ከሰጡት መልስ መረዳት ይቻላል ። መንገድ ላይ የተቀላቀላቸው ሰው “እንዲህ እየጠወለጉ” ፥ በጭንቀት እና በስሜት የሚያወሩት ስለምን እንደሆነ ይጠይቃቸዋል። የእነሱም መልስ ፥ “አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን ? በእነዚህ ቀናት በዚያ የሆነውን ነገር አታውቅምን ?” (ሉቃ.24:18) የሚል ነበር ። በዚያን ሰሞን በኢየሩሳሌም የሆነውን ነገር ያልሰማ ሰው ይኖራል ብለው ፈጽመው ስላላሰቡ ፥ የእንግዳው ጥያቄ በራሱ አስገርሟቸው ነበር ። አስከትለውም የመጠውለጋቸው ምክንያት የሆነውን ሁነት ፥ የካህናት አለቆች የናዝሬቱን ኢየሱስ ለሞት ፍርድ አንዴት አሳልፈው እንደሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነገሩት ። እነሱ እስራኤልን ይቤዠል ብለው ተስፋ አድርገው የነበረ ቢሆንም ፥ እሱ ግን ከሞተ ዛሬ ሦስተኛ ቀኑ እንደሆነ ነገሩት (ሉቃ. 24:20-21) ። ይህ ንግግራቸው የጌታ ሞት የፈጠረባቸውን ስሜት በሚገባ ያሳያል።

ይህ ብቻ አይደለም ፤ ደቀ መዛሙርቱ ዐርብ ዕለት ያዩት የጌታ ሞት ብቻ ሳይሆን በሦስተኛው ቀን የሰሙትም ነገር ግራ አጋብቷቸዋል ። ይህንም በመንገድ ለተቀላቀላቸው እንግዳ ሲነግሩት እናያለን ። “ደግሞም ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን ።” (ሉቃ. 24:22) ያስገረማቸው ሴቶቹ በመቃብር ቦታው አጋጠመን ያሉት ነገር ነው ። የጌታ ሥጋ በመቃብር አለመኖሩን ነገሯቸው ። ጴጥሮስ እና ዮሐንስም ወደ መቃብሩ ቦታ ቢሄዱ ፥ ሴቶቹ እንዳሉት ሆኖ አገኙት ። እነሱም ተመልሰው መጥተው ይህኑ

---

[1] ለምሳሌ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ጌታ መቃብር ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር እየሮጠ የሄደውን ደቀ መዝሙር “ሌላኛው ደቀ መዝሙር” ብሎ ነው ያለፈው። እሱ ራሱ መሆኑን አይነግረንም።

[2] “You must know that these two disciples belonged to the number of the seventy, and that Cleopas’s companion was Simon—not Peter or the one of Cana—but another Simon, of the seventy.” St. Cyril of Alexandria, “Sermon CLVI” *Commentary upon the Gospel according to St. Luke*, (Oxford University Press, 1859)

ሲናገሩ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እዚያው ነበሩ ። ነገር ግን ከሴቶቹም ሆነ ከጴጥሮስ እና ዮሐንስ ዜና 'ጌታ እንደተናገረው ተነሥቶ ሊሆን ይችላል' ብለው ፈጽመው አልጠረጠሩም ። ይልቁንም ሌላ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው የሆነባቸው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ነው ፥ ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ተለይተው ወደ ኤማሁስ ሲጓዙ የምናገኛቸው ።

ይህ የደቀ መዛሙርቱ ሁኔታ መልሰን ስለ እነሱ እንድናስብ እና አንዳንድ ጥያቄዎችን እንድናነሣ የሚያደርግ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ጋር የምንመለከተው ዐርብ ዕለት ባዩት ነገር የደረሰባቸውን መሪር ሀዘን ብቻ አይደለም ። የጌታ ሞት በራሱ ያልጠበቁት ነበር ። ሥጋው ከመቃብር መሠወሩ ደግሞ የበለጠ እንግዳ ነገር ነበር የሆነባቸው ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ገና አብሯቸው ሳለ ስለሞቱ እና ስለ ትንሣኤው ደጋግሞ የነገራቸውን ነገር እንዴት ጨርሰው ረሱት?

ቃል በቃል ሲናገሩ እንደሰማናቸው ፥ መምህራቸው ላይ አንድ ተስፋ ነበራቸው ፤ በወቅቱ ከነበረው የሮማውያን አገዛዝ ሀገራቸው እስራኤልን የሚቤዥበትን ቀን ሲጠባበቁ ነበር ። ይህን ሐሳብ ከየት አገኙት? በምን ምክንያት መምህራቸውን እሥራኤልን የሚቤዥ ነጻ አውጪ አድርገው ሊስሉት ቻሉ ? ይህን እንዲያስቡ ፍንጭ የሚሰጥ ምን ነገርስ ከእሱ አግኝተው ነበር ? እነዚህን ጥያቄዎች ይዘን ከጌታ ሞት በፊት ወደሆነው ወደ ሦስት ዓመቱ የደቀ መዛሙርቱ ጉዞ እንሂድ።

※ ※ ※

የጌታ ደቀ መዛሙርት የተጠሩት ድንገት የዕለት ተዕለት ሥራቸውን ከሚሠሩበት እንደሆነ ወንጌል ላይ ተጽፎ እናገኛለን ። አሳ ለማጥመድ ከወጡበት ፥ ቀረጥ ለመሰብሰብ ከተቀመጡበት ወዘተርፈ የተጠሩ ናቸው ። ምንም እንኳን የተጠሩበት ዓላማ አሳዎችን ሳይሆን "ሰዎችን ለማጥመድ" (ማቴ. 4:19) እንደሆነ ቢነገራቸውም ፥ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ከዚያ በፊት የተማሩት ይህ ነው የሚባል የሃይማኖት ትምህርት ግን አልነበራቸውም ። በወቅቱ በነበሩት ትምህርት ቤቶች ገብተው የመማር ዕድሉም አልነበራቸውም ።[3] መማር የጀመሩት ጌታን መከተል ከጀመሩ በኋላ ነው።

[3] እነሱ በነበሩበት ዘመን የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት የሚሰጥባቸው ዝነኛ ትምህርት ቤቶች እና መምህራን ነበሩ። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ ተከታትሏል።

የተማሩበትም መንገድ ለየት ይላል። በወቅቱ የነበሩት የአይሁድ መምህራን በሚያስተምሩበት ፥ መጽሐፍ ተገልጦ ፥ መምህሩም ተቀምጦ የመጽሐፉን ቃል ለተማሪዎቹ በሚተረጉምበት መንገድ ሳይሆን ፥ መምህራቸው በየሔደበት በመከተል ፥ ሲያደርጋቸው የነበሩትን ነገሮች በማየት ፥ የሚናገራቸውንም ነገሮች በመስማት ነበር ። ጌታ ያደረጋቸውን ታላላቅ ተአምራት እዚያው በአካል ተገኝተው አይተዋል ። አሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችን ሴት በልብሱ ዘርፍ ብቻ ሲፈውሳት ፥ የሞተችውን ብላቴና ጠርቶ ሲያስነሣት ፥ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ የአልጋ ቁራኛ የነበረውን መጻጉዕ አልጋውን ተሸክሞ እንዲሄድ ሲያደርገው አይተዋል ፤ በደዌ ሲሰቃዩ የነበሩ ፥ ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ብዙ ሰዎችን በሥልጣኑ ሲፈውሳቸው ፥ አጋንንትን ሲገሥፅ ፥ ባሕር እና ነፋሳትም ሲታዘዙለት ተመልክተዋል ። በኃይል እና በሥልጣን ተራራ ላይ ወጥቶ ያስተማረውን ትምህርትም ከእግሩ ሥር ሆነው አድምጠዋል። በምሳሌ ያስተማራቸውን ትምህርቶችም እንደዚሁ ሰምተዋል ። የተማሩት በዚህ መልኩ ነበር።

ጌታም ቢሆን የሚናገረውን እንዲሰሙ፣ የሚያደርገውን እንዲያዩ ሲተዋቸው እንጂ እስከ ወንጌሉ አጋማሽ ደረስ ካዩት እና ከሰሙት ሁሉ ምን እንደተረዱ ሲጠይቃቸው አንመለከትም ። ቂሣርያ የሚባል ቦታ ሲደርሱ ግን የመጀመሪያው ፈተና ቀረበላቸው ። ስለ ማንነቱ ምን እንድሚያስቡ ጠየቃቸው ። ቅዱስ ጴጥሮስም ፥ "አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ፥ ክርስቶስ ነህ ።" (ማቴ. 16:15) ብሎ መለሰለት ። ጌታም መልሶ ይህን የሰማዩ አባቴ እንጂ ሥጋና ደም አልገለጠልህም አለው ። ይህም ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን መልስ ከእግዚአብሔር ተገልጦለት ተናገረ እንጂ በቆይታው ካያቸው እና ከሰማቸው ነገሮች በመነሣት የመምህሩን ማንነት በዚያ መልኩ ለመግለጥ የሚያስችል መረዳት ላይ አለመድረሱን የሚያሳይ ነው ።

ይህ ሐቅ ፥ እዚሁ ምንባብ ላይ ፥ ጥቂት ወረድ ብሎ ይገለጣል ። ጌታ ቅዱስ ጴጥሮስን 'የሰማዩ አባቴ የገለጠልህ ይህ መልስ የቤተ ክርስቲያን የእምነት መሠረት ይሆናል ፤ ለአንተም የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ' ካለው በኋላ ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚወጣ ፥ በዚያም መከራን እንደሚቀበል ፣ እንደሚሞት ፣ በሦስተኛው ቀንም እንደሚነሣ ይነግራቸዋል ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ "ወደ እርሱ ወስዶ 'አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም' ብሎ ሊገሥፀው ጀመረ ።" (ማቴ. 16:22) ። ከላይ 'ቤተ ክርስቲያን የምትቆምበት

የእምነት መሠረት’ ተብሎ የተመሰገነ መልስ የመለሰው ፥ ቅዱስ ጴጥሮስ ፥ እልፍ ብሎ የቤተ ክርስቲያንን መመሥረት የሚቃረን ‘አይሁንብህ’ የሚል ቃል ተናገረ ። ይህ ጌታ እኔ ማነኝ ብሎ ለጠየቃቸው ጥያቄ ቅዱስ ጴጥሮስ የመለሰው መልስ ከእሱ አቅም እና መረዳት በላይ በሆነ ኃይል ተገልጦለት የተናገረው እንጂ ፥ እስከዚያ ድረስ ሲያያቸው እና ሲሰማቸው የነበሩት ነገሮች ለዚህ መረዳት እንዳላደረሱት በግልጥ የሚያሳይ ነው ።

በርግጥ ሁሉም ደቀ መዛሙርት በወቅቱ ከዚህ የተለየ ግንዛቤ አልነበራቸውም ። “አንተ ክርስቶስ ነህ” የሚለው የቅዱስ ጴጥሮስ መልስ ትርጉም ግልጥ የሚሆነው በጌታ ሞት እና ትንሣኤ ቢሆንም ፥ ቀደሞውኑ ሥጋና ደም ያልገለጠላቸው ይህ መልስ ወደ ሞት የሚያመራ መሆኑን ሲሰሙ “እጅግ አዘኑ” (ማቴ.17:23) ። ይህ እነሱ እንዲሆን የሚመኙት ነገር ጌታ ሊፈጽመው ከመጣው ነገር ጋር ምን ያህል ልዩነት እንደነበረው ያሳያል ። ገና ሙሉ መረዳት ላይ አልደረሱም ። በዚህም ምክንያት ጌታ ወደፊት የሚሆነውን ነገር በሂደት እያዩ እንዲቆዩ ብቻ ነው ያደረጋቸው ። ክርስቶስ እንደሆነ ለሌሎች እንዲነግሩ እንኳን አልፈቀደላቸውም (ማቴ. 16:20) ።

ጊዜው ሲደርስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ ። ወደ ኢየሩሳሌም የገቡባት ዕለት ለደቀ መዛሙርቱ ደስ የምታሰኝ ነበረች ። መምህራቸው በአህያ ተቀምጦ ፥ በእነሱ ታጅቦ ወደ ከተማይቱ ሲገባ ፥ በኢየሩሳሌም ያሉ ሰዎች የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በክብር ነበር የተቀበሉት ። ይህ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያስደስት እና መምህራቸው እንዲሆን ከሚመኙት ነገር ጋር የሚገጥም ነበር ።

ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ ጌታ በአይሁድ እጅ ተያዘ ። ከዚያች ከተያዘባት ሌሊት ጀምሮ በማግሥቱ እስከተሰቀለባት ሰዓት ድረስ መምህራቸው ብዙ መከራን ሲቀበል አዩ ። በመጨረሻም አስቀድሞ እንደነገራቸው ሲሰቀል ፣ ሲሞት ፣ ዕለቱንም ወደ መቃብር ሲወርድ እና መቃብሩ በታላቅ ድንጋይ ሲዘጋ በአካል ተገኝተው ተመለከቱ ።

ከዚህ በኋላ በአንድ በኩል የሚወዱትን መምህራቸውን በዚህ መልኩ በማጣታቸው አዝነው እና ደንግጠው ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በቁጣቸው ኢየሩሳሌምን ያሸበሯትን አይሁድን ፈርተው ፥ ግራ በመጋባት ፣ የሚይዙትና የሚጨብጡት ጠፍቷቸው በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ተቀምጠው ነበር ። እስከ ዕለተ እሑድ ማለዳ ድረስ በዚህ አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ነበር ፥ በማለዳ የጌታን ሥጋ ሽቱ ለመቀባት ወደ መቃብሩ ቦታ የሄዱት ሴቶች የሚያስገርም ዜና ይዘውላቸው የመጡት ። ሴቶቹ የጌታን ሥጋ በመቃብር እንዳጡት እና በዚያ ያገኟቸው መላእክት ግን በሕይወት መኖሩን እንዳበሠሯቸው ነገሯቸው ። ይህ ዜና ምንም እንኳን መምህራቸው በሕይወት ያለ መሆኑን የሚናገር ቢሆንም ፥ ደቀ መዛሙርቱ ግን ለዚህ ብሥራት ትኩረት አልሰጡትም ። ተነሥቷል ብለው ማሰብ አልቻሉም ። ይልቁንም ከሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሁኔታ እንደምንረዳው ፥ ዐርብ ዕለት በሆነው ነገር ተስፋ ቆርጠዋል ፤ የሴቶቹ ዜና ብሥራት ሳይሆን ሌላ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው የሆነባቸው ። ከዚያ በኋላ ይቀራል ብለው ያሰቡት ነገር ባለመኖሩ ፥ ኢየሩሳሌምን ለቀው ወጡ ።

ከዚህ አንድ የምንረዳው ነገር አለ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ሦስት ዓመት ሙሉ ከዋለበት እየዋሉ ፣ ካደረበት እያደሩ የተከተሉትን መምህራቸውን እውነተኛ ማንነት በአካል ከእሱ ጋር እስከነበሩባት የመጨረሻዋ ቅጽበት ድረስ አላወቁም ። የሆነውን ሁሉ አይተዋል ፤ ሰምተውማል ። ያዩት እና የሰሙት ነገር ግን ገና ግልጥ አልሆነላቸውም ። ጌታ እስከተነሣባት ዕለት ድረስ ባለው የደቀ መዛሙርቱ ሁኔታ የምንመለከተው ይህን ነው ። ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ወደ ኤማሁስ ባደረጉት ጉዞ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ የምናየውም ይህኑ ነው።

※ ※ ※

የሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጉዞ ሁለተኛው ምዕራፍ ፥ በመንገዳቸው አዲሱ እንግዳ ሲቀላቀላቸው ይጀምራል ። በመጀመሪያ ደቀ መዛሙርቱ በመንገዳቸው የተቀላቀላቸውን እንግዳ ማንነት አላውቁም ። ስለጠወለጉበት ምክንያት ሲጠይቃቸው ፥ የተፈጠረውን ነገር ባለማወቁ ተገርመው ፥ እንግዳ እንደሆነ ደመደሙ ። የሆነውንም ሁሉ ነገሩት ።

እንግዳ የመሰላቸው ሰው ግን ፥ የነገሩትን ከሰማ በኋላ ስለ ሆኑት ነገሮች ምሥጢር ይነግራቸው ጀመር ። የመምህራቸው ወደዚህ ዓለም መምጣት ፣ በአይሁድ እጅ መግባት ፣ መሞት እና ከሙታን መካከል ተለይቶ መነሣት አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ታስቦ የነበረ ሐሳብ መሆኑን እና የቅዱሳት መጻሕፍትም መልእክት ይኸው እንደሆነ እየተረጎመ አስተማራቸው ። ሲሆኑ ያዩአቸው ነገሮች በሙሉ የሚፈጸሙበት ጊዜ ሲጠበቅ የነበረ እና ጊዜው ደርሶ እነሱ ባሉበት ዘመን ፍጻሜ ያገኙ እንጂ ድንገት እንደ ክፉ አጋጣሚ የተከሰቱ

አለመሆናቸውን ከእንግዳው ተረዱ ። ይህን እየነገራቸውም ኤማሁስ ደረሱ ። ሊለያቸውም እንደሆነ ባዩ ጊዜ ወደ ቤታቸው እንዲገባ ፥ አብሯቸውም እንዲያድር ለመኑት ። እሱም አብሯቸው ገባ ። ማዕድ አቅርበው ሲበሉም ፥ ከማዕዱ ባርኮ ቢሰጣቸው ማንነቱን ዐወቁት ። ሞቱ ተስፋ ያስቆረጣቸው ፥ እንደተለያቸው ያሰቡት ፥ ለሦስት ዓመታት አብረውት የኖሩት የሚወዱት መምህራቸው ነው ።

እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባው ፥ መምህራቸውን አሁን ያወቁበት እና በፊት ያውቁበት የነበረበት መንገድ ፈጽሞ የተለያየ መሆኑን ነው ። በፊት ፥ በገሊላ ሳሉ የሚያውቁት መምህራቸው ሌላ ማንም ሰው ማድረግ የማይችላቸውን ነገሮች በሥልጣኑ ሲያደርግ የነበረ ብርቱ መምህር ነበር ። እነሱም በእሱ መምጣት በወቅቱ የሮማውያን ቅኝ ግዛት ተወግዶ ፥ የረከሰው ቤተ መቅደስ ወደ ቀደመ ክብሩ ተመልሶ ፥ ታላቋ የእሥራኤል መንግሥት የምትመሠረትበት ጊዜ እንደደረሰ ተስፋ አድሮባቸው ነበር ።

በነገራችን ላይ ፥ ይህ የሁለቱ ደቀ መዛሙርት ብቻ ሐሳብ አልነበረም ። ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች (ያዕቆብ እና ዮሐንስ) ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም እወጣለሁ ሲል ሰምተው ፥ በመንግሥቱ ሲቀመጥ አንዳቸውን በግራ አንዳቸውን በቀኝ እንዲያደርጋቸው የለመኑበትን ታሪክ እናስታውስ ። ያዕቆብ እና ዮሐንስ ኢየሩሳሌም ከደረሰ መንገሡ ስለማይቀር ፥ ቀድመን የበለጠውን ሥልጣን እንያዝ ብለው ያቀረቡት ጥያቄ ነው ። በጣም የሚገርመው ደግሞ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርትም በሁለቱ ወንድማማቾች የመቀደም ስሜት ተሰምቷቸው ተቆጥተው ነበር (ማቴ. 20፥20-24)። ይኼ "እሥራኤልን ይቤዣል ብለን ተስፋ አድርገነው ነበር ።" የሚለው የሁለቱ ደቀ መዛሙርት ንግግር በሁሉም ደቀ መዛሙርት ዘንድ የነበረውን ሥር የሰደደ ተስፋ የሚያሳይ ነው ። በገሊላ ሳሉ ደቀ መዛሙርቱ ለመምህራቸው የነበራቸው አመለካከት እንዲህ ያለውን ግንዛቤ መሠረት ያደረገ ነበር። የመጀመሪያው ዕውቀታቸው እንደዚህ ያለ ነበር።

በኤማሁስ ማዕዱን ባርኮ ከሰጣቸው በኋላ እሱን ያወቁበት መንገድ ግን ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነበር ። አብሯቸው የተቀመጠው በገሊላ አብሯቸው የነበረው መምህራቸው እንደሆነ ቢያውቁም ፥ በቀጥታ ወደ ቀደመ መረዳታቸው እንዳይመለሱ ግን መሀል ላይ የገባ ነገር ነበረ ። እሱም የዐርቡ ዕለት መስቀል ነው ። መምህራቸውንም ፣ ተስፋቸውንም ነጥቆ ፥ ተስፋ መቁረጥ እና ግራ መጋባት ላይ የጣላቸው የዐርቡ ዕለት መስቀል ። ስለዚህ በኤማሁስ መምህራቸውን ዳግመኛ ሲያገኙትም ፥ ከመስቀል በፊት ያገኙት እንደነበረ አይደለም ። ይህኛው መገናኘት ወደ ፍጹም ተስፋ መቁረጥ ያደረሳቸውን የመስቀል ሞት የተሻገረ መገናኘት ነው። ይህ መሻገር ወደ ቀደመው የገሊላ ትዝታቸው መመለስን የማይቻል ያደረገ ነበር ። የዐርቡን መስቀል እንዳልተፈጠረ አድርገው ሊረሱት አይችሉም ። ስለዚህ በኤማሁስ ሳሉ ማዕዱን ባርኮ ሲሰጣቸው አብሯቸው ያለው እነሱ ተስፋ እንዳደረጉት ሰዎችን ሳይሆን ሞትን ራሱን ድል አድርጎ የተነሣውን መምህራቸውን እንደሆነ አወቁ ። እስከዚያች ሰዓት ድረስ በዚህ መንገድ አላወቁትም ነበር ።

በመንገዳቸው ሁለተኛው ምዕራፍ ላይ የተገለጠላቸው ይህ እውነት ነው ። በመንገድ ላይ ሳሉ ሲነግራቸው የነበረውም ፥ ከበፊት ጀምሮ የነበረው የእግዚአብሔር ሐሳብ ፥ የቅዱሳት መጻሕፍትም መልእክት ስለዚህ እውነት ፥ በእነዚያ ቀናት በኢየሩሳሌም ስለ ተፈጸመው የመስቀል ላይ ሞቱ እና ሞትን ድል አድርጎ ስለመነሣቱ ፥ መሆኑን ነበር። ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ይህን ምሥጢር ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ገና እሱን መከተል እንደጀመሩ እንዲረዱት አልጠበቀም። ይልቁንም ነገሩ ባይገለጥላቸውም የሚሆነውን ሁሉ እየተመለከቱ ወደ መስቀሉ እንዲደርሱ አደረጋቸው ።

ያን ሁሉ ካዩ በኋላ በሞቱ ተስፋ ቆረጡ ። ትንሣኤውን ካዩ በኋላ ግን ፥ ሦስት ዓመት ሙሉ ሲያዩት ነገር ግን ሳያስተውሉት የቆዩት ነገር በሙሉ በዚህ አዲስ ብርሃን አማካይነት ወለል ብሎ ተገለጠላቸው ። በመንገድ ሳሉ የተረጎመላቸውም የመጻሕፍቱ ምሥጢርም ጌታ ከማዕዱ ቆርሶ በሰጣቸው ቅጽበት ተረዳቸው ። በመንገድ ሳሉ የመጻሕፍቱን ቃል ሲተረጉምላቸው ለምን ልባቸው ይቃጠልባቸው እንደ ነበርም ገባቸው። የመጻሕፍቱ ሰጪም ፥ ተርጓሚም ፥ ትርጓሜም ራሱ ከሞት የተነሣው መምህራቸው እንደሆነ አወቁ ። ከዚህ በኋላ የደቀ መዛሙርቱ ርዕዮት ፈጽሞ ተለወጠ ። ሁሉንም ነገር የሚመለከቱት በጌታ ሞት እና ትንሣኤ መነጽርነት ነው ። ከዚያ በኋላ የኖሩት ፣ ያስተማሩት ፣ የጻፉትም እና ያረፉትም በዚሁ መንገድ ነው ።

ዕውቁ የነገረ ሃይማኖት ሊቅ እንግሊዛዊ ጆን ቤህር ፥ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እንደ አዲስ የተፈጠሩባት ኤማሁስ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናት ይላል ። ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው የእግዚአብሔር ሐሳብ ሞትን ድል አድርጎ በተነሣው በልጁ የሚተረጎምባት ቦታ ናት ። በኤማሁስ መንገድ እንዳየነው ተርጓሚውም

ትርጉሙም እርሱ ራሱ ጌታ ነው ። ቤተ ክርስቲያን ከጥንት የነበረው የእግዚአብሔር ሐሳብ የሚተረጎምባት ብቻ ሳትሆን ፥ ተርጓሚው አምላክ ከምእመናን ጋር በኅብረት የሚኖርባትም ቦታ ናት ። ጆን ቤህር ቤተ ክርስቲያን በኤማሁስ መንገድ የተገለጡት የቅዱሳት መጻሕፍት ኃይል እና በማዕድ ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል የመሆን ምሥጢር የቀጠለባት በመሆኗ ፥ በእርሷ ውስጥ የምንኖር ሁሉ ዛሬም በኤማሁስ መንገድ ላይ ነን ይላል ።[4]

※ ※ ※

የኤማሁስ መገለጥ እና ብርሃን ያኔ የሆነ ብቻ ሳይሆን ዘወትር የሚሆን ነው ። ኤማሁስም ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል የምትርቅ መንደር ሳትሆን ፥ ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ናት ። በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬም የመጻሕፍት ምሥጢር ይገለጣል ፤ ጌታችን በምሴተ ሐሙስ ፥ ከዚያም በኤማሁስ ፥ እንዳደረገው ሥጋውን ቆርሶ ይሰጣል ።

ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከዚህ መገለጥ በኋላ ወዲያውኑ ተነሥተው ፥ የመንገዱ ድካምም ሆነ የቀኑ መምሸት ሳይበግራቸው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። የሆነውንም ሁሉ ለወንድሞቻቸው ነገሯቸው ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ጌታችን በተሰበሰቡበት ለሁሉም ተገለጠ ። ወደ ዓለምም ላካቸው ።

ይህ ተልዕኮ ለእነሱ በግል የተሰጠ ሳይሆን በእነርሱ በኩል ለሁሉም ክርስቲያኖች የተሰጠ ነው ። በኤማሁስ መንገድ የተጓዘ ፥ በኤማሁስ ማዕድም የተቀመጠ ሁሉ ፥ ልክ እንደ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በመንገዱ እና በማዕዱ ያየውን ሁሉ ለወንድሞቹ እንዲነግር ይላካል ።

ክርስቲያን ለመሆን በኤማሁስ መንገድ ላይ መሆን አለብን ። ቅዱሳት መጻሕፍትን ያለማቋረጥ በመመርመር እና በመረዳት መኖር አለብን ። ከኅብስቱ እና ከወይኑም መራቅ የለብንም ። ይህን በማድረግ ነውና ክርስቶስን ዘወትር የምናየው ። ከኤማሁስ ወደ ኢየሩሳሌም መሮጥም ሆነ ከኢየሩሳሌም ወደ ዓለም መላክ የሁላችንም ነው ። በካህናት እና በመምህራን የተወሰነ አይደለም ። በኤማሁስ የሆነው መገለጥ በኤማሁስ የሚቀር ሳይሆን ከኤማሁስ ባሻገር የሚታወጅ እንደሆነ ሁሉ ፥የእኛም ክርስትና ከቤተ ክርስቲያን አፀድ የሚሻገር እና በሁሉም የሕይወታችን ክፍሎች መገለጥ ያለበት ነው ። ሁላችንም ወደኤማሁስ የተጠራን ፥ ከኤማሁስም የተላክን ነን ።

የተገኘንበት ዘመን ፣ ቦታ እና ሁኔታ እንደመለያየቱ የምንላክበትም መንገድ ልዩ ልዩ ነው ። እኛም በዚህ ዘመን እና በዚህ ቦታ ራሳችንን በማግኘታችን ተልዕኳችን የሚይዘው ልዩ መልክ አለ ። እንደምንመለከተው ከሆነ ደግሞ ዘመናችን ያቀረበልን ፈተና እጅግ የተወሳሰበ እና የተደራረበ ነው ።

በአንድ በኩል ከረዥም ዘመን ጀምሮ ተሸክመናቸው የመጣናቸው ጉድለቶች አሉ ። ምንም እንኳን ክርስትና ለ1700 ያህል ዓመታት ሰፍኖባት በቆየች ሀገር ብንኖርም ፥ ክርስትናችንም ብዙውን የሕይወታችንን ክፍል ቢቃኝም ፥ ግን እንደ ክርስቲያን ማኅበር ብዙ በመካከላችን መሆን የነበረባቸው ነገሮች ሳይሆኑ ቆይተዋል ፤ ብዙ መሆን ያልነበረባቸው ነገሮችም ሆነዋል ። ኅብስቱና ወይኑ ሲባረክ እና ሲሰጥ ቢቆይም ፥ መቀበሉ ግን የሕፃናት ፣ የአረጋውያን እና በሞት አፋፍ ላይ ያሉ ሰዎች ብቻ ድርሻ እስክኪሆን ደረሰ ። ምንም እንኳን ሊቃውንቱ ነገረ ሃይማኖትን በቅዳሴ ፣ በሰዓታት ፣ በማኅሌት ፣ በቅኔ ፣ በትርጓሜ እና በሌሎችም መንገዶች አራቅቀው እና አስውበው ቢገልጡትም አለመታደል ሆኖ ምእመኑ ሊረዳው አልቻለም ። ስለዚህም በሊቃውንት እና በምእመናን መካከል ትልቅ ገደል ተፈጠረ ። ዳግመኛም ሊቃውንቱ በሕይወታቸውም ሆነ በስብከቶቻቸው ሕዝቡን ማስተማራቸው ባይቀርና ይህ አገልግሎታቸው ብዙ የሚታይ ፍሬ ቢያፈራም ፥ ከክርስትና ጋር የሚቃረኑ ልማዶች እና ዕሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ከክርስትና ጎን ለጎን መኖር ቀጠሉ ። ይህ ሁሉ እኛ ጋር ደርሷል ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ ፥ “ዘመናዊነት” የሚባለውን ክስተት ተከትሎ የመጣብን ፈተና አለ ። ሐተታው ይቅርና ፥ አስኳላ ከተጀመረ 50 ዓመት እንኳን ሳይሞላው በዚያ በኩል ያለፈው ትውልድ ወደ ክሕደት ገባ ። ኑፋቄም ተበራከተ ። ወደ ክሕደትም ወደ ኑፋቄም ያልገባው ደግሞ ስለኦርቶዶክሳዊነቱ ምንነት እና ይዘትም ይህ ነው የሚባል ዕውቀት ሳይኖረው ቀረ ። ኦርቶዶክሳዊነቱም የወላጆቹ ውርስ እና ውጫዊ መለያ ከመሆን ባለፈ ከሕይወቱ አቅጣጫ እና ግብ ጋር ግንኙነት የሌለው ሆነ ። እዚህ እውነታ ላይ የማይስማማ ያለ አይመስለኝም ። እንዲህ ላለው ትውልድ የኖረው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እና አገልግሎት ፈጽሞ እንግዳ ነገር ሆነ ። ቢያንስ በድሮው ዘመን የነበሩ ምእመናን ከሊቃውንቱ ጋር የስነ ልቡና አንድነት ነበራቸው ። የኛ ትውልድ ግን በሁሉም ረገድ ፈጽሞ የተነጠለ ሆነ ። ሊቃውንቱ በሚያውቁት ፣ በተማሩት መንገድ ያዩትን እና የሰሙትን እውነት ይመሰክራሉ ፤ ግን የሚሰማቸው የለም ።

[4] የመጽሔታችን መሪ ቃል ያድረግነውም ይህን የጆን ቤህርን አባባል ነው ።

የዚህ ዘመን ሰው ሊቃውንቱ የሚናገሩትን ቋንቋ ባለመናገሩ ለብቻው ሊወቀስ አይችልም ። ያላደገበትን እና ያልተማረውን ከየት ሊያመጣ ይችላል ። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ዘመናዊው ዓለም እና ትምህርት እርሱ የወጣበት ማኅበረ ሰብእ የማያውቃቸውን ብዙ ሐሳቦች ፣ ክሕደቶች ፣ ርኩሰቶች አስተዋውቆታል ። ለእነዚህ ሁሉ ከሊቃውንቱ መልስ ይሻል ። ነገር ግን ሊቃውንቱ ለእነዚህ ነገሮች ከእርሱ ይልቅ እንግዳ ናቸው ። እንደ ባቢሎን ሰዎች ሆነናል ።

እነዚህ ችግሮች የፈጠሯቸውን ክፍተቶች ለመሙላት ስንሞክር ደግሞ ሌሎች ፈተናዎችን ራሳችን ላይ እየጨመርን ነው ። ለምሳሌ አንዳንዶች እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት እንደ መፍትሔ ያቀረቡት "ዘመናዊ" የሚባለውን ነገር ሁሉ ትተን ቀድሞ ወደነበረው አኗኗር መመለስን ነው ። መመለስ ሲባል ደግሞ በጠቅላላው የአነዋወራችንን መርሕ ከአባቶች ጋር ማስተካከልን ሳይሆን ምንም ነገር ሳይቀየር በእያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል እነሱን ለመምሰል መጣጣርን ነው ። እንደተናገሩት መናገር ፣ እንደለበሱት መልበስ ፥ እንዳረሱት ማረስ ወዘተርፈ ። ይህ መልስ ብዙ ትልልቅ ነገሮችን ይስታል ። የመጀመሪያው አባቶቻችን ይኖሩ የነበረበት መንገድ ምንም እክል እንደሌለበት ማሰቡ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ "ዘመናዊው ዓለም" እኛ ስለተውነው እንደሚተወን ማሰቡ ነው ። ሦስተኛው "ዘመናዊው" ዓለም በብዙ ችግሮች የተተበተበ የመሆኑን ያህል በጎ ነገሮች ሊገኙበት መቻሉን ነው ። ከሁሉም በላይ ግን ክርስትና ዓለምን የመባረክ እና የመለወጥ እንጂ ከዓለም የመውጣት ጥሪ አለመሆኑን ነው ።

ሌሎች ደግሞ ሁለተኛ መፍትሔ ይዘው ቀረቡ ። ይኸውም ሁለቱን እውነታዎች የክርስትናውን እና "ዘመናዊውን" እንደማይገናኙ እና እንደማይጋጩ አስቦ ሁለቱንም ጎን ለጎን ለማስኼድ የሚሞክር ነው ። ይህ በመሠረቱ ሴኪዩላሪዝምን የተቀበለ አካሔድ ነው ። ክርስትናን መላ ሕይወታችንን የሚመለከት እና የሚመራ ሳይሆን በተወሰኑ ቦታዎች እና ሁኔታዎች ብቻ የምንተገብረው እና የምናከናውነው እንደሆነ አድርጎ ይረዳዋል ። ልክ ከሥራ ቦታው ሲወጣ ሥራውን ትቶ እንደሚወጣ ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን አፀድ ሲወጣም ክርስትናውን ትቶ ሌላ ሰው ለመሆን ይፈቅዳል ። ሕይወትን "ይህ 'ሃይማኖት' ነው ። ይህ 'ፖለቲካ' ነው ፥ 'ቢዝነስ' ነው ፥ ' ።" እያለ ይከፋፍላታል ። የኔታ ጋ ሲቀመጥ የኔታ ያሉትን ሁሉ ይቀበላል ። ፕሮፌሰር ጋ ሲኼድም እሳቸው ያሉትን ይቀበላል ። ሁለቱ የሚነግሩት ነገር የተቃረነ ቢሆንም እንኳን አይረበሽም ። "እንደ ሃይማኖት ፣ ይህ ነው ። እንደ ዓለም ደግሞ እንዲህ ነው ። " ብሎ ያልፈዋል ። በጠቅላላው ክርስትና የነገሮች ሁሉ መሠረት መሆኑን ይስታል ። አንድ እውነት ብቻ የመኖሩን እውነታ ይክዳል ።

ሦስተኛው መፍትሔ ደግሞ ሁለቱን ዓለሞች ለማቀራረብ ይሞክራል ። "ዘመናዊው" ትውልድ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጣ "ዘመናዊነቱን" እንዲተው ማስገደድ ስለማይቻል ፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ነገሮች "በማዘመን" ትውልዱን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሳብ ይጥራል ። ቤተ ክርስቲያን "ለዘመናዊነት" እንቅፋት እንደማትሆን በማስረዳት እና ይህም እንዳይሆን በመጣር ጉልበቱን ያጠፋል ። ስለዚህ ከጸሎት እና ከአምልኮ ሥርዓት ጀምሮ "ዘመናዊው" ማኅበረ ሰብእ የሚሳብበት እና የሚያስደስተው ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲፈጠር ይተጋል ። ከዚያም አልፎ ግን ትምህርትም ላይ በተቻለ መጠን ዘመናዊ መንገድ ከመጠቀም አልፎ ይዘቱንም ለዘመናዊው አእምሮ የሚስማማ ለማድረግ ይጥራል ። የዚህ መፍትሔ መዳረሻ በአጭሩ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ዘመናዊው ዓለም ከማምጣት ይልቅ ዘመናዊውን ዓለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይፈጥራል ። ዓለምን ለቤተ ክርስቲያን በማስገዛት ፋንታ ፣ ቤተ ክርስቲያንን ለዓለም ተገዢ ያደርጋታል ። ይህን በማድረግም ማንነቷን ፈጽሞ ያሳጣታል ።

ታላላቅ ችግሮች አሉብን ። እነዚህ ላይ ደግሞ የመፍትሔ ለምድ ለብሰው የመጡ ሌሎች ትልልቅ ችግሮች ተደርበውብናል ። ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች መግትሔ መሻት ይገባናል ። ያ ካልሆነ ግን አሁን በእጃችን ያሉትም መልካም ነገሮች በጊዜ ሂደት ትርጉም እና ጣዕም ማጣታቸው ፥ ምናልባትም ከእኛ ዘንድ ጨርሰው መጥፋታቸው አይቀሬ ነው ።

ሁኔታው ግራ የሚያጋባ እና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው ። መርሳት የሌለብን ግን የኤማሁስ መንገደኞችም መንገዳቸውን ሲጀምሩ በተመሳሳይ ፥ ይልቁንም ከዚህ በእጅጉ በከፋ ፥ ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ ነው ። ነገር ግን በኤማሁስ መንገድ ላይ ፥ በኤማሁስ ማዕድ ላይ ጥያቄዎቻቸው ተመለሱ ። እውነት ታየቻቸው ፤ ጥበብም ተገለጠችላቸው ። እኛም በዘመናችን ይህኑ ነው ማድረግ ያለብን ።

በሐዋርያት በኩል ከራሱ ከጌታችን ያገኘነውን እውነት መሠረት ማድረግ አለብን ። ይኸውም ብቸኛው እውነታ እርሱ መሆኑን ነው ። ከእርሱ የተቃረነም ነገር ሊኖር አለመቻሉን ነው ። ይህን መሠረት አድርገን ዘመናችን የሚያቀርብልንን ፈተናዎች ሁሉ በታማኝነት መጋፈጥ ይገባናል ።

ታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ላይ የምናስተውለው አንድ ነገር ቢኖር ምን ያሕል በጊዜያቸው ገናና ከነበሩት ሐሳቦች ጋር ጥልቅ ትውውቅ የነበራቸው መሆኑ ነው ። ይህ ጥልቅ መረዳታቸው ነው ከሐዋርያት ያገኙትን እውነት በጊዜያቸው ለኖሩት ሰዎች ተርጉመው እንዲያስተምሩና ለቤተ ክርስቲያን ዐይኖች እንዲሆኑ ያስቻላቸው ።

እኛም የእነሱን ፈለግ መከተል አለብን ። እነሱ እንዳደረጉት ሕይወታችንን በሙሉ በቤተ ክርስቲያን ማድረግ አለብን ። ከትምህርቷ እና ከምሥጢራቷ ሙላት ያለማቋረጥ መቋደስ አለብን ። ልክ እነሱ ይቀድሱት ዘንድ ዘመናቸውን በደንብ እንደመረመሩት እና እንዳወቁት ፥ እኛም ይህኑ ማድረግ አለብን ።

ከላይ እንዳየነው በብዙ ረገድ መገኘት ከነበረብን ቦታ ርቀን ነው ያለነው ። በጥቂት ሰዎች ፥ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሚሠራ ሥራ አይደለም ያለብን ። ቀድሞም ሥራው ለጥቂቶች ብቻ አልተሠጠም ። ስለዚህ ሁላችንም ሕይወታችንን የቤተ ክርስቲያን እውነታ ላይ ለመመሥረት እና ዓለሙን እና ዘመኑን ከዚህ እውነት አንጻር ለመረዳት እና በዚህ እውነት ለማጥመቅ ማጣጣር አለብን ።

ይህን ለማድረግ ደግሞ የኤማሁስ መንገደኞች በመንገዳቸው መጀመሪያ እንዳደረጉት መጠየቅ ፥ መነጋገር መጀመር አለብን ። የኤማሁስ መንገደኞች ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ከሌሎቹ ሐዋርያት ጋር እንዳደረጉት ሁሉ ፥ ዛሬም በክርስቲያኖች መካከል የሚደረግ ተዋሥኦ ያስፈልገናል ። ዳግመኛም ሐዋርያት ከኢየሩሳሌም ወጥተው በመላው ዓለም እንዳደረጉት ሁሉ ፥ ክርስቲያኖች ከተቀረው ዓለም ጋር ተዋሥኦ ልናደርግ ይገባናል ።

※ ※ ※

የዘመናችን ተዋሥኦ በይዘቱም ሆነ በመንገዶቹ በግልብነት በእጅጉ የተጠቃ ነው ። 'በይዘቱ እንዴት ?'ቢባል ሁነቶች ላይ ያተኮረ እና ወቅታዊነትን ማዕከል ያደረገ በመሆኑ ። አንድም አቋም ከመያዝና ጎራ ከፍሎ ከመናቆር ባለፈ የእውነት የመማር እና የማሰላሰል ጉጉት የማይታይበት በመሆኑ ። በዚህ ተዋሥኦ ውስጥ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ማንሣት እና ከሁነቶቹ የሚሻገር እና ሐሳባዊ የሆነ ትንተና ለማካሔድ መሞከር ትኩረት ያስነሣል ፤ ሲብስም አጉል እንደመራቀቅ ይታያል ።

የሚካሄድበት ከባቢ እና ዘመን ደግሞ ሌላ ግልብነት ደርቦለታል ። በእኛ ሀገር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሀገራት ፣ ከዘመናዊነትና ከቴክኖሎጂ መራቀቅ ጋር ተያይዞ ሕዝባዊ ተዋሥኦ በጠቅላላው ስለቱን እና ርቀቱን እንዲያጣ ሆኗል ። የሚነበብም ሆነ የሚታይ ወይም የሚደመጥ ነገር አጭር መሆን አለበት ። ነገር ግን ጠቃሚና ወሳኝ ርእሶች እንዲህ ባለ መንገድ ሊስተናገዱ አይችሉም ። የሚያጠግብ ፍሬ ከሌለበት የተመልካቹ እና የአንባቢው ብዛት ምን ጥቅም ይኖረዋል ?

እንዲህ ባለው ከባቢ ውስጥ ሁነቶችን ከሁነትነታቸው እና ከሚያመጡት ወቅታዊ ውጤት በተሻገረ መልኩ ለመመልከት እንቸገራለን ። ቀድሞውኑም (እይታችን ከመጥበቡ የተነሣ) ጠባብ አድርገን የቀረጽነውን አጀንዳ በምንገልጽበት መንገድ የበለጠ እናጠብበዋለን ።

ነገር ግን ሁነቶችን እና ሒደቶችን ከመሠረታቸው መመርመራችን እና የምናቀርባቸው መፍትሔዎችም እንዲሁ የማይናወጥ መሠረት ያላቸው መሆናቸው አስፈላጊ ከሆነ ተዋሥኦውም እንዲሁ የጠለቀ እና የረቀቀ መሆን አለበት ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ጊዜ ወስዶ ማሰብ ፣ ማንበብ ፣ ማጠናቀር ፣ መወያየት ፣ መሟገት እና እንዲህ ካለው ሒደት የሚወጡትን ሐሳቦች የሚገባውን ጊዜ ወስዶ መጻፍ እና መናገር የግድ ነው ።

በተለይ የጽሑፎች አስፈላጊነት ደግሞ የተለየ ነው ። ጽሑፍ ከሌሎች ሐሳብን ማቅረቢያ አማራጮች ይልቅ ንጥር የሆኑ ሐሳቦች የሚገኙበት መንገድ ነው ። ጸሐፊው ሐሳቡን ለመግለጽ በአንድ ጊዜና ቦታ ሳይወሰን ፣ ደጋግሞ አስቦ ፣ ደጋግሞ ሞክሮ እስኪዋጣለት እና በበቂ መጠን ለማለት የፈለግሁትን ገልጫለሁ ብሎ እስኪያስብ ድረስ ሐሳቡን የሚያጠራበትን ዕድል የሚሰጥ ጎዳና ነው ። በመሆኑም መፍጠር ለምናልመው ተዋሥኦ ጽሑፍ የማይተካ ሚና አለው ። ያለ ጸሑፍ የሐሳቦች የማደግ አቅም የተወሰነ ነው ።

እንዲህ ያለውን ጽሑፋዊ ተዋሥኦ ለማድረግ ደግሞ እንዲህ ላሉ ጽሑፎች የተዘጋጀ መድረክ መኖር አለበት ። አሁን ያለው ከባቢ ግን ጽሑፍን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዘነጋ

እና እያገለለ ያለ ነው ። እንዲህ ያለው ጥልቅ እና ሰፊ ተዋሥኦ ቀርቶ ፥ ቀድሞ የነበረው ከወቅታዊ ጉዳዮች ያልዘለለ የጋዜጣ እና የመጽሔት ተዋሥኦ እንኳን ወደ መሞት ቀርቧል ።

ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወዳለው ሁኔታ ስንመጣ ደግሞ ፥ ከላይ እንዳወሣነው ፥ እንዲህ ያለ ደንበኛ ተዋሥኦ ካለመኖሩም በላይ ፥ አሉ የሚባሉትም ምእመናንን ያገለሉ እና ዘመኑ ካመጣቸው ማዕበሎች ጨርሶ የተፋቱ ናቸው ። ራሳቸውን ካገኙበት ቦታ በግትርነት ወደፊት ከመግፋት ባሻገር ፥ መሠረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ላለማንሣት እና የቆሙበትን ቦታ ተገቢነት ላለመፈተሽ የቀረጡ ናቸው ።

በመሆኑም እንዲህ ያለው የጽሑፍ ተዋሥኦ የሚጠነሰስበት እና የሚዳብርበት ፣ ክርስትናን መሠረት ያደረገ መድረክ እንደሚያስፈልግ በማመን ፥ ኤማሁስ ፕሬስ ፥ ይህቺን ኤማሁስ የተሰኘች ፥ በጊዜያዊነት በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ፣ ወደፊት ግን በሕትመትም ጭምር ፥ በየሦስት ወሩ ለሕዝብ የምትደርስ መጽሔት የመጀመሪያ እትም እነኋት ይላል ።

※ ※ ※

ኤማሁስ ‘መጽሔት’ ብትሰኝም ቅሉ ይዘቷ ለአካዳሚያዊ ጽሑፎች የሚቀርብ ይሆናል ። ከኤማሁስ ጀርባ ያለው ሐሳብ በትምህርቱ ዓለም (ቢያንስ በፊት) እንደሚደረገው ጥልቀት ያላቸው ጽሑፎችን ማስተናገድ ሲሆን ነገር ግን አሁን እየሆነ እንዳለው ከሕዝባዊው ተዋሥኦ ያልተነጠለ ፣ ይልቁንም በአንባቢነትም ሆነ በጸሐፊነት ለመሳተፍ ለሕዝቡ ክፍት የሆነ ተዋሥኦ መፍጠር ነው ። በመሆኑም ኤማሁስ ከተለመዱት መጽሔቶች በተለየ መልኩ ከሁነቶች ይልቅ መሠረታዊ ሐሳቦች ላይ ያተኮሩ ፥ ወቅታዊ ጉዳዮችን ያማከሉ ነገር ግን ፍልስፍናዊ ይዘት እና ውቅር ያላቸውን ጽሑፎች ታስተናግዳለች ። የጸሐፊውን ስሜቶች እና አስተያየቶች መገለጻቸውን የምትወድ ፥ ነገር ግን ምክንያታዊነት ያልተለያቸው እንዲሁም የፍልስፍና እና የሐቅ መሠረት ላይ የቆሙ መሆናቸውን የምትጠይቅ ፥ ይህም መሆኑ እንዲታወቅ እንደ ትምህርታዊ ጽሑፎች በማጣቀሻዎች መደገፋቸውን የምታስገድድ ፣ ጠባብ በሆኑ የገጽ ብዛት ክልከላዎች ሐሳቦች እንዳይገደቡ ሰፊ ነፃነት የምትሰጥ መድረክ ትሆናለች ።

ከዚህ ይዘቷ እና ውቅሯ የተነሣም ወደ ሕዝብ ለመድረስ ሦስት ወር ያህል በዝግጅት ትቆያለች ። የሚነሡትን ሐሳቦች ስፋትና ጥልቀት ለማስተናገድ ስትል ሆዷን ታሰፋለች ፤ መለስ ያለ መጽሐፍ አክላ ትመጣለች ።

ለዚህ መድረክ የሚመጥኑ ጽሑፎችን ማዘጋጀት በእጅጉ አድካሚ ከመሆኑ የተነሣ ቢያንስ እስከ ጊዜው ድረስ የኤማሁስ አባላት በዋናነት የጸሐፊነት ሚናን መወጣት ቢኖርባቸውም ፣ ተስፋው ግን ከላይ እንደተባለው መድረኩ ሕዝባዊ እንዲሆን እና ብዙዎች በጸሐፊነት እንዲሳተፉ ነው ። ብዙ ሰዎችን ብቻም ሳይሆን ፥ ብዙ ዓይነት ሐሳቦችንም የሚያሳትፍ ተዋሥኦ መሆን አለበት ። የስምምነት እና የመደጋገፍ ብቻ ሳይሆን የሙግትም መድረክ ነው ለመፍጠር የምናልመው ።

ከአባቶቻችን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ትምህርቷን እና ትውፊቷን የጠበቀችው እንዲህ ባለ ክርስቲያኖች እውነትን ፍለጋ በሚሟገቱበትም ተዋሥኦ ጭምር በመሆኑ እንዲህ ያለው ሙግት ለእኛ አዲስ ነገር ሳይሆን የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት የማስቀጠል ተግባር ነው ። ሌላው ቀርቶ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉ ሰዎች እንኳን ሊሞግቱን ቢወዱ በቀናነት ለማስተናገድ በራችን ክፍት ይሆናል ። የክርስቲያኖች እምነት ባለማወቅ የሚጠበቅ ሳይሆን ተፈትኖ ያለፈ እና የጠራ መሆን አለበት ። አንድም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለነውን ከማጽናት ባለፈ ሌሎችን ወደዚህ ኅብረት መጥራትም የተልዕኮአችን ዋና አካል ስለሆነ ፥ የተዋሥኦውን አድማስ በተቻለ መጠን ማስፋት አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን ። ስለዚህም እንዲህ ያለውን ጥልቅ እና እውነትን መዳረሻው ያደረገ ተዋሥኦ የሚሹትን ሁሉ በማንበብም ፣ በመጻፍም ይሳተፉ ዘንድ እንጋብዛለን ።

እነኋት ኤማሁስ ።

# ሐሳቦች መዘዝ አላቸው*

ኤርምያስ ክንዴ

† † †

ከጥቂት ዓመታት በፊት እኔ እና አንድ ወዳጄ ለትምህርት ወደ ምዕራቡ ዓለም ተጉዛ ከነበረች እና በወቅቱ ለእረፍት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ ከመጣች ጓደኛችን ጋር ተቀጣጥረን ተገናኘን ። ከዚያም በትምህርት ቤት ስለነበሩን ትዝታዎች ስናወጋ ፥ ሌሎች ጓደቻችንንም ስናነሣሣ ከቆየን በኋላ ፥ ባሕር ማዶ ደርሰው ለመጡ ወዳጆቻችን የማናስቀረውን ጥያቄ አቀረብንላት ። "ለክርስትና ባዕድ በሆነ ከባቢ ውስጥ ክርስቲያን ሆኖ መኖር አይከብድም ?" እዚህ ላይ በመወያየት ላይ ሳለን የሰዶማዊነት ነገር ተነሣ ። እኛ በበኩላችን ሰዶማዊነት ተገቢ የሕይወት መንገድ ተደርጎ በሚቆጠርበት ሀገር መኖርን እና እንዲህ ባለ ሕይወት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ማግኘትን እንደ ከባድ ፈተና እንደምናየው ገለጽን።

እርሷ የሰጠችን መልስ ግን እኛ ከጠበቅነው በእጅጉ የራቀ ነበር ። 'እነርሱ ሰዶማውያንም ቢሆኑ ቅኖች ፥ በጎዎች ናቸው ። እኛ አበሾች ደግሞ ምቀኞች ፣ ክፉዎች ወዘተ ነን ። ስለዚህም እነርሱን የመናገር የሞራል ልእልና የለንም ።' አለችን ። በመልሷ ግር ተሰኘሁ ። በአንድ በኩል ከጥቂት ዓመታት የውጭ ቆይታ የተነሣ በዚህች ወዳጄ ላይ ያየሁት የአስተሳሰብ ለውጥ ሲያስገርመኝ ፥ በሌላ በኩል ደግሞ 'ብዙዎች እንዲህ ባለው የአስተሳሰብ ለውጥ ውስጥ እያለፉ ከሆነ ነገአችን እንዴት ይሆናል' የሚል ሐሳብ ገባኝ ። ኢትዮጵያ ውስጥ ተወልዶ ያደገና በዕሴቶቿ የተቀረጸ ሰው እንዲህ ያለ ንጽጽር ውስጥ መግባቱ ከምንጩ በእጅጉ ርቆ መሄዱን ያሳያልና ።

ይህን አጋጣሚ ያነሣሁት በቅርብ ከምናውቃቸው ሰዎች ጀምሮ ብዙዎች እንዲህ ባለው የአስተሳሰብ ለውጥ ሂደት ውስጥ እያለፉ እንደሆነ እንድጠረጥር ፥ እንደ ማኅበረ ሰብዕም በውል ልብ ያልተባለ ሽግግር ውስጥ እየገባን እንደሆነ እንዳስብ ስላደረገኝ ነው ። ይህን ጽሑፍም ለመጻፍ የተነሣሁት እንዲህ ያለው አደገኛ የአስተሳሰብ ሽግግር መነሻዎች ምን እንደሆኑ መመርመር አስፈላጊ መሆኑን በማሰብ ነው ። ዓላማዬ ሰዶማዊነትም ሆነ ሌሎች በእኛ ዘንድ እጅግ የተነወሩ ነገር ግን በምዕራቡ ዓለም እንደመልካም የሚታዩ እና የገነኑ ድርጊቶች ለምን ነውር እና ኃጢአት እንደሆኑ ማተት አይደለም ። ይልቁንም እነዚህ ነውሮች እና ኃጢአቶች ለረዥም ዘመን ከቆዩበት የኃጢአትነት መዝገብ እንዲፋቁ የሆነበትን ሂደት ማብራራት ነው ።[1] በዋናነት እነዚህ ተግባራት በምዕራባዊው ዓለም ተቀባይነት እንዲያገኙ ፥ ከተቀባይነትም አልፎ የሚኮራባቸው የማንነት መገለጫዎች እና የሕይወት መንገዶች እንዲሆኑ ትልቅ ድርሻ ያበረከቱትን ሐሳቦች እና አሳቢዎች ነው ለማንሣት የምሞክረው ።

※ ※ ※

ሰዶማዊነት አዲስ ነገር ወይም አዲስ ክስተት አይደለም ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመርያ ክፍል ውስጥ የምናገኘው ነው እንጂ ። ኦሪት ዘፍጥረት ላይ ያለውን የሎጥን ታሪክ ባሰብን ቁጥር ሰዶማዊነትን ልንዘነጋው አይቻለንም ። እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ካወረዳቸው ከባድ መቅሰፍቶች አንዱ በሰዶምና በገሞራ ላይ የሆነው ነው ። የቁጣውን ጽናት የሚያሳየው ምንባብ እንዲህ ይላል ፤ "እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ እሳትና ዲን አዘነበ ፤ እነዚያንም ከተሞች በዙርያቸው ያሉትንም ሁሉ በከተሞቹ የሚኖሩትን ሁሉ ፥ የምድሩንም ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ ።" (ዘፍ 19÷25-26) ግብሩም ስያሜውን ያገኘው ከዚሁ ታሪክ በመነሣት ነው ።

በተጨማሪም በጥንታዊው የሮም ግዛት ውስጥ ሰዶማዊ ሥራ በተለያየ መንገድና ሁኔታ ይፈጸም ነበር ። በዕድሜና

---

* ይህን ርዕስ የተዋስሁት አሜሪካዊው የሮማ ካቶሊክ ጳጳስ ሮበርት ባሮን "ideas have consequences" ብለው ከሰጡት ገለጻ/ lecture ነው ። ሮበርት ባሮን ከአምስት አመታት በፊት የሰጡት ይህ አቅርቦት ፈላስፎቹ ማርክስ ፣ ኒቼ ፣ ሳርትና ሚሼል ፉኮ እንዴት ያለንበትን ዘመን እንደቀረጹ ግሩም አድርገው የተነተኑበት ነው ።

[1] ጽሑፌ የሚያተኩረው እዚህ ጉዳይ ላይ አይደለም ። ለምሳሌ ሰዶማዊነት ለምን ኃጢአት ሆነ? የሚል ጥያቄ ያለው ሰው የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ካህንና የነገረ መለኮት ምሁር የሆኑት ቶማስ ሆፕኮ Thomas Hopko, *Christian Faith and Same-Sex Attraction: Eastern Orthodox Reflections*, Second edition (Ancient Faith Publishing, 2015). በሚል ርዕስ ያሳተሙትን መጽሐፍ ያነብ ዘንድ እመክራለሁ ።

በተክለ ሰውነት ከፍ ያለ ወንድ (Erastes) ከእርሱ የሚያንስ ወጣት ወንድ (Eromenous) ላይ የሚያደርገው ሰዶማዊ ተግባር (pederasty)[2] ፥ በባሮች ላይ የሚፈጸም ሰዶማዊነት ፥ እንዲሁም ብዙ ሰዎች በጋራ የሚፈጽሙት ሰዶማዊነትን ያካተተ ነውር (orgy) በገዢዎቹም ሆነ በተራ ተርታው ነዋሪ ዘንድ የተለመዱ ነበሩ ።[3] በሴቶች መካከል ይፈጸሙ የነበሩ ሰዶማዊ ተግባራትም እንዲሁ አያሌ ነበሩ ።

ነገር ግን ፥ ምንም እንኳን በሰዶምና በገሞራም ሆነ በጥንታዊው የሮም ግዛት ውስጥ ሰዶማዊነት ከማኅበረሰቡ ጋር የተዋሐደ ሆኖ ብናገኘውም ፥ ላለፉት 2000 ዓመታት ግን በሮምም ሆነ በታሪክ በምናውቀው በአብዛኛው የዓለም ክፍል የተጠላ ሆኖ ቆይቷል ። በእርግጥ ቀድሞም ቢሆን 'ኋላ ቀር' ወይም 'ያልሠለጠኑ' በሚባሉ ማኅበረሰቦች ውስጥ ሰዶማዊነት ከተፈጥሮ የተጻረረ ተደርጎ የሚታይ ነበር ፤ አሁንም ነው ። አፍሪካን እንደ ምሳሌ ማንሣት ይቻላል ። ከቅኝ ግዛትም ሆነ ከክርስትና እና ከእስልምና መምጣት በፊት ለረዥም ዘመን በኖሩ እና አሁንም ከዚያው አነዋወር ባልወጡ ጎሳዎች ውስጥ ሰዶማዊነት እንግዳ እና ጸያፍ ነገር ነው ።

በጥንቱ ዓለምም ሆነ በዛሬው ዓለም ሰዶማዊነት "ሥልጣኔ" ከምንለው ሁነት ጋር የሚገናኝ ነው ። ሰዶምና ገሞራም በሎጥ ዘመን ፥ ሮምም በገናናነትዋ ዘመን የነበራቸውን "መሠልጠን" ተከትሎ ነበር ሰዶማዊነት ያበበው ። ታዲያ ሠለጠነ በሚባለው የሮም ግዛት ውስጥ የተለመደ የነበረውን ሰዶማዊነት ወደ ነውር እንዲለወጥ ያደረገው ክርስትና ነበር ። ክርስትና በግዛቱ ውስጥ መንሰራፋቱን ተከትሎ ሰዶማዊነትም ከጥንቶቹ አማልክት ጋር ተጠላ ።

ነገር ግን ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ፣ በምዕራቡ የዓለም ክፍል መልሶ ብቅ አለ ። ብቅ ማለትም ብቻ ሳይሆን ነውርነቱ ባይቀርም ግን እየቀነሰ ፣ እየቀነሰ ሄዶ ተቀባይነት ያለው የሕይወት መንገድ ወደመሆን ደረሰ ። ከዚያም በአጭር ጊዜ ውስጥ ቅቡል ከመሆንም አልፎ እንዲያውም የሚኮራበት እና የሚበረታታ ወደ መሆን አደገ ። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ልጆች በትምህርት ገበታቸው ላይ መደመርን እና መቀነስን እንደሚማሩት ሰዶማዊነትንም ይማሩታል ። ሐቀኛ እና ታማኝ መሆን እንዳለባቸው እንደሚመከሩት ሁሉ ሰዶማዊነትንም መጥላት እንደሌለባቸው ፥ ይልቁንም ዝንባሌው ካላቸው ነገሩን ከመለማመድ ወደ ኋላ ማለት እንደሌለባቸው ይመከራሉ ።

ቢያንስ በጥንታዊው የሮም ግዛት አንድ ሰው ሲርበው መብላቱ እንደማያስገርም ሁሉ የሥጋ ፍላጎቱን በዚህ መንገድ ማርካቱም ለማንም ባያስገርምም ፥ የሚሞገስበት ነገር ግን አልነበረም ። ወይም ፍሬ ከሚገኝበት ትዳር እኩል ተቆጥሮ እንደ መደበኛ ሕይወት የሚካሄድም ነገር አልነበረም ። ወይም አንድ ሰው ይህን ግብር ቢጠላ እና ራሱን ከዚህ ቢያርቅ ኋላ ቀር የሚያስብለው አልነበረም ፤ ምናልባት ራሱን ከዚህ ከሚገኘው ደስታ በመከልከሉ ሞኝ ተደርጎ ይቆጠር ይሆናል እንጂ ። በዘመናችን ግን "የሠለጠኑት" ሀገራት ከሚቆረቁራቸውና ከሚያሳስባቸው ነገሮች መካከል ዋነኛው ይህ ተግባር "ኋላ ቀር" በሆኑ ሰዎች እና ሀገራት ዘንድ መነወሩ እና እንዲህ ዓይነት ፍላጎት እና ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች "መጨቆናቸው" ነው ። ይህ በእነሱ ዐይን ሰብአዊነት ላይ የሚደረግ ወንጀል ነው ።

ታዲያ ሰዶማዊነት ለብዙ ዘመናት በክርስትና ተነውሮ ከኖረ በኋላ በእኛ ዘመን ከቀደመው በላቀ መልኩ በድል አድራጊነት "የሥልጣኔ" አካል ወደ መሆን እንዲመለስ ያስቻለው እንዲሁም ከመደረጉ ይልቅ መጠላቱ ነውር እስኪሆን ድረስ ያደረሰው ምን ይሆን ? በዚህ ጽሑፍ ለማስረዳት እንደምሞክረው እዚህ የተደረሰው እንደ እንግዳ ደራሽ አንደ ውሃ ፈሳሽ ያይደለ በዘመናት ሂደት ተኮትኩተው ፍሬ ባፈሩ ፍልስፍናዎች መሠረት ነው ። በሚከተሉት ገጾች ውስጥ የእነዚህን አስተሳሰቦችና ፍልስፍናዎች ምንነት እና ያለንበትን ዘመን እንዴት እንደቀረጹት በአጭሩ እዳስሳለሁ ።

※ ※ ※

ሐሳቦች ከአእምሮ ሰሌዳ ፥ ከልቡና ጓዳ ከፈለቁ በኋላ እንዲሁ ሐሳቦች ብቻ ሆነው አይቀሩም ። አንዴ በሰው ልብ ውስጥ ካደሩ ቢዘገይም ፍሬ ማፍራታቸው ፥ በንግግርም በድርጊትም መገለጣቸው አይቀርም ። በተለይ ክፉ ሐሳቦች ደግሞ በባሕርያቸው (በኋላ እንደምናየው በውስጣችን ያሉትን ክፉ ፍትወታት እና ዝንባሌዎች የሚጭሩ እና የሚያነዱ በመሆናቸው) ውለው ሲያድሩ

[2] Pederasty ወጣቱን ወንድ ወደ ጥሩ ጎልማሳነት የሚመራ መንገድ ተደርጎ ይታሰብ ነበር።

[3] Thomas K. Hubbard, ed., *Homosexuality in Greece and Rome: A Sourcebook of Basic Documents*, Nachdr., Joan Palevsky Imprint in Classical Literature (Univ. of California Press, 2008), 390 and 422.

አንዳች ክፉ መዘዝ ማምጣታቸው አይቀርም ። ‘ክፉ ሐሳቦች ምንድር ናቸው ?’ የተባለ እንደሆነ ከእግዚብሔር በመለየት ምክንያት የሚታሰቡ ሐሳቦች ናቸው።

አንድ ሰው ‘በትክክል እያሰበ ነው’ የሚባለው ለእግዚአብሔር ቅርብ በሆነበት መጠን ነው ። እውነተኛ ብርሃን እግዚአብሔር ነውና ፥ ከእርሱ የተለየ ሰው የትኛውንም ነገር አጥርቶ ማሰብና ማየት አይቻለውም ። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር በራቀበት መጠን ክፉ ሐሳቦችን የሚያመነጭ ፥ ቅርብ በሆነበት መጠን ደግሞ እውነታን መረዳትና ነገረ ህላዌን አጥርቶ ማየት የሚችል ይሆናል ። ከእግዚአብሔር በራቀ መጠን ደግሞ የተምታታ ፣ ከእውነት የተፋታ ወደ ጥፋት የሚመሩ ሐሳቦችን ያስባል ። ነገር ግን የተምታቱ ሆነውም ሳለ ከላይ እንዳልሁት የሰውን ልጅ ፍትወታት የሚያነቃቁ ስለሆኑ ሰዎችን መግዛት እና ማታለል ይሳካላቸዋል ። አሁን ያለንበት ምስቅልቅል ውስጥ እንድንገባ ያደረጉንን ሐሳቦች ያመነጯቸው እና የዘሯቸውም እግዚአብሔር አልባ የነበሩ ኢ-አማንያን ነበሩ ።

በርግጥ ይህ ኢ አማኒነት ራሱ ከተሳሳተ ነገረ መለኮታዊ አረዳድ የተወለደ ነው። በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዘንድ የነበሩ ምስቅልቅሎች እንዲሁም ከፕሮቴስታንቲዝም መምጣት በኋላ የመጡ ከጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን ትውፊትና ሥርዐት የማፈንገጥና ለጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ፈጽሞ ባዕድ የሆኑ ልምምዶች የዘመናችንን ኢ አማኒነት የወለዱ ማሕፀኖች ናቸው። ይህ የእግዚአብሔር አልባነት ፕሮጀክት ቢያንስ ዘመነ አብርሆት (age of enlightenment) ተብሎ ከሚጠራው ዘመን ጀምሮ ሊተነተን የሚችል ሥር ያለው ቢሆንም ነገር ግን ይህን “የአብርሆታዊውን” እሳቤ[4] መነሻዎች አሁን ወደደረስንበት አቅጣጫ እና ርቀት በመግፋት ረገድ እጅግ የጎላ ሚና ያላቸውን ጥቂት ፈላስፎች ብቻ ነው የማነሣው ። ነገር ግን የእነዚህንም ጥቂት ፈላስፎች መሠረታዊ ሐሳብ ከመግለጽ ባሻገር ሥራዎቻቸውን በዝርዝር ለማየት በዚህች አጭር መጣጥፍ የማይቻል ነው ።

ከፍሬድሪክ ኒቼ[5] ልነሣ ። ኒቼ ከላይ የጠቀስነውን ‘እውነታ አንጻራዊ ነው ።’ የሚለውን ሐሳብ በተለያየ መንገድ ከጻፉ ፈላስፎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ ነው። በዚህም ምክንያት የድኅረ ዘመናዊነት[6] አባት (The father of post-modernism) እየተባለ ይጠራል።[7] በተለይም የክርስትናን የመንፈሳዊነትና የግብረ-ገብ እሳቤ አጥብቆ በመተቸትና በማነወር ይታወቃል። ለምሳሌ ባልንጀራን መውደድን በተመለከተ እንዲህ ይላል።

> “ከባልንጀሮቻችሁ ጋር ትሰበሰባላችሁ ፥ መሰብሰባችሁንም በተዋቡ ቃላት ትጠሩታላችሁ ። እኔ ግን እላችኋለሁ ለባልንጀሮቻችሁ የምታሳዩት ፍቅር የደካማነታችሁ መገለጫ ነው ። ከራሳችሁ ሸሽታችሁ ወደ ባልጀሮቻችሁ ትሮጣላችሁ ፥ ወደ እርሱ መሄዳችሁንም ጽድቅ ልታደርጉት ትፈልጋላችሁ ። እኔ ግን ሰበባችሁን ዘልቁ ሸሽታችሁን አየዋለሁ ።”[8]

[4] ድኅረ ዘመናዊነት ሲነሣ ዘመነ አብርሆትን በመተቸት ነበር ። ፈላስፎቹም (ኒቼ ፣ ፉኮ ፣ ሳርት እንዲሁም ዴሪዳ) ምዕራባዊውን ሜታፊዚክስ ውድቅ በማድረግ ረገድ ዐቢይ ሚና የተጫወቱ ፈላስፎች ናቸው ። ነገር ግን የእነርሱም የአስተሳሰብ መዋቅር ቢሆን የዘመነ አብርሆትን ፍልስፍናዊ መነሻዎች የሚጋራ ነው ። ልዩነቱ በኋላ የመጡት ሰዎች እነዚህን መነሻዎች ወደሚስማሟቸው ድምዳሜዎች ለመግፋት የበለጠ ፈቃደኝነት ማሳየታቸው ነው ። የቀደሟቸውንም ሰዎች ወደእነዚህ ድምዳሜዎች ባለመድረሳቸው ይተቿቸዋል ። ይህ ግን ሰፊ ጉዳይ በመሆኑ እዚህ ጋ በዝርዝር አንሄድበትም።

[5] ከኒቼ ስጀምር በዘመናችን ላሉ ክፋቶች ሁሉ ጠንሳሽ እያደረግሁት አይደለም። ኒቼም የምዕራቡ ዓለም ነገረ መለኮታዊ ውድቀት ውላጅ ነው። “but in nietzche’s proclamation there seems to exist an unprecedented element of historical originality, and that is the deliberate challenge to historical self-conciousness of Europe. The consciousness of the European is metaphysical; it presupposes God as a conceptual ‘first cause’ of cosmology and as the axiomatic ‘principle’ of categorical morality. Consequently the proclamation of the ‘death of God’ was a denial of the premises of European self-consciousness, a conscious challenge to the irrationality of existence, and an undermining of the useful rationality of social life. Nietzsche was conscious that the death of God meant the ‘overthrow of all values’ ”Chrēstos Giannaras et al., *On the Absence and Unknowability of God: Heidegger and the Areopagite*, 2nd ed. (T & T Clark International, 2005), 40.

[6] Christopher Butler, *Postmodernism: A Very Short Introduction* (Oxford University Press, 2002), 21.

[7] simone de Beauvoir, *The Second Sex*, 1989 edition (n.d.), 267.

[8] “Ye crowd around your neighbor and have fine words for it. But I say unto you, your neighbor-love is your bad love for your selves. Ye flee unto your neighbor from yourselves, and would fain make a virtue thereof. But I fathom your unselfishness.”John Strickland, *The Age of Nihilism: Christendom from the Great War to the Culture Wars*, Paradise and

ኒቼ ራስን ለሌላው መስዋዕት በማድረግ ላይ የተመሠረተውን የፍቅር እሳቤ አይቀበልም። ይልቁንም ደጋግሞ ይተቸዋል ። እንደ ድክመትም ይመለከተዋል ። ሊኖር የሚገባው ብቸኛ ሕይወት "the will to power'' ነው ይላል ። ይህም "ፈቃድን" እስኪችሉ ድረስ መለማመድ እና በእውነታ ከመታጠር ይልቅ ነገሮችን የሚበይነውን ኃይል (power) ገንዘብ በማድረግ በራሳችን ፈቃድ እውነታን መበየን ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን የሚያደርጉ ሰዎችን ማመስገኑን ሲተች ደግሞ እንደዚህ ይላል።

> "ሰላምን (በሰላምነቷ ሳይሆን) ወደ አዳዲስ ጦርነቶች እንደምትወስድ መንገድ አድርጋችሁ ውደዷት ፤ ከረዘመውም ሰላም ይልቅ ያጠረውን ። እናንተ (ሰላም) ከሠናያት ሁሉ ትልቃለች ፤ ሌሎች ሠናያትም ሁሉ በእርሷ ይከብራሉ ትላላችሁ ። (እኔ ግን እላችኋለሁ) ጦርነት እና ወኔ ከርኅራኄ እና ከምጽዋት ይልቅ ታላላቅ ነገሮችን አድርገዋል ።"[9]

ኒቼ ለሌላው የሚደረግን ቸርነት (charity) ከድክመት ጋር ያስተካክለዋል ። ሰላም ፈላጊነትንም የደካሞች ብሎ ይኮንነዋል።ለዚያም ነው ጦርነት እና ወኔ ለሌላው በጎ ነገር ከማድረግ (charity) በላይ ታላላቅ ነገሮችን ሠርተዋል የሚለው ። ከላይ የተጠቀሱት ምንባባት ኒቼ ለክርስትና የነበረውን ጥላቻ የሚያሳዩ ናቸው ። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ያሉ ብዙ ምንባባት አሉ ።

ኒቼ የክርስትናን የእውነት እና የግብረ ገብነት መሠረትነትና ምንጭነትን ሲክድ ፣ በምትኩ (ምትክ ስል አቻ ወይንም ተስተካካይ ማለቴ ሳይሆን የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት የመሞከሩን ነገር ማንሣቴ ነው) ሌላ እሳቤ ይዞ መጥቷል ። ይኸውም የእውነታ አንጻራዊነት ነው ። በኒቼ መዝገበ ቃላት ውስጥ ይህ እሳቤ ፐርስፔክቲቪዝም (perspectivism) ተብሎ ይጠራል ። ፐርስፔክቲቪዝም በአጭሩ 'ወጥና ቋሚ እውነታ የሚባል ነገር የለም ፤ ሁላችንም ከየራሳችን አንጻር የምንበይነውና የምንረዳው እንጂ ።' ማለት ነው ።[10]

በምዕራቡም ሆነ በምሥራቁ ዓለም እግዚአብሔር የፍጹም እውነትና የፍጹም ግብረ ገብ መሠረት እንደሆነ ይታሰብ ነበር ። ከዘመነ አብርሆት በኋላ ግን ይህ መሠረት ጥያቄ ውስጥ ስለገባ ሁሉም ሰው የራሱን እውነታ ፈጥሮ መኖር እንደሚችል ይታመናል ።[11] ይህ ከኒቼ ጀምሮ በስፋት የሚቀነቀነው የእውነት አንጻራዊነት እሳቤ ከእርሱ በኋላ በመጡ ፈላስፎች ዘንድ ተስፋፍቶ የቀጠለ አስተሳሰብ ነው ። ነገር ግን በፈላስፎቹ ብቻ ተወስኖ አልቀረም ። ወደ ዕለት ተዕለት ንግግር እና ድርጊትም ዘለቀ እንጂ ። በየዕለቱ የምንሰማቸው አንድን ሐሳብ 'ከእገሌ አንጻር ስህተት ነው ፤ ከእገሌ አንጻር ግን ትክክል ነው ።' ወዘተ የሚሉ ንግግሮች የዚህ አስተሳሰብ ፍሬዎች ናቸው ።

ይህን የኒቼን ሐሳብ በአጭሩ እንተቸው ። 'ሁላችንንም የሚገዛ እውነት የለም ።' የሚለው ዐረፍተ ነገር በራሱ ሁላችንንም የሚገዛ ነውን ? ፍጹም እውነታ የለም የሚለው አስተሳሰብስ ፍጹም ነው ? ሁላችንንም የሚገዛ እውነታ አለመኖሩ የኒቼ ብቻ እውነታ ነው ወይስ ሁላችንንም የሚገዛ ነው ? ሁላችንንም የሚገዛን ነው ካልን እንዲያ በማለታችን ሐሳቡ ሐሰት ነው ማለታችን አይደለም ? አይ የኒቼ ብቻ እውነታ ነው ካልን ደግሞ ኒቼን ለምን እንቀበለዋለን ? በሁለቱም መንገድ ኒቼን ለመቀበል በቂ ምክንያት አይኖረንም ። ምክንያቱም ሐሳቡ በራሱ ትርጉም አልባ ስለሆነ ነው ።

የኒቼን የሐሳብ ፈለግ ከተከተሉ ፈላስፎች ውስጥ ቀጥለን ልንጠቅሰው የሚገባን ዦን ፖውል ሳርት (Jean Paul Sartre) የተባለውን ፈረንሳዊ ፈላስፋ ነው ። ሳርት ኤግዚስተንሺያሊዝም (Existentialism) ለሚባለው ፍልስፍና አባት ነው ። ይህ ፍልስፍና "existence precedes essence - ህልውና (ህላዌ) ምንነትን ይቀድማል" የሚል ነው ። ማለትም 'አንድ ሰው

Utopia: The Rise and Fall of What the West Once Was, volume 4 (Ancient Faith Publishing, 2022), 55.

[9] "Ye shall love peace as a means towards new wars – and the short peace more than the long. Ye say that it's a good cause which halloweth every cause. War and courage have done more great things than charity" Strickland, *The Age of Nihilism*, 50.

[10] Friedrich Nietzsche and Friedrich Nietzsche, *The Gay Science: With a Prelude in German Rhymes and an Appendix of Songs*, 3. print, ed. Bernard Williams, Cambridge Texts in the History of Philosophy (Cambridge University Press, 2004), 110–12.

[11] ይህንን ጉዳይ መተዋወቅ የሚፈልግ ሰው "The benedict option" በሚል ርእስ የተሰናዳውን መጽሐፍ ቢያነብ ብዙ ቁምነገር ያገኛል የሚል እምነት አለኝ።

*መጀመሪያ ህልው ነው ፤ ከዚያ በኋላ ምንነቱ ይከተላል ።'* የሚል ነው።

ሳርት የሰው ልጅ ራሱን በራሱ ከሚፈጥርበት የራሱ ብቻ የሆነ ፕሮጀክት ውጭ ምንም ነው ብሎ ያምናል ። ይህን ሐሳቡን "Existentialism is humanism" በሚለው መጽሐፉ በስፋት ያብራራዋል። መጽሐፉ የእግዚብሔርን ህልውና ፥ ተከትሎም የግብረ ገብና የእውነታ መሠረትነቱን የሚክደው የኒቼ ፍልስፍና ቅጥያ ነው ማለት ይቻላል ። እንደ ሳርት ከሆነ 'ሁሉም ሰው ራሱን ይሠራል ፣ በዚህም መሠረት ሁሉም ሰው ለራሱ ምርጫዎች እና ውሳኔዎች ኃላፊነት አለበት ።' ከራሱ አንደበት እንስማው።

> *"ሰው ራሱን ይሠራል እንጂ ወደ ዓለም ሲመጣ ጨርሶ ተሠርቶ አይመጣም ። ይልቁንም የራሱን ሥነ ምግባር በመምረጥ ራሱን ይሠራል ። ራሱን ከሚያገኝበት ሁኔታ (ራሱን ተፈጥሮ ወይም 'ሆኖ' ማግኘቱን ለመግለጽ ነው) አንጻር ደግሞ አንዳች ሥነ ምግባር (ግብረ ገብ) ያለመምረጥ ምርጫ የለውም ።"*[12]

እንደ ሳርት ከሆነ የሰው ልጅ የራሱን ግብረ ገብ ይመርጣል ፥ ያን ሲያደርግ ደግሞ የራሱን ማንነት ይገነባል ። ነገር ግን ፍጹም እውነታ የሌለ በመሆኑ የሚመርጠውን ምርጫ የሚዳኝበት መለኪያ (reference) የለውም ። በዚህ የአስተሳሰብ መዋቅር ውስጥ እውነትና ሐሰት ፣ መልካምና ክፉ ፣ ጥሩና መጥፎ ጨርሶ የሌለ በመሆኑ ምርጫው የሚመሠረተው በእርሱ ፍላጎት መሠረት ይሆናል ። ስለዚህ 'ጾታ ማህበራዊ ውቅር ነው' ብሎ ቢያምን ፣ 'ሰዶማዊነት ተገቢ የሕይወት መንገድ ነው' ቢል ፥ ሰዎችን ቢገድል ፥ ብዙ የዝሙት አጋሮች ቢኖሩት ፥ ራሱን ቢያጠፋ ወዘተርፈ ራሱ መርጦ እስካደረገው ድረስ ለምን ስህተት ይሆናል ? በዚህ የአስተሳሰብ መዋቅር ውስጥ ስህተት እና ትክክል የለም ። ያለው ድንገቴ (spontaneous) ምርጫ ብቻ ነው። ይህኑ ሐሳብ በሌላ ቦታ እንዲህ ሲል ያብራራዋል።

> *"ነገሮችን እንዳሉ መቀበል አለብን ። እኛ ዕሴትን እንፈጥራለን ማለትም ከዚህ የተለየ አይደለም ። ሕይወት በራሷ ምንም ትርጉም አልባ ናት ። እስከትኖር ድረስ ምንም አይደለችም ። እኛ ነን እንጂ ትርጉም የምንሰጣት ፤ ዕሴት ማለትም ይህ እኛ ለሕይወት የምንሰጣት (ምንም እንስጣት ምን) እንጂ ሌላ አይደለም ።"*[13]

ሕይወት ቀዳሚ ትርጉምም ዓላማም የየሌለው እና እኛ ትርጉም የምንሰጠው ከሆነ የትኛውንም ነገር ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ ከግለሰባዊ ፈቃድና ምርጫ ውጭ ሌላ ምክንያትም ሆነ ማመሳከሪያ ሊኖር አይችልም ። በዘመናችን ያለው የሰዶማዊነት ንቅናቄ ርእዮተ ዓለማዊ መሠረቱ የሚመዘዘው ከዚህ እሳቤ ነው ። ኒቼ እና ሳርት ያዳበሩት እና ከድኅረ ዘመናዊነት በኋላ በገሃድ ምዕራባዊው ዓለም ውስጥ ራሱን የገለጠው ፍልስፍና 'የሰው ልጅ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ፥ ክርስቶስን የመምሰል ጥሪ ያለው ግሩምና ድንቅ ፍጥረት ነው ።' የሚለውን ክርስቲያናዊ እሳቤ ከሰው ልጆች ልቡና በምልአት ለማጥፋት የሚጥር ነው ። ስለዚህም የሰው ልጅ የሚበላ ፣ የሚጠጣ ፣ የሚያሰላ ፣ የሚገድል ፣ ፍትወቱን የሚፈጽም ፥ እስከመጨረሻው ጥግ ሄዶ ስሜቶቹን ለማርካት የሚሻ (Hedonist) ፥ ሃይማኖትን ጨምሮ ሁሉንም ላዕላይ እሴቶች ለራሱ ፍላጎት ለማስገዛት የሚፈልግ ፥ ሁሉን ነገር የሚደነግገውና የሚወስነው በልቅ ስሜቶቹ (passions) መሠረት እንደሆነ የሚያስብ ፍጥረት ወደ መሆን ደርሷል።

ሳርት 'The second sex' የሚባል ታዋቂ መጽሐፍ የጻፈችው የሲሞን ዴ ቡቮ የፍቅር አጋር ነበር ። ዴ ቡቮ በዚህ መጽሐፏ የሳርትን ፍልስፍና መሠረት አድርጋ ጾታ ማህበራዊ ውቅር (social construct) እንደሆነና ምንም ዓይነት ሥነ ሕይወታዊና ተፈጥሯዊ መሠረት እንደሌለው ትናገራለች ።[14] ይህ አስተሳሰብ ዛሬ በየከርክሩ ፣

---

[12] "Man makes himself; he doesn't come to the world fully made, he makes himself by choosing his own morality, and his circumstances are such that he has no option other than to choose a morality"Jean-Paul Sartre et al., *Existentialism Is a Humanism =: L'Existentialisme Est Un Humanisme) ; Including, a Commentary on The Stranger (Explication de L'Étranger* (Yale University Press, 2007), 46.

[13] "Things must be accepted as they are. What is more, to say that we invent value means neither more nor less than this; life has no meaning apriori. Life itself is nothing until it's lived, it's we who give it meaning, and value is nothing more than (what) we give it." Sartre et al., *Existentialism Is a Humanism* =, 51.

[14] "One is not born, but rather becomes, woman. No biological, psychic, or economic destiny defines the figure that the human female takes on in society; it is civilization as a whole that elaborates this

በየውይይቱ የምንሰማው ሆኗል ፤ ሐሳቦች ውጤት አላቸውና ። ይልቁንም ክፉ ሐሳቦች መዘዝ አላቸው ። ሳርት በ1970ዎቹ ከዚህች የፍቅር አጋሩ ፥ እንዲሁም ከሌሎች የፈረንሳይ ምሁራን ጋር በመሆን ከሕፃናት ጋር ሩካቤ የፈጸሙ ሰዎች ከእሥር እንዲለቀቁ መጠነ ሰፊ ዘመቻ ሲያደርጉ እንደነበር ዘጋርዲያን በፈረንጆች አቆጣጠር በ2001 ይዞ የወጣው ዘገባ ያስረዳል።[15] በእርግጥ ይህን ማድረጋቸው ብዙ የሚያስደንቅ አይደለም ። በምዕራቡ ዓለም ገናና እና ተሰሚ ያደረጓቸውን ሐሳቦች በሥራ ላይ ማዋላቸው ለምን አስደንጋጭ ይሆናል ?

ወደ ሚሼል ፉኮ እንለፍ ። የእነ ሳርትን ዱካ ተከትሎ ብቅ ያለው ፉኮ ፥ 'The history of sexuality' በሚል ርእስ በጻፈው ሦስት ቅጽ መጽሐፍ ይታወቃል ። የጥናት ፍላጎቱ በብዛት ጾታንና ሩካቤን የተመለከተ በመሆኑ የጻፋቸው ነገሮችም እንዲሁ በብዛት በእነዚህ ርእሶች ዙሪያ ያጠነጠኑ ናቸው ። በተለይ በሁለተኛው ቅጽ መጽሐፉ 'በጥንታውያኑ ግሪክና ሮማ ዘንድ የነበረው የሩካቤ መንገድ አሁን እንዳለው አይደለም ። ስለዚህ ለምን በዚህ ዘመን ያለውን መቀበል ይኖርብናል ?' የሚል ሐሳብ ይሰነዝራል ።[16] ፉኮ ይህን ሲል ወደ ጥንቱ እንመለስ እያለ አልነበረም ። ይልቁንም በዚያ ዘመን ከእኛ ዘመን ፈጽሞ የተለየ ግብረ ገብ መኖሩ አንድ ፍጹም የሆነ ተፈጥሮአዊ የሥነ ምግባር መመሪያ እንደሌለ እና ሁሉም በልማድ ሳይታጠር ፍላጎቶቹን ያለመከልከል እየፈጸመ መኖር እንደሚችል ማስረጃ ይሆነናል ማለቱ ነው።[17] 'ሥነ ምግባር' ፥ 'መልካም እና መጥፎ' ፥ 'ክፉ እና በጎ' የምንላቸው ነገሮች በራሳቸው ህላዌ የሌላቸው ፥ ሰዎች የሚፈጥሯቸው ናቸው እያለ ነው ። በዋናነት ደግሞ ኃይል እና ሥልጣን ያላቸው ሰዎች የበላይነታቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የሚሠሯቸው ናቸው ። ስለዚህም 'ይህ በጎ ነው' ወይም 'ይህ መጥፎ ነው' የሚሉት አገላለጾች በሙሉ ምርጫን ያሳያሉ እንጂ ፍጹም ከሚባል እውነት ጋር ግንኙነት የላቸውም ባይ ነው ። በሌሎች ላይ የበላይ የሆነ ሰው ከበታቹ ያሉትን ሰዎች 'ይህ መጥፎ ነው' ሲላቸው የምር እያላቸው ያለው 'ይህ የበላይነቴ ላይ አደጋ ስለሚደቅን አልወደውም እና አታድርጉት' ነው ። ማለትም ያለውን ኃይል ተጠቅሞ እያስፈራራ ነው ። ተገዢዎቹ ሰዎች ደግሞ ይህን ከተቀበሉት ወይ የሚደርስባቸውን ፈርተው እየተገዙ ነው አሊያም መገዛትን ስለሚወዱ ነው ማለት ነው ። እንጂ ለፉኮ የትኞቹም የሥነ ምግባር አጥሮች ሰው ሠራሽ እና ከዚያ የዘለለ ህልውና የሌላቸው ናቸው ።

ይህ ፍልስፍናው ደግሞ ሐሳባዊ ብቻ አልነበረም ። ፉኮ ራሱ ሰዶማዊ የነበረ[18] ፥ እጅግ ብዙ የዝሙት አጋሮች የነበሩት ፥ እጅግ ጤናማ ያልሆነ ወሲባዊ ጠባይዕ የነበረው (pervert) እና በተደጋጋሚ ራሱን ለማጥፋት የሞከረ ሰው ነበር ።[19] በአብሮ ሠሮቹ (colleagues) ኤድስን ይፈራ እንደሆነና እንዲሁም ሞትን ይፈራ እንደሆነ ሲጠየቅ የመለሰውን መልስ የሕይወት ታሪኩን የጻፈው ጀምስ ሚለር እንዲህ ይነግረናል "And besides, he added, "to die for the love of boys: what could be more beautiful?"[20] ይህን ካለ ከአንድ አመት በኋላ ኤድስ አመንምኖና አሰቃይቶ ይገድለዋል ። ከመሞቱ በፊት በአልጋው ላይ በከባድ ስቃይ ውስጥ ሆኖ በማጣጣርና በፈገግታ መካከል የሆነ ግራ ገብ ገጽታ እንደነበረው እና ይህም ከዚያ በኋላ የእውነት ነገር የማያሳስበው መሆኑን ከማሰብ እንደሆነ የሕይወት ታሪክ ጸሐፊው ይነግረናል ።[21]

ፉኮ ፣ ሳርት እና ኒቼ የሚከበሩና ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው መሆኑ ፥ በተለይም የሃያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን አኗኗርና አስተሳሰብ የቀረጹ መሆናቸው ፥ የምንኖርበት ዓለም ምን ያህል የታመመ እንደሆነ የሚያሳይ ይመስለኛል ። ጉዳዩን ጠቅልሎ ለመረዳት ያሙች ዘንድ በእነዚህ ሰዎች እሳቤ ላይ

intermediary product between the male and the eunuch that is called feminine" de Beauvoir, *The Second Sex*, 267.

[15] https://www.theguardian.com/world/2001/feb/24/jonhenly

[16] .Michel Foucault, *The History of Sexuality, Vol. 2: The Use of Pleasure* (Knopf Doubleday Publishing Group, 2012), 35–90.

[17] Gary Gutting, *Foucault: A Very Short Introduction*, 2nd edn (Oxford University Press, 2019), 145.

[18] Because he was a homosexual, writing about the history of modern sexuality must have been a personal enterprise for Foucault.Gutting, *Foucault*, 127.

[19] "He also practiced perverse forms of sexuality with an endless stream of unknown male lovers",Strickland, *The Age of Nihilism*, 400.

[20] Jim Miller, *The Passion of Michel Foucault* (Simon & Schuster, 1993), 254.

[21] "he did so knowing that he would soon slip over the other side of that treshhold, just dust without words now, no longer speaking, no longer listening, no longer seeking, no longer caged, truly a worldless thing in an empty place - free of the need of the truth at lastMiller, *The Passion of Michel Foucault*, 374.

የተገነባውን የዚህን የድኅረ እውነታ ዓለም ሁለት መሠረታዊ መገለጫዎች ላንሣ ።

**በሰውነትና በፍጹም እውነታ ላይ የተደረገ አመጽ**

'ሰውን ሰው የሚያሰኘው ምንድር ነው?' የሚል ጥያቄ ሲነሣ ክርስትናን የተገነዘበ ሰው ተከለ ሰውነታዊ መዋቅሩ (Anatomical structure) ብሎ የሚመልስ አይመስለኝም ። ምክንያቱም የሰውነት ትርጉም ከዚህ የረቀቀ የጠለቀ ነውና። የሰው ልጅ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ እንዲሁም ክርስቶስን እየመሰለ የመኖር ጥሪ ያለው ነው ። ሰውነትን የምንተረጉመውም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ አንጻር ነው ።

> "ሰውነትን የሚበይነው መለኮታዊው ሰውነት ፥ እርሱም ክርስቶስ ነው ። ስለማንነታችን የሚቀርብን ጥያቄ ልንመልስ የምንችለው የክርስቶስን ማንነት መሠረት በማድረግ ነው ። 'ሰው' ማለት እርሱ ነው ። የፍጥረት ሁሉ በኩር ፥ እያንዳንዱ ሰው ፍጽምና ላይ ሲደርስ ሊሆን የሚገባውን የምናይበት የሰውነት አብነት እርሱ ነው ።"[22]

'ሰው ምንድር ነው ?' ለሚለው ጥያቄ መልሱ 'ሰው ክርስቶስ ነው ።' የሚል ይሆናል ። ፍጹሙ ሰው ክርስቶስ ነውና ሰውነታችን የሚበየነው ከክርስቶስ ፍጹም ሰውነት አንጻር ነው። ስለዚህ ሰው በእውነት 'ሰው' ይሆን ዘንድ አምላክ መሆን (ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን) አለበት ። ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው ሰውን አምላክ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ሰውን ሰው ያደርገው ዘንድም ነው ። ከዚህ የሰውነት ጉዞ መውጣት ሰውነትን አለማሟላት ነው ። ሰውን ከእግዚብሔር ጋር ካለው ግንኙነት ነጥሎ ለመመልከት መሞከር ወደ ትክክለኛው የሰውነት ብያኔ አያደርስም ፤ ጥፋትን ያመጣል እንጂ ።

ይህን ብያኔ የማይቀበሉ ሰዎች 'ሰው' ሲሉ ከምን መሠረት ተነሥተው ነው ? ለምሳሌ 'ሰብአዊ መብቶች' የሚለውን ሐሳብ እንመልከት ። በዚህ ሐሳብ መሠረት ማንም ሰው በሰውነቱ ብቻ በሕይወት የመኖር ፣ የመሥራት ፣ የመዘዋወር ወዘተርፈ መብቶች አሉት ። ይህን ሐሳብ እንዳለ ከመቀበላችን በፊት መጠየቅ ያሉብን ጥያቄዎች አሉ ። በመጀመርያ የምንጠይቀው 'ሰብአዊ' ሲባል ምን እየተባለ እንደሆነ ፥ 'መብት' ሲባልም ምን እየተባለ እንደሆነ ነው። ሰውነት ምን ስለሆነ ነው ከላይ የተዘረዘሩትን መብቶች የሚያስገኘው ? ሰው እነዚህ መብቶች አሉት ሲባልስ ከማን ስለተቀበላቸው ነው ? እነዚህ ጥያቄዎች መልስ ሊያገኙ የሚችሉት ወጥና እውነተኛ የሰውነት ብያኔ የኖረ እንደሆነ ብቻ ነው።

ስለዚህ ማንኛውም ሰውነትን (Humanity) በተመለከተ የሚነገር ነገር በመጀመሪያ የሰውነትን ብያኔ ከወዴት እንደቀዳ መታወቅ አለበት ። መነሻው ስሕተት ከሆነ መድረሻው ትክክል አይሆንምና ። የሰው ልጅ ክቡር መሆኑን አምኖ ፥ ክብሩ የሚመነጨው በአርአያ ሥላሴ ከመፈጠሩ የተነሣ መሆኑን አለማመን ተዋሥአውን አንድ እርምጃ ወደኋላ የሚመልስ ጥያቄ ያስነሣል ፤ 'የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ተለይቶ የከበረው ለምንድር ነው ?' የትኛውም የኢ አማኒ አእምሮ በቂ መልስ ሊያገኝላቸው ከማይችላቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ ይህ ይመስለኛል ። የሰው ልጅ ክብር ፣ ልዕልና ፣ ኃያልነት እንዳለው ተቀብሎ ይህ የተገኘው ከእግዚአብሔር መሆኑን የማያምን ሰው ይህ ክብር ፣ ልዕልናና ኃያልነት የተገኘው ከወዴት እንደሆነ የማብራራት ግዴታ ይወድቅበታል ።

ከድኅረ ዘመናዊነት (post modernism) በኋላ የሰውነት ብያኔ እየተቀየረ እንደሆነ እንመለከታለን ። ሲ ኤስ ሊዊስ 'The abolition of man' በሚለው መጽሐፉ ይህን እውነታ በደንብ ያስገነዝበናል ። መጽሐፉ ሊዊስ እውነተኛ ስማቸውን ላለመጥቀስ ጋየስና ቲተስ ሲል የጠራቸው ሁለት ጸሐፊያን ለልጆች ሰዋስው ማስተማርያ እንዲሆን ባዘጋጁት መጽሐፍ ውስጥ ያስቀመጡትን 'መርዘኛ' (Poisonous) ሐሳብ ለመሞገት እና ለመከላት የጻፈው ነው ። ሦስት አጫጭር ምዕራፎችን ብቻ የያዘ ትንሽ መጽሐፍ ቢሆንም አሁን የምንኖርበትን ዓለም አኳኋን በደንብ ለመገንዘብ የሚያበቃ ነው ብዬ አምናለሁ ።

ለሰዋስው ማስተማሪያ በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ኮልሪጅ ከሚባለው ታዋቂ ገጣሚ ሥራዎች መካከል 'At the waterfall' የተባለውን በመንተራስ ነው ሊዊስ 'መርዘኛ' ያለው ሐሳብ የተነሣው ። በግጥሙ ውስጥ

[22] "It is the idea of divine humanity that establishes the norm for man – Christ - our idea of Christ is the model of reference to which we can answer the question about who we are. He is the man, the first born of every creature, the archtype of which every man is, interms of his potentialities, the image." Charles T. Rubin, *Eclipse of Man: Human Extinction and the Meaning of Progress,* New Atlantis Books (Encounter Books, 2014), 18.

ሁለት ጎብኚዎች (Tourists) አንድን ፏፏቴ ይመለከታሉ። ይህን ፏፏቴ አንዱ ጎብኚ 'ቆንጆ' (Pretty) ፥ ሁለተኛው ደግሞ 'ግሩም' (Sublime) በማለት ይገልጡታል ። ኮልሪጅ ራሱ የሁለተኛውን ጎብኚ አገላለጽ ደግፎ የመጀመሪያውን አገላለጽ ይኮንናል ። ሁለቱ የሰዋስው መጻሕፍት አሰናጆች ግን ከኮልሪጅ በተቃራኒ ሁለቱ ሰዎች የተጠቀሟቸው ቃላት ፏፏቴውን የሚገልጹ ሳይሆኑ ፏፏቴውን ሲያዩ የተፈጠረባቸውን የግል ስሜት የሚገልጹ ናቸው ይላሉ ። በመሆኑም የተሰማቸውን ስሜት ለመግለጽ የተለያዩ ቃላትን መጠቀማቸው ተገቢ እንደሆነ ፥ የተጠቀሟቸውም ቃላት በየራሳቸው አንጻር ትክክል እንደሆኑ እና አንደኛው የተሻለ ነው ሊባል እንደማይችል ያብራራሉ ። ይህ ማብራሪያ የድኅረ እውነታው ዓለም ፈጣሪያን ከሆኑት ከፉኮ እና ከሳርት ርእዮት ጋር ፍጹም ስምምነት ያለው ነው ። ዋናው ጉዳይ ስሜቶቻችን እና ፍላጎቶቻችን መሆናቸውን የሚሰብክ እና ሁላችንም ልንገዛለት የሚገባ እና ሁሉንም ነገር (ስሜቶቻችንንም ጭምር) የሚዳኝ አንድ እውነታ መኖሩን የሚከድ ማብራሪያ ነው ።

ሲ ኤስ ሊዊስ ይህን ማብራሪያ በመቃወም 'ስሜቶቻችንና ፍላጎቶቻችን (Our sentiments) በእውነታ ላይ የተመሠረቱ ካልሆኑ ከእንስሳት የምንለየው በምንድር ነው ?' የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ይሰነዝራል ። መብላትን ፣ መጠጣትን ፣ መተኛትን ፣ በተድላ ደስታ መማለልን ፣ መፍራትን ፣ መጣላትን እና የመሳሰሉትን ነገሮች እንደ እንስሳት ሁሉ በሰው ልጅም ዘንድ እናገኛቸዋለን ። ታዲያ የሰውን ልጅ ከእንስሳት ምን ይለየዋል ቢሉ ልክ እንደ እንስሳት እሊህ ስሜቶች የማይሰለጥኑበት ፥ ይልቁንም እርሱ የሚሰለጥንባቸው ፣ የሚገዛቸውና የሚቆጣጠራቸው በመሆኑ ነው ። ይህን የሰው ልጅ ስሜቶቹን የሚገራበትን እና በቁጥጥር ስር የሚያውልበትን የሰውነቱን ክፍል ሲ ኤስ ሊዊስ ከቻይኖች ጥንታዊ ፍልስፍና ቃል ተውሶ "The tao" ሲል ይጠራዋል ።[23] በአማርኛችን ልቡና የምንለው ማለት ነው ።

ሰው በፍላጎቶቹና ባልተገሩ ስሜቶቹ እንስሳትን ይመስላቸዋል ፤ በአእምሮው (intellect) የተነሣ የሚኖርበትን ከባቢ እና ዓለም በመመርመሩ እና በመረዳቱ ደግሞ ልዩ ነው ። ታዲያ በእነዚህ በሁለቱ መካከል ሆኖ የትኛውን ስሜቶቹን ማስተናገድ ፣ የትኛውን ደግሞ መከላት እንዳለበት የሚነግረው አካል (ልቡና) ከሌለው ፥ ከእንስሳት የሚለየው ስሜቶቹን ለማርካት የሚያስችለው ከፍ ያለ ችሎታ (አእምሮ) ስላለው ብቻ ይሆናል ። ስለዚህም በእንስሳት ላይ ስሜትን ከማርካት ያለፈ ልዕልና ይኖረን ዘንድ ይህ ማእከላዊ አካል ያስፈልገናል ።

> "ንጉሥ በአዋጅ ሀገሩን እንደሚገዛ ፣ በሰውም ውስጥ አእምሮ ስሜቶችን መንፈሳዊ በሆነው የሰውነት ክፍል በኩል መግዛት አለበት ፤ ራስ ሆድን በደረት (ልብ) በኩል መግዛት አለበት ፤ ይህ ልቡና ፥ አላነስ የተባለ ጸሐፊ እንዳለው ፥ የሰውነት ፍትወታት በማያቋርጥ ልምምድ አማካይነት ተገርተው ፥ ረግተው እና የሚገባቸውን ቦታ ይዘው የሚቀመጡበት መንበር ነው ።"[24]

"አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና ።" (ምሳ 4÷23) እንዲል መጽሐፍ ፥ ያለ ልቡና ክርስቲያን (ሙሉ ሰው) መሆን ይቅርና ሰው ለመሆን መጀመርም የማይቻል ነው ። ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ከጌታ ስድስት ወር አስቀድሞ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" (ማቴ 3÷1-2) ሲል ለሕዝቡ ያደረገውን ጥሪ ወንጌላውያኑ ወደግሪክ ቋንቋ ሲመልሱት ፥ 'ንስሐ' የሚለውን ሐሳብ ለመተርጎም 'Metanoia' (μετάνοια) የሚለውን ቃል ነው የተጠቀሙት ። ይህም ወደ አማርኛ ሲመለስ 'የአእምሮና የልቡና ለውጥ' ማለት ነው ።[25] አእምሯዊ ልህቀት ብቻውን ሰው ለመባል አያበቃም ፣ የግድ የልቡና ለውጥ ያስፈልጋል ። አለዚያ ግን አእምሮ በራሱ የስሜት ተገዢ ስለሚሆን በምቾትና በቴክኖሎጂ ከመራቀቃችን በስተቀር ከእንስሳት በተለየ መንገድ ልንንቀሳቀስም ልንታይም አንችልም ። ለከብት ቀንዱ ፥ ለአንበሳ ኃይሉ ፣ ለዝሆን ግዝፈቱ ፣ ለአቦ ሸማኔ ፍጥነቱ ከሆነው የተለየ አይሆንም የአእምሮአችን አገልግሎት ። እነዚህን እንስሳት የተሰጧቸውን ስጦታዎች ተጠቅመው ስለሚያደርጉት ሁሉ በጎ ወይም ክፉ አደረጉ ብለን እንደማንፈርድባቸው እና ተጠያቂ

[23] Lewis, C. S., *The Abolition of Man* (Harper One, 2009), 18.

[24] "As the king governs by his executive, so reason in man must rule the mere appetites by means of "Spirited element", the head rules the belly through the chest - the seat, as alanus tells us, of magnanimity of emotions organized by trained habits into stable sentiments" Lewis, C. S., *The Abolition of Man*, 24.

[25] David Bentley Hart, ed., *The New Testament: A Translation* (Yale University Press, 2017), 461, https://doi.org/10.12987/9780300188493.

እንደማናደርጋቸው ሁሉ እኛም ራሳችንንም ሆነ አንዳችን ሌላችንን በዚህ መንገድ ልንጠይቅ አንችልም ። ሊዊስ የተቃወማቸውን ሁለት ጸሐፍት ተከትሎ የሰው ልጅ አእምሮና አካል ብቻ እንደሆነ ያወጀውና ልቡናን የካደው ድኅረ ዘመናዊ ዓለምም ይህን ባደረገ ቅጽበት ክፉና ደግ ፣ ጥሩና መጥፎ ፣ እውነትና ሐሰት የሚባሉትን መደቦች (categories) አብሮ ከዷል ።

ልቀጥል ፤ ስሜታችን እና ደመ ነፍሳችን ለእውነታው ተገዢ ናቸው ? ወይስ እውነታው ለስሜታችን እና ለደመ ነፍሳችን ተገዢ ነው ? መልሱ የክርስትናን መሠረታውያንን ለተረዳ ሰው አሻሚ አይደለም ።

አሁንም ከሊዊስ ልጥቀስና ፥ ደመነፍሳችን እና ስሜታችን ብቻቸውን በቂ ከሆኑ ጋየስና ቲተስ የጻፉትን ጨምሮ ሌሎች መጻሕፍት የመጻፋቸው ፋይዳ ምንድር ነው? ለማንኛውም ሰው ከራሱ ስሜት እና ደመ ነፍስ ያለፈ መምህር እና መመሪያ ለምን ያስፈልገዋል ? ቀድሞውኑም ሰዎች በሕፃንነታቸው ለስሜት የተሰጡ ናቸው ። ታዲያ ደመ ነፍስ እና ስሜት በራሳቸው በቂ ከሆኑ ሕፃናት በወላጆቻቸውም ሆነ በሌሎች ሰዎች መመራታቸው እና መገራታቸው ለምን ያስፈልጋል ? ይህ የመጀመርያው ጥያቄ ነው ።

ሌላው ደግሞ ስሜቶቻችን እና ደመ ነፍሳዊ ምላሾቻችን ሁልጊዜ ወጥና ተመሳሳይ አይሆኑም ። ስለዚህ እነርሱ ሲለያዩና እርስ በእርሳቸው ሲቀዋወሙ በምን መሠረት ልንዳኛቸው ነው ? ለምሳሌ ወላጆቻችን በሆነ ምክንያት ቢያበሳጩን እና በእነሱ ላይ ክፉ ነገር የመናገር ወይም የማድረግ ፍላጎት ቢያድርብን ፥ ግን ደግሞ በዚያው ቅጽበት ካለን ጥብቅ ቁርኝት የተነሣ የርኅራኄ እና የሐዘኔታ ስሜት ቢሰማን የትኛውን ስሜት ማዳመጥ እንዳለብን ማን ይነግረናል ? ወይም አንድ ሰው የምንወደውን ሰው ሊያጠቃ ቢመጣ እና በአንድ በኩል ከመውደዳችን የተነሣ ጥቃቱን የማስቆም መነሣሣት ቢኖረን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን በማድረጋችን በእኛ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስበን ብንፈራ ከሁለቱ ስሜቶች መካከል የሚሻለውን እንድንመርጥ የሚረዳን ምንድን ነው ? ከልጆችን ጋር እየተጓዝን በጣም ተርበን ሳለ ለአንድ ሰው የማይበቃ ምግብ ብናገኝ የጨጓራችንን ጩኸት ሰምተን ለራሳችን እንብላው ወይስ የአባት አንጀታችንን ተማጽኖ ሰምተን ለልጆቻችን እናጉርሰው ?

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ‘እውነት አንጻራዊ ነው’ እና ‘ስሜትና ደመ ነፍስ በራሳቸው ትክክል እና በቂ ናቸው’ የሚሉትን ሐሳቦች ቅጥሮቻቸውን የሚያፈራርሱ ሆነው አገኛቸዋለሁ ።[26] ወጥ እና በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የሚሠራ እውነታ (objective truth) ከሌለ ብዙ የተስማማንባቸውን ጉዳዮች እንደገና መጠየቅ አስፈላጊ ይሆናል ። ሊዊስ ይህን የሚያስረዳ ጥሩ ምሳሌ ያመጣል ።

‘ማኅበረ ሰብእ መቀጠሉ ጥሩ ነገር ነውና መጠበቅ አለበት ።’ በሚለው ሐሳብ ሁሉም አገራት ይስማማሉ። ለዚህም ነው የመከላከያ ሠራዊት ፥ የጤና ሚኒስቴር ወዘተ ያለው። ነገር ግን ማኅበረ ሰብእ ለምን መጠበቅ ይኖርበታል ? ማኅበረ ሰብእ መጠበቅ እንዳለበት ለምን እንስማማለን ? ማኅበረ ሰብእ መጠበቅ አለበት ለሚለው አስተሳሰብ መሠረቱ ምንድር ነው ? ከስሜትና ደመ ነፍስ ተነሥቶ እዚህ ድምዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል ? ምናልባት ሌላው ሰው ሁሉ ከየራሱ ስሜት ተነሥቶ እዚህ ላይ ቢስማማ ራሱ ግን የኔ ስሜት ካልተቀበለው እስማማበት ዘንድ ግድ የሚለኝ አመክንዮ ምንድነው ?

ይህን ጥያቄ ሳንጠይቅ ‘ማኅበረ ሰብእ መጠበቅ አለበት ።’ የሚለውን ሐሳብ ብንቀበል ራሱ ግን ቀጥሎ የሚመጣ ከባድ ጥያቄ አለ ። ማኅበረ ሰብዕን ለመጠበቅ ከተፈለገ ማኅበረሰቡን ሊያጠፉ የሚችል አደጋ ሲከሰት ከማኅበረሰቡ መካከል የተወሰኑ ሰዎች ያን አደጋ ተጋፍጠው ማስቆም አለባቸው ። ስለዚህ ማኅበረሰቡ እንዲቀጥል ከመካከሉ የተወሰኑ ሰዎች መጎዳት ወይም መሞት ይኖርባቸዋል ። ነገር ግን እነዚያ ሰዎች ማኅበረሰቡን ለመጠበቅ ይሞቱ ዘንድ የሚጠየቁት በምን መሠረት ነው? የብዙዎችን ሕይወት ለማቆየት ጥቂቶች ውድ ሕይወታቸውን የሚሰዉበት አመክንዮአዊ መሠረት ከወዴት ነው የሚመጣው?

ለምሳሌ አንድ ሰው ከደመ ነፍሱ በመነሣት ‘ከእነዚያ ጥቂት ለሞት ከታጩ ሰዎች መካከል እኔ ለምን አንዱ እሆናለሁ ? ይልቁንም መሞት ስለማልፈልግ እኔ ቆይቼ በሌላው ሰው መስዋዕትነት ለምን መኖሬን አልቀጥልም ?’ ቢል በምን መሠረት ትክክል አይደለህም ሊባል ይችላል ? ሁሉም ሰው እንዲሁ ቢያስብስ ? የትኛውንም ሰው ራሱን ለማኅበረሰቡ መስዋዕት እንዲያደርግ የሚያሳምነው ምን አመክንዮ ሊኖር ይችላል ?

---

[26] Lewis, C. S., *The Abolition of Man*, 36.

ከእኛ ስሜት እና ፍላጎት በላይ ያለን እውነታ ለማየትና እውቅና ለመስጠት ፈቃደኝነት ከሌለን ከምን ተነሥተን ስለ መስዋዕትነት ልንነጋገር እንችላለን ? ደግሞም እውነት አንጻራዊ ከሆነ የማኅበረ ሰብዕን መጠበቅና ደኅንነት አስፈላጊነት በተመለከተ ለምን እንስማማለን? ከዚህ በተቃራኒ የሚያስብ ሰው መጥቶ 'ማኅበረ ሰብእ መጥፋት አለበት' ቢል ከምን የጋራ መነሻ ተነሥተን እንከራከረዋለን ? ደግሞም ሰዎች ለሌሎች ሰዎች (በተለይም ጨርሶ ለማያውቋቸው ሰዎች) ራሳቸውን መስዋዕት የማድረግ ደመ ነፍሳዊ እና ጠንካራ ዝንባሌ (የላቸውም እንጂ) ቢኖራቸው እንኳን ይህ ደመ ነፍሳዊ ዝንባሌ ሊቆጣጠሩት ወይም ሊተገብሩት የሚገባ መሆን አለመሆኑን በምን እናውቃለን ?[27]

ሊዊስ እንዲህ ያለውን እውነትን በምናውቅበት ክፍል (Faculty) ላይ የሚደረግን አመጽ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

> "የዘመናችን ርእዮቶች በልቡና ላይ የሚያደርጉት አመጽ ፥ ቅርንጫፎች በዛፉ ላይ የሚያደርጉትን አመጽ ይመስላል ። አማጽያኑ ድል ባደረጉ ቅጽበት ራሳቸውን ማጥፋታቸውን ይገነዘባሉ ። "[28]

ስሜቶች ከእውነታ ጋር ግንኙነት የሌላቸው እንደሆነ በራሳቸው ምንም ዓይነት ረብሕ/Relevance የሌላቸው ይሆናሉ ። የትኛውም ነገር ትርጉም ይሰጥ ዘንድ ከፍጹም እውነታ ጋር የተገናኘ መሆኑ የግድ ነው ። ከድኅረ ዝመና (Postmodernism) በኋላ ግን በእውነትም ላይ ፥ እውነትንም በምናውቅበት ክፍል (Faculty) ላይ በምልትአ አመጽ ስለተደረገ የትክክልና የስሕተት ፣ የመልካምና የመጥፎ መስፈሪያ የሌለ በመሆኑ ፥ እያንዳንዱ ሰው ተድላን ያመጣልኛል ብሎ ባሰበው ነገር ሁሉ ውስጥ ይዋልላል ። 'እስከተመቸህ ፥ ተድላ እስካስገኘልህ ፥ ስሜትህን እስካረካልህ ድረስ በራስህ መንገድ ትክክል ነህ ።' የሚለው እሳቤ ብዙዎች የሕይወታቸውን መሠረት የጣሉበትና የሚመሩበት ነው። እንዲህ ባለው "መርሕ" እየተመሩ ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር የሚገኘን ሐሴት (Spiritual joy) እና ተራ እና ከንቱ የሆነውን ተድላ እና ደስታ (Hedonistic pleasure) መካከል ያለውን ልዩነት ለመገንዘብና ለማጤን እስከማይችሉ ድረስ ፈጽመው ታውረዋል ። ሊዊስ የጋየስ እና የቲተስ ክህደት በምልዐት ተቀባይነት ካገኘ ይፈጠራሉ ብሎ የተነበየላቸው እና 'ደረት (ልቡና) አልባ ሰዎች' (men without chests) ብሎ የጠራቸው እንዲህ ያሉትን ነው ።

ይህ ትንቢት በዘመናችን መፈጸሙን እያየን ነው ። በምዕራቡ ዓለም ውርጃ (Abortion) ፣ ጾታ "ቅየራ" (Transgenderism) ፣ ሰዶማዊነት ወዘተርፈ በዚህ መጠን የማኅበረ ሰብእ ዕለታዊ ኑሮ አካል የሆኑት ወጥ የሆነ እውነታ (Objective truth) በመደምሰሱና ሁሉም "የየራሱ እውነታ" (ይህም ሲያደርገው ደስ የሚሰኝበት ነገር ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም ያለው ነገር አይደለም) እንዳለው የሚነገርበት ፥ ይህ ሐሰትም በስፋት የታመነበት ዘመን በመሆኑ የተነሣ ነው።

የፍጹም እውነታ መኖር ተክዶ ስሜቶች እና ፍላጎቶች ከነገሡ በኋላ ፥ ጥንት ለእውነት ይሰጥ የነበረው ትኩረት እና ጥንቃቄ ወደ "ነጻነት" ዞሯል ። በዚህ ሁሉም "የየራሱን እውነት" በሚያውጅበት እና በሚኖርበት ዘመን የዕሴቶች ሁሉ ቁንጮ የተደረገው አንዱ ሰው ስሜቱን እና ፍላጎቱን ለማርካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከሌሎች ሰዎች ጣልቃገብነት ያለው "ነጻነት" ነው ። ማንም 'ፍጹም እውነት ነው' ብሎ የሚያስበውን ነገር ሌሎች ላይ በመጫን "የራሳቸውን እውነት ከመኖር" እንዳያግዳቸው ፥ የእያንዳንዱ ሰው "ነጻነት" መከበሩ አስፈላጊ ሆኗል ። በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ነጻነት በእጅጉ የከበረች ናት ። ነገር ግን ድኅረ ዘመናዊው ዓለም የሚሰብከው "ነጻነት" እና ክርስትና የሚሰብከው ነጻነት በአንድ ቃል ይጠሩ እንጂ ፈጽሞ የተቃረኑ ናቸው ። በእውነት ላይ የተደረገው አመጽ ሌላኛው ገጽታም በነጻነት ስም በእውነተኛው ነጻነት ላይ የተደረገው ነው ።

### በነጻነት ስም እውነተኛው ነጻነት ላይ የተደረገ አመጽ

ነጻ መሆን ምንድር ነው? አንድ ሰው ነጻ ሆነ የሚባለውስ መቼ ነው ? ነጻነት ማለት ምንም ነገር መምረጥ የመቻል አቅም ማለት ነው ? ከሆነስ የምንመርጠው ነገር ትክክል መሆን አለመሆኑን በምን እናውቃለን ? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ነጻነትን በተመለከተ ሳስብ ወደ አእምሮዬ

---

[27] Lewis, C. S., *The Abolition of Man*, 35.

[28] "The rebellion of new ideologies against the tao is a rebellion of the branches against the tree; if the rebels could succeed they would find that they had destroyed themselves" Lewis, C. S., *The Abolition of Man*, 44.

የሚመጡ ናቸው ። ከላይ እንደ ጠቀስሁት ከዘመናዊነት በተለይም ከድኅረ ዘመናዊነት መምጣት በኋላ 'ነጻነት' የሚለው ቃል አማራጭ ከማብዛት እና ፍላጎቶቻችንን ሁሉ መፈጸም ከመቻል ጋር ተያይዟል።

> "የዘመናዊነት ትልቁ ዕሴት የሆነው እና በዘመናዊነት ከቀደሙት ዘመናት ሁሉ በተለየ መንገድ እንዲበየን የሆነው 'ግለሰባዊ ራስ ገዝነት' ፥ ሁሉም ነገሮች የተመሠረቱት ከሁሉም አስቀድሞ በነበረ ባዶነት ላይ እንደሆነ እንድናምን ያስገድደናል ። ይህ እጅግ ለም የሆነ ባዶነት ፥ ያሰብነው እና የፈለግነው ሁሉ የሚቻልበት ፥ የእኛን ፈቃድ የሚጻረር ምንም እንቅፋት የሌለበት ፥ ስለዚህም እያንዳንዳችን ራሳችንን በመረጥነው መንገድ መፍጠር የምንችልበት ነው ። ማለትም ከራሳችን የማይጠየቅ ፈቃድ ሌላ ምርጫዎቻችንን የሚዳኙበት ወጥ መለኪያ እንደሌለ እናምናለን ። በመሆኑም ማንኛውንም ፥ መለኮታዊም ሆነ ምድራዊ ፥ የፍርድ ቃል ነጻነታችን ላይ የተሰነዘረ ጥቃት አድርገን ነው የምንመለከተው ። የርእዮታችን ዐቢይ መገለጫ ይህ ነው ። ባልተኳኳለ አማርኛ ሲገለጥ ዘመናዊነት 'ሁሉም ነገር ትርጉም አልባ ነው' የሚለው እምነት (አልባነት) (nihilism) ነው ።"[29]

ምርጫዎችን በማብዛት እና በግለሰባዊ ራስ ገዝነት ላይ የሚመሠረተው ይህ የነጻነት እሳቤ በክርስትና ካለው የነጻነት እሳቤ ፈጽሞ የተቃረነ ነው ፤ ኦርቶዶክሳዊው የነጻነት መረዳት ምርጫ ማብዛት ላይ ሳይሆን በትክክል መምረጥ መቻልን ዓላማ ያደረገ ነው ።

ከላይ የተዋስነው ጥቅስ ባለቤት ፥ ዴቪድ ቤንትሌይ ሃርት ፥ የሁለቱን መረዳቶች ልዩነት ለማብራራት አንድ አጭር ታሪክ (Short story) ይጠቀማል ። ታሪኩ የአሜሪካዊው የአጫጭር ታሪኮች ደራሲ ፍራንክ ስቶክተን ሲሆን 'ወይዘሪቷ ወይስ ነብሩ ?' (The lady or the tiger?) ይሰኛል ። ታሪኩ በአጭሩ ሲጠቃለል እንደሚከተለው ነው ።

በአንድ ጥንታዊ ግዛት ውስጥ አንድ ሰው ሕግ ተላልፎ ከተገኘ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ (Arena) ከሁለት የተዘጉ በሮች ውስጥ አንዱን እንዲመርጥ ይደረጋል ። በአንደኛው በር እጅግ የተራበ ነብር ሲኖር ፥ በሌላኛው ደግሞ ወጣት እና መልከ መልካም ሴት ትኖራለች ። ፍርደኛው በየትኛው በር ምን እንዳለ አያውቅም ። ዕድሉ ሆኖ የተራበ ነብር ያለበትን ከከፈተ የመበላት ዕጣ ይገጥመዋል ፤ ሴቲቱ ያለችበትን በር ከከፈተ ደግሞ አግብቷት እንዲኖር ይገደዳል ። በዚህ ጥንታዊ ግዛት ውስጥ የሚኖር አንድ የንጉሡ ባለሟል ከንጉሡ ልጅ ጋር ፥ እሷም ከእሱ ጋር በፍቅር ይወድቃሉ ። ታዲያ ንጉሡ ልጃቸው ከዚህ ባለሟል ጋር ያላትን ግንኙነት ሲያውቁ እሱን በወታደሮች ያስይዙታል ። ለድፍረቱም ከላይ የተገለጸውን ቅጣት እንዲቀበል ይፈርዱበታል ። በፍርዱም መሠረት ከሁለቱ በሮች አንዱን ይመርጥ ዘንድ ይገደዳል ። ልዕልቲቱ ፍርዱ ከሚፈጸምበት ጊዜ ቀደም ብላ የትኛው በር ውስጥ ምን እንዳለ አስቀድማ አጣርታ ትረዳለች ። ከየትኛው በር ጀርባ ምን እንዳለ ብታውቅም ግን ልቧ ከአጣብቂኝ አይድንም ። ወዳጇ መልከ መልካም ሴት ያለችበትን በር ከከፈተ በሕይወት መትረፉ ደስ ቢላትም ከሌላ ሴት ጋር መጋባቱ ግን የምትፈልገው ነገር አይደለም ። በነብር መበላቱንም ልትሻ አትችልም ። ታሪኩ የሚቋጨው እሱ ከሁለቱ በሮች ፊት ቆሞ እሷ ወዳለችበት ሠገነት ሲያንጋጥጥ ፥ እሷም ከሁለቱ በሮች መከፈት የሚገባውን ስታመላክተው ነው ። ወደ የትኛው ጠቆመችው የሚለው ያልተፈታ ምሥጢር ሆኖ ይቀራል ።[30]

ይህ ሰው ከሁለቱ በሮች ውስጥ አንዱን መምረጥ ይችላል ። ከሁለቱ በሮች የፈለገውን መምረጥ መቻሉ ነጻ ያደርገዋል ወይስ ከበሮቹ ጀርባ ያለውን ነገር መረዳቱ ?

---

[29] "Modernity's highest ideal — its special understanding of personal autonomy requires us to place our trust in an original absence underlying all of reality, a fertile void in which all things are possible, from which arises no impediment to our wills, and before which we may consequently choose to make of ourselves what we choose. We trust, that is to say, that there is no substantial criterion by which to judge our choices that stands higher than the unquestioned good of free choice itself, and that therefore all judgment, divine no less than human, is in some sense an infringement upon our freedom. This is our primal ideology. In the most unadorned terms possible, the ethos of modernity is—to be perfectly precise—nihilism" David Bentley Hart, *Atheist Delusions: The Christian Revolution and Its Fashionable Enemies* (Yale University Press, 2009), 21.

[30] frank stockton, *The Lady, or the Tiger? And Other Stories* (Airmont publishing company, 1968), 11–19.

ለምሳሌ ያህል ምርጫው በሁለት በሮች መሃል መሆኑ ቀርቶ በሃያ በሮች መካከል ቢሆን የበለጠ ነጻ ሆኗል እንላለን ? በሮቹ ሁለት ብቻ ሆነው ግን ከበሮቹ ጀርባ ያሉትን ነገሮች ግን ቀድሞ ቢያውቅስ ? ምክንያታዊ የሆነ ማንኛውም ሰው ከበሮቹ መብዛት ይልቅ በየትኛው በር ውስጥ ምን እንዳለ ማወቁ የበለጠ ነጻ ያደርገዋል እንደሚል እገምታለሁ ።

የምንመርጠውን ማወቅ ስንል እውቀታችን እውነታ ላይ መመሥረት ይኖርበታል ማለታችን ነው። አለበለዚያ ነጻነት ማለት ማለቂያ ከሌላቸው ምንነታቸው ግን ካልታወቀ አማራጮች (infinite unknowns) መካከል በጨለማ የሚደረግ የአቦሰጥ ምርጫ እንጂ ትርጉም የሚሰጥ ነገር ወደ መሆን ከፍ ሊል የሚችልበት ዕድል የለም። እንዲያውም መራጩ ስለሚመርጠው ነገር ካለማወቁና ከምርጫዎቹ መብዛት የተነሣ የሚወዛገብና የሚዋልል ይሆናል ። ድኅረ ዘመናዊው ዓለም ግን ነጻነት የሚለው እንዲህ ያለውን ሁኔታ ነው ።

ክርስትና የሚሰብከው እና የሚሰጠው እውነተኛ ነጻነት ደግሞ በአንጻሩ ስለሚመርጡት ነገር ያለ ትክክለኛ ዕውቀትና እዚህ ዕውቀት ላይ የሚገነባ መልካም እና ውብ ሕይወት ነው። ስለዚህም ነው ክርስትና ኃጢአት መሥራትን እንደ መቻል ሳይሆን እንደ አለመቻል ፣ እንደ ነጻነት ሳይሆን እንደ ባርነት የሚመለከተው ። አውግስጢኖስ እንደሚለው እውነተኛ ነጻነት ኃጢአት መሥራት መቻል (Posse non peccare) ሳይሆን ኃጢአት መሥራት አለመቻል (non posse peccare) ነው ።[31] ወይም በተሻለ መንገድ ለማስቀመጥ ኃጢአት ማለት ጽድቅን ማድረግ አለመቻል ፥ ጸድቅን ከማወቅ እና ከማድረግ መጉደል ነው ። ስለዚህም ጽድቅን እስካልሠራን ድረስ ምንም ያህል ብዙ ምርጫዎች ቢኖሩን ነጻ ነን ልንል አንችልም ።

አንድ በሱስ ውስጥ የሚኖርን ሰው ምሳሌ አድርገን እንውሰድ ። ይህ ሰው ነጻ ነው ወይንስ አይደለም ? ነጻ የሚያደርገው የሚፈልገውን ሁሉ ነገር ማድረጉ (ሱሱን ማርካቱ) ወይስ ራሱን ከሱስ መከልከል መቻሉ ? የበለጠ ነጻ የሚሆነው ሱሱን የሚያረካባቸው ብዙ አማራጮች በተፈጠሩለት ቁጥር ወይስ ከሱስ ራሱን ባነጻ መጠን ?

በሱስ ውስጥ መውደቅ ነጻነትን በፈቃድ ማጣት መሆኑ የሚያስማማ ይመስለኛል ፤ ምክንያቱም ሰው ሱሰኛ ለሆነለት ነገር ለእርሱ ተገዝቶ ባርያ ነውና ፤ ሱሱ የእርሱ ባለቤት እንጂ እርሱ ባለቤታዊነቱን (ፈቃዱን) አጥቶአልና ፤ ስሜቶቹ በእርሱ ላይ እንጂ እርሱ በእነሱ ላይ የበላይ መሆን አልቻለምና ። ከዘመናዊነት በኋላ የመጣው እሳቤ ግን ይህን ነው ነጻነት የሚለው ። የሰውን ልጅ ነጻ ነው የሚለው ፍትወታቱን የሚያረካባቸው አማራጮች በበዙለት ቁጥር ነው ። ሁሉንም ዓይነት ነገር ለመብላት እና ለመሸመት ፥ ከፈለገው ሰው ጋር በፈለገው ጊዜ ሩካቤ ለመፈጸም ፥ እስከፈቀደ ድረስ የትኛውንም ተግባር ለመፈጸም መቻሉ ነው ባለንበት ዘመን 'ነጻነት' የሚባለው ። ይህ ደግሞ የእውነተኛው ነጻነት ፍጹም ተቃራኒ እና ጠላት ነው።

በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ አንድ ሰው ከኃጢአት በራቀና ፍትወታት እኩያትን ድል በነሣበት በዚያው መጠን ነጻ ሲሆን ፤ ለፍትወታት እኩያት በተገዛበት በዚያው መጠን ደግሞ ባርያ ነው። ስለዚህ እውነተኛው ነጻነት በክርስትና ክርስቶስን መምረጥ እንጂ አማራጭን ማብዛት ወይም ፍላጎትን ያለገደብ የመፈጸም ችሎታ አይደለም ።

የምንመርጠውን ነገር በትክክል ማወቃችን ምርጫችንን ጥቂትና ውሱን ያደርገዋል ፤ ምክንያቱም ስለምርጫዎቻችን ያለን ዕውቀት በጨመረ ቁጥር አብዛኛው ምርጫ የማይጠቅም መሆኑን ስለምናውቅ ። "ሁሉ ተፈቅዶልኛል ፣ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር ስንኳ አይሰለጥንብኝም" (1ኛ ቆሮ 6÷12) እንዲል ሐዋርያው። ዶክተር ሃርትን ደግሜ ልጥቀስ ፤

> "በጎውን ነገር ለመምረጥ ፥ በፕሌቶ አገላለጽ 'የጽድቅን ፀሐይ' አጥርተን ማየት አለብን ። ጽድቅን የበለጠ አጥርተን ለማየት ደግሞ በጎውን ነገር እየመረጥን መቀጠል አለብን ። በዚህ መንገድ ከክፋት እና ከተጭበረበረ ዕይታ በተላቀቅን መጠን እይታችን በእጅጉ እየጠራ ይመጣል ፤ ዕይታችን በጠራ መጠን ደግሞ (የሚያጭበረብረን ነገር ስለማይኖር) ምርጫዎቻችንም ውሱን ይሆናሉ ።"[32]

[31] Hart, *Atheist Delusions*, 25.

[32] "To choose well we must ever more clearly see the "sun of the Good" (to use the lovely Platonic metaphor), and to see more clearly we must continue to choose well; and the more we are emancipated from illusion and caprice, the more perfect our vision

በትክክል ለመምረጥ እና ካለንበት ድንግዝግዝና ጨለማ እንዲሁም የተጥበረበረ ዕይታ ወጥተን አጥርተን ለማየት መለኮታዊ ብርሃን ሊበራልን ይገባል ። ማለትም ምርጫችን ፍጹም እውነታን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት ። ፍጹም እውነታን ሳናውቅ እና ሳንረዳ በፍትወታት ታውረን በዳበሳ የምናደርገው ምርጫ ግን የበለጠ ባርያ ያደርገናል እንጂ በፍጹም አርነት አያወጣንም ።

እንዲህ ያለው የነጻነት መረዳት በፈቃድ ባርነትን የመሸመት እና እግዚአብሔርን በልቡና ውስጥ የመግደል ጎዳና ነው። ሴራፊም ሮዝ የተባሉት ሊቅ ኒቼን ጠቅሰው እንደሚናገሩት ፥ "ዘመናዊው" ሰው እግዚአብሔርን በልቡናው ውስጥ ገድሎታል ።[33] በዚህም ምክንያት አዲስ "ሰው" ፣ አዲስ "ማኅበረ ሰብእ" ወዘተ በመፍጠር ተፈጥሮንም ሆነ ሥርዓተ ህላዌን በራሱ ፍላጎት መሠረት መልሶ ለመበየን ጥረት በማድረግ ላይ ነው ። ይህንም የሚያደርገው በነጻነት ስም ነው ። ነባሩን ሥርዓተ ሕላዌ በማጥፋት ሂደት ራሱንም እያጠፋ እንደሆነ አይገነዘብም ። ምክንያቱም ሰው በእግዚአብሔር አርአያ መፈጠሩ እውነት ስለሆነ ፥ ሰውነቱን ደግሞ ፍጹም የሚያደርገው ክርስቶስን በመምሰል በፍትወታቱ ላይ ሲሰለጥን ነውና ፥ በነጻነት ስም ራሱን ለብዙ ፍትወታት አሳልፎ በሰጠ መጠን ከክርስቶስ እየራቀ ይመጣል ። በራቀበት በዚያው መጠን ደግሞ ሰውነቱም ፣ ህልውናውም እየደበዘዘ ፥ እየጠፋ ይሔዳል ።

> "ቀድሞ እግዚአብሔር በነበረበት አሁን ባዶነት ነግሧል ። ሥርዓት ፣ መረዳት ፣ እምነት በነበሩበት አሁን ውጥንቅጥ ፣ ግራ መጋባት ፣ መርሕ አልባነት እና ቀቢጸ ተስፋ ሰፍነዋል ።"[34]

ድኅረ ዘመናዊው ዓለም እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ከኑሮው ማእከል ፈቀቅ ያደረገ በመሆኑ ሁሉንም ነገር እንደ አዲስ ይበይናል ፤ ነባሩን እውነታ ይደመስሳል ፤ ከእውነት ጋር በመጣላቱ ምክንያት ወደ ጥልቅ አለማወቅና ተስፋ መቁረጥ ይገባል ፤ ከብርሃን መለየት ጨለማ ፥ ከዕውቀት መለየት ድንቁርና ነውና ። ነጻነቱን ያወጀ እየመሰለው ወደ ባርነት ፣ ወደ ብርሃን የወጣ እየመሰለው ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይሰጥማል ።

ድኅረ ዘመናዊው የነጻነት መረዳት አንድ ሰው የራሱን ስሜቶች እና ፍላጎቶች ብቻ እንዲያዳምጥ እና እንዲያስተናግድ ስለሚያበረታታ አንድ ሰው የበለጠ "ነጻ" በሆነ ቁጥር ለሌሎች ግድ እያጣ ፥ እንደ ሰው ሳይሆን እንደ ስሜቱ መጠቀሚያዎች ወይም እንቅፋቶች ብቻ አድርጎ እየተመለከታቸው ይመጣል ። "ነጻነቱ" በጨመረ መጠን በራሱ ብቻ እየታጠረ ይመጣል ። በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ግን ነጻነት ከፍትወታት እኩያት መላቀቅ እና ራስን በፈቃዳችን እንዲሁም በክርስቶሳዊ ፍቅር ለሌላው መስጠት መቻል ነው ። አንድ ሰው (ከፍትወታት እኩያት) ነጻ በሆነ መጠን ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት ፍትወታቱን ከመፈጸም ጋር የተጣበቀ ሳይሆን ክርስቶስን አብነት በማድረግ ራሱን ለሌሎች መስዋዕት የማድረግ ዓላማ ያለው ይሆናል ። የራሱ ፍትወታት መጋረጃ ስለማይሆኑበት ሌሎችን እንደራሱ ለማየት አይቸገርም ። በዚህ ጎዳና እየተጓዘ ነው የሚጠሉትን እስከ መውደድ ፣ ለሚያሳድዱት እስከ መጸለይ የሚያደርስ ፍጹም ነጻነት ላይ የሚደርሰው ። የእነ ፉኮ ዓለም የሚሰጠን "ነጻነት" ፍቅርን ከሰውነት የሚያጠፋ ሲሆን ክርስትና የሚሰጠን ነጻነት ግን ወደ ፍጹም ፍቅር የሚያደርስ ነው ።

ፍጹም እውነታ አለ ተብሎ በሚታመንበት ዓለም አንድ ሰው በነጻነት ስም ለሚያደርጋቸው ነገሮች አንዳች አጽዳቂ ምክንያት ያስፈልገዋል። ከነጻነቱ ጋር አብሮ ነጻነቱን በትክክል ለመጠቀም የሚወስደው ኃላፊነት ይኖራል ። በዘመናዊነትና በድኅረ ዘመናዊነት እሳቤ ግን ይህ ጨርሶ ስለማይታመን አንድ ሰው ነጻነቴን ተጠቅሜ አደርጋቸዋለሁ ለሚላቸው ነገሮች ከሚያስገኙለት እርካታ ባለፈ ምንም ዓይነት አጽዳቂ ምክንያት (Justification) ማቅረብ አያሻውም ። "If it feels good, do it" (ካስደሰተህ አድርገው) የሚለው አነጋገር ለሁሉም ነገር አጽዳቂ ምክንያት የሆነበት ጊዜ ላይ ደርሰናል ።

> "በዚህ ባለንበት ዘመን ነጻነት ከምክንያታዊነት ራሱ የላቀ ነገር ነው ። ነጻነታችንን ተጠቅመን

---

becomes, and the less there is really to choose." Hart, *Atheist Delusions*, 25.

[33] God is dead in the hearts of modern man, this is what the death of God means, and it is as true of the atheists Satanists who rejoice in the fact, as it is of the unsophisticated multitudes in which the sense of the spiritual reality has simply disappeared. Seraphim Rose, *Nihilism: The Root of the Revolution of the Modern Age*, Second Edition (St. Herman of Alaska Brotherhood, 2020), 60.

[34] "Where there was once God, there is now nothing, where there were once order, certainty, faith, there are now anarchy, confusion, arbitrary and unprincipled action, doubt and despair" Rose, *Nihilism*.

> የምናደርጋቸውን ነገሮች በምክንያታዊነት ሚዛን መዝነን የማጽደቅ ግዴታ እንዳለብን አይሰማንም ። ነጻነትን የግለሰቡ ያልተገደበ እና ያልተገራ የፈቃድ እንቅስቃሴ አድርገነዋል ። ይህ ያልተገደበ እና ያልተገራ ፈቃድ ደግሞ እራሱ የራሱ ሚዛን ፥ የራሱ መዛኝ እና የራሱ እውነት ሆኗል ።"[35]

አንድ ሰው የሚያደርጋቸውን ነገሮች ትክክለኛነት ማረጋገጥና ማስረዳት እንደማይጠበቅበት እና ለሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የሚያገኝባቸው ግልብና ርካሽ[36] ደስታ በቂ ምክንያት ነው ብሎ እንዲያስብ በመሆኑ ፥ ፍሬ ያለው ተዋሥኦ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል ።

በኦርቶዶክሳዊው እሳቤ ግን አንድ ሰው ከፍትወቶቹ በነጻ መጠን የራሱን ፈቃድ ከመፈጸም ይልቅ የራሱን ፈቃድ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ያስገዛል ። እግዚአብሔር ደግሞ ፍጹም እውነታ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ፈቃዱን ባስተካከለ መጠን እውነትን (ጽድቅን) እያወቃት ፣ እየፈጸማትም ይመጣል ። በዚሁ መጠን ደግሞ ፍጹም ሰውነትን ፥ ነጻነትንም እየተላበሰ ይመጣል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንደተናገረው ፥ "እውነትን ታውቃላችሁ ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል ።" (ዮሐ 8፥32) የነጻነት መሠረቷ እውነት ነው ። እውነት ደግሞ ክርስቶስ ነው (ዮሐ 14፥6) ።

※ ※ ※

ይህ በእውነት እና በነጻነት ላይ ፥ ማለትም በእግዚአብሔር ላይ የተደረገ አመጽ በምዕራቡ ዓለም ያለውን አነዋወር በጥቂት አሥርት ዓመታት ውስጥ ጨርሶ ለዋውጦታል ። ከመቶ እና ሁለት መቶ ዓመታት በፊት በዚያው በምዕራቡ ዓለም ከሰውነት የተቃረኑ መሆናቸው አያጠያይቅ የነበሩ ሐሳቦች እና ድርጊቶች ለዛሬው ምዕራባዊ ዓለም የሰብአዊነት መገለጫዎች ሆነዋል ። በመግቢያዬ ለዚህ እውነታ ማሳያ እንዲሆን አነሣሁት እንጂ ፥ ሰዶማዊነት ይህ ማዕበል ካስነሣቸው ብዙ ወጀቦች አንዱ ብቻ ነው ። ስለ እውነታ ፣ ስለ ሥነ ምግባር ፣ ስለ ሰብአዊነት ፣ ስለ ነጻነት ፣ ስለ ፍቅር ወዘተርፈ ያለን መረዳት ምን ያህል እንደተራራቀ በምልአት መግለጥ ቢከብድም ፣ ለአብነት ያህል ግን ጥቂት ምሳሌዎች ላንሣ ።

ጾታና ጾታዊ ዝንባሌ ለሁሉም ወጥ ያልሆነ ከሰው ወደሰው የሚለያይ እና በዋናነት ለባለቤቱ ምርጫ የተተወ ነገር ነው የሚለውን እሳቤ እንይ ። ይህ አመለካከት መሠረታዊ የሥነ ሕይወት እውነታን (Basic biological reality) የሚሽር ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ያለውን ሐሳብ ከሰው ልቡና የሚያጠፋና የሰውነትን ትክክለኛ ብያኔ የሚደመስስ ነው።

በመጀመርያ ጾታ ምንድር ነው? ወንድ ምንድር ነው? ሴትስ ምንድር ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች ላይ ስምምነት በሌለበት የሚደረግ ተዋሥኦ ፍሬ ቢስ ከመሆን ውጭ አማራጭ የለውም ። አንድን ነገር በትክክል ለመበየን ደግሞ ወጥ እና ፍጹም እውነታ ላይ መመሥረት አለብን ። ወጥና ፍጹም እውነታ (አምላክ) የሌለ እንደሆነ የትኛውንም ነገር መበየን እንደምን ይቻላል? ስለዚህ ብየና የግድ የአምላክን መኖር ይጠይቃል ። ምክንያቱም ፍጹማዊ መነሻ ከሌለ ትክክለኛ ብያኔ ሊኖር አይችልምና።

ፍጹም እውነታ በሰው ሕይወት ካለው ልዕልና ተሽሮ የየሰዉ ስሜት በመንበሩ በተተካበት ዓለም ጾታ ጭምር ሳይቀር ለምርጫ የተተወ ነገር ሆኗል ። ማት ዋልሽ የሚባል አሜሪካዊ የፖለቲካ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ ባሰናዳው 'What is a woman?' የተሰኘ ዶክመንታሪ ላይ በየጎዳናው ላይ አስቁሞ ከጠየቃቸው የተለየ ንባብ እና ዕውቀት ከሌላቸው ሰዎች ጀምሮ ጾታን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እስከሚያስተምሩ ፕሮፌሰሮች ድረስ 'ሴት ማለት ምን ማለት ነው ?' የሚል ጥያቄ በተጠየቁ ጊዜ "ሴት ማለት ሴት ነኝ ያለ ሁሉ ነው ። " በሚል ምላሽ ተባብረዋል ። እንደ እነዚህ ሰዎች ከሆነ ጾታ ሥነ ሕይወታዊ መሠረት ያለውና ከተፈጥሯችን ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ ውቅር (Social construct) ነው ፤ ስለዚህም አንድ ሰው ሰውነቱ የወንድ ቢሆንም እንኳን ሴት መሆን ከፈለገ ሴት መሆን ይችላል ። ከላይ ያነሣናት ፈረንሳዊት ፈላስፋ ሲሞን ዴ ቡቮ ከሳርት ፍልስፍና በመነሣት ያመነጨችው ሐሳብ ነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ ማኅበራዊ ተቀባይነት አግኝቶ እና

---

[35] "Freedom for us today is something transcendent even of reason, and we no longer really feel that we must justify our liberties by recourse to some prior standard of possible rationality. Freedom – conceived as the perfect, unconstrained spontaneity of individual will – is it's own justification, its own highest standard, its own unquestionable truth." Hart, *Atheist Delusions*, 105.

[36] ዘለዓለማዊ የሚመስል ፣ ነገር ግን በቅጽበት እንደ ጉም ተኖ የሚጠፋ ፣ ከተደረገም በኋላ ሰላምን የሚነጥቅ ፣ ተቅበዝባዥ የሚያደርግ።

በተቋማት እና በሕግ የተደገፈ ሆኖ የምናገኘው ። በማት ዋልሽ ፊልም ላይ ካሉት ግሩም ትዕይንቶች አንዱ ዋልሽ ወደ አፍሪካ መጥቶ ማሳይ ለሚባል ጎሳ አባላት ይህን ሐሳብ ሊያስረዳቸው ሲሞክር የሚያሳየው ነው ። ይህን ሐሳብ ለማብራራት በሞከረ ቁጥር በሰዎቹ ፊት ላይ ከሚታየው ፍጹም ግራ መጋባት ፥ እንዲሁም ልክ ምንም ካልገባው ሕፃን ጋር ወይም ከነሆለለ ሰው ጋር እንደሚያወሩ መረዳታቸውን ከሚገልጸው ፈገግታቸው እና ሳቃቸው በላይ ምዕራባውያን ከእውነታ ለተፋቱበት መጠን ምስክር የሚገኝ አይመስለኝም ። ያን የሚያይ ሰው የጾታ ትርጉም ከጠፋበት "ሥልጡን" ማኅበረ ሰብእ እና ምንም ዓይነት የቴክኖሎጂ ፍንጭ በሌለበት ፣ የተጣራ ውሃ ፣ መብራት ፣ ዘመናዊ ሕክምና ወዘተርፈ በሌለበት ከሚኖሩት "ኋላ ቀር" ጎሳ እንዴት የኋለኛውን ላይመርጥ እንደሚችል አላውቅም ።

ሌላ ምሳሌ ልጨምር ። "National review" በተሰኘው ወርኀዊ መጽሔት የጥቅምት ሁለት 2023 እትም ላይ 'The end of medicine'[37] በሚል ርእስ አሌክሳንደር ራይኪን የተባለ ጸሐፊ ያሰናዳው አንድ ጥሩ መጣጥፍ ወጥቶ ነበር ። መጣጥፉ ትኩረት የሚያደርገው በሕክምና/በሐኪም እገዛ ስለሚደረግ ሞት ነው። ይህም ነገር በምዕራቡ ዓለም በስፋት ተግባር ላይ በመዋል የሚገኝ ነው። አንድ ሰው መሞት ከፈለገ በሕክምና ባለሙያዎች ታግዞ እንዲሞት ይደረጋል ። መጀመርያ መሞት መፈለጉን ይናገራል ፤ ከዚያም በፊርማው ያረጋግጣል ። የተቀረው የሕክምና ባለሙያው ሥራ ይሆናል ። በመጣጥፉ ውስጥ ብዙ አስደንጋጭ ታሪኮች ተካትተዋል ፤ አንዱን ብቻ ልጥቀስ ። አንዲት የሠላሳ ስድስት ዓመት የካንሰር ታማሚ መሞት መፈለጓን በፊርማዋ ታረጋግጣለች ። ጸሐፊው እንደሚነግረን መሞት እፈልጋለሁ ባዩ ሰው ድጋሚ የመጠየቅ ዕድል እንኳን አይሰጠውም ። አንዴ ካለ አለ ነው ። ታዲያ ይህችን ሴት የሚገድላትን መርፌ ይወጓታል። የወጓት መርፌ ግን ሊገድላት አልቻለም ። ስለሆነም አጠገቧ ባለው ትራስ አፍነው ይገድሏታል ።[38] ሰብአዊነት ።

ባጭሩ ሰዶማዊነትንም ሆነ የጠቀስኳቸውን ሌሎች ድኅረ ዘመናዊነት የወለዳቸው ችግሮች ቅቡልነት ያለው የማኅበረ ሰብእ አወቃቀር አካል ለማድረግ የሚሞከረውን ሙከራ ከመሠረታዊ ፍልስፍናዊ መነሻዎቹ ጋር አቆራኝቶ መመልከት ይገባል ብዬ አምናለሁ ። በሀገራችን የሚደረጉ የጸረ ሰዶማዊነትም ሆኑ ሌሎች መሰል እንቅስቃሴዎች በዋናነት የሚጎድላቸው ይህ ግንዛቤ ይመስለኛል ። ሰዶማዊነትን ከፍቺ ፣ ከውርጃ ፣ ከዘመናዊው የዝሙት ባህል እና ሌሎችም በየጊዜው ወደሀገራችን የሚተዋወቁ ነውሮች ነጥሎ መመልከት ይስተዋላል ። ሌሎችንም ችግሮች በተመለከተ እንቅስቃሴ ሲደረግ ከጀርባቸው ያለውን እና የሚጋሩትን መርዛማ ፍልስፍና ዘንግቶ ነገሩ ልንቃወመው የሚገባ መሆኑን ማጠየቅ ብቻ ይስተዋላል ። ነገር ግን አእምሮው በእነዚህ መርዛማ ሐሳቦች የተበከለ ሰው ነገሮችን የሚመለከትበት ዐይን ፈጽሞ የተለየ በመሆኑ ነገሩ መጥፎ መሆኑን በመናገር ሊያሳምኑት አይቻልም ። ይልቁንም ወደኋላ ሔዶ ስለ እውነት እና ስለ ነጻነት ያለውን ግንዛቤ ባዶነት ማሳየት ፤ በዚያ ባዶነትም ምትክ ፍጹም እውነታን ፥ ክርስትናን ፥ መተካት ያስፈልጋል ። ያ ካልሆነ ግን ሥራችን ሁሉ አረምን ከላይ ቀነጣጥቦ ወይም ጨፍጭፎ መተውን ይመስልብናል ። መፍትሔው ሥሩን ፈልጎ መንቀል ብቻ ነው ። 'ነገርን ከሥሩ ፣ ውሃን ከጥሩ' እንዲሉ አበው ።

፨ ፨ ፨

**ይህ ጽሑፍ ሳንጠግበው ለተለየን ፥ የሕይወቱ ልዩ መዓዛ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ ለጠራ ፥ የፍቅሩና የርኅራኄው ነገር ሁልጊዜም ለሚታወሰው ለውድ ወንድማችን ለናትናኤል ማርቆስ መታሰቢያ ይሁንልኝ ።**

[37] Alexander Raikin, "The End of Medicine," *National Review*, October 2, 2023, 27–32.
[38] Alexander Raikin, "The End of Medicine," *National Review*, October 2, 2023, 28.

## ምንጮች

Beauvoir, Simone de. *The Second Sex*. 1989 edition. n.d.

Butler, Christopher. *Postmodernism: A Very Short Introduction*. Oxford University Press, 2002.

Foucault, Michel. *The History of Sexuality, Vol. 2: The Use of Pleasure*. Knopf Doubleday Publishing Group, 2012.

Giannaras, Chrēstos, Andrew Louth, and Haralambos Ventis. *On the Absence and Unknowability of God: Heidegger and the Areopagite*. 2nd ed. T & T Clark International, 2005.

Gutting, Gary. *Foucault: A Very Short Introduction*. 2nd edn. Oxford University Press, 2019.

Hart, David Bentley. *Atheist Delusions: The Christian Revolution and Its Fashionable Enemies*. Yale University Press, 2009.

Hart, David Bentley, ed. *The New Testament: A Translation*. Yale University Press, 2017. https://doi.org/10.12987/9780300188493.

Hopko, Thomas. *Christian Faith and Same-Sex Attraction: Eastern Orthodox Reflections*. Second edition. Ancient Faith Publishing, 2015.

Hubbard, Thomas K., ed. *Homosexuality in Greece and Rome: A Sourcebook of Basic Documents*. Nachdr. Joan Palevsky Imprint in Classical Literature. Univ. of California Press, 2008.

Lewis, C. S. *The Abolition of Man*. Harper One, 2009.

Miller, Jim. *The Passion of Michel Foucault*. Simon & Schuster, 1993.

Nietzsche, Friedrich, and Friedrich Nietzsche. *The Gay Science: With a Prelude in German Rhymes and an Appendix of Songs*. 3. print. Edited by Bernard Williams. Cambridge Texts in the History of Philosophy. Cambridge University Press, 2004.

raikin, alexander. “The End of Medicine.” *National Review*, October 2, 2023, 27–32.

Rose, Seraphim. *Nihilism: The Root of the Revolution of the Modern Age*. Second Edition. St. Herman of Alaska Brotherhood, 2020.

Rubin, Charles T. *Eclipse of Man: Human Extinction and the Meaning of Progress*. New Atlantis Books. Encounter Books, 2014.

Sartre, Jean-Paul, John Kulka, Arlette Elkaïm-Sartre, and Jean-Paul Sartre. *Existentialism Is a Humanism =: L’Existentialisme Est Un Humanisme) ; Including, a Commentary on The Stranger (Explication de L’Étranger*. Yale University Press, 2007.

Stockton, frank. *The Lady, or the Tiger? And Other Stories*. Airmont publishing company, 1968.

Strickland, John. *The Age of Nihilism: Christendom from the Great War to the Culture Wars*. Paradise and Utopia: The Rise and Fall of What the West Once Was, volume 4. Ancient Faith Publishing, 202

# “ክፋትን እፈጥራለሁ”

ብንያም ፈቃዱ

† † †

“ብርሃንን ሠራሁ ፥ ጨለማውንም ፈጠርሁ ፤ ደኅንነትን እሠራለሁ ፥ ክፋትንም እፈጥራለሁ ፤ እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ።”

ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥7

※ ※ ※

“ክፋትን ስናየው እናውቀዋለን ።”[1] (We know evil when we see it.) የሚል አንድ አባባል አለ ። ይህ አባባል ምንም እንኳን የሚናገረው የክፋት መኖር ለሁሉም የሚታይ ገሀድ፣ ለማስረዳት ረቂቅ አመክንዮ የማያሻው መሆኑን ለማጠየቅ ቢሆንም አጥብቀው ሲከተሉት ግን ወደ ሞራላዊ አንጻራዊነት (Moral Relativism) የሚመራ ሆኖ ይገኛል ። ማለትም ለአንዱ በማያጠራጥር መልኩ እኩይ ሆኖ የታየው ለሌላው እንዲያ ሳይታየው ከቀረ ሁሉም ሰው ከራሱ የግል ዕይታ ተነሥቶ የራሱ ብቻ የሆነ የእከይ ብያኔ ላይ ይደርሳል ። ስለዚህም እኩይ የሚለው ቃል ከተናጋሪው ስሜት እና ምርጫ የሚሻገር ቀዋሚ ትርጉም አይኖረውም ።

ፕሌቶ ጽፎ ካኖራቸው የሶቅራጥስ ተዋሥኦዎች መካከል በአንደኛው ውስጥ የዩቲፍሮ አጣብቂኝ (The Euthyphro Dilemma[2]) ተብሎ የሚጠራ ጥያቄ አለ ። ሶቅራጥስ ዩቲፍሮ ከሚባል ወዳጁ ጋር ሲነጋገር ያቀረበለት ነው ። “Is the pious being loved by the gods because it is pious, or is it pious because it is being loved by the gods?[3] – ጻድቁ ጻድቅ የሆነው አማልክቱ ስለወደዱት ነው ? ወይስ አማልክቱ የወደዱት ጻድቅ ስለሆነ ነው ?” በሌላ አነጋገር በጎ እና ክፉ ፣ ቅዱስ እና ርኩስ ስንል የአማልክቱን መውደድና መጥላት ማለታችን ነው ወይስ በጎነት እና ክፋት ከአማልክቱ በአፍአ ያሉ ቀዋሚ ነገሮች ናቸው?

ለምሳሌ አሥርቱን ትእዛዛት ብንወስድ ፣ የተከለከሉት ነገሮች የተከለከሉት እግዚአብሔር ስለማይወዳቸው ነው ወይስ እግዚአብሔር ያልወደዳቸው ነገሮቹ በራሳቸው ክፉ ስለሆኑ ነው ? ማመንዘር ክፉ የሆነው እግዚአብሔር ስለከለከለው ነው? ወይስ እግዚአብሔር ማመንዘርን የከለከለው ድርጊቱ በራሱ ክፉ ስለሆነ ነው ?

እርግጥ ሶቅራጥስ ሌላ ቦታ ላይ ከክሪቶ ጋር በነበረው ሙግት ይህን የራሱን ጥያቄ እንዲህ ሲል መልሶታል ።

> “መቼም ቢሆን እያወቅን ስሑት የሆነውን ነገር ማድረግ የለብንም እንላለን ? ወይስ አንዳንዴ (አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥመን) ብናደርገውም ግድ የለም እንላለን ? ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንደተስማማነው ስሑት የሆነው ነገር መቼም ቢሆን በጎ ሊሆን አይችልም ? ወይስ ከዚህ በፊት የነበሩን ስምምነቶች ሁሉ ባለፉት ጥቂት ቀናት (የሞት ፍርድ ስለተፈረደብኝ) ተሽረዋል ? እኔ እና አንተስ በዚህ ዕድሜያችን ከልጆች የማንሻል መሆናችንን ሳናስተውል ኖሯል ቁም ነገር በመነጋገር ጊዜያችንን ያጠፋነው ? ወይስ አሁንም ቢሆን ያኔ በተስማማንበት ነገር እንጸናለን ፤ ብዙዎች ቢስማሙም ባይስማሙም ፥ አሁን ካጋጠመን የባሰም ሆነ ያነሰ ፈተና ቢገጥመን ፥ በማንኛውም ሁኔታ የማይገባውን

[1] Taylor Triston, “Demons of the Self: Tristen Taylor Wonders How to Define Evil,” *Philosophy Now* Published By Anja Publication 148, no. 148 (2022): 24.

[2] George Matthews and Christina Hendricks, eds., *Introduction to Philosophy: Ethics* (Rebus Community, 2019), 19.

[3] Plato et al., *The Trial and Death of Socrates: Euthyphro, Apology, Crito, Death Scene from Phaedo*, 3rd ed (Hackett Pub, 2000), 11.

ነገር ማድረግ ክፉና አሳፋሪ ነገር ነው ። በዚህ አቋማችን እንጸናለን ወይስ አንጸናም ?”[4]

ክፉት እንደ ተመልካቹ ነው ከሚሉት ጋርም ሆነ ከሶቅራጥስ ጋር ከመስማማታችን ወይም አባባላቸውን ከመንቀፋችን በፊት ግን ‘ክፉትን ክፉት ፣ በጎንም በጎ የሚያሰኘው ምንድነው ? ክፉት ምንድነው ? በጎነትስ?’ የሚሉትን ጥያቄዎች ማስቀደም ይገባል ።

**የክፉት ምንነት**

በኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያው ምዕራፍ መጨረሻ ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናገኛለን ፥ “እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ ዐየ ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ ”(ዘፍ 1፥31)። ምንም እንኳ በዚህ ክፍል ውስጥ በፍጥረት መካተቻ ዕለት የተፈጠሩት ሁሉ መልካም እንደሆኑ ተዘግቦ ቢገባደድም በወንጌል ደግሞ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ ከ’ክፉ አድነን’ (ማቴ 6፥13) ብለን እንድንለምን አስተምሮናል ። ያለ ምንም ተሰናስሎታዊ ሐሳብ ፣ አገናኝ እና ማብራሪያ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐረጋት ለሚመለከት የተቃረኑ ሊመስለው ይችላል ።[5] የቀደመው ጥቅስ ፍጥረት ሁሉ መልካም መሆኑን ያስረዳናል ። የኋለኛው ደግሞ ድኅነትን እንድንለምን የሚያደርገን ክፉት መኖሩን ያስረዳናል ።

ወደ ትንቢተ ኢሳይያስ ሄደን በዚህ ጽሑፍ መጀመሪያ የጠቀስነውን ክፍል ስንመለከት ደግሞ እግዚአብሔርን በነቢዩ በኩል “ደኅንነትን እሠራለሁ ፤ ክፉትንም እፈጥራለሁ ።” ሲል እናገኘዋለን ። ስለዚህም ክፉት መኖሩን ብቻ ሳይሆን ፈጣሪውም ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረው እና ፈጥሮ ሲያበቃም የፈጠረው ሁሉ መልካም መሆኑን ያየው ያው ፈጣሪ መሆኑን የሚነግረን ይመስላል ። ቅራኔውም ካለፈውም የሚበረታ ይመስላል ።

እነዚህ ቃላት ተጻራሪ እንደሆኑ የተሰማው ሰው ከሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መካከል ‘ክፉት ምንድነው ? እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ ባየበት ዓለም ውስጥስ ክፉት ከየት መጣ ?’ የሚሉት ዐበይት ናቸው ። እነዚህ ጥያቄዎች ፍልስፍናዊ በሆኑ ውይይቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ይስተዋላሉ ። ገፋ ሲልም ‘የእኩይ ፣ የመከራ እና የሥቃይ መኖር ከሃሌ ኵሉ (omnipotent) ፣ ምሉእ በኵለሄ (omnipresent) እና ማእምረ ኵሉ (omniscient) ከሆነው እግዚአብሔር መኖር ጋር እንዴት ይታረቃል ?’ የሚል ጥያቄ ይቀርባል ። በእግዚአብሔር ህልውና የማያምኑ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ስለ እምነት ጥያቄዎች በቁም ነገር የሚያስቡ አማኞችም ጭምር ብዙውን ጊዜ ይህን መሳይ ጥርጣሬ ይገባቸዋል ፦ “እግዚአብሔር ካለ ፣ በእርግጥ ክፉት በዓለም ላይ ለሺህ ዓመታት እንዲነግሥ ይፈቅድ ነበር ?”[6]

ለእነዚህ ጥያቄዎች በተወሰኑ አባቶች ትምህርት ውስጥ መልስ ልናገኝላቸው እንሞክራለን ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስን የመጀመሪያ እናድርገው ። እንዲህ ይላል ፦

> “ክፉት ሁሉ በጠባዩ ከመልካም ነገር መራቆት አለበት ። ክፉት በራሱ አይኖርም ፣ ምንነት ያለው ተደርጎ መታሰብም አይችልም ። ምክንያቱም ማንኛውም ዓይነት ክፉት ከሠሪው ፈቃድ ውጭ ራሱን ችሎ አይገኝምና ። ይልቁንም የመልካም ነገር አለመኖር (መታጣት) ነው ‘ክፉት’ ተብሎ የተጠራው ። ቀድሞውኑ ህልውና የሌለው ነገር ምንነት የለውም ፥ ከዚህ ተገኘ ፣ ከዚህ ተበጀ አይባልም ። ህላዌ እና ምንነት የሌላቸውን ነገሮች ያስገኘው ደግሞ ህላዌ እና ምንነት ያላቸውን ነገሮች የፈጠረው እርሱ አይደለም ። ስለሆነም ‘የሆኑትን’ ነገሮች የፈጠረው አምላክ ክፉትን ያስገኘው አይደለም ፣ እርሱ ‘ያልሆኑትን’ (ህላዌ የሌላቸውን) ነገሮች አልፈጠረምና ። ዕይታን ያስገኘ እርሱ ዕውርነትን አልፈጠረም ፤ ጽድቅን የገለጠ እርሱ የጽድቅን መታጣት ደግሞ አልገለጠም ፤ በነጻ ፈቃድ በሚደረግ ውድድር ጽድቅን ገንዘብ ላደረጉ በጎ የሆነውን ሁሉ ሽልማት አድርጎ ያቀረበው እርሱ ራሱን ለማስደሰት ሲል የሰውን ልጅ ያለፈቃዱ የሚገዛው ፣ ሕይወት እንደሌለው እቃ ሳይፈልግ በጎ ወደሆነው

---

[4] Plato et al., *The Trial and Death of Socrates: Euthyphro, Apology, Crito, Death Scene from Phaedo,* 3rd ed (Hackett Pub, 2000)

[5] Tomáš Špidlík, “*The Spirituality of the Christian East.* 1,” in The Spirituality of the Christian East. 1, Cistercian Studies Series 79 (Cistercian Publ, 1986), 137.

[6] Alexander Schmemann, *A Voice for Our Time* (Saint Vladimir’s Seminary Press, 2021), 341.

ምርጫ የሚነትተው ቀንበር አልጫነበትም ። ብራ በሆነ ሰማይ ላይ ፀሐይ በድምቀት እያበራች ሳለች አንድ ሰው በራሱ ፈቃድ ዐይኖቹን ቢዘጋ ፣ ላለማየቱ እርሷ ተጠያቂ ልትደረግ አትችልም ።"[7]

በዚህ የጎርጎርዮስ ንግግር ዉስጥ ክፋት 'የበጎነት አለመኖር ወይም መታጣት' እንዲሁም 'በራሱ ህላዌ እና ምንነት የሌለው' ተብሎ ተገልጧል ። በሌላ አባባል ክፋት ፍጡር ለባሕርይው የተሠጡትን የአነዋወር አማራጮች (existential possibilities) ይሁነኝ ብሎ በመቃወም ፥ የተገቡ ሆነው ወደ አልተሰጡት አማራጮች በመሄድ ፥ ለተፈጥሮ በተሠራው ዕቅድ ውስጥ ባልነበሩት ፥ ባልተፈጠሩት ኩነቶች ውስጥ በመሳተፍ [8] በፍቅር እና በነጻነት አኳኋን ላይ የሚደረግ አመጽ ነው ።

"እከይ ምንጊዜም ቢሆን ፈቃድ ካላቸው አካላት ነው የሚመጣው ። ቃሉን በተመጠነ ትርጉሙ መሠረት ስንጠቀመው ፣ እከይ ባለፈቃድ በሆኑ ነዋሪዎች እና በእነሱ ፈጠራዎችና ድርጊቶች ውስጥ ብቻ ነው የሚገኘው ። አካላዊ ለሆነውም ሆነ በተፈጥሮ ራሱን ለሚገልጠው እከይ ምንጩ ፈቃድ ያለባቸው ድርጊቶች ናቸው ። ለዚህም ነው እከይ ኃይል የሚኖረው ፤ የተጣመመም ቢሆን ፈቃድ ያለበት እንቅስቃሴ ነውና ። ነገር ግን መቼም ቢሆን ከፈቃድ ፈጽሞ ሊላቀቅ አይችልም ። ያን ለማድረግ ሊታለፍ የማይችል ገደብ አለበት ። ነገር ግን ክፋት ወደዚህ ጨርሶ ወደሚያጠፋው ገደብ ለመድረስ ያለው ዝንባሌ እና የሚያደርገው ግስጋሴ በየቦታው ኃይልን ይሰበሳል ፣ ይደርባልም ።"[9]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከላይ ፀሐይን ተጠቅሞ ያደረገውን ምሳሌ 'የሙሴ ሕይወት' በሚለው በሌላኛው መጽሐፉ የበለጠ ያብራራዋል ። እዚህ ጋ ደግሞ አሪት ዘጸአት ላይ 'እግዚአብሔር የፈርኦንን ልብ አደነደነው ።' የሚለውን ቃል ለማብራራት ፥ ከቅዱስ ጳውሎስ "እግዚአብሔርን ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ።"(ሮሜ 1÷28) የሚለውን አገላለጽ በመዋስ የክፋትና የርኩሰት ሁሉ ምንጭ የገዛ ፈቃዳችን እንደሆነ ያሳየናል ።

"ይህ ፀሐይን ላለማየት ዐይኑን የጨፈነን ነገር ግን በጉድጓድ ሲወድቅ ደግሞ 'በፀሐይ ምክንያት ወደቅሁ' ብሎ የሚያማርርን ሰው ይመስላል። መቼም ሰማያዊት የሆነችው ፀሐይ 'ለምን አላየኸኝም ?'ብላ በንዴት ሰውን ገፍትራ ወደ ጉድጓድ አትጥልም ። ሁነቱን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ከተመለከትነው ፥ ሰውየው ጉድጓዱን እንዳያይ እና እንዲወድቅ ያደረገው በብርሃኑ ውስጥ አለመሳተፉ እንደሆነ አያጠያይቅም ። የሐዋርያውም መልእክት እንዲሁ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል ።

[7] "Now all wickedness has its form and character in the deprivation of the good; it exists not by itself, and cannot be contemplated as a substance. For no evil of any kind lies outside and independent of the will; but it is the non-existence of the good that is so denominated. Now that which is not has no substantial existence, and the Maker of that which has no substantial existence is not the Maker of things that have substantial existence. Therefore the God of things that are is external to the causation of things that are evil, since He is not the Maker of things that are non-existent. He Who formed the sight did not make blindness. He Who manifested virtue manifested not the deprivation thereof. He Who has proposed as the prize in the contest of a free will the guerdon of all good to those who are living virtuously, never, to please Himself, subjected mankind to the yoke of a strong compulsion, as if he would drag it unwilling, as it were his lifeless tool, towards the right. But if, when the light shines very brightly in a clear sky, a man of his own accord shuts his eyelids to shade his sight, the sun is clear of blame on the part of him who sees not."Gregory et al., Gregory of Nyssa, *Dogmatic Treatises* (Cosimo Classics, 2007), 897–98.

[8] Christos Yannaras, *The Enigma of Evil* (Holy Cross Orthodox Press, 2012), 107.

[9] "Evil is created by personal agents. Evil, in the strict sense of this word, exists only in persons or in their creations and their acts. Physical and cosmic evil also originates from these personal acts. And that is why evil can have a power, can be active. For evil is a perverse personal activity. But this activity inevitably spreads itself to the impersonal. Evil de-personalizes personality itself. Complete de-personalization, however, can never be achieved; there is a potential limit which can never be attained. But the tendency and the aspiration of evil toward this limit of total disintegration is energetically accentuated everywhere…" Georges Florovsky, *The Collected Works of Georges Florovsky. 3: Creation and Redemption* (Büchervertriebsanst, 1976), 87.

> እግዚአብሔርን በአምላክነቱ ያላወቁት ናቸው ለነውራቸው የተተውት ። እናም የጨቋኙ የፈርኦን ልብ የመደንደኑ ምክንያት መለኮታዊ ፈቃድ በፈርኦን ነፍስ ውስጥ አሻፈረኝ ባይነትን አስቀምጦበት አይደለም ፤ የፈርኦን ነጻ ፈቃድ ወደ ክፋት ያዘነበለ በመሆኑ ልብን የሚያለሰልሰውን ቃል ለመቀበል አሻፈረኝ በማለቱ እንጂ ።”[10]

የጎርጎርዮስን እንዲህ እጅግ በጣም በጥቂቱ ከተመለከትነው ሁለተኛ የምናደርገው ዲዮናስዮስን ይሆናል። ዲዮናስዮስ ‘Divine Names’ በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ በአራተኛው ምዕራፍ ነገረ-ክፋትን ይዳስሳል ። እንደ ዲዮናስዮስ ገለጻ ክፋት “‘ኋኝ’ ያይደለ፤ ‘በሆኑ’ ነገሮች ውስጥም የሌለ” ነው[11]።” ለምን የተባለ እንደሆን ህልው የተባለ ሁሉ እና ራሱ ህልውናም (existence) የተገኘው ፍጹም መልካም ከሆነው ልዕለ-ባሕርይ (Super-Essence) ነውና ።

እዚህ ጋ መነሣት የሚኖርበት ትልቅ ነጥብ ቁስ አካል (matter) በራሱ ክፉ ያለመሆኑ እውነታ ነው ። ይህን እውነት አባቶች በተደጋጋሚ በማያሻማ መልኩ አስተምረውታል ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሰውነት ወይም ሥጋዊ አካል (body) የክፋት መቀመጫም ፣ ምንጭም እንዳይደለ በብርቱ ሞግቷል ። ለምን የተባለም እንደሆነ “The body is the handiwork of God - ሥጋ የእግዚአብሔር የእጁ ሥራ ነውና ።”[12] ቅዱስ ባስልዮስም በተመሳሳይ በታወቀ ስብከቱ ላይ “ከእግዚአብሔር እጅ የሚወጣው ሁሉ መልካምነቱን የሚገልጥ ነው ።” ብሏል[13]። ስለሆነም ከእርሱ መሆንን ያገኙ ነገሮች ሁሉ መልካም ናቸው ። ለዚህም ነው ዲዮናስዮስ አጋንንትም እንኳን ቢሆኑ በተፈጥሮአቸው ክፉ አይደሉም የሚል ።[14] “(የአጋንንት) እኩይነታቸው ከተሰጣቸው ገንዘብ (ባህርይ) መውጣታቸው ነው ። ዳግመኛም በማንነታቸው እና በአነዋወራቸው ከተገባቸው መልአካዊ ፍጽምና መለወጣቸው ፣ መጉደላቸው ነው ። መሆንን ፣ መኖርን እና ማሰብን ዓላማ እስካደረጉ ድረስ በጎነትን ያልማሉ ። በጎነትን ዓላማ ባላደረጉ መጠን ግን አለመሆንን (ኢህላዌን) ዓላማ ያደርጋሉ ። ይህ ግን ዓላማ አይደለም ፥ የእውነተኛው ዓላማ መጥፋት እንጂ።”[15] ስለሆነም ፥ ክፉ የሆነ ነገር ኢ-ህልው (non-existent) ነው።[16]

“(ከዚህ በኋላ) ክፋት መልካም የሆነው ነገር እጥረትና መዳከም ነው ብለን መደምደም ብቻ ነው ያለን አማራጭ ። . . . ስለዚህም ክፋት የእድገት ፣ የዓላማ ፣ የባህርይ ፣ የአመክንዮ ፣ የምንጭ ፣ የግብ ፣ የብያኔ ፣ የፈቃድና የምንነት ተቃራኒ ነው። ክፋት ጉድለት፣ እጥረት፣ ድካም፣ አለመመጣጠን፣ ኃጢአት (ማጣት) ነው ።”[17]

---

[10] “It is as if someone who has not seen the sun blames it for causing him to fall into the ditch. Yet we do not hold that the luminary in anger pushes into the ditch someone who does not choose to look at it. Rather, we would interpret this statement in a more reasonable manner: It is the failure to participate in the light that causes the person who does not see to fall into the ditch. In the same way, the thought of the Apostle should be clear, that it is those who do not acknowledge God who are delivered up to shameful affections, and that the Egyptian tyrant is hardened by God not because the divine will places the resistance in the soul of Pharaoh but because the free will through its inclination to evil does not receive the word which softens resistance.”Gregory Nyssa, *The Life of Moses*, The Classics of Western Spirituality (Paulist Press, 1978), 74.

[11] “The Evil, then, is not an actual thing, nor is the Evil in things existing.”Dionysius the Areopagite, *The Works of Dionysius the Areopagite*. 1 (Southampton-Street, Strand, London; and 27 Broad Street, Oxford., 1897), 71.

[12] Špidlík, “*The Spirituality of the Christian East*. 1,” 138.

[13] Ibid, p.138

[14]“But their evil is from the declension from their own proper goods, and a change – the weakness, as regards their identity and condition, of the angelic perfection befitting them. And they aspire to the Good, in so far as they aspire to be and to live and to think. And in so far as they do not aspire to the Good, they aspire to the non-existent; and this is not aspiration, but a missing of the true aspiration.” Areopagite, *The Works of Dionysius the Areopagite*. 1, 71.

[15] Areopagite, The Works of Dionysius the Areopagite. 1, 71.

[16]ጎርጎርዮስ ዘኑሲስም በተመሳሳይ ስለ አጋንንት “(They are) angels by nature, and angelic dignity is not completely abolished in them.” ይላል። *Florovsky, The Collected Works of Georges Florovsky*. 3, 91.

[17] "What we are left with is this, namely, that evil is a weakness and a deficiency of the Good . . . Thus, evil is contrary to progress, purpose, nature, cause, source, goal, definition, will, and substance. It is a defect, a deficiency, a weakness, a disproportion, a

እንደ ዲዮናስዮስ አገላለጽ ክፋት የመልካምነት ተውሳክ (ጥገኛ) ሆኖ (parasitical existence) የሚኖር ነው ። ካንሰር የሚገኘው በሰውነት ውስጥ ሆኖ የሚኖርበትን ሰውነት እንደሚያበላሽና እንደሚያጠፋ ፤ መኖሩም በዚያ አካል መጎዳትና መጥፋት እንደሚታወቅ ሁሉ ክፋትም የሚኖረው በሚያጠፋው (deform) መልካም ነገር ወይም በጎ ነገር ብቻ ነው ። መልካም እና በጎ የሆነው ደግሞ ከላይ እንዳነሣነው ከእግዚአብሔር የተገኘውና የእርሱ ፈቃድ የሆነው ሁሉ ነው ። እንዲህ ባለው መረዳት መሠረት ፤ የክፋት ምንጩ ኃጢአት ነው ፤ ምክንያቱም ኃጢአት ከእግዚአብሔር መቃረን እና ከእርሱ መለየት ነውና ።[18] ከዚህም የምንረዳው ክፋት የራሱ ማንነት ወይም ምንነት ያለው የመልካምነት ባለጋራ ሳይሆን የመልካምነት ሐሰተኛ ቅጂ (counterfiet) ፥ የመልካምነት መጣመምና መዛባት መሆኑን (perversion) ነው[19]። ክፋት የመንፈስ ክሂላት(spiritual faculities) ወደ ተሰጣቸው መዳረሻ ያይደለ ወደ ሌላ ነገር የሚያደርጉት ኢ-ምክንያታዊ እንቅስቃሴ ነው ።[20] እዚህ ጋር ሊሰመርበት የሚገባው ዐቢይ ነጥብ ክፋት ከፈቃድ የሚወለድ እንጂ ፍጥረት ከሆኑ ነገሮች ወገን የሆነ በራሱ የሚቆም ፍጡር አለመሆኑ ነው ፤ ይልቁንም ክፋት ጥላ ብቻ ነው ፤ ማለትም የምክንያታዊ ፍጥረታት ልብ እና አእምሮ ከእግዚአብሔር ብርሃን ፈቀቅ ማለት እና ወደ ምንምነት (nothingness) መዞር ነው ።[21]

ከቅዱስ ጎርጎርዮስ እና ከዲዮናስዮስ በተጨማሪ ፤ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ለየት ባለ ቋንቋ ይህንኑ ሐሳብ ያጠናክራል ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደ ሁለቱ አባቶች ረቂቅ ፍልስፍናዊ ቋንቋን ከመጠቀም ይልቅ ሥነ ምግባራዊ እና ተጨባጭ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ቢያተኩርም ያው በሁለቱ አባቶች ውስጥ የተገለጠው ሐሳብ ግን እርሱም ጋር በምልአት ይገኛል ። ይህ አባት ‘ኢጋንንት በሰዎች ጉዳይ ሥልጣን አላቸው’ ባዮችን በተቃወመበት ድርሳኑ “በራሳቸው እኩያን ‘የሆኑ’ ነገሮች አሉ ፡- እነርሱም ማመንዘር ፤ ዝሙት ፤ ፍቅረ ንዋይ እና ቁጥር የሌላቸው መሰል የሚያስጠሉ እና የሚያሳፍሩ የመጨረሻው ዘለፋና ቅጣት የሚገባቸው ነገሮች ናቸው ። ሌሎች ደግሞ አሉ ፥ እኩያት ተብለው የሚጠሩ ነገር ግን በእውነቱ እኩያት ያይደሉ ። እነዚህም ረኃብ ፤ ወረርሽኝ ፤ ሞት ፤ በሽታ እና የመሳሰሉት ናቸው ። እነዚህ እኩያት አይደሉም ፤ ናቸው እንላቸዋለን እንጂ ። ምክንያቱም እኩያት ቢሆኑ ትዕቢታችንን በመገሰጽ ፤ ስንፍናችንን በማባረር ፤ ወደ መነሣሣት እየመሩን እና ትኩረታችንን ወደሚገባው ቦታ እየሳቡልን የመልካም ነገር መገኛ ባልሆኑልን ነበር ።”[22] ይላል ።

---

sin.” Pseudo-Dionysius et al., *Pseudo-Dionysius: The Complete Works*, The Classics of Western Spirituality (Paulist Press, 1987), 66.

[18] “. . . Undoubtedly evil lives only through the Good which it deforms, but which it also adapts to its needs... And the meaning of evil is a radical opposition to God, a revolt, a disobedience, a resistance. And the unique source of evil, in the strict sense of the term, is sin, the opposition to God and the tragic separation from Him.’’ Florovsky, *The Collected Works of Georges Florovsky*. 3, 91. በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ፍሎሮቭስኪ “Hell is a sinister testimony to the staggering power of evil – ሲኦል ማለት ሚዛን ለሚያሳጣ(ለሚያንገዳግድ) የክፋት ኃይል ምስክር ነው”ይላሉ።(እዚህ ጋር መነሣት የሚገባው ነጥብ ቢኖር Christos Yannaras “*The Enigma of Evil*” በሚለው መጽሐፉ የ George Florosvskyን የነገረ ክፋት መረዳት ከመሠረቱ እንደሚተቸው ነው።ለበለጠ ንባብ መጽሐፉን ይመልከቱ።)

[19] “evil’ is not the open refutation of ‘good’ but its counterfeit and perversion.” Christos Yannaras and Keith Schram, *Faith as an Ecclesial Experience*, Contemporary Christian Thought Series, number 62 (St. Sebastian Orthodox Press, 2020), 97.

[20] “Evil is the irrational movement of the spiritual faculties toward something else than toward their final goal, because of a mistaken judgment. Now the final goal I call the Cause of things, toward which all things move in a natural way, even if evil, covering its envy under the image of goodness, by cunning persuades man to turn his longing toward something else than the Cause of all things, creating in him the ignorance of the Cause.” Dumitru Stăniloae, *Orthodox Spirituality* (St. Tikhon’s Seminary Press, 2002), 78.

[21] “Evil is born in the will: it consists not in some other separate thing standing alongside the things of creation, but is only a shadow, a turning of the hearts and minds of rational creatures away from the light of God back toward the nothingness from which all things are called.” David Bentley Hart, *The Doors of the Sea: Where Was God in the Tsunami?* (Wm. B. Eerdmans Publishing Co, 2011), 73.

[22] “There is then evil, which is really evil; fornication, adultery, covetousness, and the countless dreadful things which are worthy of the utmost reproach and punishment. Again there is evil, which rather is not evil, but is called so, famine, pestilence, death, disease, and others of a like kind. For these would not be evils. On this account I said they are called so only. Why then? Because, were they evils,

ይህንም በማለቱ ክፉት እና እክይ በተፈጥሮ ከሚመጡ እና በሰው ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ሁነቶች ወይም ያለ ፈቃዳችን ከሌሎች ሰዎች ከምንቀበለው መከራ ጋር ሳይሆን በፈቃዳችን ከምንፈጽማቸው እና ከእግዚአብሔር ፈቃድ እንድንወጣ ከሚያደርጉን ሐሳቦች እና ድርጊቶች ጋር መያያዛቸውን ያስተምረናል ። በጥቅሉ እከይ ወይም ክፋት ትክክለኛ ትርጉሙ የሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ የመለየቱን ሁናቴ ፣ ማለትም ኃጢአትን የሚያሳይ እንደሆነ የሦስቱ አባቶች ምስክርነት ያስረዳናል ።

እንግዲህ የክፉትን ትርጉም በጥቂቱም ቢሆን ይህን ያህል ካየን ፥ አሁን ደግሞ ቀድመን ያስቀመጥነውን ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥7 ላይ የሚገኘውን 'ክፉትንም እፈጥራለሁ' የሚለውን ኃይለ ቃል ይህን የእነርሱን ብያኔ ይዘን ለመረዳት እንሞክራለን ። ኃይለ ቃሉን በቀጥታ ለመተርጎም ከመሞከራችን በፊት ግን የተባለበትን ዓውድ መረዳት ይኖርብናል ።

**ጥቅል ዓውድ**

በጥቅሉ ከምዕራፍ 40-48 ያለው የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል ከቀደመው ክፍል (ከምዕራፍ 1-39) እጅግ በጣም የተለየ ይዘት እንዳለው ገና ከጅምሩ በሚጠቀመው ርኅራኄ የተሞላበት የአነጋገር ሁኔታ በቀላሉ መረዳት ይቻላል ። ለሕዝቡ የማጽናናት ቃል በማሰማትና ኃጢአታቸው ይቅር እንደተባለላቸው በመናገር ነው የሚጀምረው (ኢሳ 40፡1) ። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር በንጉሥ ቂሮስ አማካይነት ተስፋ ሰንቀው የኖሩትን ሕዝቦቹ እንዴት ከባቢሎናውያን እጅ እንደታደገና ወደ አገራቸው እንደመለሳቸው ይተርካል ። እግዚአብሔር ራሱ ቂሮስን *“ሕዝቤን የምታስተዳድርልኝ እቅዴን ሁሉ የምትፈጽም፤ ኢየሩሳሌም እንድትሠራና የቤተ መቅደሱም መሠረት እንዲጣል የምታደርግልኝ”* ይለዋል (ኢሳ 44፡ 28) ። ቂሮስ ባቢሎናውያንን አሸንፎ ከ539-333 ዓ.ዓ ልዑለ ኃይል ሆኖ የቆየውን ሥርወ መንግሥት የመሠረተው የፋርስ (የዛሬይቱ ኢራን) ንጉሠ ነገሥት ነው ። ይህ ክፍል በዋናነት የባቢሎን ኃያልነት ማብቃቱን ፥ የአይሁዳውያንም ስደት መፈጸሙን ያስረዳል ። ባቢሎንና አማልክቷ ፍጻሜአቸው እጅግ በጣም የሚያሳዝን እንደሚሆን ነቢዩ በተደጋጋሚ ይናገራል ። እግዚአብሔር ከማንም ጋር ሊወዳደር እንደማይችልና እርሱንም የሚመስል ሌላ አምላክ እንደሌለ በመግለጽ ፥ ኢየሩሳሌምን የሚያድንበትንና ለእስራኤልም ክብርን የሚያጎናጽፍበት ጊዜ መቃረቡን በመናገር ሕዝቡን ያጽናናል (ኢሳ 46) ። በዚህ ክፍል በነቢዩ ትኩረት የተሰጠው ሌላው ጉዳይ በእግዚአብሔር የተደገፈው ፥ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትና ሕዝቡን ሁሉ በትክክለኛ ፍትሕ የሚያስተዳድረው መልካም አገልጋይ ዜና ነው ። ይህ አገልጋይ ድምጹን ከፍ አድርጎ የማይጮኽ ፣ የተቀጠቀጠ ሸንበቆ እንኳ የማይሰብር ፣ ፈጽሞ ተስፋ የማይቆርጥ ፣ ፍትሕን በምድር ላይ የሚመሠርትና በሩቅ ያሉ አገሮች ሁሉ የእርሱን ትምህርት ለመስማት በብርቱ የሚናፍቁት መልካም አገልጋይ እንደሆነ ነቢዩ በስፋት የሚያስረዳበት ክፍል ነው[23]።

ይህን ዓውድ ያመጣሁበት መሠረታዊ ዓላማ ለማብራራት የመረጥነውን ዓረፍተ ነገር በጊዜው ከነበረው ታሪካዊ ሐቅ ጋር በጥብቅ አገናኝተው የጻፉ ብዙ መተርጉማን ስላሉ ነው። ለምሳሌ በአይሁድ ታናክ (Tanakh) ውስጥ እግዚአብሔር ‘ብርሃንን ሠራሁ፥ ጨለማውንም ፈጠርሁ ፤ ደኅንነትን እሠራለሁ ፥ ክፉትንም እፈጥራለሁ ።’ ማለቱ ጨለማ በራሱ የብርሃን አለመኖር እንጂ በራሱ ምንም ስለሆነ . . . ክፉትም እዚህ ጋር የተሠጠው ትርጓሜ የሰላም አለመኖር - ማለትም ጦርነት - መሆኑን የሚናገር ትርጓሜ አለ ። በዚህ ትርጓሜ መሠረት ‘ክፉትን እፈጥራለሁ’ ማለቱ እግዚአብሔር በፋርስና በባቢሎን መካከል ጦርነትን እንደሚያመጣ እና ንጉሥ ቂሮስን እንደሚያበረታው ፥ የባቢሎንን ንጉሥ ደግሞ እንደሚያዳክመው ሲናገር ነው ።[24] በተጨማሪም ለቅኖች ብርሃንን የሠራ ለባቢሎንም ጨለማን የፈጠረ እርሱ እንዲሁ ለቅኖች ደኅንነትን የሚሠራ፥ ለክፉዎች ደግሞ

they would not have become the sources of good to us, chastening our pride, goading our sloth, and leading us on to zeal, making us more attentive.” St. John Chrysostom, “Against Those Who Say That Demons Govern Human Affairs,” John Chrysostom, *On the Priesthood ; Ascetic Treatises ; Select Homilies and Letters ; Homilies on the Statues*, ed. Philip Schaff, trans. W. R. W. Stephens (Cosmo Classics, 2007), 249.

[23] *ነቢይ ማነው?* (2006)፣ በአባ ምሥራቅ ጥዩ የተዘጋጀ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ *ሥራ መምሪያ የታተመ* ፣ 57።

[24] “For darkness is nothing by itself, it is but the absence of light…The same is to be said concerning and causeth evil. By evil war is meant as the opposite of peace, or the sickness under which man labours, as being at war with his constitution. These antitheses are used to indicate that in the same way God will strengthen Cyrus and weaken the king of Babylon.” Ibn Ezra, Sefaria.

ክፉትን የሚሠራ (እንደሥራቸው ብድራታቸውን የሚመልስላቸው ፣ የሚያጠፋቸው) በማለት የተረጎሙም አሉ። [25]

እዚህ ጋር ልብ ማለት የሚገባው ጨለማን የፈጠረ ሲባል ከላይ በጎርጎርዮስም ይሁን በዲዮናስዮስ ምሳሌ እንደተረዳነው ጨለማ ከእግዚአብሔር ብርሃንነት ሱቱፍ ሳይሆን ሲቀር ያለ አኳኋን (state) ነው እንጂ ኳኝ ሆኖ ከእርሱ የተገኘ አይደለም ። ቅዳሴ ማርያም ላይ መስዋዕቱን አስመልክቶ የተሰጠው ሐተታ ለዚህ ጥሩ አስረጂ ነው ። “ወዮ ከአንቺ የተገኘ ኅብስት በማመን ከእርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትንና ደኅንነትን የሚሰጥ ነው ። ወዮ ከአንቺ የተገኘ ኅብስት በማመን ከእርሱ ለማይቀበሉ ሰዎች የማይላመጥ ጽኑ ነው ። ይኸውም ኃያል የሚሆን የአድማስ ደንጊያ ነው ። ወዮ ከአንቺ የተገኘ ጽዋ በማመን ከእርሱ ለሚጠጡ ሰዎች ጥበብን የሚገልፅ ሕይወትንም የሚሰጥ ነው። ወዮ ከአንቺ የተገኘ ጽዋ ፣ በማመን ከእርሱ ለማይጠጡ ሰዎች የሚያሰክርና የሚያፍገመግም ፣ የሚጥልና ኃጢአትን ስለሚያስተው ፈንታ ኃጢአትን የሚጨምር ነው ።”[26] ኅብስቱ አንድ ነው ፤ ጽዋውም አንድ ነው ። ውጤቱ ግን እንደተቀባዮቹ እምነትና አነዋወር የሚለዋወጥ ነው ።

ቀጥለን ደግሞ ይህን የነቢዩን የኢሳይያስን ቃል የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንዴት እንደተረጎሙት እንመልከት።

**ክፉትን እፈጥራለሁ?**

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን ምንባብ እንዲህ ይተረጉመዋል ።

> “እኩይ የሚለውን ቃል ስለ ሌብነትና ስለ አመንዝራነት (ወዘተርፈ) ብቻ ሳይሆን ስለ ተፈጥሮአዊ አደጋና ጥፋት ወይም መቅሰፍት (calamities) ለመናገርም ቃሉን መጠቀም ስለለመድን ፤ ነቢዩም ይህን ቃል ለመጠቀም ፈቀደ ። በዚህ መንገድ ነው ነቢዩ (አሞጽ) “እግዚአብሔር ያላደረገው ክፉ ነገር በከተማይቱ ውስጥ የለም” (አሞ 3፥6) ያለው ። ይህን ደግሞ በኢሳይያስ አማካኝነት እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ግልጽ አድርጓል ፡- “እኔ ሰላምን የማደርግና ክፉትን የምፈጥር አምላክ ነኝ” በማለት በድጋሚ ጥፋትን ወይም መቅሠፍትን ክፋት ብሎ ሰይሟል ።[27] ክርስቶስም ለደቀ መዛሙርቱ፣ “ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል" ሲል ይህን ማለቱ ነው ፤ ስቃዩ ፣ መከራው ለማለት ነው ። እዚህም ጋ (ነቢዩ አሞጽ) የእኛን ልማድ ተከትሎ ክፋት ያለው ቅጣትን እንደሆነ ግልጽ ነው ። ይህንም በማለቱ እግዚአብሔር ቅጣትን በእኛ ላይ ማምጣቱን ያረጋግጣል ። ይህም ስለመግቦቱ የላቀ እይታ ይሰጠናል ። ባለመድኃኒቱ በሽተኛውን ወደ አትክልት ስፍራና ወደ ሜዳ ሲያወጣ ወይም ወደ ገላ መታጠቢያ ገንዳና ወደ መዋኛ ገንዳ ሲያወጣ ፣ የተጌጠ ጠረጴዛም በፊቱ ሲያዘጋጅ ብቻ ሳይሆን፤ ያለ እህል እንዲቆይ ሲያዘው፣ በረኃብ እና በውሃ ጥም ሲያስጨንቀው፣ በአልጋው ላይ አስሮ ቤቱን እስር ቤት ሲያደርግበት፣ ብርሃን እንዳይደርስበት በሁሉም አቅጣጫ ያለውን ክፍል በመጋረጃ ሲጋርድበትም ሊመሰገን ይገባዋልና ። ሲቆርጥ ፣ ሲተኩስ (ሲያቃጥል) እና መራራ መድኃኒቶችን ሲሰጠው ፤ ያኔም እንዲሁ ሐኪም ነው ።”[28]

---

[25] “. . . Who forms light for the righteous and creates darkness for Babylon, and the same applies to “Who makes peace and creates evil.” Rashi, Sefaria.

[26] *መጽሐፈ ቅዳሴ* (2005) ፤በአባ ጥዑመ ልሳን ኪዳነ ማርያም የተዘጋጀ ፣ አክሱም ማተሚያ ቤት ፣ ገጽ 179 ።

[27] እዚህ ላይ የእኛም ትርጓሜ ‘አነ እፈጥር ሰላመ ወአመጽእ እኪተ’ የሚለውን ሲተርጉም ‘ፍቅር አንድነትን የማደርግ ፣ መከራን የማመጣ እኔ ነኝ ፤ አንድም ተድላ ደስታን የማደርግ ፣ መከራን የማመጣ እኔ ነኝ ፤ አንድም ሚጠትን(መመለስን) የማደርግ ፄዋዌን(ምርኮን) የማመጣ እኔ ነኝ ።’ ማለቱ የዮሐንስ አፈወርቅን ትርጓሜ ይመስለዋል ።

[28] “For since we are accustomed to use the word evil to speak of calamities, and not only of thefts and adulteries, so the prophet allows this usage. On this basis the prophet can say, ‘There is no evil in the city that the Lord has not done.’ This too, by means of Isaiah, God has made clear, when he said, “I am God who makes peace and creates evil,” again naming calamities evils. This evil also Christ hints at, thus saying to the disciples, ‘Sufficient for the day is the evil thereof,’ that is to say, the affliction, the misery. It is manifest then on all sides that he here calls punishment an evil, even as we commonly do, affirming at the same time that God brings these on us. This affords us the greatest view of his providence. For the physician is not only to be commended when he leads forth the patient into gardens and meadows, nor even into baths and pools of water, nor yet when he sets before him a well-furnished table, but when he orders him to remain

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ክፋት ወይም እኩይ ማለትን በጋራ ለመቅሰፍትም ስለምንጠቀምበት ነው ነቢዩ የተጠቀመው እያለን ነው። ስለዚህም የክፋት ዋና ብያኔው ይህ አይደለም ማለት ነው ። በተጨማሪም መቅሰፍት ለምክንያት ሊመጣ መቻሉን እና እርሱ ክፋት ተብሎ ሊጠራ አለመቻሉን አብሮ እየነገረን ነው ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትንቢተ ኢሳይያስን ጠቅሶ ባስተማረበት ስብከቱ እንዲህ በማለት ይተረጉማል፡-

> “እነዚህ ነገሮች (አደጋዎች እና መቅሰፍቶች) በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ መጥፎ ፥ አንዳንዶቹ ጥሩ እና አንዳንዶቹ ደግሞ በሁለቱ መካከል እንደሆኑ በግልጽ ተመልክታችኋል . . . በመንፈስ የተነሣሣው ደራሲ በሁለቱ መካከል ያሉት ነገሮች (ለምሳሌ እንደ ምርኮ፣ ባርነት ግዞት የመሳሰሉት) የምር እኩያት አይደሉም ፥ ነገር ግን በጠቅላላው ሕዝብ ዘንድ እኩያት ተደርገው ይታሰባሉ እያለ ነው ። እንዲህ ያለበትን ምክንያት ማብራራት ያስፈልጋል ። እግዚአብሔር ፍቅርን እና ምሕረትን ለማሳየት የፈጠነ ፣ በቀልንና ቅጣትን ለመፈጸም ደግሞ የዘገየ እንደመሆኑ ፥ አይሁድን ላለመቅጣት የቃላቸውን ማስጠንቀቂያ ሰምተው እንዲደነግጡ እና እንዲመለሱ በማሰብ ነቢያትን ላከ ። ዲያቢሎስ በበኩሉ እንዲህ ያለው ማስጠንቀቂያ ሊያመጣ ያለውን ተሐድሶ ለማከሸፍ ሐሰተኛ ነቢያትን ወደ ሕዝቡ ልኮ ከእውነተኞቹ ነቢያት የግዞት፣ የባርነት እና የረኃብ ዛቻ በተጻራሪ ሰላምን፣ ብልጽግናንና ሌሎችንም ብዙ መልካም ነገሮችን እንዲሰብኩ አደረገ ። እውነተኛዎቹ ነቢያትም ‘ሰላም፣ ሰላም ትላላችሁ ፥ ታዲያ ሰላም ወዴት አለች?’ በማለት ሐሰተኞቹ ነቢያት ላይ ተሳለቁባቸው። እውነተኞቹ ነቢያት ለአምላኩ እንዳይቀና ሕዝቡን በሚያሰናክሉት ሐሰተኛ ነቢያት ላይ የተናገሩት እያንዳንዱ ነገር ጊዜውን ጠብቆ በትክክል መፈጸሙን ደግሞ የኋላ ዘመን ሊቃውንት መስክረዋል ። ስለዚህ ሐሰተኞቹ ነቢያት ሕዝቡን በዚህ መንገድ ሲያዋርዱትና ሲያረክሱት እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል “እኔ እግዚአብሔር ሰላምን አደርጋለሁ እኩያትንም እፈጥራለሁ ።” አለ ። እንዴት ያሉ እኩያት? የተጠቀሱትን - ምርኮኝነትን ፣ ባርነትን እና የመሳሰሉትን - ማለቱ ነው (እንጂ) እንደ ዝሙት ፣ ሴሰኝነት፣ ፍቅረ ንዋይ እና እነዚህን የመሳሰሉትን አይደለም። ሐሰተኛ ነቢያት እንዲያዋርዷችሁ አትፍቀዱላቸው ፤ እግዚአብሔር ሰላምን ሊሰጣችሁም ወደ ምርኮ ሊወስዳችሁም ይችላል ፤ "ሰላምን ማድረግ እና እኩያትን መፍጠር" ማለት ይህ ነው። ይህ ትክክል መሆኑን ታውቁ ዘንድ እያንዳንዱን አገላለጽ ለያይተን እና አበክረን እንመርምር። በቅድሚያ “ብርሃንን እና ጨለማን ወደ መኖር ያመጣሁት እኔ ነኝ” ካለ በኋላ “ሰላምን አደርጋለሁ እና እኩያትንም እፈጥራለሁ” ብሎ ቀጠለ። በመጀመሪያ ሁለት ተቃራኒዎችን አመጣ ፤ ከዚያም ሁለት ተቃራኒዎችን አስከተለ ። በቅድሚያ ብርሃንን ከጨለማ ጋር አነጻጸረ ። ቀጥሎ ደግሞ ሰላምን ከእኩይ ጋር ። ይህን ያደረገው የሚናገረው ስለ ዝሙት ሳይሆን ስለ ጥፋት መሆኑን ትረዱት ዘንድ ነው። ጨለማ ለብርሃን እንደሆነው የሰላም ተቃራኒ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው ምንድን ነው? ምርኮኝነት እንጂ ሴሰኝነት ወይም ዝሙት ወይም ፍቅረ ንዋይ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ በመጀመሪያ ብርሃንን እና ጨለማን እንደጠቀሰው፣ ቀጥሎም ያመጣቸው ሁለት ነገሮች እንዲሁ ተቃራኒ ናቸው ። የሰላም ተቃራኒ ደግሞ ዝሙት ወይም ማመንዘር ወይም ሴሰኝነት ወይም ሌሎች ምኞቶች አይደሉም ፥ ምርኮና ባርነት እንጂ።”[29]

without food, when he oppresses him with hunger and lays him low with thirst, confines him to his bed, making his house a prison, depriving him of the very light and shadowing his room on all sides with curtains. When he cuts, and when he cauterizes and when he brings his bitter medicines, he is equally a physician.’’ Elliott and Oden, *Isaiah 40-66,* 74–75.

[29] “These things have thus been clearly shown to you to be in some cases bad, some good and some in between, … the inspired author is saying the in-between things are not really bad but are thought to be by the general run of people—things like captivity, servitude and exile. Now, it is necessary to explain the reason for this statement. Loving as [God] is and quick to show mercy, while slow in exercising retribution and punishment, God sent prophets so as to avoid consigning the Jews to punishment,

ስለዚህም ከትንቢተ ኢሳይያስ አምጥተን ርእሳችን ያደረግነው "ክፋትንም እፈጥራለሁ" የሚለው ቃል የተነገረው በዚህ ቃል ሊጠራ የሚገባውን ፤ ከሰው ፈቃድ የሚመነጨውን ክፋት በሚመለከት አይደለም ። ይልቁንም ምርኮን ፤ ስደትን እና የመሳሰሉትን ነገሮች እኛ በልማድ 'ክፉ' ብለን ስለምንጠራቸው መጽሐፉም የእኛን ቋንቋ በመዋስ እንዲህ ብሎ ጠራቸው እንጂ ።

※ ※ ※

ነገራችንን እንጠቅልል ፤ ምንም እንኳን ነገረ እከይ እንዲህ በቀላሉ የሚጠቀለል ባይሆንም ። አባቶችን በመጥቀስ እንዳሳየነው እከይ ብለን ክርስቲያኖች የምንረዳው (ልንረዳው የሚገባን) የሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ መለየቱን ነው ። ነገር ግን ዮሐንስ አፈወርቅ እንደሚለው ሰዎች በጠቅላላው ስቃይን እና መከራን ወደ እኛ የሚያመጣውን ነገር ሁሉ ክፉ አድርገን እንቆጥረዋለን ።

ክፉ እንላቸዋለን እንጂ የእውነት ክፉ አይደሉም ብሎ ዮሐንስ አፈወርቅ ከጠቀሳቸው ነገሮች አንዳንዶቹ የሰው ፈቃድ ያለባቸው ናቸው ፤ ጦርነት ፤ ምርኮ ፤ ባርነት እና የመሳሰሉት ። ሌሎቹ ደግሞ በተፈጥሮ ሂደት የሚከሰቱ ናቸው ፤ ድርቅ ፤ በሽታ ፤ ወረርሽኝና የመሳሰሉት ።

ክፋትን ከሰዎች ወይም ከሌሎች ነጻ ፈቃድ ካላቸው ፍጡራን የሚመነጭ ነው በማለታችን እንዲህ ያሉትን የሰውን ልጅ ሕይወት የሚያናጉ ሁነቶች ምንነት እና የመሆን ምክንያት ሙሉ በሙሉ ማስረዳት አንችልም ። እኩያን ናቸው ባንል እንኳን እነዚህ ሁነቶች የሚያደርሱትን ጥፋትና መከራ ፥ እንዲሁም ሰለባ በሚያደርጓቸው ሰዎች ላይ የሚደቅኑትን መንፈሳዊ ፈተና ልንክድ አይቻለንም ።

በአንድ በኩል ቅዱሱ እንዳለው ማስተማሪያ የሚሆኑበት ጊዜ አለ ። በተከሰቱ ቁጥር የሚገልጡልን እውነታ ፥ የሚያስታውሱን ቁም ነገር ይኖራል ። በሌላ በኩል አንዳንዶቹ ሁነቶች ከሰው ፈቃድ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ሁሉ ፥ ሌሎቹም ከሰውም ሆነ ከረቂቅ ፍጡራን ፈቃድ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል ። በጻድቁ ኢዮብ ላይ መከራ በደረሰ ጊዜ መከራዎቹን እግዚአብሔር በቀጥታ አላደረጋቸውም ፤ ሰይጣን እነዚያን ነገሮች እንዲያደርግ ፈቀደለት እንጂ ። ሰይጣንም ኢዮብ ላይ መከራን ለማምጣት አንዳንድ ሰዎችን ተጠቀመ ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ተፈጥሮን ራሷን መሣሪያ አደረጋት ። ነገር ግን አንዱንም ሆነ ሌላውን ማድረግ የተቻለው እግዚአብሔር ስለፈቀደለት ነው ። እግዚአብሔር ግን ለምን ይህን እንዲያደርግ ፈቀደለት ? ኢዮብን ያስተምረው ዘንድ ነው ? ኢዮብ ከመከራው በኋላ የተማረው ነገር ነበር ። ነገር ግን እኛ መማር እንደሚገባን እንዲማር ኢዮብ እንደኛ አመጸኛ አልነበረም ። ከመከራው በፊትም ሆነ በመከራው ጊዜ ጻድቅ ነበር እንጂ ። እውነት ነው ፥ የኢዮብ መከራ ለእኛ እንድንማርበት ተሰጥቶናል ። ነገር ግን ቀድሞ ኢዮብ ላይ መከራ ይደርስ ዘንድ የቀረበው ምክንያት ኢዮብ ይፈተን ዘንድ ነው ። ጻድቅ ቢሆንም እግዚአብሔር ማለቂያ በሌለው መከራ መፈተኑን ፈቀደ ። ለምን ? ኢዮብ ይህን ጥያቄ ጠይቆት ነበር ። መልሱን አላገኘም ። መልሱን ያገኝ ዘንድ እንዳይችል ፥ እንዳይገባውም ተረዳ እንጂ ።

intending to frighten them in word, so as not to punish them in deed… Observing this and wishing to undermine the reform that was the result of such a threat, the devil sent down false prophets, and in contradiction of the prophets' threats of captivity, servitude and famine, false prophets preached the opposite—peace, prosperity and enjoyment of countless good things. Hence, the genuine prophets also mocked the false by saying, "Peace, peace, and where is peace?" This every scholar knows, that everything happened just as the prophets had foretold against the false prophets, who were undermining the people's zeal. So when they undermined the people in this way and corrupted them, God said through the prophets, "I, God, am making peace and creating evils." What sort of evils? Those mentioned—captivity, servitude and the like. Not fornication, licentiousness, avarice and anything else like that.…Do not let the false prophets undermine you; God can give you peace and consign you to captivity, which is the meaning of "making peace and creating evils." For you to learn that this is true, let us make a precise examination of the individual expressions. After saying before, "I am the one who brought light and darkness into being," he then went on to say, "making peace and creating evils." He cited two opposites first, and two opposites after that, for you to learn that he is referring not to fornication but to calamities. I mean, what is set as the opposite of peace? Clearly captivity, not licentiousness or fornication or avarice. So, just as he cited two opposites first, so too in this case; the opposite of peace is not fornication, or adultery, or licentiousness or the other vices, but captivity and servitude.'' Elliott and Oden, *Isaiah 40-66,* 76.

ምናልባት ግን ኢዮብ ከመከራዎቹ በኋላ ከደረሰበት ፍጹም ትህትና ፣ ሊያየው እንዳይችል ከተረዳው የእግዚአብሔር ኃይል እና ሊመረምረው እንዳይችል ከተረዳው ገናናነቱ በተጨማሪ አንድ ለነገራችን ቁልፍ ሊሆን የሚችል ነገር አለ ። ይኸውም የሰይጣን ምርጫ እና ፍላጎት ነው ። ሰይጣን ከሕይወቱ በስተቀር በሚቻለው ነገር ሁሉ ኢዮብን ፈተነው ። ፈተናው ግን ምን ነበር ? እነዚያን መከራዎች ማድረስ በራሱ ግብ አልነበረም ። ይልቁንም ዋናው ዓላማ የኢዮብን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ መነጠል ነበር ። ሰይጣንን የጨነቀው እና ያሳሰበው ፥ ኢዮብ እጅግ ሀብታም መሆኑ ፣ ብዙ ልጆችን ማፍራቱ ወይም ጤናማ መሆኑ አልነበረም ፤ ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አንድ ማድረጉ እንጂ ።

መከራዎቹ በራሳቸው ለሰይጣን ግብ አልነበሩም ። ልክ ይህን የፈቃድ አንድነት ለማፍረስ በኢዮብ ላይ ድህነትን ፣ ሐዘንን እና ሕማምን ያመጣበትን ያህል ፣ በተቃራኒው ሀብትን ፣ ተድላን እና ጤናን በብዙ እጥፍ ጨምሮ በመስጠት ይህን ግብ ማሳካት እንደሚችል ቢያስብ ያን ከማድረግ አይመለስም ነበር ። ሰይጣን የክፋት አባት ከሆነ ፣ ክፋት እሱ በእጅጉ የሚፈልገው ነገር መሆን አለበት ። ይኸውም እኛን ከእግዚአብሔር ፈቃድ መለየት ነው ።

ስለዚህም ኢዮብ በደረሱበት መከራዎች ሁሉ ክፋት ወደ እርሱ አልተጠጋም ፥ በመከራው ወይም (ለልጆቹ ይፈራ እንደነበረው) በድሎቱ የተነሣ እግዚአብሔርን ቢበድል ነበር ኢዮብን እውነተኛው ክፋት የሚያገኘው ።

፨ ፨ ፨

**ይህ ጽሑፍ ሳንጠግበው ለተለየን ፥ የሕይወቱ ልዩ መዓዛ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ ለጠራ ፥ የፍቅሩና የርኅራኄው ነገር ሁልጊዜም ለሚታወሰው ለውድ ወንድማችን ለናትናኤል ማርቆስ መታሰቢያ ይሁንልኝ ።**

### አማርኛ ምንጮች

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ፤ *የሙሴ ሕይወት* ፤ ትርጉም የካፑቺን ፍራንቸስካዊ የምርምርና የጽሞና ማእከል ፤ አዲስ አበባ፤ 2010 ዓ.ም.

አባ ምሥራቅ ጥዩ ፤ *ነቢይ ማነው?* ፤ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ *ሥራ መምሪያ የታተመ* ፤ አዲስ አበባ ፤ 2006 ዓ.ም.

### እንግሊዝኛ ምንጮች

Areopagite, Dionysius the. *The Works of Dionysius the Areopagite.* Southampton-Street, Strand, London; and 27 Broad Street, Oxford., 1897.

Elliott, M. W., and Thomas C. Oden, eds. *Isaiah 40-66*. Ancient Christian Commentary on Scripture 11. InterVarsity Press, 2007.

Florovsky, Georges. *The Collected Works of Georges Florovsky. 3: Creation and Redemption*. Büchervertriebsanst, 1976.

Gregory, Philip Schaff, and Henry Wace. *Gregory of Nyssa, Dogmatic Treatises*. Cosimo Classics, 2007.

Hart, David Bentley. *The Doors of the Sea: Where Was God in the Tsunami?* Wm. B. Eerdmans Publishing Co, 2011.

John Chrysostom. *On the Priesthood ; Ascetic Treatises ; Select Homilies and Letters ; Homilies on the Statues*. Edited by Philip Schaff. Translated by W. R. W. Stephens. Cosmo Classics, 2007.

Matthews, George, and Christina Hendricks, eds. *Introduction to Philosophy: Ethics*. Rebus Community, 2019.

Nyssa, Gregory. *The Life of Moses*. The Classics of Western Spirituality. Paulist Press, 1978.

Plato, G. M. A. Grube, and John M. Cooper. *The Trial and Death of Socrates: Euthyphro, Apology, Crito, Death Scene from Phaedo*. 3rd ed. Hackett Pub, 2000.

Pseudo-Dionysius, Colm Luibhéid, and Paul Rorem. *Pseudo-Dionysius: The Complete Works*. The Classics of Western Spirituality. Paulist Press, 1987.

Schmemann, Alexander. *A Voice for Our Time*. Saint Vladimir’s Seminary Press, 2021.

Špidlík, Tomáš. “The Spirituality of the Christian East. 1.” In *The Spirituality of the Christian East.* Cistercian Studies Series 79. Cistercian Publ, 1986.

Stăniloae, Dumitru. *Orthodox Spirituality*. St. Tikhon’s Seminary Press, 2002.

Triston, Taylor. “Demons of the Self: Tristen Taylor Wonders How to Define Evil.” *Philosophy Now Published By Anja Publication* 148, no. 148 (2022): 24–28.

Yannaras, Christos. *The Enigma of Evil*. Holy Cross Orthodox Press, 2012.

Yannaras, Christos, and Keith Schram. *Faith as an Ecclesial Experience*. Contemporary Christian Thought Series, number 62. St. Sebastian Orthodox Press, 2020.

### የመተግበሪያ ምንጭ

Sefaria

# ባለጸግነት እና እጦት

**ፋኑኤል ተረፈ**

† † †

የሰው ልጅ የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል ነው ። ይህ ትምህርት የሰውን ልጅ ምንነት ወይም ማንነት ፣ በዚህ ዓለም የሚኖርበትን አነዋወርና ፣ እውነተኛ መዳረሻውን በተመለከተ ምንም ለማለት መነሻችን ነው ።[1] ኦርቶዶክሳዊ ለሆነው የዶግማም ሆነ የሥነ ምግባር ትምህርት ሁሉ ይህ እውነት መሠረት ነው ።

ሀብት እና ድህነት በሰው ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመረዳትም እንዲሁ ከዚህ እውነታ መነሣት ግዴታችን ነው ። ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል እንደመፈጠሩ ተልዕኮውም በምሳሌው የፈጠረውን ፈጣሪ ማምለክ እና እርሱን በመምሰል ያለማቋረጥ ማደግ ነው ። ይህን ተልእኮውን አጥብቆ በያዘ መጠን የሰው ልጅ ራሱንም ሆነ በምድር ያለውን ግዙፍ ዓለም (material world) ያነጻል ፣ ያከብራል ፣ መንፈሳዊ ያደርጋል ። ከዚህም አልፎ አንድ ፣ ሁለት እያለ ለሚቆጥረው ጊዜ ፍጽምናን ፣ ዘለዓለማዊነትን ያቀዳጃል ። በፍጥረት እና በፈጣሪ መካከል አማካይ (mediator) ሆኖ ፍጥረትን ወደ ፈጣሪ የማቅረብን ሚና ይጫወታል ።[2]

በተቃራኒው ሰው ሥነ ፍጥረታዊ ማንነቱን ሲረሳ እና ግቡን ሲስት መንፈሳዊነቱን ያጣዋል ፥ አምላኩንም ይረሳል ። ይልቁንም በዙሪያው ያሉት ወደ ፈጣሪው ሊያቀርባቸው የተሰጡትን ቁሳቁሶች እንደ ግብ ይወስዳቸውና የልቡን ጎዶሎ የሚሞሉለት ፣ የነፍሱን ቁስልም የሚያክሙለት ይመስለዋል ። ገንዘብ ፣ ዝና ፣ ቁስ እና ጌጥ ይማርኩታል ። እነርሱን ብቻ ያሳድዳል ። ነገር ግን ሲያገኛቸውም ነፍሱ አትረካም ። ስለዚህ ማሰሱን እና መቅበዝበዙን አያቆምም ። ቁሳዊነት (materialism) ማለት ይኸው ነው ። ሰው እግዚአብሔር አምላኩን መስሎ መፈጠሩ ለገዢነት ሆኖ ሳለ ማንነቱን በመዘንጋቱ ለተፈጥሮው በማይስማማ መልኩ ለማይመጥኑት እና ለማይተካከሉት ለገንዘብ እና መሰል ነገሮች ባርያ እና ተገዢ ይሆናል ። ከሰውነት ወደ ቁሳዊነት የሚደረግ የቁልቁለት ጉዞውን ይጀምራል ። ይህ ጉዞውም በዘመናችን የደመ ነፍስ ከመሆን አልፎ "በዕውቀት" ተደግፎና ተብራርቶ ራሱን ከስቷል ። ራሱን ከከሰተባቸው መልኮችም መካከል ተምኔታዊነት (utopianism)[3] እና

[1] Harrison V., "Poverty in the Orthodox Christian Tradition", *Saint Vladimir's Theological Quarterly*, vol. 34 no. 1 (1990), p. 15

[2] ቀሲስ መብራቱ ኪሮስ ገብሩ (ዶ/ር) (2016) ፣ *አኰቴተ ቁርባን ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት ፣ ታሪካዊ እድገት እና ይዘት* ፣ ካሊፎርኒያ ፣ 6ተኛ ዕትም ፣ ገጽ 260.

[3] ዩቶጵያ የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው በቶማስ ሞር በ1516 ቢሆንም እሳቤው ግን ከፕሌቶ ጀምሮ የነበረ ነው ። ዩቶጵያ የሚለው ቃል የሁለት የግሪክ ቃላት ጥምር ሆኖ በስተኋላው 'ኢያ' ('ia') የሚል ቅጥያ (suffix) የታከለበት ነው ። 'ዩ'( የጥንቱ 'ouk' ፣ የአሁኑ 'u') ማለት 'ያልሆነ' ('not') የሚለውን አፍራሽ ቃል የያዘ ሲሆን 'ቶፖስ' ('topos') ደግሞ 'ቦታ' ('place')'' ማለት ነው ። ከቃሉ ተነሥተን ስንበይነው "ቦታ ያልሆነ ቦታ (a place which is a non-place)" የሚል ትርጉም አለው ። የቶማስ ሞር ዩቶጵያ ከሚታወቀው ዓለም የተለየች ቦታ ናት ፤ እንደ ፕሌቶ ምናባዊ ከተማ አይደለችም ። የፕሌቶ ከተማ ምናባዊት ብትሆንም ግን ወደ እውነታነት መቀየር የምትችል (achivable) አድርጎ ነበር ፕሌቶ የቀጠራት ። ቶማስ ሞር ግን ከነስሟ ጭምር ፍጹም ምናባዊት ፥ በእውነት ምድር ላይ ልትኖር የማትችል አድርጎ ነበር ያሰባት ። የከተማይቱ ማኅበረ ሰብእ እና የሚተዳደሩበት ሕግ የሚደንቅ ስለሆነ ''Eutopia'' ( a good place - መልካም ስፍራ ) ሲልም ጠርቷታል ።
ነገር ግን ምንም እንኳን ቶማስ ሞር ''ዩቶጵያ'' የሚለውን ቃል ቢፈጥርም ዩቶጵያዊነትን (utopianism) አልፈጠረም ። ዩቶጵያዊነት (ተምኔታዊነት) ምንም ሕጸጽ የሌለበትን ማኅበረ ሰብእ በምድር ላይ ለመመሥረት የማለም አባዜ ነው። ይህ ምኞት በአንድ ርእዮተ ዓለም ዘንድ ብቻ ያለ ሳይሆን የብዙ ዓይነት ርእዮቶች መገለጫ ነው ። ለዚህ በየቦታው የሚገኘ እና ይዘቱ ይህ ነው የማይባል እሳቤ ብያኔን መስጠት አጥኚዎችን ያከራከረ መሆኑ አልቀረም ። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ አሁን ያለንበትን ማኅበረ ሰብእ ችግሮች ሙሉ በሙሉ በመቅረፍ ችግር የሌለበትን ማኅበረ ሰብእ መፍጠርን ዓላማ ያደረጉ ሁሉ በዚህ ስም መጠራት ስለመቻላቸው ግን ስምምነት አለ ። Clays G. (2010), *The Cambridge Companion to Utopian Literature*; edited by Gregory Clays, Cambridge University Press. See from p3-7.

የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴዎች (New age movements)[4] ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ።

እነዚህ እሳቤዎች ከክርስትና ጋር ፈጽመው ሊሄዱ የማይችሉ ቢሆኑም የቁሳዊነትን ፅንሰ ሐሳብ ከክርስትናው ቀይጠው ውሸትን የሚናገሩ ነጣቂ ተኩላዎች ወደ መንጋው መምጣታቸው ግን አልቀረም ፤ “የክርስትና መለኪያው ብልጽግና ነው’’ የሚሉ ፥ ገንዘብም አምላካቸው የሆነላቸው ናቸው ። ምስኪኑን ሕዝብ ድሎት ፣ የተድላና የተንደላቀቀ ኑሮ ከእግዚአብሔር ነው ይሉታል ፤ መጻሕፍትን በማጣመም “ኃይልን በሚሰጥ በክርስቶስ ሁሉን ትችላለህ’’ እያሉ ስለዚህ ዓለም ብቻ ያሳስቡታል ። መስማት የሚያስፈልገውን ሳይሆን እነርሱ የሚሹትን እና ተደማጭነት ያስገኝልናል ብለው የሚያስቡትን ብቻ ይሰብካሉ ። እንዲህ ያለው የ’አይዞህ’ እና የ’በርታ’ ስብከት ቀድሞ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ ነበር ጎልቶ የሚሰማው ። አሁን ግን በእኛም ቤት ሳይታወቅም ሆነ ታውቆበት እየገነነ መምጣቱ የሚያስደነግጥም ፣ የሚያሳዝንም ነው ።

አንድ ክርስቲያን ገና ከተወለደበት ሥፍራ ፣ ዕውቀት ከቀሰመበት ትምህርት ቤት ፣ ከሚያነባቸው መጻሕፍት ፣ ከሚመለከታቸው ፊልሞች እና በሕይወቱ ከሚገጥሙት ሰዎች ተነሥቶ ፍጹም ዓለማዊ እና ኦርቶዶክሳዊ ከሆነው እሳቤ እጅግ የማይገጥም ርእዮትን ሊያዳብር ይችላል።

ዛሬ የሀብትን እና የድህነትን ምንነት ለማስረዳት የሚሞክሩ ብዙ ክርስቲያኖች የሐሳባቸው መሠረት ቁሳዊነት እንጂ ክርስትና አይደለም ። ከዚህ የተነሣ ክርስትናን ያስተማሩ እየመሰላቸው ከክርስትና ጋር ፈጽም የሚቃረኑ ነገሮችን ሲናገሩ እና ሲጽፉ እናገኛቸዋለን ።

በዘመናችን ተደጋግመው ሲነገሩ ከምንሰማቸው ሐሳቦች አንዱ ፥ ገንዘብ እና ጤንነት እግዚአብሔር ለወደዳቸው እና ለመረጣቸው ሰዎች የሚሰጡ ሽልማቶች መሆናቸው ነው ። ባለጸግነትን እና እጦትን ቁሳዊ በሆነ መንገድ የሚረዱ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ሀብት እና ጤንነት አለፍ ሲልም ዝና ያለው ሰው እግዚአብሔር የመረጠው እና የወደደው ድህነት እና የጠና ሕመም የሚገጥመው ሰው ደግሞ በተቃራኒው እግዚአብሔር ፊቱን ያዞረበት ነው የሚል ምልከታ አላቸው ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ግን የአልዓዛር እና የባለጸጋውን ታሪክ መሠረት አድርጎ ባስተማረው ትምህርት ውስጥ[5] አልዓዛርን ደጋግሞ የታደለ ፣ አለፍ ሲልም ባለጸጋ እያለ ሲጠራው እንመለከታለን ። እንግዲህ ጉዳዩን ቁሳዊነት ላይ ተንተርሰን ካየነው አልዓዛር እንዴት የታደለ ይሆናል? የሀብታም ሰው በር ሥር ተኝቶ የማዕዱን ፍርፋሪ በልቡ የሚመኝስ ከሆነ እንዴት ባለጸጋ ሊባል ይችላል? የእውነተኛውን ባለጸግነት እና የእውነተኛውን እጦት ምንነት መለየት ሊያወዛግበን የሚችለው የቆምንበት መሬት ቁሳዊነት ሆኖ አእምሮአችን ከቤተ ክርስቲያን አእምሮ ሲለይ ብቻ ነው ።

እንዲህ ያለው ዝንባሌ በእጅጉ ሲያይል በቁስ ወደ መስከር ያደርሳል ። ይህም ስካር ገንዘብን ፣ ሀብትን እና ቁሳቁስን ፍጹም ስግብግብነት በተሞላበት መንፈስ ያለአገባባቸው እንዲውሉ (abuse) ያደርጋቸዋል ። የሰከረውም ሰው በቅንጦቱ ድህውን ይበድላል ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አልዓዛርን የበደለው ሀብታም ሰው ሕይወቱ በምን ዓይነት ቅንጦት ውስጥ እንደነበረ ሲነግረን እንዲህ ይላል ፤

> “ይህ ሰው አልጋው ከዝሆን ጥርስ የተሠራ እና የሚጠጣውም ወይን የተጣራ ነበር . . . ሌሎቹ ኃጢአቶቹ ለምሳሌ ስካሩ ፣ አብዝቶ መብላቱ ፣ ሴሰኝነቱ እጅግ በጣም ተራም ቢሆን ደስታ ሊሰጡት ይችላሉ ። ነገር ግን ከዝሆን ጥርስ የተሰራ አልጋ ላይ መተኛት ምን ደስታ አለው ? ምን ምቾት አለው ? የአልጋው ማማር

[4] እ.አ.አ በ1970ዎቹ የተመጀመረ እንቅስቃሴ ነው ። ወጥ የሆነ ብያኔ ለዚህ እንቅስቃሴ መስጠት ያስቸግራል ። ምክንያቱም እጅግ በጣም ብዙ ርእዮቶችን እና እምነቶችን አደባልቆ የያዘ ነው ።ለምሳሌ ቡድሂዝም ፣ ሂንዱይዝም ፣ አረማዊነት ፣ ታኦኢዝም ፣ የዜን አርምሞ (zen meditation) ፣መንፈሳዊ ህክምናዎች (spiritual therapies) ፣ አዎንታዊ እሳቤ (positive thinking) ወዘተርፈ እና (ፈገግ በሚያስብል መልኩ) ፈጽሞ የማይገጥመው ክርስትና ሳይቀር በዚህ እንቅስቅሴ ውስጥ የሐሳብ ምንጭ ተደርገው ይጠቀሳሉ ። ምንም እንኳን የአዲሱ ዘመን አቀንቃኞች (new agers) በሐሳቦቻቸውም ሆነ በሁናቴያቸው ልዩ ልዩ ስለሆኑ ለእንቅስቃሴው አንድ ብያኔ መስጠት ከባድ ቢሆንም ሁሉንም ግን የሚያስማማቸው ማዕከላዊ እሳቤ አለ ፤ እርሱም ‘የራስ መንፈሳዊነት’ (self spirituality) የሚባለው ነው ። ይኸውም የሰው ልጅ ከተበከለ ማንነቱ (contaminated mode of being) መውጣት አለበት ፥ እንዲሁም ሁሉም ሰው በራሱ የተቀደሰ ብቻ ሳይሆን አምላክም ነው የሚል ነው ። Heelas P. (1996), *The new age movement: the celebration of the self and the sacralization of modernity*; Blackwell publishers, see introduction ‘አነቃቂ ተናጋሪዎች’ የሚባሉት ሰዎች እንዲህ ካለው የክርስትና ባለጋራ ከሆነ አንቅስቃሴ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሳለ ፥ መንጋውን ይጠብቃሉ የተባሉት የቤተ ክርስቲያን መምህራን እንኳ ሳይቀሩ እንዲህ ላሉት ሰዎች አበረታች እና አስተዋዋቂ ፣ በመድረኮቻቸውም ተጋባዥ እና መስካሪ ሆነው መቅረባቸውን እያየን መሳቀቃችን አልቀረም ።

[5] ትምህርቱ ‘On Welath and Poverty’ ተብሎ እንደ መጽሐፍ ታትሟል ።

> እንቅልፍህን ጣፋጭ ያደርገዋልን ? . . . የአልጋን እውነተኛ ውበት ማየት ትፈልጋለህ ? የዜጋም ያይደለ የወታደርም ያይደለ ነገር ግን ውብ የሆነውን የንጉሥ አልጋ አሁን አሳይሀለሁ ፤ መቼም ከንጉሥ አልጋ የበለጠ ውብ አልጋ እንደማትመኝ እርግጠኛ ነኝ ። በዚህም ላይ የተራ ንጉሥን አልጋ አይደለም ፥ ከንጉሦች ሁሉ የላቀውን ፥ ዛሬ ድረስ በመላው ዓለም በመዝሙር የምናከብረውን የቅዱስ ዳዊትን አልጋ ነው የማሳይህ ። የዳዊት አልጋ ምን ዓይነት ነበር? በእንባ እና በንስሐ የተሞላ እንጂ በወርቅ እና በነሐስ ያሸበረቀ አልነበረም ። ይህንም ራሱ እንዲህ ብሎ ነገረን ፥ ‘ሌሊቱን ሁሉ በእንባዬ አልጋዬን አጥባለሁ ፤ መኝታዬንም አርሳለሁ ።’’[6]

እንዲህ ባለ ቅንጦት በመኖር ምስኪኑን ድሀ መበደል እንዴት ያለ ኢ ፍትሃዊ ድርጊት ነው? የአልጋ ዓላማው እንድንተኛበት ብቻ ነው ፤ ሌላ ምንም ትርጉም የለውም ። በቁሳዊነት ለሰከረ ሰው ግን አልጋውን ማስጌጥ ቁም ነገር ይመስለዋል። ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስም ስለዚህ ስካር እንዲህ ይናገራል ፤

> “እስኪ ንገረኝ ? ጠረጴዛው ከነሐስ ፥ ወንበሩም ከዝሆን ጥርስ ቢሠራ ከተራው ጠረጴዛ እና ወንበር ምን የተለየ አገልግሎት ይኖረዋል ? . . . የሚለምኑህን ሁሉ ፍላጎት ማሟላት የማይቻል ነው በማለት አንዳችም ነገር ላለመስጠት ሰበብ ትደረድራለህ ። በአፍህ እውነታው ይህ መሆኑን ትናገራለህ ፤ እጅህ ግን ያሳብቅብሃል ፤ በጸጥታ ሐሰተኛነትህን ይመሰክርብሀል ።” [7]

እንደዚህ ባለ ቅንጡ ሕይወት እና ቁስን ያለአግባብ በመጠቀም ድሀውን መበደልን ዛሬም በዘመናችን በብዙ መልክ እናገኘዋለን ። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች የገዙት ስልክ 6 ወር ወይም አንድ ዓመት ሲሞላው ከዘመኑ ጋር መሄድ አለብኝ በሚል ሰበብ ሌላ ስልክ ለመግዛት ብዙ ወጪ ያወጣሉ ። ምናልባትም የገዙት ስልክ ቀድሞ ከነበራቸው ጋር ምንም ልዩነት የሌለው ወይም ደግሞ እርባና የሌለው ትንሽ ለውጥ ቢኖረው ነው ። ዳሩ ግን እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎች የዚያ ቁስ ዓላማ ምን እንደሆነ ማሰብ እስኪሳናቸው ድረስ ቁስን በማካበት የሰከሩ ናቸው ። ሌላ ቀለል ያለ ምሳሌ እንጨምር :- ልብስ እንደሚታወቀው ዓላማው ሰውነትን ከብርድ መጠበቅ ነው ። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች እጅግ በጣም የተቦጫጨቀ ልብስ በውድ ዋጋ ገዝተው ሲለብሱ እንመለከታቸዋለን ። ምን ጥቅም የሚያገኙበት ይመስላቸው ይሆን ? ምስኪኑ ነዳይ ግን በዚያ ሰዓት ራሱን ከብርድ የሚጠብቅበት ጨርቅ እንኳን የለውም ። እንደዚህ ዓይነት ድርጊት ለምን እንደሚፈጽሙ ሲጠየቁም “ፋሽን ነው’’ ወይም “ያምራል’’ የሚል ምላሽ ይሰጣሉ ። ቅዱስ ባስልዮስ ስለእንደዚህ ዓይነት በደል ሲናገር “ስለዘነጠ በሕይወቱ ላይ አንድ ቀን የጨመረ ሰው ማን ነው ? ገንዘብን በማስቀመጡ ሞትን ያስቀረስ አለ ?’’[8] ይላል ። እንዲህ ያሉ ሰዎች ውበትን የሚለኩት በቁሳዊ መሥፈርት ነው ። እውነተኛውን ውበት እንዳይመለከቱ በዐይናቸው ላይ ቁሳዊነት አዚም አድርጓል ። በቁሳዊነት ልባቸው የተለከፉ ሰዎች ቤተክርስቲያንን አያውቋትም ። ውበቷንም አይረዱም ። ውብ ናት ካሉም ቅጽሯን እና ሕንጻዋን በማየት ነው እንጂ እውነተኛውን ውበት በመመልከት አይደለም ። እንዲህ ላሉት ሰዎች ምናልባትም ጉስቁል ባለችና በጭቃ ወይም በቆርቆሮ በተሠራች ሕንጻ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን አምራ ላትታያቸው ነው ። ለሥርዓተ አምልኮም ያላቸው ዕይታ እንዲሁ ነው ። ወደ ቤተክርስቲያን የሚወስደው መንገድ በፊኛ እና በብልጭልጭ ካጌጠ እና መሸት ሲል ደግሞ ሕዝበ ክርስቲያኑ ተሰባስቦ በእጃቹ ጧፍ ካበራ ነው ውበት ማለት ለእነርሱ ። በሥርዓተ አምልኮው ፣ በቅዳሴው ይዘት ውስጥ ያለው ውበት እና መንፈሳዊ ከፍታ ግን አይታያቸውም ፤ በተለይ ደግሞ ያማረ ሕንጻ ፣ ያማሩ አልባሳት በሌሉበት ከተከናወነ ። ምክንያቱም እንዲህ ያሉ

[6] St. John Chrysostom, On wealth and Poverty, Translated by Catharine P. Roth (1981), Crestwood, New york, St. Vladimir’s Seminary Press, pp. 24- 25.

[7] “Tell me, what better service do silver-encrusted tables and chairs or ivory-inlaid beds and couches provide than their simpler counterparts? … you refuse to give anything, insisting that it is impossible to satisfy the needs of those who beg of you. You profess this to be true with your tongue, but your hand gives you the lie; silently, your hand bears witness to the falsehood.” St. Basil the Great, *On Social Justice*, Translated by C. Paul Schroeder, (St. Vladimir’s Seminary Press, 2009) p. 39

[8] “What well-dressed person has ever been granted even one additional day of life? Has death ever spared anyone on account of wealth?’’ St. Basil the Great, *On Social Justice*, p. 43

ሰዎች ውበትን የሚያዩት በዐይናቸው እንጂ በልቡናቸው አይደለምና ።

በቁሳዊነት መነጽር ነገሮችን መመልከት ከጀመርን በኋላ በኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ ውስጥ ያለውን እውነት ለመቀበል እጅግ በጣም ከባድ እና መራራ ነው ። ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ አልዓዛር እና ባለጠጋው በሰበከበት ትምህርቱ እንዲህ ሲል የምናገኘው "የምነግራችሁ ነገር በጣም እንደሚያም አውቃለሁ ። ነገር ግን በውስጡ ያለው ጥቅም በዋጋ የማይተመን ነው ። ያ ባለጠጋ ሁልጊዜ ከቅንጡ አነዋወር እና መስማት የሚፈልገውን ብቻ ከሚነግሩት ሸንጋይ ጓደኞች ይልቅ እንደዚህ ያለ ምክር የሚሰጠው ሰው ቢኖረው ኑሮ ወደ ሲኦልም ባልወረደ ፥ ከአቅም በላይ ለሆነ ሥቃይም ባልተዳረገ የረፈደ ንስሐም ባልገባ ነበር ።"[9]

ኦርቶዶክሳዊ ነጽሮትን ገንዘብ ያደረገ ሰው ባለጸግነትንና እጦትን ቁሳዊነትን የተቀበለ ሰው በተረዳበት መንገድ ፈጽሞ ሊረዳቸውና ሊበይናቸው አይችልም ። በቤተክርስቲያን አስተምህሮ ባለጸጋ ተብሎ የሚጠራው ሰው ገንዘብ ያከማቸ ፣ ብዙ ጌጣጌጦችና አገልጋዮች ያሉት ሳይሆን በሥጋዊ ፈቃዱ እና በምድራዊ ፍላጎቶቹ (earthly desires) ላይ ፈጽሞ የሠለጠነባቸው ነው ። በተቃራኒው ያጣ (ኃጥእ) ማለት ደግሞ ይህን ፈቃዱን እና ፍላጎቱን ለማርካት ዘወትር የሚጣጣር ነገር ግን (እንዲህ ያለው ፍላጎት በማግኘት የሚብስ እንጂ የሚረካ ስላልሆነ) ምንም ያህል ቢያገኝ የማይጠግብ ፣ ይልቁንም ባገኘ ቁጥር ይበልጥ የሚስገበገብና ባለው ነገር የማይደሰት ማለት ነው። በቁሳዊነት መነጽር ማጣት ማለት ያን ያካበቱትን ገንዘብ ማጣት ነው ። በኦርቶዶክሳዊ ዐይን ግን ማጣት ማለት ከሚያስፈልገው በላይ ገንዘብን ማከማቸትና በእርሱም አለመርካት ማለት ነው ። ይህን ኦርቶዶክሳዊ ብያኔ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይገልጸዋል ፤

> "ባለጸግነት እና እጦት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ በጥንቃቄ ማጤን ይኖርብናል ። ለሁሉም ነገር የሚስገበገብ አንድ ሰው ካያችሁ ተዝቆ የማያልቅ ገንዘብ ቢኖረውም እንኳን ከሁሉ በላይ ድሀ አድርጋችሁ ቁጠሩት ። በሌላ በኩል ጥቂት ፍላጎቶች ያሉት አንድ ሰው ካያችሁ ምንም ነገር ባይኖረውም እንኳ ከሁሉ በላይ ባለጸጋ እንደሆነ አድርጋችሁ ቁጠሩት። ምንም ያህል ውሃ ቢጠጣ ጋብ የማይል ጥማት ያለበትን ሰው ብዙ ምንጮች ባሉበት ሥፍራ ስለሚኖር ብቻ (ያ ሁሉ ውሃ ጥሙን ጥቂት እንኳን የማያስታግስለት ከሆነ ምንም አይረባውምና) ጤናማ እንደማንለው ሁሉ ፥ ባለጸግነትን እና እጦትንም መለካት ያለብን የአንድ ሰው ሐሳብ (ልብ) ባለበት ቦታ ነው እንጂ ባለው የቁስ መጠን አይደለም ።"[10]

ስለዚህም የባለጸግነት እና የእጦት መለኪያውና የብያኔው መሥፈርት ሰዎች ያላቸው የቁስ መጠን ሳይሆን ሰዎች ለዚያ ነገር የሚሰጡት ግምት ነው ። ማለትም 'የአንድ ሰው አእምሮው እና ልቡ ከማን ጋር ነው ያለው ?' የሚለው ጥያቄ ነው የብያኔ መሥፈርት ሊሆን የሚገባው ።[11] በመጽሐፍ ቅዱስ የምናውቃቸው አብርሃምንና ኢዮብን የመሰሉ ቅዱሳን የተትረፈረፈ ምድራዊ ሀብት ነበራቸው ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ከነበራቸው ሀብት መጠን ጋር የተያያዘ አልነበረም ።ለዚህም ማሳያው የኢዮብ ሀብት በጠፋ ጊዜ ኢዮብ አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት አላቋረጠም ። "እግዚአብሔር ሰጠ ፥ እግዚአብሔርም ነሣ ። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን"(ኢዮ 1÷21)። በማለት የገንዘቡ መኖር ወይም አለመኖር እግዚአብሔርን ከማመስገን ሊያግደን እንደማይገባ አስተማረን እንጂ ።

በመሆኑም ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚታወቀው በሀብታቸው እና በድህነታቸው ሳይሆን በልባቸው አጥብቀው በሚወዱት ነገር ነው። ለዚህም ነው

[9] St. John Chrysostom, *On wealth and Poverty*, p. 44

[10] "We ought to consider this the definition of poverty and wealth. So if you see someone greedy for many things, you should consider him the poorest of all, even if he has acquired everyone's money. If, on the other hand, you see someone with few needs, you should count him the richest of all, even if he has acquired nothing. For we are accustomed to judge poverty and affluence by the disposition of the mind, not by the measure of one's substance, just as we would not call a person healthy who was always thirsty, even if he enjoyed abundance, even if he lived by rivers and springs (for what use is that luxuriance of water, when the thirst remains unquenchable?)" St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 40

[11] "If we do not have the right relationship with God, the rest of the relationships that we have in the world are distorted." Clapsis E., "Wealth and poverty in christian Tradion", *Greek Orthodox Theological Review*, Vol 54, no.s 1-4 (2009), p. 172

አምላካችን እግዚአብሔር “ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ ።” በማለት የሚጠይቀን ። ልበ አምላክ የተባለ ክቡር ዳዊትም ለዚሁ ነው “አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ”(መዝ 50÷10) በማለት የሚማጸነው ። ከዚህ አንጻር ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ቅርበት የቱን ያህል እንደሆነ ለገንዘብና ለምድራዊ ሀብት በሚሰጡት ወይም በሚነፍጉት ዋጋ ይታወቃል ። ክፋቱ ያለው ገንዘቡ ላይ ሳይሆን ገንዘብን መውደድ ላይ ነው ። መጻሕፍትም ለዚህ ነው ገንዘብን መወደድ የክፋት ሁሉ ሥር መሆኑ የሚነግሩን (1ኛ ጢሞ 6÷10) ።

※ ※ ※

ቁሳዊነትን ለሚሰብኩ ሰዎች ሥራ እና ሀብት አንድ ናቸው ። ለእነሱ ሥራ ማለት ገንዘብ የሚያስገኝ ሁሉ ነው ። በተቃራኒው ገንዘብ እስካላስገኘ ድረስ የትኛውም ልፋትና ጥረት ሥራ መፍታት ነው ። ስለሆነም ‘ማካበት እና ገንዘብ መውደድ ፣ ቅንጦት ትክክል አይደሉም’ ማለትን ሥራን እንደመጥላት እና እንደማነወር ያዩታል ። ኦርቶዶክሳዊው የሥራ መረዳት ግን ከዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው ። ሥራ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸምን እንጂ ገንዘብ ማግኘትን ዋና ዓላማው ያደረገ ግብር አይደለም ። እውነት ነው ፥ ሰዎች ሠርተው ገንዘብ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል ፥ ይገባቸውማል ። ነገር ግን ገንዘቡ በራሱ ግብ ሊሆናቸው አይገባም ። ከእግዚአብሔር ፈቃድ የሚጻረር ሲሆን የትኛውም ገንዘብ የማግኛ መንገድ ሥራ ሊባል አይችልም ። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የተስማማ ከሆነ ደግሞ ምንም ገንዘብ ባያስገኝ እንኳን በእጅጉ የከበረ ሥራ ነው ።

ቁሳዊነት በወረሰው ዘመናችን ግን ይህ ክርስቲያናዊ የሆነ የሥራ ብያኔ ገለል ተደርጎ በምትኩ ሥራ በሀብት እና “በስኬት” እንዲለካ ሆኗል ። ድህነት ደግሞ ከሥራ ፈትነት እና ከስንፍና ጋር እንዲያያዝ ሆኗል ። ቁሳውያኑን የሚቃረኑ የሚመስላቸው ሰዎች ሳይቀሩ ይህን ብያኔ ተቀብለው በእነሱ ቤት “መንፈሳዊ” ያልሆነን ሥራ ሁሉ “ለሥጋ ማድላት” አድርገው ይቆጥራሉ ። ስለዚህም ድህነትን በራሱ መልካም ነገር እንደሆነ አድርገው ያዩታል ። ነገር ግን በክርስቲያናዊ አስተምህሮ መሠረት የአንድ ሰው ሀብት ሰውየው በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ዋጋ እንደማይናገረው ሁሉ ፣ ድህነትም በራሱ ጽድቅን አይናገርም ።

እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳን ማካበትን ግብ ካደረጉ ሰዎች ጋር ጠብእ ያላቸው ቢመስላቸውም ግን ከእነሱ ጋር ያላስተዋሉት ስምምነት አላቸው ። የቁሳዊነት አቀንቃኞች ሰው ይህን ዓለም የሚሻገር ሰማያዊት ነፍስ ያለችው ፍጡር እንደሆነ በመርሳት መነሻውንም ሆነ መድረሻውን በዚህች ምድር አድርገው ሲያጥሩት ፣ እነዚህ ደግሞ በተራቸው ሰው ይህችን ምድር እና የያዘቻቸውን ፍጥረታት በሙሉ ለመቀደስ እና ለማንጻት መፈጠሩን ረስተው “ሥጋዊ” የሚሉትን በሙሉ የሚጣል እና የሚጠላ እንጂ ምንም ዓይነት ቅድስና የማይስማማው አድርገው ያስባሉ ። በዚህም ሁለቱም ወገኖች የሰውን ተፈጥሮ እና ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ግብር ይዘነጋሉ ። ስለሥራም እንዲሁ ስሑት መረዳት ነው ያላቸው ፤ የመጀመሪያዎቹ ገንዘብ ከማስገኘት አንጻር ብቻ ሲበይኑት ፣ እነዚህ ደግሞ ገንዘብ የሚያስገኝን ሥራ ሁሉ ዋጋ የሌለው ያደርጋሉ ። የቅዱሳት መጻሕፍት መረዳታቸውም እንዲሁ የተጣመመ ነው ።

እርግጥ ነው ፥ ለፍጥረቱ ሁሉ መጋቢ የሆነ ጌታ “ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ አይዘሩም ፥ አያጭዱምም ፥ በጎታም አይከቱም ፤ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል ። እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን ? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው ?”(ማቴ 6÷26) ብሎ መጋቢነቱን እና ፍቅሩን አስተምሮናል ። ነገር ግን ጌታችን ይህን ስብከቱን የደመደመው “ከሁሉ በፊት መንግሥቱን እና ጽድቁን ፈልጉ ፥ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል ።” በማለት ነበር ። ይህንም በማለቱ ዋናው ቁም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም እንደሆነ ነገረን ። ስለምንበላውና ስለምንጠጣው ፣ ወይም ስለምንለብሰው ብለን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መተላለፍ እንደሌለብን እንጂ ፣ ወፎች እንደማይዘሩት እኛም መዝራት እንደሌለብን ፣ አበቦች እንደማይፈትሉት እኛም መፍተል እንደሌለብን አላስተማረንም ።

ለዚህ ነገር ማሳያ ይሆነን ዘንድ ከወንጌል ትርጓሜ ሁለት ታሪኮችን እናምጣ ።

> “ሁለት መነኮሳት ናቸው። (ከላይ የተማርነውን የወንጌሉን ጥቅስ ይዘው) በተባሕትዎ ሁነው በረኃብ ፣ በጽምእ የሚያልቁ ሆነዋል ። ኋላ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ ‘እለ ኢይዘርኡ አለ እንጂ እለ ኢይሰርሩ አለ?’ (አይዘሩም አለ

እንጂ አይበሩም አለ ?) አላቸው ። ከዚህ በኋላ ተግባረ እድ ይዘው ራሳቸውን ሁነዋል ።

“በአንዲት ቀንም አንድ ታካች የሆነ መነኮስ ወደ ሽማግሌው አባ ስልዋኖስ መጣ ። አባ ስልዋኖስንም ከደቀ መዝሙሩ ጋር ሥራ ሲሠራ ባየ ጊዜ ‘ለኃላፊ ምግብ ትሠራላችሁ ፥ ትደክማላችሁ ። የዘላለም ሕይወት ለሚሆን ምግብ ሥሩ ፣ ድካሙም እንጂ በከበረ ወንጌል እንደተጻፈ ።’ ብሎ ጠቀሰላቸው ። ሽማግሌው አባ ስልዋኖስም ይህን በሰማ ጊዜ ደቀ መዝሙሩን እንዲህ ሲል አዘዘው ። ይህን መነኮስ እንግዳ ማረፊያ ቤት አስገብተህ የሚያነበው መጽሐፍ ስጠው ። በሩንም በላዩ ላይ ዝጋ ። በእርሱ ዘንድም ምንም ምን አትተው ። ረድኡም የታዘዘውን አደረገ ። ዘጠኝ ሰዓትም ሲሆን መነኮሳቱ ተሰብስበው ከአባ ስልዋኖስ ጋር ጸሎት አድርገው ምግባቸውን ተመገቡ ። ያን እንግዳ መነኮስ ግን አልጠሩትም ። እርሱም ቢጠሩኝ ብሎ ወደ ደጃፍ እየተመለከተ ይጠብቅ ነበር ። በረኃብም በተቃጠለ ጊዜ ከበዓቱ ወጥቶ ወደ አባ ስልዋኖስ ቀርቦ ‘አባቴ መነኮሳቱ ራታቸውን በሉን ?’ ብሎ ጠየቀው ሽማግሌውም ‘አዎን’ ብሎ መለሰለት ። ሁለተኛም ‘እኔ እንግዳ ስሆን ለምን አልጠራችሁኝም ?’ አለ ። የከበረ አባት አባ ስልዋኖስም ‘አንተማ ሥጋዊ መብል የማትሻ መንፈሳዊ ሰው ነህ ። እኛ ግን ሥጋውያን ሰዎች ለሥጋዊ መብል የምንሠራ የምንደክም ነን ። ስለሆነም ለምግባችን የሚሆነውን በእጃችን እንሠራለን ።’ ብሎ መለሰለት። ያ መነኮስም በንግግሩ እንደበደለ አውቀ ። አባ ስልዋኖስንም ‘አባቴ ሆይ እኔ በድያለሁና ይቅር በለኝ ።’ ብሎ ሰገደለት ። ያ ታካች የነበረ መነኰስም በዚህ አባት ተመክሮና ተገስጾ ሁልጊዜ የሚሠራ ከእርሱም የሚተርፈውን የሚመጸውት ሆነ ። ”[12]

በጠቅላላው ትጋትና ሀብት ፣ ስንፍና እና ድህነት ተመሳሳይ ነገሮች አይደሉም ። ሥራ እና ትጋት የሚመዘኑት ከገንዘብ ጋር በተያያዘም ሆነ ባልተያያዘ ዓውድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ጋር ብቻ ነው ። ከዚህ የወጣ እና ገንዘብን ብቻ ግቡ ያደረገ መባተል ግን ከእግዚአብሔር መለየትን ያመጣል ፤ ጌታችን “ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም ።” ሲል እንዳስተማረን ። ስንፍና ማለትም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመፈጸም ቸል ማለት ነው ። ጠቢቡ ሰሎሞን ፤ “አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ መንገዱንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን ። አንተ ታካች! እስከ መቼ ትተኛለህ ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ ?’’(ምሳ 6÷6-9) ። በሌላ ምዕራፍም እንዲህ ይላል ፤ “የታካች እጅ ችግረኛ ታደርጋለች ፤ የትጉሕ እጅ ግን ባለጠጋ ታደርጋለች ”(ምሳ 10÷4)። ይህን ሲል ምድራዊ ሀብትን ስለማፍራት እየተናገረ ከመሰለን ተሳስተናል ። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ስለመትጋት ተናገረ እንጂ ።

※ ※ ※

ሀብትም ሆነ ድህነት ከነገረ እከይ (problem of evil) ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት የላቸውም ። ሀብት በራሱ ሠናይም እኩይም ሊባል አይችልም ፤ ድህነትም እንዲሁ ። ምድራዊ ሀብት የነበራቸው ፥ ነገሥታት የነበሩ ቅዱሳን አሉ ፤ ሀብት ያላቸው ሁነው በሀብታቸው የተሰናከሉም አሉ ። ድሆች ሁነው ድህነታቸው እግዚአብሔርን ከማግኘት ያልከለከላቸው አሉ ፤ ድህነታቸውን በማማረራቸውና እግዚአብሔርን ደፍረው በመሳደባቸው በክረምትም በበጋም ፍሬ የማይሰጡ ዕፅዋትን መስለው የቀሩም አሉ። ኦርቶዶክሳዊ አእምሮ ላለው ሰው ባለጸግነት እና እጦት በራሳቸው የጽድቅ መገለጫ ሊሆኑ አይችሉም ። ጽድቅ እና ኩነኔ ከሀብት ከጤና ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የላቸውም ። አንድ ሰው ጤነኛ እና ምድራዊ ሀብትን ያካበተ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ያልታደለ ሊሆን ይችላል ። ምናልባትም ሀብታም ባይሆን ይሻለው ነበር ይሆናል ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይላል ፤ “ወዳጆቼ ሆይ ፥ ጽድቅን የሚፈጽማትን እንጂ ሀብታሙን የታደለ አንበለው ፤ ክፉውን እንጂ ድሀውን መከረኛ አንበለው ።’’[13]

[12] የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ ፤ ስንክሳር ዘወርኀ ሚያዝያ 1 ። (በሁለቱም መጻሕፍት ታሪኩ አንድ ሁኖ ሳለ ነገር ግን ያ እንግዳ መነኮስ የጠቀሰው ጥቅስ በአንድምታው ማቴ 6÷26 ሲሆን በስንክሳሩ ደግሞ “ማርያምስ የማይቀሟትን በጎ ዕድል መረጠች” የሚለው ነው ።)

[13] “Therefore my beloved , let us call fortunate not the wealthy but the virtuous ; let us call miserable not the poor but the wicked.” St. John Chrysostom (1981), p. 37

ለዚህ ነው ቁሳዊነትን መሠረት ያደረገ አስተሳሰብ ባለጸግነትን ሲገልጽ (ሲበይን) ፈጽሞ ከኦርቶዶክሳዊው ርእዮት ጋር ሊገጥም የማይችለው ። ምክንያቱም ቁሳዊነት ሀብት (ብልጽግና) ሲል ብል ሊበላው እና ሌባ ሊሰርቀው የሚችለውን እንጂ ፈጽሞ ሰማያዊውን ጸጋ አይደለም ። ሁለቱ አመለካከቶች የሰማይ እና የምድር ያህል ልዩነት ነው ያላቸው ። ለዚህ ነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዚሁ ትምህርቱ "አልዓዛር በምድርም በሰማይም አግኝቷል ።" ሲል የሚያስተምረን ። "በምድር ሳለ ምንም እንኳን ብዙ መከራ ቢደርስበትም መከራዎቹ መልካም በሆነ ተስፋ ይመገባሉ ። በአልዓዛር ውስጥ ያለች ነፍስ ከወርቅ በላይ ውድ ናት ።" ከሞት በኋላም ደግሞ ተስፋው ተፈጽሞ በአባቱ አብርሃም እቅፍ መልካም እረፍትን አገኘ ። በተቃራኒው ያ ሀብታም ሰውም በምድርም በሰማይም አላገኘም ። በምድር ሳለ የአልዓዛር ሥጋ እንደቆሰለ ሁሉ የእርሱም ነፍስ በኃጢአት ምክንያት ጎሰቆለች ። የአልዓዛርን ቁስል ውሾች ይልሱት እንደነበር ሁሉ የዚህን ሰው ኃጢአት ደግሞ አጋንንት ይልሱት ነበር ።[14] ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከዚህ በመነሣት ባለጠግነትን እና እጦትን በአፍአ ከምናየው ነገር ተነሥተን መበየን እንደሌለብን ይነግረናል ። 'ውስጡን እንጂ ውጪውን አትመርምሩ ፤ ፍሬውን እንጂ ቅጠሉን አትመልከቱ' ይለናል ።[15] ስለ አልዓዛር ሲናገር "ያችሁት ድሀውን ደጅ ላይ ተኝቶ ፥ ውጪው ድሀ ፣ ውስጡ ግን ባለጸጋ ።''[16] ይላል ፤ "ነፍሱ ጤነኛ ስለሆነች በሰውነቱ መድከም ምን ጉዳት ደረሰበት ? ''[17]

ቅዱሱ በዐይናችን የምንመለከታቸው ቁሳቁሶች ሁሉ ሕልም እንጂ እውነታ ፤ ጥላ እንጂ አካል አለመሆናቸውን ሲያስረዳን ይህችን ዓለም በቲያትር ይመስላታል ። የሰው ሁሉ ውጫዊ ሁናቴው ተዋንያን ወደ መድረክ ሲወጡ እንደሚላበሱት ገጸ ባህርይ ነው ። ምድራዊ ሀብት እና ድህነት ፣ ጤና እና ሕማም ሁሉ ለቲያትር ሲባል እደሚጠለቁ ጭምብሎች ናቸው ። የነዌ ሀብት እና የአልዓዛር ድህነትም እንዲሁ ያሉ ሚናዎች እንጂ

[14]St. John Chrysostom, *On wealth and Poverty*, p. 35
[15] "if you see someone, do not evaluate his outside but his inside. Examine the fruit and not the leaves'' St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 107
[16] "The poor man lay at the gate, you see: poor outwardly, but rich inwardly'' St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 107
[17] "What harm came to him from the weakness of his body, since his soul was healthy?'' St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 107

የእውነተኛ ማንነታቸው መገለጫዎች አልነበሩም ። በቲያትር ውስጥ ተዋንያን የራሳቸው ያይደለን ሌላ ገጽታ ይላበሳሉ ። አንዱ ፈላስፋ ይሆናል ፤ ነገር ግን በእውነታው ፈላስፋ አይደለም ፤ ሌላው ንጉሥ ይሆናል ፤ ግን ተራ ዜጋ ነው ። ሌላው ሐኪም ይሆናል ፥ የሐኪም ልብስም ይለብሳል ፤ ነገር ግን ስለ ሕክምና ምንም አያውቅም ። ሌላው ባርያ ሆኖ ይተውናል ፤ በእውነታው ግን ነጻ ሰው ነው ።[18] የአልዓዛር እና የነዌም ነገር እንዲሁ ነው ። ነዌ ውስጡ ነዳይ ሲሆን ሀብታም ሆኖ ተወነ ፤ አልዓዛር ደግሞ በነፍሱ ባለጸጋ ሲሆን ነገር ግን የዳቦ ፍርፋሪ እንደሚለምን ነዳይ ሆኖ ተወነ ። ከዚህ በኋላ ግን መጋረጃው ተዘጋ ። በዚህ ጊዜ ተዋናዮቹ ወደ እውነተኛ ማንነታቸው እንደሚመለሱ ሁሉ ሀብታሙ ከሁሉ የበለጠ ያጣ ሆነ ። በሚተውንበት ጊዜ ለአልዓዛር የዳቦ ፍርፋሪ እንኳን ያልሰጠ አሁን ግን ምላሱ ከሚነደው ነበልባል ይድንለት ዘንድ አልዓዛር የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ ያበርድለት ዘንድ አብርሃምን ለመነ ። ነዳይ ሁኖ ይተውን የነበረው አልዓዛርም ትወናው ካለቀ በኋላ እውነተኛ ማንነቱ ተገለጠ ። የሰማይ መላእክት አጅበው ወደ አባቱ እቅፍ አስገቡት ። በሕመም ይሠቃይ የነበረው አልዓዛር አሁን ግን የነፍስ ድሎት ላይ ነው ።[19] ምድራዊ ሀብት እና ድህነት ማለት ይኸው ነው - ተራ ጭምብል ።

※ ※ ※

በአራተኛው መቶ ክፍለዘመን የኖረው ቅዱስ ሰራጵዮን (St. Serapion) ምጽዋትን ከፍቅር ጋር ያዋሐደ ታላቅ አባት ነው ። በአንድ ቀንም ይህ አባት የለበሰውን ልብስ አውልቆ በመንገድ ላይ ለወደቀ ነዳይ ይሰጥና የውስጠኛውን ልብስ ብቻ እንደለበሰ መንገዱን ይቀጥላል ። አሁንም ሌላ ነዳይ ባየ ጊዜ የውስጥ ልብሱንም አውልቆ ሰጠውና ዕርቃኑን ቀረ ። እጁ ላይ የነበረውን ወንጌል ይዞ እርቃኑን ቁጭ አለ ። ደቀ መዛሙርቱ አግኝተውት "አባታችን ፡ ልብስህን ማን ወሰደብህ ?" ብለው በጠየቁት ጊዜ በጣቶቹ ወደ ወንጌሉ እየጠቆመ ''እሱ ዘረፈኝ ።" ሲል መለሰ ። በሌላም ቀን በእጁ የነበረችውን ወንጌል ሸጠና ገንዘቡን ለድሆች መጸወተ ። ደቀ መዝሙሩም "ወንጌልህ ከወዴት አለ ?" ብሎ ቢጠይቀው "ልጄ እመነኝ ፥ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ ያለኝ ራሱ ወንጌሉ ነው ።'' ብሎ መልሶለታል ። በሌላ ቀን

[18] St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 46 & pp. 109-110
[19] St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 108

ደግሞ አንዲት መበለት ወደ እርሱ መጥታ "እባክህ ልጆቼ ተርበውብኝ ነው ።" ብላ ብትማጸነው ምንም የሚሰጣት ስላልነበረው ለአረማውያን እንድትሸጠው አስገደዳት ። ባርያም ሆኖ መኖር ጀመረ ። በኋላ ግን የገዙትን አረማውያን ሳይቀር ማርኮ ወደ ቀናች ሃይማኖት አመጣቸው ።[20]

ምጽዋት እንዲህ በፍቅር መነሻነት ሲደረግ እውነተኛ ይሆናል ። ድህነትም ለራሱ ሲባል ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማስደሰት ፣ የራስን ፈቃድ በመተው የእርሱን ፈቃድ ለማድረግ ሲደረግ ሰማዕትነት ይሆናል ። ስለዚህ ሥራ ከመፍታትና ከመታከት የመጣ ሳይሆን ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የሚገባበት ድህነት እጦት ሳይሆን ባለጸጋነት ነው ። ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምናሳየው እርሱ እንዳዘዘን ባልንጀሮቻችንን በመውደድ ነውና ካለን ገንዘብ እና ንብረት ላይ ሳንሰስት ባካፈልን ቁጥር ወደ እግዚአብሔር እየቀረብን እንመጣለን ። ያለንን ማካፈል በተለይም ራስን አሳልፎ መስጠት የፍቅር መገለጫ ነው ካልን ደግሞ ገንዘብን ማካበት ፍቅርን የማጣት መለያ ይሆናል ማለት ነው። "For the more you abound in wealth, the more you lack in love - ሀብትህን ባበዛህ መጠን ፍቅርን እያጣህ ትመጣለህ ።"[21] እንዲል ታላቁ አባት ቅዱስ ባስልዮስ ።

የአልዓዛር ድህነት እጅግ የከፋ ነበር ። ጌታችን ይህን ሲያሳየን ''ከባለጠጋውም ማዕድ ከሚወድቅ ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር ።'' ይለናል ። ከዚህም አልፎ ሰውነቱ በቁስል ተመትቶ ነበር ። ቁስሎቹን የሚልሱትን ውሾች እንኳን ለማባረር አቅም አልነበረውም ። ብዙ ሰዎች ይታመማሉ ፤ ነገር ግን መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ይችላሉ ። ሌሎች እጅግ ድሆች ቢሆኑም በጤንነት ይኖራሉ ። አልዓዛር ግን ከሁለቱም ያጣ ሰው ነው ።[22] አልዓዛር እንዲህ ባለ ሁኔታ ባለጠጋው ደጅ ላይ ተኝቶ ሳለ ያ ክፉ ባለጠጋ ግን አንዴ አይደለም ዘወትር ሲወጣና ሲገባ እየተመለከተው አንድም ጊዜ ርኅራኄ አላደረገለትም ። ልቡን እና ዐይኑን ያከማቸው ገንዘብ ሰውሮበት ነበርና ፍቅር ከእርሱ ዘንድ አልነበረችም ። ስለዚህም እጅግ ብዙ ሊሰጠው የሚችለው ነገር እያለው መስጠትን አላወቀም ።

አንድ ሰው ገንዘቡን በምንም ዓይነት መንገድ ቢያመጣው ሰጪው እግዚአብሔር ነው። የእኛ የሆነ ምንም ነገር የለም ። በስርቆት የመጣ ገንዘብ ቀድሞውንም የእኛ አልነበረም ። ለፍተን ያገኘነው ገንዘብም ቢሆን የራሳችንን ፍላጎትና አምሮት ብቻ እንድናረካበት አልተሰጠም ፤ ቅዱስ ጳውሎስ "የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሰራ ይድከም" እንዲል (ኤፌ 4÷28) ።[23] በእኛ ዘንድ ግን ሠርቶ የተገኘ ሀብት ባለቤቱ በወደደው መንገድ ሊያጠፋው የተገባ እንደሆነ ማሰብ የተለመደ ነው ። ያገኘነው ገንዘብ እና ያፈራነው ንብረት ወደዚህ ዓለም ይዘን የመጣነው ፣ ወይም ራሳችን በችሎታችን ካለመኖር ወደመኖር ያመጣነው እንደሆነ የምናስብ ይመስላል ። ነገር ግን እውነቱ ይህ ሀብት እና ንብረት እግዚአብሔር ለሁሉም ያዘጋጀውና አሳላፊው እንሆንለት ዘንድ በአደራ እኛ ዘንድ ያስቀመጠው መሆኑ ነው ። እንዲህ ስላለው ስሑት መረዳት ቅዱስ ባስልዮስ እንዲህ ይላል ፤ "እስኪ ንገረኝ ያንተ የሆነው ነገር ምንድን ነው ? ወደዚህ ሕይወት ምን ይዘህ መጣህ ? ከማንስ ተቀበልከው ? አንድ ሰው ቲያትር ለመመልከት የመጀመሪያውን ቲኬት ቆርጦ ወደ አዳራሹ ከገባ በኋላ (ቀድሞ መግባቱን ምክንያት አድርጎ) ሌሎች ገብተው እንዳይታደሙ ቢከለክል እና ለሁሉም የተዘጋጀውን ትርኢት ብቻውን ቢታደም ብላችሁ አስቡ ። ሀብታሞች ይህን ነው የሚያደርጉት ፤ ለሁሉም ጥቅም እንዲሆን የተሰጠውን እነሱ ጋር ቀድሞ ስለተገኘ ብቻ የራሳቸው ብቻ ንብረት አድርገው ይቆጥሩታል።''[24] ስለዚህ ያለንን አለማጋራት ወንጀል ነው ።[25] ድህነትን በተመለከተ የክርስቲያናዊው ትውፊት መሠረት በነዳዩ ላይ አድሮ

[20] Harrison V., "Poverty in the Orthodox Christian Tradition", p 36

[21] St. Basil the Great, *On Social Justice*, p. 35

[22] St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 29

[23] St Basil the great, *On Social Justice*, p.88

[24] "Tell me, what is your own? What did you bring into this life? From where did you receive it? It is as if someone were to take the first seat in the theater, then bar everyone else from attending, so that one person alone enjoys what is offered for the benefit of all in common — this is what the rich do. They seize common goods before others have the opportunity, then claim them as their own by right of preemption." St Basil the great, *On Social Justice*, 57

[25] St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, pp. 49–52

የሚኖረውን ክርስቶስን ማየት ነው ፡፡[26] ለዚህም ትምህርት መነሻ የሆነው የባለቤቱ የጌታችን ትምህርት ነው ፡፡

> “የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክት ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል ፡፡ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ፡፡ ተርቤ አብልታችሁኛልና ፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና ፤እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና ፤ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና ፡፡ ጻድቃንም መልሰው ጌታ ሆይ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ ? እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ . . . እውነት እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳን ስላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አደረጋችሁት ይላቸዋል ፡፡”ማቴ 25÷31-41

በመሆኑም ምጽዋትን በፍቅር ማድረግ በነዳዩ ላይ አድሮ ለሚኖረው ክርስቶስ መስጠት ፥ ስለዚህም የዘላለም ሕይወትን ማግኛተ ማለት ነው ፡፡ አንድ ሰው እሷን የማያደርጋት ከሆነ ሌሎች በጎ ምግባራት ቢኖሩት እንኳ ከተጠያቂነት ከቶ አያስወጣውም ፡፡

እማሆይ ማርያ በምሥራቃውያን ዘንድ በትሕርምት ሕይወታቸው የታወቁ እናት ናቸው ፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በመንገድ ከወደቁ ስደተኞች ጋር እየዋሉ እና እያደሩ ስለተንከባከቧቸው ‘መነኩሲት ሳለሽ በጾምና በጸሎት በገዳም ልትጠመጂ እንጂ በዓለም ካሉ ሰዎች ጋር ልትውዪ አይገባሽም’ በሚል ለደረሰባቸው ወቀሳና ትችት የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነበር ፡፡ “በመጨረሻው የፍርድ ቀን ‘በምን ያህል ትሕርምት ኖረሻል ?’ ወይም ‘ምን ያህል ስግደት ሰግደሻል ?’ ተብዬ አልጠየቅም . . . ነገር ግን የተራበውን ስለማብላቴ ፤ የታረዘውን ስለማልበሴ ፤ የታሰሩትን ስለመጠየቄ ፥ ስለ እነዚህ ሁሉ እጠየቃለሁ ፡፡” [27]

ምጽዋትን የሚያደርግ ሰው ሀገሩ መንግሥተ ሰማያት መሆኑን እና ይህችን ዓለም ጥሏት እንደሚሄድ በእጁ ይመሰክራል ፡፡ “ለሁለት ጌቶች ልትገዙ አይቻላችሁም’’ እንደተባለ (ማቴ 6÷24) ምድራዊ ገንዘብ እንደማይገዛን አንዱ ማሳያ ምጽዋት ነው ፡፡ ስለዚህም ያ ሀብታም ሰው የገንዘብ ባሪያ ስለነበር ሰማያዊው ዓለም አልታየውም ፡፡ በዚህ ጥፋቱም ተፈርዶበት ሲኦል ገባ ፡፡ ቀድሞ ሀብታም የነበረው አሁን ግን የሚለምን ሆነ ፡፡ ያን ጊዜ ደጁ ስር ተኝቶ ሲወጣ ሲገባ አልታይ ያለው አልዓዛር በሲኦል ውስጥ ሲሆን ግን ታየው ፡፡ ስለዚህም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “እንደዚህ ዓይነት የዳበረ ዕይታ አሁን ለምን ኖረህ ? ከደጅህ ተኝቶ የነበረው እርሱ አልነበረምን ? አጠገብህ ሁኖ ሳለ አላየኸውም ፡፡ አሁን ግን ታላቅ ገደል ባለበት ርቀት ታየዋለህን ?’’[28] ሲል ይወቅሰዋል ፡፡

ሌሎችን ልንረዳበት እየቻልን ያልዘረጋነውን እጅ ፣ በኋላ እኛ ከሌሎች አንዳች ነገር ባስፈለገን ጊዜ ወደ እነርሱ ብንዘረጋው ፣ ያን ማድረጋችን ከፍቅር የተነሣ እንዳልሆነ ይታወቃል ፡፡ ስለዚህ ሌሎች በፍቅር ወደ እኛ እጃቸውን ቢዘረጉም እንኳን የእኛ እጅ በፍቅር የተሰጠውን ለመቀበል አይችልም ፡፡ ነዌ አብርሃምን አባቴ አለው ፣ ነገር ግን ጌታችን “የአብርሃምስ ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ትሠሩ ነበር ፡፡” እንዳለ ፣ እርሱም በምድር ሳለ የአብርሃምን ሥራ አልሠራምና አብርሃምን አባቴ ብሎ ሊጠራው አይገባውም ነበር ፡፡ አብርሃምም ልጄ ብሎ መለሰለት ፡፡[29] ይሁን እንጂ በአብርሃምና በእርሱ መካከል ያለው ገደል ሰፊ ነበርና አብርሃምም እንኳን ምንም ልጄ ቢለው የጠየቀውን ሊፈጽምለት ዘንድ አልቻለም ፡፡ ምናልባት የአብርሃምን ሥራ ባለመሥራቱ በእርሱና በአብርሃም መካከል የተፈጠረው ርቀት ይሆናል ገደል የተባለው ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነዌን እንዲህ

---

[26] John Anthony McGukin, *The Orthodox Church: An Introduction to Its History, Doctrine, and Spritual Culture*, (Blackwell Publishing, 2008) p. 401
“The poor were the body of Christ, and the believer’s attitude to them was a fundamental part of their salvation.”

[27] John Anthony McGukin, *The Orthodox Church: An Introduction to Its History*, p. 401

[28] “Why do you have such keen sight now? Was he not at your gate? How could you avoid seeing him? … now do you see him from a distance, even across such a chasm?” St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 111

[29] St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 76

ይለዋል ። "በቸርነቱ ፤ በእንግዳ ተቀባይነቱ ሳትመስለው ለምን አባቴ ትለዋለህ ?" የአብርሃም ቸርነት ለነዌ ከመጥቀም ይልቅ ምስክር ሆኖ እንደሚከስሰው ሲያስረዳም እንዲህ ይላል ። "ሐዋርያዉ ጳውሎስ አባትህ ቢሆን ፤ ሰማዕታትም ወንድሞችህ ቢሆኑ እንኳን ፥ በጽድቃቸው ካልመሰልካቸው ዝምድናቸው ይፈርድብሃል እንጂ አይጠቅምህም . . . መጥምቁ ዮሐንስ አይሁድን ምን ነበር ያላቸው ? 'እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ በልባችሁም ፦ አብርሃም አባት አለን ማለትን አትጀምሩ ። ጻድቅ አባት አለህን ? ከመሰልኸው ታተርፋለህ ። ካልመሰልኸው ግን አባትህ ራሱ ከሳሽህ ይሆናል ፤ ከጣፋጭ ወገን የተገኘህ መራራ ፍሬ ሆነሃልና ።"[30]

ከምጽዋት ጋር በተያያዝ በብዙ ክርስቲያኖች ልብ ያለ አንድ አስፈሪ እና አደገኛ አስተሳሰብ አለ ፤ 'ከእኔ የሚጠበቀው ምጽዋት ነው ። ስለዚህ እመጸውታለሁ ። ግን ሀብትም እንደልቤ አካብታለሁ ።' የሚል ። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከጀርባው ድብቅ የሆነ ቁሳዊ ማንነት እንዳለ የሚያሳብቅ እና ክርስትናችንን ወጥመድ ውስጥ የሚከት ነው ። ይህን የሚል ሰው በመጀመርያ ያልተረዳው ገንዘብን ባበዛ ቁጥር ራሱን ሊወጣበት የማይችለው ፈተና ውስጥ እየከተተ እንደሆነ ነው። ይህን አሳብ ግልጥ ለማድረግ ያህል በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 19 ላይ ያለውን የአንድ ባለጸጋ ወጣት ታሪክ እንመልከት ። ታሪኩ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው ። ይህ ጎበዝ ወደ ጌታችን ቀረብ ብሎ 'ቸር መምህር ሆይ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ ?' አለው ። መድኃኒት ጌታም የኦሪትን ትእዛዛት እንዲፈጽም ነገረው ። ጎበዙም 'ትእዛዛትን ሁሉ ፈጽሜአለሁ ።' ብሎ መለሰለት ። ጌታችንም 'እንግዲያስ ፍጹም ልትሆን ብትወድስ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥና ተከተለኝ ።' አለው ። ያም ጎበዝ ይህን በሰማ ጊዜ ብዙ ሀብት ነበረውና እያዘነ ተመለሰ ።

ቅዱስ ባስልዮስም ስለዚህ ሰው ማንነት እንዲህ ይላል "የዚህ ሰው ድርጊት የተምታታ ነው። በአንድ በኩል ፈሪሳውያንን ሁሉ ካለፈ በኋላ እውነተኛውን መምህር 'ቸር መምህር' ይለዋል . . . የድኅነትን ነገር ከሰማ በኋላ ግን እያዘነ ይመለሳል ።" ከዚህም በኋላ እንዲህ በማለት ይወቅሰዋል ". . . መምህር ትለዋለህ ፤ ነገር ግን የተማሪነትን ግዴታ አትወጣም ። መልካም እያልኸው የሚሰጥህን ግን አትቀበለውም ።''[31] ልብ እናድርግ ጌታችን ይህን ሰው ካለህ ሀብት ላይ መጽውት አይደለም ያለው ። ይልቁንም ያለውን ሙሉ በሙሉ እንዲሸጥ ነው የተናገረው ። ሙሉውንም ሽጦ ለቤተሰቦቹ ወይም ደግሞ ለሚስትህ ስጥ አይደለም የተባለው ፤ ለድሆች እንጂ ። ጌታችን ፍጹም የመሆንን መንገድ አሳየው ። ይህ ሰው ግን ይህን መቀበል ተሳነው ።

የጌታን ቃል ለመቀበል ያልቻለበትንም ምክንያት ቅዱስ ማቴዎስ ሲነግረን 'ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ ።' ይለናል። ይህ ሰው ብዙ ንብረት ስለነበረው ንብረቱን ከጌታ ጥሪ አስቀደመ ። በማካበት የተለከፉ ሰዎች እንመጸውታለን ቢሉም ውሸታቸውን ነው ። ይህ ሰው 'ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ' የሚለውን ሕግ ፈጽሜያለሁ ብሎ ነበር ። ነገር ግን ይህን ማለቱ ሐሰት ነበር ። ባልንጀራውን ቀድሞውኑ የሚወድ ቢሆን ኖሮ ይህን ቃል መስማት በቀለለው ነበር ።[32]

ይህ ሰው ፍጹምነትን እንዳያይ ገንዘቡ እንቅፋት ሁኖበት እንመለከታለን ። የማካበት ችግሩ ይህ ነው ። ሳናስበው ገብጋባ ያደርገናል ። ይህ ሰው ከሁኔታው እንደምንረዳው ባልንጀራውን ሳይሆን ገንዘብን ነበር ይወድ የነበረው ። ገንዘብን መውደድ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው የክፋት ሁሉ ሥር ናት (1ኛ ጢሞ 6÷10) ። ከሥሯም የሚበቅሉ ቅርንጫፎች ልዩ ልዩ ናቸው ፤ ቅናት፣ ስግብግብነት ፣ ነፍሰ ገዳይነት እና የሚሸነግሉ ጓደኞችን ማፍራት ። እነዚህ ሰፋፊ ቅርንጫፎችም ወደ ፍጽምናው መንገድ ፤ ወደ ጠባቡ ጎዳና መግባት እንዳንችል ይዘው ያስቀሩናል ። ስለዚህም ነው ገንዘብ ለሚያካብት ሰው መጽደቅ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ያ ጎበዝ አዝኖ ከሄደ በኋላ ጌታችን "እውነት እውነት እላችኋለሁ ፥ ሀብታም

[30] "If you have Paul the apostle for your father, if you have martyrs for your brothers, but you do not imitate their virtue, the relationship is of no benefit to you, but rather it harms and condemns you . . . What does John the Baptist say to the Jewish people? "Bear fruits that befit repentance, and do not presume to say, 'We have Abraham as our father.' Do you have a glorious ancestor? If you emulate him, you have profited; but if you do not emulate him, your noble ancestor becomes your accuser, because you are a bitter fruit from a righteous stock'', St. John Chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p .111-112

[31] St. Basil the Great, *On Social Justice*, pp. 33-34
[32] St. Basil the Great, *On Social Justice*, p. 34

መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ።'' ብሎ የነገረን ።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አልዓዛር ደጁ ላይ ተኝቶ ሳለ ላልተመለከተው ለዚያ ሀብታም ሰው ወደ ጠባቡ መንገድ እንዳይገባ ከከለከሉት እና ፍጽምናን እንዳያይ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ይህ ሰው ሀብቱን ብቻ ፈልገው የሚመጡ በከንቱ የሚያወድሱት የሚሸነግሉት ጓደኞች ስለነበሩት የእነርሱ ከንቱ ውዳሴ እውነትን እንዳያይ እንዲሁም ከደጁ የወደቀውን አልዓዛርን እንዳይመለከት ዓይኖቹን ስለጋረደበት ነበር ይለናል ።[33] ይህ ሰው ብዙ ገንዘብ ባያካብት እንደዚህ ዓይነት ነፍስ አጥፊ ወዳጆችን ባላፈራም ነበር ። በዚህም ምክንያት ይህ ሰው እውነተኛውን ባለጸጋነት እና እጦት ከረፈደ አወቀ ። በምድር ሳለ በልቡ ሀብታም ዝነኛ ነኝ ቢልም በቅዱሳት መጻሕፍት ግን ስሙ እንኳን የለም ።[34]

ወደ ጎበዙ እንመለስ ። ያ ጎበዝ የጌታን ቃል ቢሰማ ኑሮ እጅግ በጣም ባለጸጋ ይሆን ነበር ። ነገር ግን በቤቱ ያከማቻት ያቺ ንብረት እውነቱን እንዳያይ ጋረደችው ። ስለዚህ ሰው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የማቴዎስ ወንጌልን በተረጎመበት ድርሳኑ "ለዚህ ሰው ክርስቶስ ካካበተው ገንዘብ በላይ እንደሚጨምርለት እና ምንም እንደማያጣ መከረው''[35] ሲል እናገኘዋለን ። ቅዱስ ባስልዮስም በተራው እንዲህ ይለዋል ፤ "በወርቅህ ፈረስ ስትገዛ ያልከፋህ በሚጠፉ ነገር መንግሥተ ሰማይን የምትቀበልበት አጋጣሚ ሲኖር ትከፋለህን ?"[36]

ያለንን ንብረት ሁሉ ሸጦ ጌታን መከተል በእርግጥም ቀላል የሚባል ትእዛዝ አይደለም ። ከታሪኩ እንደምንማረው ያ ጎበዝ እያዘነ ከሄደ በኋላ የጌታችን ትእዛዝ ከብዶ የታያቸው ደቀ መዛሙርት ''እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል?''(ማቴ 19÷25) ሲሉ ጠይቀውታል። ይሁን እንጂ የጌታችን መልስ ግን የነገሩን ቀላልነት የሚያሳይ አልነበረም ። ይልቁንም የሰውን ድካሙን ያውቃልና "ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም ። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል ።'' (ማቴ 19÷26) አላቸው እንጂ ። የትኛውንም ክርስቲያናዊ ምግባር በራሳችን ያለእርሱ እርዳታ ልናደርገው አንችልም ። ክርስቲያን ሆኖ መኖር ቀላል ነው ያለው ማነው ? ክርስቲያን ሆኖ መገኘትን ፥ ማለትም ራስን አሳልፎ መስጠትን ፥ እውነትን እስከ ሞት ድረስ መመስከርን ፥ ያለንን ሁሉ በመሸጥ ራስን ባዶ ማድረግን ፥ የሰው ልጅ በራሱ አቅም በፍጹም ሊያደርገው የሚችለው አይደለም ። ነገር ግን ከሁሉም በፊት መፈለግ ይቀድማል ። ይህን ሕይወት አጥብቀን ስንሻው እናገኘዋለን ። ወደዚህ ሕይወት የሚያስገባውንም በር ስናንኳኳው ይከፈትልናል ።

---

33 St. John chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p 106

34 St. John chrysostom, *On Wealth and Poverty*, p. 105

35 St. John Chrysostom, *Homilies on the Gospel of Matthew*, Edited by Boer P.A. Sr., (Veritatis Splendor Publications, 2012), pp. 986-7

36 St. Basil the Great, *On Social Justice*, p. 38

## ዋቢ መጻሕፍት


### አማርኛ ምንጮች

መብራቱ ኪሮስ ገብሩ(ዶ/ር፣ቀሲስ) ፣ *አኰቴተ ቁርባን ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቅዳሴ መሠረት፣ ታሪካዊ እድገት እና ይዘት* (ካሊፎርኒያ ፣ 6ተኛ ዕትም ፣ 2016 ዓ.ም )

መጽሐፈ ስንክሳር

*ወንጌል ቅዱስ ፤ ከቀድሞ አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው* ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፤ 1997 ዓ.ም ፤ አዲስ አበባ

### Youtube and podcast sources

ኤማሁስ ሚዲያ ፣ ምጽዋት

Josaiah Trenham, Money and the Christian, PNP

Josaiah Trenham, Wealth, PNP

Spiridon, MONEY

Thomas Hopko , Christ and the Poor

### እንግሊዝኛ ምንጮች

Clays, Gregory. *The Cambridge Companion to Utopian Literature*; edited by Gregory Clays, (Cambridge University Press, 2010)

Clapsis, Emmanuel. “Wealth and Poverty in Christian Tradion”, (Greek Orthodox Theological Review, 2009)

McGukin John Anthony, *The Orthodox Church:An Introduction to its history, doctrine, and spritual culture* (Blackwell publishing, 2008)

Heelas, Paul. *The New Age Movement : The Celebration of the Self And the Sacralization of Modernity* (Blackwell Publishers, 1996)

St. Basil the Great, *On Social Justice* (Trans. C. Paul Schroeder. Yonkers, New york; St. Vladmir’s Seminary Press, 2009)

St. John Chrysostom. *Homilies on the Gospel of Matthew* (ed. Paul A. Boer Sr., Veritatis Splendor Publications, 2012)

St. John Chrysostom, *On wealth and poverty* (Trans. Catharine P. Roth. Crestwood , New york : St. Vladmir’s seminary press, 1981)

# ስለ ሕይወት ትርጉም መታጣት

**ዮሐንስ ሙሉጌታ**

† † †

በዘመናችን ምን ያክል ሰዎች 'የሕይወት ትርጉም ምንድነው?' የሚለው ጥያቄ እያሳሰባቸው እንዳለ ፥ ምን ያክል ሰዎች መልስ እንዳላገኙለት እና ምን ያክል ሰዎች ደግሞ መልስ ማጣታቸው ተስፋ እንዳስቆረጣቸው በቁጥር ማስቀመጥ ባንችልም ፥ ትርጉም የማጣቱ ስሜት እና የሚያስከትለው ተስፋ መቁረጥ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደመጣ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም ። ሌላው ቢቀር ራስን የማጥፋት ዜናዎችን የምንሰማበት ድግግሞሽ መጨመር ብቻ ለዚህ ጥሩ ምስክር ይሆናል ። በእኛም ሆነ በምዕራቡ ዓለም የምንመለከተው ማኅበራዊ ቀውስም ሌላ ምስክር ነው ። ነገር ግን እነዚህ ምስክሮች ባይኖሩ እንኳን በዘመናችን ግላዊነት (individualism) መሠረታዊ የአኗኗር ፍልስፍናችን መሆኑን ከማስተዋል ብቻ በመነሣት[1] ብዙ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ትርጉም ስለማጣታቸው እርግጠኛ መሆን እንችላለን ።

እዚህ ጋ አንድ ሰው ፥ "የግላዊነት መስፋፋት የሕይወትን ትርጉም ከማጣት ጋር ያለው ዝምድና ምንድን ነው?" ብሎ ሊጠይቅ ይችላል ። ምንም እንኳን በዘመናችን ግላዊነት የነጻነት አቻ ተደርጎ ቢሰበክም እውነታው ግን ግላዊነት ከሌሎች ሰዎችና ፍጥረታት ጋር ያለንን ዝምድና በመቀነስ የራሳችንን ልቅ ስሜቶች ለማርካት የምናደርገው እንቅስቃሴ መሆኑ ነው ። ግላዊነት በሰፈነበት ማኅበረ ሰብእ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ዓላማው የራሱን "ነጻነት" መጠቀም ፥ ማለትም ስሜቶቹን እና ፍላጎቶቹን በተቻለ መጠን ማርካት ነው ። ከሌሎች ሰዎች እና ፍጥረታት ጋር ያሉት ግንኙነቶች ደግሞ ልዩ ልዩ ግዴታዎችን ይዘውበት ስለሚመጡ ስሜቶቹ እና ፍላጎቶቹ ከእነዚህ ግዴታዎች ጋር በተቃረኑበት መጠን ለዚህ ዓላማው እንቅፋት ይሆናሉ ። ልጅነትም ሆነ ወላጅነት ፥ ዝምድናም ሆነ ጉርብትና ፥ ትዳርም ሆነ ወዳጅነት ፥ የእድር እና የቀዬ አባልነትም እንኳን የየራሳቸውን ኃላፊነቶች ይዘው ይመጣሉ ። እነዚህ ኃላፊነቶች ደግሞ ብዙ ጊዜ የግል ስሜትንና ፍላጎትን የሚገድቡ ወይም የሚጻረሩ ናቸው ። ስለዚህ እንዲህ ያሉት ግንኙነቶች ግላዊነትን መመሪያው ላደረገ ግለሰብም ሆነ ማኅበረ ሰብእ እንደ ማሰሪያ እና እንደ እንቅፋት መቆጠራቸው አይቀሬ ነው ። ስለዚህም የበለጠ ግላዊ በሆንን መጠን ፥ ማለትም ስሜቶቻችንን እና ፍላጎታችንን ማእከል ባደረግን መጠን ፥ እንዲህ ያሉት ዝምድናዎች እና ግንኙነቶች መቀነሳቸው አይቀሬ ይሆናል ። አንዳንዶቹን ጨርሰን ልንተዋቸው እንችላለን ፤ ሌሎቹን ደግሞ ባንበጥሳቸውም ግን አሳሪነታቸው እንዳይሰማን ፥ አሳሪነታቸው ከተሰማን ደግሞ በቀላሉ አውልቀን ለመጣል እንዲያመቸን ፥ በእጅጉ እናላላቸዋለን[2] ። የሕይወታችን ምሉእነት መለኪያም በእነዚህ ግንኙነቶች ውስጥ ያሉብንን ኃላፊነቶች ምን ያክል መወጣታችን ሳይሆን ፥ ምን ያክል በእነዚህ ግንኙነቶች ሳንታጠር ስሜቶቻችንን እና ፍላጎቶቻችንን መፈጸም ችለናል የሚል ይሆናል ። ዋናው ተግባራችን ራሳችንን ማፍቀር ፥ ማለትም ከውስጣችን የሚመጡትን ስሜቶችና ፍላጎቶች በተቻለ መጠን ለማርካት መሞከር ነው ማለት ነው ።

ብዙ አጥኚዎች ግላዊነትን ከዘመነ "አብርሆት" (Enlightenment) እና ያን ዘመን ተከትለው ከመጡ ክስተቶች ጋር ያያይዙታል ። የኢኮኖሚ እድገት ፣ ኢ አማኒነት ፣ ዘመናዊው ባህልና ፖለቲካዊ ፍልስፍና ወዘተርፈ ለግላዊነት መዳበር ምክንያት ተደርገው ይጠቀሳሉ ።[3] ይህ አመክንዮ ትክክል ቢሆንም ፥ ምሉእ ግን አይደለም ። በግላዊነትና በኅብረታዊነት ፥ ራስን በማፍቀርና ሌሎችን በማፍቀር ፥ እንዲሁም ትርጉም በሌለውና ትርጉም ባለው ሕይወት መካከል ያለው መስመር ከምንገምተው በላይ አሻሚ ነው ። ስለዚህ

---

[1] Henri C. Santos et al., *Global Increases in Individualism*, in Psychological Science 28, no. 9 (July 13, 2017), 1228–39. https://doi.org/10.1177/0956797617700622.

[2] በኋላ እንደምናየው እነዚህን ግንኙነቶች እንዲህ በሚታይ መልኩ ሳንተዋቸው ወይም ሳንቀንሳቸውም ፥ ነገር ግን ስሜቶቻችንን እና ፍላጎታችንን ለማርካት መጠቀሚያ ልናደርጋቸው እንችላለን ።

[3] Henri C. Santos, Michael E. W. Varnum, and Igor Grossmann. *Global increases in individualism*, 1228–39. https://doi.org/10.1177/0956797617700622.

ምንም እንኳን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ግላዊነትን ተመራጭ እና ገዢ ወደሆነ ማኅበራዊ መርሕ በመቀየር ረገድ ከፍተኛ ሚና ቢኖራቸውም ፥ እነዚህ ምክንያቶች ከመኖራቸውም በፊት ግላዊነት በተለያየ መንገድ ራሱን ይከሥት ነበር ። እንዲያውም የሰው ልጅ በዚህ ዓለም መኖር ሲጀምር ጀምሮ ይህ ዝንባሌ ተለይቶት አያውቅም ። ስለዚህም እነዚህ አጥኚዎች የችግሩን ሥር በትክክል አግኝተውታል ለማለት ያስቸግራል ።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ፣ የባህል ለውጦች ፣ አዳዲስ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ፍልስፍናዎች ለግላዊነት መስፋፋት ተጽዕኖ ማሳደራቸው ባይካድም ፥ ተጽዕኗቸው ግን ቀጥተኛ ሳይሆን ተዘዋዋሪ ነው ። ግላዊነትን በማበረታታት ሌሎችን እንዳንመለከትና የራሳችን ስሜቶች እና ፍላጎቶች ላይ ብቻ እንድናተኩር ይገፋፉናል ። ነገር ግን ይህ ግፊት መጠኑ እንዲጨምር እና አኳኋኑ እንዲለወጥ አደረገው እንጂ ራስን ማፍቀር አስቀድሞም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የነበረ ነው ።

ኅብረታዊ በሚመስል መልኩ ተሰብስበው ያሉ ሰዎች እንኳን ራሳቸውን በማፍቀራቸው ምክንያት ግላዊ ሊሆኑና ነገሮችን ከፍትወቶቻቸው አንጻር ብቻ ለመረዳት ሊሞክሩ ይችላሉ ። ሌላው ቀርቶ ክርስትናን ሳይቀር ራሳቸውን ለማፍቀር ጭምብል እና መሣሪያ አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ ። በዚህ ጽሑፍ ግላዊነት ፥ ራስን ማፍቀር እና ራስን ከማፍቀር ጋር አብረው የሚያይሉት ፍትወታት እንዴት የሕይወትን ጣዕም እና ትርጉም ወደ ማጣት እንደሚያደርሱ ለማብራራት እሞክራለሁ ። ክርስትናም በምን መንገድ እንዲህ ላለው ጉዞ ጭምብል ሊደረግ እንደሚችል እንመለከታለን ።

ከዚያ በፊት ግን የትርጉምን ፣ የእውነትን ፣ የፍቅርን ፣ የልቅ ስሜቶችን ፣ የኅብረታዊነትንና የግላዊነትን ምንነት መረዳት አስፈላጊ ነው ። ምክንያቱም በዘመናችን እነዚህ ቃላት ክርስትና ከሚሰጣቸው ብያኔ የሚቃረኑ አዳዲስ ብያኔዎችን እንዲይዙ ተደርገዋል ። ስለዚህ በቅድሚያ ፍቺያቸውን ሳናብራራ ብንቀጥል በቀላሉ ወደተለያየ መረዳት ልንበተን እንችላለን ። ቤተ ክርስቲያናችን እንደምታስተምረን የእነዚህን ቃላት ፍቺ በራሳችን ልንወስን አንችልም ። ይልቁንም ትርጉማቸውን የምናገኘው ከመለኮታዊ መገለጥ ነው ። ስለዚህ ለውይይታችን መሠረት የሚሆነንን ማዕቀፍ ለመፍጠር በመጀመሪያ እነዚህን ቃላት ኦርቶዶክሳዊ ርእዮተ ዓለምን መሠረት አድርገን እንዳስሳለን ።

## እውነታ ፍቅርና ኅብረታዊነት በምስጢረ ሥላሴ

አማናዊ እውነታ ራሱ እግዚአብሔር ነው ። ከእግዚአብሔር መሠረትነት ውጪ በራሱ 'የሆነ' ነገር የለም ። ፍጥረታትም እውነታነትን የሚያገኙት ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው ። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬን ሊያፈራ እንደማይችል ሁሉ (ማቴ 7፥18) እግዚአብሔርም እውነታ ሆኖ ሐሰትን አያስገኝም ። ስለዚህም ሐሰት የተፈጠረ ነገር አይደለም ፤ በራሱ 'ህልው' ሆኖ ሊገኝም አይችልም ።

ከእግዚአብሔር የሚገኘው ሁሉ መልካምና እውነት ነውና ፥ ሐሰት ከእርሱ ጋር አይስማማም ፤ እውነታ ግን መነሻው ከእግዚአብሔር ነው ። ሐሰት የራሱ አካል ያለው ነገር ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተገኘ እና ፈቃድ ያለው አካል እውነታን በመቃረን የሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው ። ይህንም ያልነው ሐሰት የክፋት ዓይነት ስለሆነ ነው ። ክፋት ደግሞ የበጎነት አለመኖር እንጂ በራሱ አካል ያለውና ወደ ሌላ አካል ያለፈቃድ የሚተላለፍ ነገር አይደለም ። ታላቁ ዲዮናስዮስም "ክፋት የመልካምነት መታጣት ነው ።"[4] ሲል ይህን ማለቱ ነው ።

ሐሰት ደግሞ የክፋት ዓይነት ስለሆነ ፥ እሱም እንደ ክፋት ሁሉ የእድገት ፣ የዓላማ ፣ የባህርይ ፣ የአመክንዮ ፣ የምንጭ ፣ የግብ ፣ የብያኔ ፣ የፈቃድና የምንነት ተቃራኒ ነው ።[5] ሐሰት 'የሆነ' ነገር አይደለም ፤ አሊያም ህያው በሆኑ ነገሮች 'ህልው' ሆኖ አይቀመጥም ። ይልቁንም እውነታን በፈቃዳችን በመግፋታችን የሚፈጠረው ባዶነት ነው ።[6] በአጭሩ ፥ ሐሰት ሕላዌም ሕይወትም የለውም ።

---

[4] "What we are left with is this, namely, that evil is a weakness and a deficiency of the Good.", "(ከዚህ በኋላ) ክፋት መልካም የሆነው ነገር መታጣት እና መዳከም ነው ብለን መደምደም ብቻ ነው ያለን አማራጭ ።" Dionysius the Areopagite, *Pseudo-Dionysius: The Complete Works*, trans. Paul Rorem and Colm Luibheid (New York: Paulist Press, 1987), 95.

[5] "Thus, evil is contrary to progress, purpose, nature, cause, source, goal, definition, will, and substance. It is a defect, a deficiency, a weakness, a disproportion, a sin.", "ስለዚህም ክፋት የእድገት ፣ የዓላማ ፣ የባህርይ ፣ የአመክንዮ ፣ የምንጭ ፣ የግብ ፣ የብያኔ ፣ የፈቃድና የምንነት ተቃራኒ ነው። ክፋት ጉድለት፣ እጥረት፣ ድካም፣ አለመመጣጠን፣ ኃጢአት (ማጣት) ነው ።" Dionysius the Aeropagite, *Pseudo-Dionysius, The complete works*, p. 95.

[6] "In short, evil, as I often, so often said, is weakness, impotence, a deficiency of knowledge, of ceaseless knowledge, of belief, of desire, and of activity of the

ስለዚህ ሐሰትን ‘እውነት’ ነው ብሎ መቀበል መሳሳት ብቻ ሳይሆን ከሕይወት መጉደል ነው ። ሐሰት ኃጢአት (ማጣት) ነው ፤ ይኸውም በነጻ ፈቃድ ከእግዚአብሔር የመለየት መንገድ ነው ።

ለምሳሌ “ክብ የሆነን አራት መአዘን ተመለከትኩ ።” ብላችሁ ፥ የዚህ አባባል ትርጉሙ ምን ይሆናል ? ክብ ትርጉም አለው ፤ አራት መአዘን ትርጉም አለው ፤ መሆንና መመልከትም ትርጉም አላቸው ። ዓረፍተ ነገሩ ግን በጠቅላላው ምንም ትርጉም የለውም ። ትርጉም ሊኖረው ይቅርና በሐሳባችን እንኳ ልናስበው አንችልም ። እንደዚሁ ሐሰት እውነታን እውነታነቱን እንዲያጣ አድርጎ ለማዋቀር መሞከር (በሌላ አነጋገር የእውነትን ውቅር ማፍረስ) ነው ። ምንነቱም ይኸው ነው ፥ የእውነት መዛባት እና መፍረስ ። የአንድ ሕንጻ ፍራሽ ለሕንጻው እንደሆነው ፥ ሐሰትም ለእውነት እንዲሁ ነው ። ነገር ግን እውነት በራሱ መዛባት የማይችል በመሆኑ እንዲህ ባለው ሙከራ የሚዛባውም ሆነ የሚፈርሰው ሐሰትን የተቀበለው ሰው ፈቃድ እና ማንነት ነው ። ማለትም ከእግዚአብሔር ያገኘውን እና በማንነቱ ውስጥ ያለውን እውነት ያጣል ፤ በዚያው መጠን ደግሞ ራሱን እያጣ ፥ ‘እያልሆነ’ ይሄዳል ። ሐሰት ከእግዚአብሔር መለየት ነው ። እውነታ እግዚአብሔር ነው ።

እግዚአብሔር እውነታ እንደሆነ ሁሉ ፥ ፍቅርም ነው (1ኛ ዮሐ 4፥16) ። ፍቅር ራስን ለሌላ ስጦታ አድርጎ መስጠትና ሌላው ራሱን መልሶ ስጦታ አድርጎ እንዲሰጠን መጠበቅ ነው ።[7] አብ ፍጹም አካል ያለው ባለቤት ሲሆን ፤ ወልድም ፥ ከአብ የተወለደ ፥ ፍጹም አካል ያለው ባለቤት ነው ፤ መንፈስ ቅዱስም ፥ ከአብ የወጣ ፥ ፍጹም አካል ያለው ባለቤት ነው ።[8] በአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፥ በወልድ አብና መንፈስ ቅዱስ ፥ በመንፈስ ቅዱስም አብና ወልድ ህልው ሆነው ይኖራሉ ። ይህን የፍቅር አኗኗር ኅብረታዊነት እንለዋለን ። ያለ ፍቅር ፣ ያለ ቅድስት ሥላሴ ኅብረታዊነት ሊኖርም ሊታሰብም አይችልም ።

ፍቅር አንድነትን ፣ ኅብረታዊነትን ፣ እውነታን ይገልጣል ።[9] እግዚአብሔር በጸጋው ማለትም በመግቦቱ ፣ በምሕረቱ ፣ በቸርነቱ ፣ በጠባቂነቱ ራሱን ለፍጥረታት ይገልጣል ። እኛም በእርሱ ፍቅር በአንድነት እንኖራለን ። አካላዊው ቃል ፥ የአብ የባሕርይ ልጅ ወልድ ፥ አካሉን ከሰው ባሕርይ ጋር በማዋሐዱ ከእኛም እንደ አንዱ በመቆጠሩ እኛ በወልድ ለአብ የጸጋ ልጆች ሆነናል ። በልጅነታችን ከአብ ለምንቀበለውም ፍቅር መንፈስ ቅዱስ በረቂቅ ጥበቡ እየሰበሰበን እና እያነቃን ምላሽ እንሰጥ ዘንድ አስችሎናል ። ይህን ፍቅር ስንቀበል እና በቻልነው አቅም የፍቅር ምላሽ ስንሰጥ ደግሞ ከሥላሴ አኗኗር በጸጋ ተካፋይ እንሆናለን ፤ በሌላ አነጋገር እግዚአብሔርን መስለን እንኖራለን ። ይህ መለኮታዊ ፍቅር ደግሞ ታላቁ ዲዮናስየስ እንደሚለው ‘ወደር በሌለው ትፍሥሕት የሚመላ ነው ። ከዚህ ትፍሥሕት የተነሣም አፍቃሪው ባለቤትነቱ የራሱ ሳይሆን የተፈቃሪው ይሆናል ።’[10]

ስለሆነም ፥ ፍቅር በምንነቱ ኅብረትን ስለሚጠይቅ ፥ አንድ ነጠላ አካል ብቻውን አፍቃሪ ሊሆን አይችልም ።

Good.”, Dionysius the Aeropagite, *Pseudo-Dionysius: The complete works*, p. 96.

[7] Dumitru Stăniloae, *Eternity and Time* (Oxford: Slg Press, 2001).

[8] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አካል (Hypostasis) የሚለው ቃል ጽኑ እውነታን የሚያመለክት ነው ። ጽኑ እውነታ ስንል ከህሊናችን ምናብ ውጪ በራሱ ሆኖ የሚገኝን ነገር የሚጠቁም ነው ። ነገር ግን ሁሉም አካል ማንነት የለውም ። ለምሳሌ ድንጋይ አካል ቢሆንም ‘ማን ነህ ?’ ሊባል አይችልም ፥ አንተ/አንቺ አይባልም ፤ ራሱንም እኔ አይልም ፤ ልዩ አይደለም ፤ አያፈቅርም ። በዚህ ትንተና ውስጥ ይህን የማንነት መኖር ለማሳየት የገባው ቃል ደግሞ ባለቤት (prosopon) የሚለው ነው ።

[9] “Love is characterized by this paradox: On the one hand it unites subjects who love each other, on the other, it doesn’t confuse their identity, Love brings one subject to another, without merging their identities, because in this case love would cease. It would kill the persons who love each other; it wouldn’t assure them of a permanent existence. This paradox can be explained by the radiation of love, as energy which is communicated from one person to another without them being depleted in this communication.”, “ፍቅር በዚህ ግራ ቀኝ ክስተት ይገለጣል፤ በአንድ በኩል የሚፋቀሩ ባለቤቶችን አንድ ያድርጋል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ማንነታቸውን አያደባልቅም። ፍቅር አንድ ባለቤትን ወደ ሌላ ባለቤት ማንነታቸውን ሳይደባልቅ ያመጣል፥ ማንነታቸው ቢደባለቅ ኖሮ ግን ፍቅር ይጠፋ ነበር፤ ቋሚ የሆነን ህልውና ለየሚፋቀሩት ባለቤቶች ከማረጋገጥ ይልቅም በገደላቸው ነበር። ይህ ግራ ቀኝ ክስተት ከአንድ ባለቤት ወደ ሌላ ባለቤት ባለቤትነታቸውን ሳያጠፋ እንደሚተላለፍ ኃይል የፍቅርን ነጸብራቅ በማየት መግለጽ ይቻላል።”, Dumitru Stăniloae, *Orthodox Spirituality : A Practical Guide for the Faithful and a Definitive Manual for the Scholar* (St. Tikhon’s Seminary Press, 2003), 52–53.

[10] “This divine yearning brings ecstasy so that the lover belongs not to self but to the beloved.”, ‘ወደር በሌለው ትፍሥሕት የሚመላ ነው ። ከዚህ ትፍሥሕት የተነሣም አፍቃሪው ባለቤትነቱ የራሱ ሳይሆን የተፈቃሪው ይሆናል ።” Dionysius the Areopagite, *Pseudo-Dionysius: The Complete Works*, 82.

ለምሳሌ በእስልምና አስተምህሮ እንደሚሰበከው ያለ ጥብቅ አንድነት ብቻ ያለው አምላክ ፍቅር ሊሆን አይችልም ፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው አምላክ ራሱን አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ ሊቀበለው የሚችል ሌላ (ባለቤታዊ) አካል ስለሌለው ፥ በራሱ ከመታጠር ውጪ አማራጭ የሌለው ስለሆነ ነው ። በተመሳሳይ እኛም ራሳችንን እንደ ስጦታ ለሌሎች እስካልሰጠን ድረስ ብቻችንን ሆነን በፍቅር አንኖርም ። ያለ ኅብረት ፍቅር አይታሰብም ። በመሆኑም ግላዊነት ፥ ማለትም ራስን በራስ ለራስ ለመስጠት መሞከር ፥ ወይም በሌላ አገላለጽ ራስን ማፍቀር የፍቅር ተቃራኒ ነው ።

እግዚአብሔር ፍቅርና እውነት እንደሆነ ሁሉ ፥ ሕይወትም ነው (ዮሐ 1፥4፣ ዮሐ 14፥6) ። ፍጥረት ሁሉን ያገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ሱታፌ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ፥ "በእሱ በእግዚአብሔር እንኖራለን፤ በእሱ እንንቀሳቀሳለን፤ በእሱ የመሆናችንን ምንነት ወይም ባሕርያችንን እናገኛለን።" (የሐዋ ሥራ 17፥28) በማለት የሕይወታችን መሠረት እግዚአብሔር መሆኑን ያስታውሰናል። ፍጥረታት ሁሉ ከመፈጠራቸው አስቀድሞ በስማቸው ፣ በሥርዓታቸው ፣ በልኬታቸው እና ልዩ ልዩ በሆነ አነዋወራቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ይታሰቡ ነበር ። የፍጥረት ሁሉ መነሻና ጠባቂ እግዚአብሔር ነው ። ሁሉም ፍጥረት ህልውናቸውን የሚያገኙት ከእግዚአብሔር ኃይል በመሳተፍ ነው። ከእግዚአብሔር የተለየ አካል ሁሉ 'የሆነ' ሆኖ ሊኖር አይችልም ፤ ከማንነትና ከምንነት ተራቁቶ 'ምንም' ይሆናል እንጂ ።[11] እግዚአብሔር በማይቀየር የመለኮታዊ ሕሊናው ንድፍ መሠረትነት በመልካም ፈቃዱ ፍጥረትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣል ። በዚህ ንድፍ መሠረትም በጠባቂነቱ ፍጥረትን ያሳድጋል ፤ በፈራጅነቱም ፍጥረትን ፍጽምና ላይ ያደርሳል ። ታላቁ ዲዮናስዮስ ይህን ሲገልጽ፦

> "የሆነ ሁሉ እና ዘመናት ሁሉ ህልውናቸውን የሚያገኙት 'አስቀድሞ ከሆነው' ከእርሱ ነው ። ዘለዓለማዊነትና ጊዜ ከእርሱ ነው ። 'አስቀድሞ የሆነው' እርሱ የሁሉ ዘለዓለማዊነት ፣ የሁሉ ጊዜ ፣ የሁሉም ዓይነት አካል ምንጭና ምክንያት ነው ። ሁሉ ነገር ከእርሱ ይሳተፋል ። ከእርሱም ከመሳተፍ የሚቀር አካል የለም ። እርሱ ከሁሉ በፊት ነው ፤ በእርሱም ሁሉ ነገር በአንድነት ይሰበሰባል ። ባጭሩ ፥ የየትኛውም ነገር ህልውና ያለው የሚታየው እና የሚጠበቀው አስቀድሞ በሆነው በእርሱ ነው።"[12]

ይህ ጽሑፍ ካለው ወሰን አንጻር ወደ እዚህ ነገረ ሃይማኖት ትንተና በጥልቀት ሳንገባ ጉዳዩን ለማሰር ያክል የሁሉ ፍጥረታት መሠረታዊ መርሕ ወይም ንድፍ አንዱ ክርስቶስ ነው ። ቅዱስ ጳውሎስም ይህን እውነታ ሲገልጽ ስለ ክርስቶስ እንዲህ ይለናል ። "ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥረዋል ፤ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ፤ ሁሉም በእሱ ተጋጥመዋል (በአንድነት ተሰብስበዋል)" (ቆላ 1፥17) ስለዚህ ፍጥረት ሁሉ መነሻውንና መድረሻውን፤ ግቡንና ትርጉሙን የሚያገኘው በክርስቶስ ነው ። ስለዚህም የእውነታ ፣ የፍቅር ፣ የሕይወት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር ነው ።

### ራስን ማፍቀርና ትርጉም አልባ ሕይወት

ከላይ ባየነው ትርጉም መሠረት፣ ፍቅር ራስን ለሌላው ስጦታ አድርጎ መስጠትና ሌሎችም ራሳቸውን ስጦታ አድርገው እንዲሰጡን መከፈት ከሆነ፣ ራስን ማፍቀር ማለት ራስን በራስ ለራስ ለመስጠት የመሞከር ድርጊት ነው። ማፍቀር እግዚአብሔርን መምሰልና በምንችለው ልክ እንደ እርሱ መኖር ነው ። ሌሎችን በእግዚአብሔር ፍቅር በወደድን ቁጥር እግዚአብሔርን እየመሰልን እንመጣለን ። ፍቅር ሌሎችን እንድናይ ያደርገናል ። ዮሐንስ ዘሰዋስው እንዳለው፥ "አንድ አፍቃሪ የተፈቃሪውን መልክ በህሊናው ዐይን (በልቡናው) ያኖረዋል፤ በፍቅርም አጥብቆ ይጠብቀዋል።"[13]

---

[11] ምንም (non-being) የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው። የመጀመሪያው ከመሆን ወይም ከሆነ ነገር በላይ ሆኖ ያለ ማለት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ምንም ነው ሲባል እግዚአብሔር የሆነ ቢሆንም ግን ከመሆን በላይ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በተቃራኒው ምንም የሚለው ቃል መሆንን ማጣት ሊያመለክት ይችላል፤ ለምሳሌ ክፋት ምንም ነው ስንል መሆንን አጥቷል ወይም ያልሆነ ነው ማለት ነው። እዚህ ጋር በሁለተኛው ትርጉም እየተጠቀምን ነው።

[12] "Every being and all the ages derive their existence from the Preexistent. All eternity and time are from him. The Preexistent is the source and is the cause of all eternity, of time and of every kind of being. Everything participates in him and none among being falls away, He is before all things and in him all things hold together. In short, the existence of anything whatsoever is there in the Preexistent and is perceived and preserved by Him.", Dionysius the Areopagite, *Pseudo-Dionysius: The Complete Works*, 98-99.

[13] "Someone truly in love keeps before his mind's eye the face of the beloved and embraces it there

ራስን ማፍቀር ግን የዚህ ፍቅር ተቃራኒ ነው ። ራስን ማፍቀር በእኛ ውስጥ የተሳለውን የእግዚአብሔርን መልክ ማደፍረስ ነው። ራሳችንን ባፈቀርን ቁጥር ሌላ የሚባል ነገር ይጠፋል ፤ በሁሉም ነገር ላይ ራሳችንን ማየት እንፈልጋለን ። በራሳችንም እንታጠራለን ።

አንድ አይተነውም ሆነ በሌላ መንገድ አግኝተነው የማናውቀው ሰው ረዘም ያለ መልእክት በጽሑፍ ቢልክልን ፥ ጽሑፉን ስናነብ ላኪው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ መረዳት ሊከብደን ይችላል ? ግላዊ ባሕርይውን ፣ የመጣበትን ባህል ፣የቃላት አጠቃቀሙን ፣ የቋንቋ ችሎታውን እና ሌሎችም ብዙ ስለ እሱ የማናውቃቸው ነገሮች ስላሉ ለማለት የፈለገውን ሙሉ በሙሉ አንረዳውም ። እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ በዚህ የተነሣ የሚፈጠረውን ክፍተት የምንሞላው በራሳችን ግምትና ሐሳብ ነው ። ለምሳሌ እሱ ያስቀይማል ብሎ ያላሰበው አገላለጽ እኛ ከራሳችን ማንነት እና ባህል የተነሣ ሊያስቀይመን ይችላል ። ይህ ማለት ያን ሰው ለመረዳት የሚያስፈልገው ዕውቀት ባጠረን ቁጥር የሚፈጠረውን ክፍተት የምንሞላው በራሳችን ማንነት ነው ማለት ነው ። የምንግባባው ከላኪው ጋር ሳይሆን ከራሳችን ጋር ይሆናል ማለት ነው። በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በአካል በሚደረግ ንግግርም ይኸው ችግር ሊፈጠር ይችላል ።

በተቃራኒው በእጅጉ የምናውቀው ፣ የምንወደው እና እሱም የሚወደን ሰው የጽሑፍ መልእክት ቢልክልን ደግሞ ለመረዳት አያስቸግረንም ። ተሳስቶ ለማለት ያልፈለገውን ነገር ፥ ለማለት የፈለገውን ተቃራኒ ራሱ ቢጽፍ አርመን ልናነበው እንችላለን ። ለምን እንደተሳሳተም ሆነ ምን ለማለት እንደፈለገ በቀላሉ ይገባናል ። ስለዚህ የሰዎችን ሐሳብ የምንረዳበት መጠን ከእነሱ በወጣው ነገር ብቻ ሳይሆን በራሳችን ህሊናም ይወሰናል ማለት ነው ።

ራሱን የሚያፈቅር ሰው ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት ህሊናው እንደ መጋረጃ ይሆንበታል። ራሱን የሁሉም ነገር ማእከል ስለሚያደርግና ሁሉም ነገር ስለ ራሱ ስለሚመስለው ከሰዎች ጋር ሲነጋገር እንኳ የሚያወራው ከራሱ ጋር ነው ። በዚህም ምክንያት ሌሎችን መረዳት አይችልም ፤ የሌሎች ችግርና ሕመምም ሊሰማው አይችልም ። ሌሎችን የሚፈልጋቸው ለራሱ ደስታ እንደሚያገለግሉ እቃዎች ብቻ ነው ። ስለዚህ ከሌሎች ጋር እውነተኛ ኅብረት መፍጠር አይችልም ።

ራሱን የሚያፈቅር ሰው፣ በትዳርም ሆነ በጓደኝነት ወይም በማኅበረ ሰብዕ ውስጥ እውነተኛ ዝምድና መመሥረት አይችልም። ግንኙነቱ ሁሉ ሐሰተኛና የቅዠት ነጸብራቅ ነው ። ሁሉንም ነገር የሚመዝነው በራሱ ደስታና ሕመም ሚዛንነት ስለሆነ ፥ የነገሮችን እውነተኛ ትርጉም ፣ ምክንያትና ዓላማ ሊረዳ አይችልም ።

ከላይ እንዳየነው ፥ የነገሮች ሁሉ አማናዊ ምክንያት ፣ ትርጉምና መርሕ እግዚአብሔር ነው ። ራሱን የሚያፈቅር ሰው ግን ከራሱ ዓለም ወጥቶ እግዚአብሔርን መመልከት ስለማይችል ፥ ራሱን በሚወድበት መጠን የነገሮችን ትርጉም መረዳት ያቅተዋል ።

※ ※ ※

ራሱን የሚያፈቅር ሰው መገለጫው ፍትወታት የሚነግሡበት መሆኑ ነው።[14] ታዋቂው ራሺያዊ የልቦለድ ጸሐፊ ዶስቶየቭስኪ በልብ-ወለድ ሥራዎቹ ውስጥ ይህን በተለያየ መልኩ በማሳየት ጉዳዩን በጥልቀት እንድንረዳው በር ይከፍታል ። በዚህ ሰው መጻሕፍት ውስጥ እብሪተኝነት ፣ ከንቱ ውዳሴን መሻት ፣ ትዕቢት ፣ በቀል ፣ ጭካኔ ፣ ጥላቻና እና መሰል ፍትወታት የሚመጡት ራስን ከማፍቀርና እግዚአብሔርን ካለማየት ነው ። ይህን ለማሳየት ፥ ከዶስቶየቭስኪ "ወንጀልና ቅጣት" መጽሐፍ ራስኮልኒኮቭ የተባለ ችግረኛ ተማሪ የግድያ ወንጀል እንዲፈጽም የሆነበትን ሂደት እንደ ምሳሌ መመርመር እንችላለን ። ራስኮልኒኮቭ አራጣ አበዳሪ የሆነችን አንዲት አሮጊት መግደል እና ገንዘቧን መውሰድ ተገቢ እንደሆነ ራሱን ለማሳመን በአእምሮው ውስጥ ብዙ ምክንያቶችን ደርድሮ ነበር ። ከእነዚህም መካከል ፥ መጠጥ ቤት ቁጭ ብሎ ሳለ አንድ ተማሪ ስለዚች አሮጊት ሲናገር የሰማው የጥቅማዊነት[15] ሙግት ይገኝበታል ።

> "በአንድ በኩል ፥ ለማንም የማትጠቅም ፥ ይልቁንም ለሁሉም ጠንቅ የሆነች ፥ ለምን በሕይወት እንደምትኖር እንኳን የማታውቅ ፥

tenderly.", Saint John Climacus, *The Ladder of Divine Ascent* (New York: Paulist Press, 1982), 287.

[14] ሰፋ ላለ ትንተና *Orthodox Spirituality: a practical guide for the faithful and a definitive manual for the scholar* የተሰኘውን መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል እንዲያነቡ እጠቁማለሁ።

[15] የጥቅማዊነት ሙግት(Utilitarian argument) አንድ ድርጊት ውጤቱ ለብዙሃኑ ደስታን እስካስገኘ ድረስ ጥቂቶችን ቢጎዳ እንኳን መደረግ አለበት ብሎ የሚሞግት ነው።

> ነገ በራሷ መሞቷ የማይቀር ፥ ደደብ ፣ የማትረባ ፣ ከፉ ፣ በሽተኛ አሮጊት አለች . . . በሌላ በኩል ደግሞ በትኩስ ኃይል የተሞሉ ፥ ነገር ግን ድጋፍ በማጣት የሚባክኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ለጋ ወጣቶች በየቦታው ይባክናሉ ። ይህቺ አሮጊት ስትሞት አንዱ ገዳም ወርሶት ያለ ምንም ፍሬ የሚቀረው ገንዘብ ፥ ብዙዎችን የሚጠቅሙ እልፍ አእላፋት ሥራዎች ሊጀመሩ የሚችሉበት ነው ። በእርሷ ገንዘብ በሙቶዎች ፣ ምናልባትም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ትክክለኛው የሕይወት መስመር መመለስ ይችላሉ ፤ ብዙ ቤተሰቦች ከድህነት ፣ ከመበስበስ ፣ ከጥፋት ፣ ከሕመም ይድናሉ ። እርሷን ገድለህ ገንዘቧን ትወስድና ፥ ከዚያ በኋላ እሱን ይዘህ መላውን የሰው ዘር ለማገልገል ትተጋለህ ። ምን ይመስልሃል ? በሺዎች የሚቆጠሩ መልካም ሥራዎች እዚህ ግባ የማትባልን አንዲት ወንጀል አያካክሱም ትላለህ ?”[16]

ብዙ ጊዜ የምንሰማቸው ነገሮች ትኩረታችንን የሚስቡትና በህሊናችን ውስጥ የሚቀሩት ፣ አስቀድመን እያሰብናቸው ከነበርናቸው ነገሮች ጋር የሚገናኙ ከሆኑ ነው ። ራስኮልኒኮቭም ይህ በአጋጣሚ የሰማው ሙግት አስቀድሞ በአእምሮው ሲያብሰለስለው የነበረ በመሆኑ ፥ ከሌላ ሰው ሲሰማው ወንጀሉን የመፈጸም ሐሳቡን አጸናለት ።[17]

ራስኮልኒኮቭ ለወንጀሉ እንደ ምክንያት ያቀረበው ሌላ ፍልስፍናዊ ሐሳብም ነበረ ። ይህን ሐሳብ እንደ መጣጥፍ ጽፎ ወደ አንድ ጋዜጣ ልኮት ታትሞለት ነበር ። በዚህ ሐሳብ መሠረት ሰዎች 'ተራ' እና 'ልዩ' ተብሎ ለሁለት ይከፈላሉ ። 'ተራ' ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ በመዋለድ ራሳቸውን ከማባዛትና በሌሎች ከመመራት በቀር ያለፈ ተልዕኮ የላቸውም ። በተቃራኒው፣ 'ልዩ' ሰዎች አዲስ ነገርን መናገርና መሥራት የሚችሉ ናቸው።[18] ስለዚህ እነዚህ ‘ልዩ’ ሰዎች ይህን የተለየ ተልዕኮአቸውን ከግብ ለማድረስ ሲሉ ፥ ወንጀል መፈጸምን ጨምሮ ፥ ማንኛውንም ሰው ሰራሽ ድንበር የማለፍ መብት አላቸው ። ለምሳሌ፣ “ኒውተን ግኝቶቹን ለመላው የሰው ዘር ለማሳወቅ ሲል አስር ወይም መቶ ሰዎችን የማስወገድ መብት አለው ፤ እንዲያውም ይህ ግዴታውም ጭምር ነው ።”[19]

እርግጥ ነው ፥ ተራዎቹ ሰዎች ይህን መብት አይቀበሉትም ፤ ይልቁንም ልዩ የሆኑትን ሰዎች ይገድሏቸዋል ወይም ያሳድዷቸዋል ። ያም ሆኖ ግን ድንቅ ሰዎች ምንጊዜም የተራዎቹ ሰዎች መሪ መሆናቸው አይቀሬ ነው ። ምክንያቱም ልዩዎቹ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ተራዎቹ ሰዎች ሐሳባቸውን ተቀብለው ያከብሩታል ።[20]

ራስኮልኒኮቭም ራሱን ከልዩዎቹ ሰዎች ጎራ በመመደቡ አሮጊቷን መግደል ለእርሱ ጥፋት ሳይሆን መብቱ ፥ ሲልም ግዴታው ፥ እንደሆነ ወሰነ ። አደረገውም ። ከአደረገው በኋላ ግን የቀደመውም ሆነ ሁለተኛው አመክንዮ እንደ ቀድሞው ግድያው ትክክል ወይም መብቱ እንደነበረ ሊያሳምኑት አልቻሉም ። ውስጡ ፈጽሞ ሰላም አጣ ።

መጠጥ ቤት ተቀምጦ የሰማውም ሆነ በጋዜጣ የወጣው ትወራ ራስኮልኒኮቭ እውነተኛው ምክንያቱን ከራሱ ለመሰወር የተጠቀመባቸው መንገዶች ነበሩ ። ይህ እውነተኛ ምክንያት የተገለጠው ፥ ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ ፈጽሞ ሰላሙን ያጣው ራስኮልኒኮቭ በወጣትነቷ

---

[16] “On the one hand you have a stupid, meaningless, worthless, wicked, sick old crone, no good to anyone and, on the contrary, harmful to everyone, who doesn't know herself why she's alive, and who will die on her own tomorrow... Listen, now. On the other hand, you have fresh, young faces that are being wasted for lack of support, and that by the thousands, and that everywhere! A hundred, a thousand good deeds and undertakings that could be arranged and set going by the money that old woman has doomed to the monastery! Hundreds, maybe thousands of lives put right; dozens of families saved from destitution, from decay, from ruin, from depravity, from the venereal hospitals—all on her money. Kill her and take her money, so that afterwards with its help you can devote yourself to the service of all mankind and the common cause: what do you think, wouldn't thousands of good deeds make up for one tiny little crime?”, Fyodor Dostoyevsky, *Crime and Punishment*, trans. Richard Pevear and Larissa Volokhonsky (New York: Toronto, 1993), 65.

[17] Fyodor Dostoyevsky, *Crime and Punishment*, p. 66

[18] Fyodor Dostoyevsky, *Crime and Punishment*, p. 260

[19] Fyodor Dostoyevsky, *Crime and Punishment*, pp. 259-260

[20] Fyodor Dostoyevsky, *Crime and Punishment*, p. 260

ወደ ሴተኛ አዳሪነት ተገፍታ ከገባችው እና በዕድሜ ከምታንሰው ፣ በትምህርትም ከማትተካከለው ከሶንያ ጋር ባዳበረው ግንኙነት አማካይነት የንስሐ ጉዞውን ሲጀምር ነበር ።

አእምሮው ውስጥ ለሰዎች ሁሉ ንቀት አድሮበት ነበር ። ሁሉም ደደቦች እና ደካሞች እንደሆኑ ፥ የመለወጥም ተስፋ እንደሌላቸው ወስኖ ነበር ። በእነዚህ ደካማ ሰዎች መካከል ወኔው እና ቆራጥነቱ ያለው አንድ ሰው ቢኖር ግን ያ ሰው እንደፈለገ እንደሚገዛቸው ፣ ከወኔው የተነሣ የፈለገውን ማድረግ እንደሚችል ፥ መቻል ብቻ ሳይሆን የፈለገውን በማድረጉ ትክክል እንደሚሆንም ጭምር አመነ ። ያን ሰው ለመሆንም ፈለገ ። ያን ኃይል ፣ ያን ሥልጣን ፣ ያን የበላይነት ፈለገው ። ያን ሰው መሆን መቻሉን ፥ ወኔው እና ቆራጥነቱ ያለው መሆኑን ለማወቅ ሲል አሮጊቷን ገደላት ።

> "ወኔው ያለኝ መሆኑን ማወቅ ፈለግሁ ሶንያ ፥ ይኸው ነው ፤ ወኔው እንዲኖረኝ ስለፈለግሁ ብቻ ነው የገደልኳት ።"

ስለዚህ፣ የወንጀሉ መነሻ ፍልስፍናዊ አመክንዮ ሳይሆን ፥ ከትዕቢት የመነጨና እግዚአብሔርን ከሥፍራው አውርዶ ራሱን የሁሉም ነገር ፈራጅ ፣ ፈቃጅና የበላይ ገዥ ለማድረግ የነበረው አደገኛ ፍላጎት ነበር ። የሶንያ ምላሽም የችግሩን ሥር የተረዳ ነበር ፤

> "እግዚአብሔርን ካድክ ፤ እግዚአብሔርም መታህ ፤ ለሰይጣንም አሳልፎ ሰጠህ !"[21]

በዚህ ምላሿ፣ ሶንያ የራስኮልኒኮቭ ትዕቢት ከእግዚአብሔር በመራቅ ራስን የማፍቀር ጥልቅ መንፈሳዊ ደዌ መገለጫ መሆኑን እንደ መስታወት ሆና እያሳየችው ነበር።

※ ※ ※

ሰውን በጨለማ አስረው የሚያቆዩ ስሜቶች ማለትም የምግብ ፣ የሩካቤ ፣ የሥልጣን ፣ የገንዘብ ፍትወት ፥ መቆጣት፣ ድብርት ፣ ስንፍና ፣ ውዳሴን መሻትና ትዕቢት ሁሉ ከላይ እንዳየነው ራስን ከማፍቀር ጋር በጥብቅ የተያያዙ ናቸው። እነዚህ ፍትወታት ሲያይሉ ደግሞ የልቡናችን የማገናዘብ አቅም ይደክማል ። የምናደርገውን ነገር በሙሉ ከሚያስገኝልን እርካታ እና ከሚያስቀርልን ሥቃይ አንጻር ብቻ እንወስናለን ። በእርግጥ እንደ ራስኮልኒኮቭ ራሳችንን ለማታለል ምቹ ምክንያታዊ የሚመስሉ ሐሳቦችን ፥ መልካም የሚመስሉ ግቦችን ለራሳችን እንነግራለን ። ማድረግ የማንሻቸው ነገሮች ለምን ማድረግ እንደማንችል ወይም እንደሌለብን ራሳችንን ለማሳመን የተወሳሰቡ ሰበቦች እንፈጥራለን ። ፍትወቶቻችንን ከማርካት የሚከለክሉንን ሐሳቦች ፣ እና መረጃዎች እናጣጥላቸዋለን ፥ ወደ እኛ የሚመጡባቸውን በሮችም በሙሉ እንዘጋለን ።

ፍትወታት በመጀመሪያ ወደእኛ ሲመጡ ከእውነታው የተለየ የተጋነነ ምስል ህሊናችን ውስጥ ይፈጥራሉ ። ሔዋን የእባብን ቃል ከሰማች እና ወደ ልቡናዋ ካስገባችው በኋላ እስከዚያ ዕለት የተለየ መስሕብ ያላየችበት እፀ በለስ ከሌላው ጊዜ በላይ አምሮና ደምቆ ታይቷት ነበር (ዘፍ 3፥ 6) ። ይህ የሆነው ዕፀ በለሱ በራሱ ተቀይሮ ከሌላው ጊዜ በተለየ ያማረ ስለሆነ አልነበረም ፤ ይልቁንም ሔዋን ለፍትወቷ ራሷን አሳልፋ በሰጠች ቅጽበት በለሱ ደምቆና አምሮ እንዲታያት ሆነ እንጂ ።

ነገር ግን ፍትወታቱ ወደ አእምሮአችን እና ወደ ሰውነታችን ሲመጡ የሚፈጥሩት የተጋነነ ፣ የተዛባ እና ሐሰተኛ ምስል ያን የፈለጉብንን ነገር እስከናደርግ ብቻ የሚቆይ እና ወደ እውነታነት የማይለወጥ ነው ። ምክንያቱም ቀድሞም እውነት ስላልነበረ ። ሳይገባን የተመኘነውን ድርጊት ካከናወንን በኋላ ፥ ምግቡን ከበላነው ፥ ሩካቤ ከፈጸምን ፥ ገንዘቡን በእጃችን ካስገባን ፥ ሥልጣኑን ከተቆናጠጥን ፥ ንዴታችንን ከተወጣን ወዘተርፈ በኋላ ያ ቀድሞ እንደ ሚራዥ ከርቀት ይታየን የነበረው ቅዠት ከፊታችን ይጠፋል ። በውስጣችን ባዶነት ይነግሣል ።

ራሳችንን ከማፍቀራችን የተነሣ የበለጠ ራሳችንን ለፍትወታት አሳልፈን በሰጠን ቁጥር ደግሞ ይህ የባዶነት ስሜት እየጨመረ ሔዶ መላ ሕይወታችንን ይቆጣጠረዋል ። የትኛውም ዓላማ ፣ ድርጊት ፣ ግንኙነት ወይም ሌላ የሕይወት ገጽታ የዚህ ባዶነት ጥላ ይወድቅበታል ። ታዲያ ይህን ባዶነት ለማምለጥ በፈለግን ቁጥር የምንሄደው እርካታን ፍለጋ ነው ፥ ከእነዚሁ ባዶነትን በውስጣችን ካነገሡት ፍትወታት ዘንድ ቅጽበታዊ ተድላ እንሻለን ። እነሱም ያን የተጋነነ የደስታ ተስፋ መልሰው ይሰጡናል ። የምንሸሸውን ባዶነት ከመፍራታችን የተነሣ ቀድሞውኑም ወደዚያ ባዶነት ያመጡን እነዚሁ አሁን ሌላ ሐሳዊ ተስፋ እየሰጡን ያሉት ፍትወታት መሆናቸውን ልብ አንልም ።

---

[21] Fyodor Dostoyevsky, *Crime and Punishment*, p. 418

ስለዚህም ተስፋውን ለመጨበጥ በመሻት ወደቀደመው ጉድጓድ እንወድቃለን ። ይህ ሒደትም ያለማቋረጥ ይቀጥላል ። በወደቅን ቁጥር ጉድጓዱ ይጠልቃል ። ባዶነቱ ይበረታል ፤ ፍርሀታችን እና ሽሽታችንም በዚያው ልክ ይጸናል ፤ አለማስተዋላችንም እንዲሁ ። በመመጨረሻም ባዶነቱ መላ ሕይወታችንን ይቆጣጠራል ፤ ስለዚህም ሁሉም ነገር ባዶ ፣ ትርጉም አልባ ነው ወደሚል ድምዳሜ እንገፋለን ። ለሁሉም ነገር ግድየለሽ እንሆናለን ፤ ምንም ነገር አይገደንም ፤ ስንፍናም ያጠቃናል ። በአጠቃላይ የባዶነት ሕይወትን ዕለት ከዕለት እንቀምሳለን። ይህን ባዶነት ለማምለጥ ደግሞ ከፍትወቶቻችን ሌላ ምንም መንገድ አይታየንም ። እነሱ ደግሞ በተደጋጋሚ እያሳዩ ከነሡን ተስፋ የተነሣ ባዶ መሆናቸውን ወደ መረዳት እንደርሳለን ። ነገር ግን ሌላ አማራጭ አይታየንም ። ስለዚህም ከባዶነት ለማምለጥ የሚታየን ብቸኛ አማራጭ አለመኖር ይሆናል ። ይህ ስሜት ከበረታ ደግሞ ራስን ወደማጥፋት ሊወስድ ይችላል ። ይህ ሁሉ ራስን በማፍቀር ይከሰታል።

## በሃይማኖት ስም የተደበቀ ራስን ማፍቀርና ትርጉም አልባነት

ራስን ማፍቀርን ከእውነተኛ ፍቅር መለየት እጅግ ከባድ ነው ። የድርጊቶችን ውጫዊ ገጽታ ብቻ በመመልከት ‘ይህ የንጹሕ ፍቅር መገለጫ ነው ። ይህ ደግሞ 'የራስ ወዳድነት ውጤት ነው ።’ ብሎ መፍረድ አዳጋች ነው ። ለምሳሌ አንድ ሰው ‘ሃይማኖተኛ ነኝ’ ወይም ‘እግዚአብሔርን እወዳለሁ’ በማለቱና አዘውትሮ ቤተ ክርስቲያን በመሄዱ ብቻ ‘የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው’ ብሎ መደምደም አይቻልም ። ይልቁንም ፥ ይህ ውጫዊ ተግባሩ ፥ እውነተኛ እምነትን የመፈለግ ሳይሆን ፥ ሃይማኖተኛ ሆኖ ከመታየት ፍላጎት የመነጨ ሊሆን ይችላል ፤ እግዚአብሔርን ሳይሆን ራሱን እየወደደ ሊሆን ይችላል ።

አንድ ሰው በሦስት መንገዶች ራስን ወደ ማፍቀር አዙሪት ውስጥ ሊገባ ይችላል ። አንደኛው መንገድ ምንም ያለ ምንም አመክንዮ እና ሰበብ ፥ ከሌሎች በላይ መሆንን በመሻት ብቻ የከፋትን ጎዳና ሲከተል ነው ። ሰይጣን ሌሎቹን መላእክት ‘እኔ ነኝ የፈጠርኋችሁ’ ሲላቸው ያ እውነት እንዳልሆነ ያውቃል ። እሱን የተከተሉት አጋንንትም የእግዚአብሔርን ኃይል ያውቃሉ ፥ ቸርነቱንም እንዲሁ ፥ ነገር ግን ያም ቢሆን ከእሱ መራቅን እና እርሱን ጠላታቸው ማድረግን ይመርጣሉ ። በዚህ የጥፋት መንገዳቸው ደግሞ የቻሉትን ያህል ሌሎች ፍጥረታትንም ማምጣት ይፈልጋሉ ። ይህንም ለማድረግ ያለዕረፍት ይተጋሉ ። ሰውም እንዲሁ በተለያየ ደረጃ እንዲህ ራስን ማፍቀሩን ያለምንም ሽፋን ሊያስሄደው ይችላል ።

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከራስ ወይም ከሌሎች በመነጩ ሐሳቦች አጽዳቂነት ራስን ማፍቀር ነው ። ይህኛው መንገድ የሚሠራው ሰውን ራሱን ማፍቀሩ ተገቢ ወይም ቢያንስ የማይነቀፍ እንደሆነ በማሳመን ነው ። የዓለምን አኳኋን በተሳሳተ መንገድ በመሣል እና የሰውን እና የፍጥረትን ዓላማ በማዛባት ሰዎች ሊያደርጉ ከሚገባቸው በተቃራኒው ማድረጋቸውን የሚገባ ነገር አስመስሎ ያሳያል ። በመግቢያችን እንዳነሣነው ከዘመነ “አብርሆት” ጀምሮ በተለያየ መንገድ የተሰበከው ግላዊነት ለዚህ በእጅጉ ጥሩ ማሳያ ነው ። በውስጣችን ያለውን ራስን የማፍቀር ዝንባሌ ሸሽተን ልናመልጠው ፥ ታግለን ልናሸንፈው የሚገባ ነገር መሆኑ ቀርቶ እንዲያውም ልንመግበው እና ልናሳድገው የሚገባ እንደሆነ ሰበከ ። የሰው ልጅ ዓላማ ደስታዎቹን እና ምቾቶቹን ማብዛት ፥ ሥቃዮቹን ደግሞ መቀነስ ነው የሚል መግባባትም ፈጠረ ። ስለዚህም በዘመናችን እንደግለሰብም ሆነ እንደ ማኅበረ ሰብእ ራስን የማፍቀር ድርጊቶች የተለመዱ ብቻ ሳይሆን የሚያኮሩም ሆነዋል ።

ሦስተኛው መንገድ ደግሞ ራስን በመተው ፥ በመስዋዕትነት ሽፋን የሚደረግ ራስን ማፍቀር ነው ። በዚህ መንገድ የሚሄድ ሰው ለሚያደርጋቸውን ነገሮች የሚያቀርበው ምክንያት ለሌሎች ሲል የሚያደርጋቸው መሆኑን ነው ። ነገር ግን ወይ በሌሎች ሰዎች መልካም መስሎ ለመታየት ፥ ሲብስ ደግሞ ራሱንም ጭምር ለማታለል ፣ ማለትም ጥሩ ሰው እንደሆነ እያሰበ እርካታ እንዲያገኝባቸው ያደርጋቸዋል ። በፍትሕ ስም ፣ በእውነት ስም ፣ በፍቅር ስም ራሱን ሊያፈቅር ይችላል ።

ለምሳሌ፣ ‘ሞት የነገሮች መጨረሻ ነው’ የሚለው ሐሳብ የሚያስጨንቀው አንድ ሰው ከዚህ ጭንቀት ለማምለጥ እንዲህ የሚል እምነት ሊያዳብር ይችላል ፦ "ከሞት በኋላ ክፉና መልካም ቦታዎችን የፈጠረ አምላክ አለ፤ የተወሰኑ ሕጎችንና ሥርዓቶችን ከፈጸምኩ ደግሞ ይህ አምላክ በመልካሙ ስፍራ ያኖረኛል።" ከዚያም ይህን እምነቱን የሚደግፉ ጽሑፎችን እየጻፈ፣ የራሱን ሥርዓት እየዘረጋ ወይም ሌሎች የሠሩትን ሥርዓት እየተከተለ እውነታን በዚህ መነጽር እየተረጎመ ይኖራል ።

በተቃራኒው ከሞት በኋላ ፍርድ ይኖራል የሚለው ሐሳብ የማያስጨንቀው ሰው ደግሞ ፥ ‘ከሞት በኋላ ምንም የለም

። ያለው ይህ ዓለም ብቻ ነው ።' የሚል ሐሳብ አመንጭቶ ልክ እንደቀደመው ሰው በደንብ አዳብሮት እና ተከታዮችን አፍርቶ ሊኖር ይችላል ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ሁለቱም እውነትን ይዘናል ይላሉ ። የሚሠሩትና የሚደክሙትም ለእውነት እንደሆነ ለሌሎችም ሆነ ለራሳቸው ይነግራሉ ። ነገር ግን እውነታው በእነዚህ ሐሳቦቻቸው አማካይነት ራሳቸውን እያመለኩ መሆኑ ነው ። ከዚህ ሐሳባቸው ላለመናጠብም ምንም ነገር ሊያደርጉ ይችላሉ ። ለማይስማሟቸው እውነቶች ዐይናቸውን ሊዘጉ ይችላሉ ፤ ጨርሶ ከማይስማሟቸው ሰዎች ጋር ጨርሶ ማውራት እና መገናኘት ሊተዉ ይችላሉ ። ምናልባትም ሌሎችን ከእነሱ ጋር እንዲስማሙ እስከማስገደድ ፥ ይህንም ለማድረግ ጦርነት እስከማወጅም ሊደርሱ ይችላሉ ። ይህ ፍጹም እርግጠኝነትን የመሻት እና ምንም ዓይነት ከእኛ የተለየ ሐሳብን ላለመስማት የሚደረግ ትግል ጠለቅ ብለን ስንመረምረው ከሕመም ለመራቅና እርካታን ለማግኘት የሚደረግ መጣጣር ነው።[22]

የኒዮ-ፕላቶኒዝም ፍልስፍና[23] ሲተነተን ስማቸው በቅድሚያ ከሚጠሩት አንዱ የሆነው ፕሎታይነስ ፥ የሰው ልጅ የሕይወት ትርጉም ከማንኛውም ሐሳብና ዕውቀት በላይ ከሆነው 'ከአንዱ' (The One) ጋር መዋሐድ ነው ይላል ። እንደ እርሱ አባባል ፥ የሰው ልጅ ነፍስ 'ከአንዱ' የተገኘች ስትሆን፣ ወደ መገኛዋ ስትመለስ ደስታን ፣ ብርሃንንና ነጻነትን ታገኛለች ።[24]

ይህን የፕሎታይነስን "ወደ አንዱ" የሚደረግ ጉዞ በጥሞና ስንመረምረው ግን ፥ እንቅስቃሴው ወደ ራስ የሚደረግ መሆኑን እንረዳለን ። ጉዞው ፥ በተለያዩ ሐሳባዊና ምስጢራዊ ልምምዶች አማካኝነት የራስን የተደበቀ አቅም የማውጣት ፥ ራስን ከፍ አድርጎ በመሣል ወደዚያ ሥዕል ለመድረስ የመጣር ፥ ከራስ ተነሥቶ በራስ አማካኝነት ለራስ ወደሆነ ግብ ለመጓዝ የመሞከር ነው ። ምክንያቱም ነፍስ የተገኘችው 'ከአንዱ' ስለሆነ ወደ አንዱ የምታደርገውም ጉዞ ሌላን ሳይሆን ራሷን ለማግኘት የምታደርገው ነውና ። በዚህ ፍልስፍና መሠረት፣ ለእውነት ትርጉም የምንሰጠው ራሳችን ነን ፤ እውነትም መንገድም እኛው ነን ። ይህ ራስን ማምለክንና ማፍቀርን የሚያበረታታ ፍልስፍና ነው ።

ይህ ራስን እና ሌሎችን በማታለል ፣ እውነትን በማዛባት የሚደረግ ራስን ማፍቀር በክርስትና ስምም ሊፈጸም ይችላል ። ክርስትናን በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ራስን ለማፍቀር መሣሪያ ማድረግ ይቻላል ። ብዙ ኑፋቄዎችም እንዲህ ካለ አቀራረብ ወጥተዋል ። በኦርቶዶክሳዊነት ውስጥ ሳይቀር ይህን የሚያመላክቱ ዝንባሌዎች ይታያሉ ። ለምሳሌ ጾምን ፣ ጸሎትን እና ስግደትን ደካማነታችንን ለማሸነፍ የምናደርጋቸው ሳይሆኑ የጥንካሬያችን መገለጫ አድርገን የምናስባቸው ከሆነ ፥ ሥርዓት በመጠበቃችን አዘውትረን በቤተ ክርስቲያን በመገኘታችን ከሌሎች የተሻልን እና ለእግዚአብሔር የቀረብን ፥ በመሆኑም በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም እግዚአብሔር ውለታችንን ቆጥሮ የሚከፍለን ከመሰለን እንዲህ ያለው አደጋ ውስጥ ነን ።

አንድ ሰው ቅዱስ ቁርባንን የተድላ ሕይወት ያስገኝልኛል ፥ ወይም የምፈልጋቸው ነገሮች እንዲሳኩልኝ ያደርግልኛል ብሎ ቢቀበለው ፥ ወይም መቀበሌ በመንፈሳዊ ሕይወት ከሌሎች ሰዎች በተሻለ ደረጃ ላይ ያስቀምጠኛል ብሎ እያሰበ ቢቀበለው ፣ ይህን በማድረጉ የተጓዘው ወደ ክርስቶስ ሳይሆን ወደ ራሱ ነው ።

(እርግጥ ነው ፥ እነዚህ ሐሳቦች ሁሉንም ሰው መፈተናቸው አይቀርም ። ፈተናውን ማወቅ እና ለመቋቋም መትጋት ያስፈልጋል ለማለት ነው እንጂ ብዙ ቅዱሳን ሳይቀር እንዲህ ባለው አዝማሚያ ይፈተናሉ ። ለዚህም ነው ራስን በማፍቀር እና በእውነተኛ ፍቅር መካከል ያለው ድንበር አሻሚ ነው ያልነው ። እንኳን ሌላ ሰው ራሱ ባለቤቱም ይህን ለማወቅ እጅግ ይቸገራል ።)

※ ※ ※

ከእግዚአብሔር ጋር ፥ በእርሱም ከፍጥረት ጋር አንድ ለመሆን ራስን ባዶ ማድረግ ያስፈልጋል ። ይህም ንስሐ ነው ። ራስን ባዶ ማድረግ ስንል ራስን እንደሌለ መቁጠር ወይም ማንነታችንን መለወጥ ማለት አይደለም ።

---

[22] ክርስቶስ ያናራስ በመጸሐፉ ይህን ሐሳብ ደግፎ ይሞግታል። Christos Yannaras, *Against Religion: The Alienation of the Ecclesial Event* (Holy Cross Orthodox Press, 2013).

[23] "ኒዮፕላቶኒዝም ከፕሎቲነስ ጀምሮ በንጉሠ ነገሥት ጀስቲንያን በ529 ዓ.ም. የፕላቶ አካዳሚ እስከ ተዘጋበት ጊዜ ድረስ የዘለቀውን የፕላቶ ፍልስፍና ለማመልከት የሚያገለግል ስም ነው።" Christian Wildberg, *Neoplatonism*, ed. Edward N. Zalta, in 'Stanford Encyclopedia of Philosophy' (Metaphysics Research Lab, Stanford University, 2019), https://plato.stanford.edu/entries/neoplatonism.

[24] ለበለጠ ንባብ ይህን ይመልከቱ ፦ Plotinus, *The Enneads*, ed. Lloyd Gerson, trans. George Boys-Stone et al. (Cambridge: Cambridge University Press, 2019), 881–98.

ይልቁንም ፥ ልክ አፍንጫ ሲመታ ዓይን እንደሚያለቅሰውና በዚህም የሁለቱን የማይነጣጠል አንድነት እንደምንረዳው ሁሉ ፥ ራስን ለሌሎች አሳልፎ በመስጠት ከእነርሱ ጋር በአዲስ ኅብረታዊ አኗኗር ለመኖር ራስን መክፈት ነው ። ይህ ማለት በአንድ ልብ ፣ በአንድ ምክርና በእውነተኛ ተዋሕዶ መኖር ማለት ነው ። በዚህ ኅብረታዊ አኗኗር ካልኖርን በቀር ትርጉም ባለውና እውነተኛ በሆነው እውነታ ውስጥ ልንኖር አንችልም ።

ይህን ራስን ባዶ የማድረግን መንገድ ያስተማረን ፥ በተግባር ያሳየንና እኛም እንዲሁ እንድናደርግ ኃይል የሰጠን ክርስቶስ ነው። እርሱ ራሱን ባዶ በማድረጉ እኛም ራሳችንን ባዶ እንድናደርግ አስችሎናል ። ቅዱስ ቄርሎስ ቃል *ሥጋ* መሆኑን ራስን ባዶ የማድረግ ትርጉም አድርጎ ሲያቀርበው እንዲህ ይላል፡-

> "የምስጢራቱ መጋቢ ፥ የወንጌል አዋጅ ቅዱስ አገልጋይ ፥ በሁሉ ጥበበኛ የሆነው ጳውሎስ (የቃልን *ሥጋ* መሆን) እንዲህ ሲል ይህን ለእኛ ያስረዳናል። ‘በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ሐሳብ በእናንተ በእያንዳንዳችሁ ይኑር ፤ እሱ በእግዚአብሔር (ባሕርይ) መልክ (morphē)[25] ያለ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን እኩልነት ቀምቶ የሚያገኘው አይደለም ፤ ነገር ግን የሰውን (ባሕርይ) መልክ (morphē) ነሥቶ ራሱን ባዶ አደረገ ፤ በሰውም ምሳሌ ሆኖ መጥቶ እንደ ሰው ራሱን ዝቅ አደረገ እስከ ሞት ድረስም የታዘዘ ሆነ ፤ በመስቀል ላይ የሆነ ሞት ።’ (ፊል 2፡5-8) እናም በእውነትም አንድያ ልጅ የሆነው ቃል ምንም እንኳ ፤ (ከባሕርይ) አምላክ የተወለደ (የባሕርይ) አምላክ ፥ የወላዲው የክብሩ ነጸብራቅና ፍጹም አምሳያ ቢሆንም (ዕብ 1፥3) ሰው የሆነው እሱ ነው ። ራሱን ወደ *ሥጋ* አልለወጠም ፤ በምንም ዓይነት መደባለቅ ወይም መቀየጥ ወይም እንዲህ ባለ ሂደት ውስጥ አላለፈም ፤ ነገር ግን ባዶ ይሆን ዘንድ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ‘በፊቱ ስለተሰናዳው ክብርም ነውርን እንደ ምንም ቆጠረው’ (ዕብ 12፥2) ። የሰውን ባሕርይ ጉስቁልናም አልተጸየፈም ። እግዚአብሔር እንደ መሆኑ በግልጥ በኃጢአትና በሞት የተያዘውን ያን *ሥጋ* (የሰውን ባህርይ) ከኃጢአትና ከሞት በላይ ያደርገው ዘንድ ወደደ ፤ የራሱም አደረገው ።"[26]

ክርስትናን ከኒዮ-ፕላቶኒዝም ሆነ ከሌሎች ፍልስፍና የሚለየውም ይህ ነው ። ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን ማለት ክርስቶስ ራሱን ባዶ አድርጎ የፍጡራንን አኗኗር እንደተካፈለ በዚህም አዲስ የህልውና አኗኗር እንደሰጠን ሁሉ እኛም ራሳችንን ባዶ አድርገን ያን የህልውና አኗኗር መካፈል ነው ። የንስሐ ትርጉም ወደዚህ አኗኗር በክርስቶስ ለመግባት መወሰን ነው ። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ክርስትናን መረዳት እንደ ፕሎታይነስ ዓይነት የተደበቀ ግላዊነትና ራስን ማፍቀር ያለበት የቅዠት እንጂ የምር ያልሆነን እንቅስቃሴ ማድረግ ነው ። ራሳችንን ባፈቀርንበት መጠን ከእግዚአብሔር እየተለየን ፥ ከእግዚአብሔር በተለየንበት መጠን ደግሞ የነገሮች ትርጉም እየጠፋብን ይመጣል ። ራስን ማፍቀር ልቅ ስሜቶችን ያስከትላል ፤ ልቅ ስሜቶች ደግሞ ባዶ ናቸው ። ስለዚህ ራስን ማፍቀር የባዶነት ሕይወት መሠረት ነው ።

ክርስትናን ከራስ ፍቅርና ከራስ ጥቅም አንጻር መረዳት ፥ ዕለት ተዕለት በሃይማኖት ስም የምንፈጽማቸውን ሥርዓቶች ወደ ራስ ማምለኪያ መሣሪያነት ሊለውጣቸው ይችላል ። ይህ እውነታ ፥ ከዘመናዊው ዓለም ቴክኖሎጂ ፣ ሳይንስና ፍልስፍናዎች ጋር ካለን ጥብቅ ቁርኝት ጋር ሲደመር ፥ ፍትወቶቻችን እንዲቆጣጠሩንና የእነሱ ባሪያዎች እንድንሆን በር ይከፍታል ። ይህ አካሄድ መጨረሻው ለባዶነት ሕይወት እጅ መስጠት ነው ። አማናዊው ትርጉም ግን ራሱ እግዚአብሔር ነው ።

---

[25] Morphē የሚለው ቃል መልክ ወይም ቅርጽ የሚል ትርጉም አለው ። ነገር ግን መልክ የሚለው ቃል ራሱ በሁለት መንገድ ሊፈታ ይችላል ። ለምሳሌ ወልድ ባሕርይ ዘእምባሕርይ ከአብ በመወለዱ የአብ መልኩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር መልክ ቢፈጠርም የእግዚአብሔር ባሕርይ አይደለም ። ስለዚህ የባሕርይና የጸጋ መልክ አለ። እዚህ ጋር መልክ ሲል ባሕርይን ለማሳየት የገባ ነው።

[26] Saint Cyril of Alexandria, *On the Unity of Christ*, trans. John Mcguckin (Crestwood, Ny: St. Vladimir’s Seminary Press, 2000), 54–55.

## ዋቢ መጻሕፍት


Climacus, Saint John. *The Ladder of Divine Ascent*. New York: Paulist Press, 1982.

Dionysius the Areopagite. *Pseudo-Dionysius: The Complete Works*. Translated by Paul Rorem and Colm Luibheid. New York: Paulist Press, 1987.

Dostoyevsky, Fyodor. *Crime and Punishment*. Translated by Richard Pevear and Larissa Volokhonsky. New York: Toronto, 1993.

Plotinus. *The Enneads*. Edited by Lloyd Gerson. Translated by George Boys-Stone, John Dillon, Lloyd Gerson, R.A.H King, Andrew Smith, and James Wilberding. Cambridge: Cambridge University Press, 2019.

Saint Cyril of Alexandria. *On the Unity of Christ*. Translated by John Mcguckin. Crestwood, Ny: St. Vladimir's Seminary Press, 2000.

Santos, Henri C., Michael E. W. Varnum, and Igor Grossmann. "Global Increases in Individualism." *Psychological Science 28, no. 9* (July 13, 2017): 1228–39. https://doi.org/10.1177/0956797617700622.

Staniloae, Dumitru. Eternity and Time. Oxford: Slg Press, 2001.

Staniloae, Dumitru. *Orthodox Spirituality : A Practical Guide for the Faithful and a Definitive Manual for the Scholar*. St. Tikhon's Seminary Press, 2003.

Wildberg, Christian. "Neoplatonism." Edited by Edward N. Zalta. *Stanford Encyclopedia of Philosophy*. Metaphysics Research Lab, Stanford University, 2019. https://plato.stanford.edu/entries/neoplatonism

Yannaras, *Christos. Against Religion: The Alienation of the Ecclesial Event*. Holy Cross Orthodox Press, 2013.

# እስኪ እንነጋገር

**በርናባስ ሽፈራው**

†

የዘመን ጉዟችን ፡ በምን ተመከረ
ክረምት አልፎ በጋ ፡ በጋም አልፎ ክረምት
ክረምቱን ከረምነ ፡ በጋውን ባጀነ
እስኪ እንነጋገር ፡ ብዙ ነገር አለ ።

. . .

ጭምት እንደረጋው ፡ እንደጨፈው ውሃ
ሆኗል መንፈሳችን ፡ ከውስጡ በስብሶ
ቆሟል ቀጥ ብሎ ፡ አምሮ እንደ ምሰሶ
ከውስጡ በስብሶ ፡ ቁንቁን ቆርጥሞት
መንፈሳችን ቁሞ ፡ ይመስላል ያማረ ፡ የቆመ በውነት
እስኪ እንነጋገር ፤
አለ ብዙ ነገር ።

ዮሐንስ አድማሱ

† † †

በፍጥነት ወደ ምዕራብ የሚገሰግስ ረዥም ባቡር ላይ ተሳፍራችሁ ፤ በቻላችሁት ፍጥነት ወደ ምሥራቅ ብትሮጡ የት ትደርሳላችሁ ?

## ፩

“አባቴ ወደ ዳኝነቱ ቦታ ፥ እናቴ ደግሞ ወደ ገበያ ስትሄድ ፥ ልጆች ሁሉ ተማሪ ቤት ስንሆን ፥ ቤታችንን የሚጠብቁ እሥረኞች ነበሩ ። እሥረኞች ዘበኛ አልነበራቸውምና እንኳን ጠፍተው ሊሄዱ ቤት ለመጠበቅ ይታመኑ ነበር ። በዚያ ዘመን ሰው ይቅርና እሥረኞች እንደ ቅዱሳን መታመናቸውን በታላቁ ይፈጽሙት ነበር ። ሙሉ ንብረታችን ያለበት ቤታችን እንደ ባንክ ነበር ። ግን የብረት ቁልፍ እንኳ በሳንቃው የለምና እንደ አቁማዳ ጫፍ በገመድ ቋጠሮ ይዘጉታል ። በዚያ ጊዜ ሌባ እንኳ ሲሰርቅ የተሰረቀውን ነገር ባለቤቱ እንዳያውቅ ትንሽ ብቻ ይሰርቃል እንጂ ፥ እንደ አሁኑ ዘመን ሌባ ይሉኝታ የለሽ አልነበረም ። ስለዚህም ወላጆቻችን ቤታቸውን በገመድ ዘግተውት ሲሔዱ ፥ ሌባ ሰርቆ እንደሆነ ለማወቅ በገመዱ አስተሳሰር ላይ ምልክት ያደርጉ ነበር እንጂ ፥ ምን እንደተሰረቀ ቶሎ ለማወቅ አይችሉም ።”[1]

ይህ የሚሆነው ከተመሠረተች ገና አምሳ ዓመት እንኳን ያልሞላት በነበረችው በደብረ ማርቆስ “ከተማ” ነው ። የከተማው ዳኛ የብላታ ገብሬ ልጅ ተመስገን ገብሬ ከጣሊያን ወረራ በኋላ “ዘመናዊነት” እየነገሠባት

[1] ተመስገን ገብሬ ፣ *ሕይወቴ* (2001) ፣ ገጽ 4-5 ።

በመጣችው አዲስ አበባ ሆኖ ነው በደብረ ማርቆስ ስላሳለፈው ልጅነቱ የሚያጫውተን ፤ በልጅነቱ ዓለም እና በሚጽፍበት ወቅት እየኖረ ባለበት ዓለም መካከል ባለው ልዩነት እየተደነቀ ።

ከዚያ ዘመን ብዙም ባልራቀ ዘመን ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ፈረንሳይ ለህክምና በቆዩበት ጊዜ አንድ የተራበ ሰው አጋጥሟቸው ከመጸወቱት በኋላ ሠለጠነ በተባለ ሀገር የሚራብ እና የሚጠማ ሰው በመኖሩ የተሰማቸውን ስሜትና የገባቸውን ሐሳብ እንዲህ ያጫውቱናል ።

> "የሰው ሕይወት አንዱም እንዲህ ፣ ሌላውም እንዲያ ሆኖ በመኖሩ ፥ ይልቁንም የሰው እውቀት ከፍ አለ በተባለበት አገር ፥ አስገረመኝ ። ባገራችን በኢትዮጵያ አንዳንድ ባለጸጎችም ቢኖሩ በኑሯቸው ምንም ያህል ከሌላው የበለጠ የደስታ ኑሮ የላቸውም ። ጌታም የሚባለው ሁሉ ከብዙ በላተኞች ጋራ ተከፋፍሎ ነበር እንጂ የሚበላው ለብቻው ገንዘብ የሚሰበስብ እና የሚያጠራቅም ያውሮፓ ስብከት እስከገባበት ቅርብ ጊዜ ድረስ ብዙ ሰው አልነበረም ። በፊትም አንዳንድ ሰዎች እንኳን ቢኖሩ ፥ በመላው ሕዝብ አስተያየት የተጠሉ እና የተናቁ ነበሩ እንጅ ፥ የማዕረግ ክብረት ስም አልነበራቸውም ።
>
> በሕዝቡ መህል ግን በኢትዮጵያ የእህልና የውሃ ዋጋ አልነበረውም ፤ ይኸውም ከሃይማኖቱ ጋር የተያያዘ አኳኋን ነበር ። ማናቸውም መንገደኛ ካገር ወዳገር የሚተላለፈው ሁሉ በጣም የሚበዛው ስንቅ ሳይዝ የብዙ ቀን መንገድ ሔዶ አሰበበት ደርሶ ይመለስ ነበር ። በየቦታው ያለችግርና ያለዋጋ የሚበላና የሚጠጣ የሚያገኝ ስለሆነ ።
>
> ማንም ድሃ ሰው እሌላው ፣ አለው ሰው ዘንድ ሔዶ የእግዚአብሔርን ስም ከጠራ ፥ እህልና ውሃ የማይሰጠው ሰው አልነበረም ። በአውሮፓ ግን እንደተመለከትሁት እጅግ የጭካኔ ነገር ሞልቷል ። ገንዘብም ከሰው ይልቅ የከበረ እና የተወደደ ነው ።"[2]

ጽሑፌን በእነዚህ ምንባቦች ለመጀመር የወደድሁት እኔ በራሴ ቃላት ላብራራ ከምችለው በላይ እነሱ አንባቢ ላይ የሚፈጥሩት መደነቅ እና ግርምት ለጽሑፉ መነሻ የሆነኝን ነጥብ ይገልጹታል ብዬ ስለማስብ ነው ። በእነዚህ ምንባቦች መስኮትነት የምናየው ዘመን እና ኅብረተ ሰብእ ምን ያህል አሁን ካለንበት ዘመን እና ከምንኖርበት ኅብረተ ሰብእ የተለየ እንደሆነ ልብ አለማለት ይቻላል ?

ልዩነቱ በብዙ "ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊ እና ታሪካዊ" ምክንያቶች ሊብራራ ይችል ይሆናል ። ለራስ እምሩ ግን በአውሮፓ በታዘቡት አሳዛኝ ሁኔታ እና በኢትዮጵያ በነበረው ሁኔታ መካከል ያለው ልዩነት ዐቢይ ምክንያት "ከሃይማኖቱ ጋር የተያያዘ አኳኋን" ነበር ።

በእርግጥም ሁለቱን ምንባቦች የሚያመሳስላቸው ዐቢይ ነገር (ቢያንስ በእኔ ዐይን) እጅግ ክርስቲያናዊ መንፈስ የሚታይባቸው መሆኑ ነው ። ምንም እንኳን እኛ ካለንበት ዘመን ያላቸው ርቀት ጥቂት ቢሆንም ግን በዚህ ጠባያቸው ከእኛ ዘመን ይልቅ ስለ መጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ለምናውቀው እውነታ እና ስንክሳር ላይ ለምናገኛቸው ታሪኮች ይቀርባሉ ። የዳኞችን ቤቶች በእስረኛ ማስጠበቅም ሆነ ስንቅ እና ገንዘብ ሳንይዝ ለረዥም ቀናት መጓዝ በዘመናችን እና በሀገራችን ለመሞከር የምንጋበዛቸው ነገሮች አይመስሉኝም ።

እነዚህ ምንባቦች ክርስትና በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ እንዴት ያለ ትልቅ ሚና ይጫወት እንደ ነበረ ያሳያሉ ብዬ አስባለሁ ። ምናልባት ይህ ሐሳብ ተቃውሞ ሊገጥመው ይችላል ። እነዚህ ትረካዎች አካባቢያዊ ክስተቶችና የጥቂት ግለሰቦች አስተውሎዎች እንጂ ፥ በዚያ ዘመን በመላው ሀገር የነበረውን ሁኔታ ለማሳየት የሚበቁ አይደሉም ሊባል ይችላል ። ምናልባት ።

አለመታደል ሆኖ በአንጻራዊነት ቅርብ ሊባሉ በሚችሉ ዘመኖች ጭምር የነበረው የማኅበረባችን የዕለት ተዕለት አነዋወር ለእኛ በሚገባ የተዘገበ አይደለም ። ለረዥም ዘመናት የጽሑፍ ጥበብ በጣም አስፈላጊ በተባሉ ጉዳዮች የተወሰነ ሆኖ ፣ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እና ትልልቅ እና ልዩ ተብለው የታሰቡ ታሪካዊ ሁነቶችን ከመመዝገብ ባለፈ በስፋት ጥቅም ላይ አይውል ስለነበር ፥ ዛሬ እኛችን ላይ የዚያ ዘመን የዘወትር ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር የሚያስረዱን ምንጮች እንደ ልብ የሉንም ።

ይህም የሆነው ታሪክ ጸሐፊዎቻችን ነገሥታትን በማወደስ ስለተጠመዱ ወይም 'ታሪክ ሰሪው ሰፊው ሕዝብ

[2] ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ፣ *ካየሁት ከማስታውሰው* (2008) ፣ ገጽ 217-8

መሆኑን' ስለሚክዱ ሳይሆን ፣ ሰዎች በተፈጥሯቸው ሲወለዱ ጀምረው በየዕለቱ ሲታዘቧቸው እና ራሳቸውም ሲያደርጓቸው የኖሯቸውን ነገሮች ነገ የሚመጣ ሰው ላያውቃቸው ይችላል ብለው ስለማይጠረጥሩ ፣ ከተለመደው የወጣውን እንጂ እንዲያ ሆኖ የኖረውን እና ነገም እንዲያ ሆኖ የሚኖረውን (በእነሱ ሐሳብ) ነገር መዝግቦ የማቆየት ሐሳቡ ስለማይመጣላቸው ፥ ዋጋውም ስለማይታያቸው ነው ። ይልቁንም የተለመደውን የሕይወት ፍሰት የሚያደፈርስ ሁነት ሲፈጠር ያን መመዝገብ ይገባዋል ብለው ያስባሉ ። በአመዘኙ ደግሞ ትክክል ነበሩ ፤ ለረዥም ዘመናት ከጥቂት ለውጦች ሌላ የሕይወት ፍሰት ሳይለወጥ እንዳለ ይቀጥል ነበርና ።

ይህ ነገር በተለይ የእኛን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የየትኛውንም ሕዝብ ታሪክ በተመለከተ እውነት ይመስለኛል ። የጽሑፍ ባህልከመዳበሩ የተነሣ ጽሑፍ ራሱ የዕለት ተዕለት ሕይወት አካል ካልሆነ (ደብዳቤዎች ፣ ግለ ታሪኮች ፣ ልብወለድ ታሪኮች ወዘተርፈ እንደልብ ካልተጻፉ) ፥ አሊያም ተመስገን ገብሬ እና ራስ እምሩ እንዳጋጠማቸው ያለ የባህልመለወጥ እና መናወጥ ካልተፈጠረ ፥ ወይም እንግዳ ከሆኑ ባሕሎች ጋር መስተጋብር እና ተዋሥኦ የማድረግ እድል ካላጋጠመ ወይም ካልተጠበቀ በስተቀር ማኅበረሰቡ ወስጥ የተለመዱ እና ተራ ሆነው የሚቆጠሩትን ሁነቶች እና ሂደቶች መዝግቦ ለማስቀመጥ የሚያነሣሣ አጋጣሚ እና ምክንያት አይኖርም ።

እኛም ራሳችን ብንሆን ፣ ምንም እንኳን ሕይወት በየዘመኑ መለዋወጧን ለማየት የተሻለ ዕድል ቢኖረንም ፣ አያቶቻችን እና አባቶቻችን ፣ አባቶቻችን እና እኛ ፣ እኛ እና ልጆቻችን ከየኖርንባቸው ዘመኖች ልዩነት የተነሣ ልዩ ልዩ ፍጥረቶች መሆናችንን በግልጽ ብናይም ፥ ነገር ግን ሐሳባችን ከጥንቱ ብዙም አልተለወጠም ። ምንም እንኳን የዕለታዊ እንቅስቃሴያችን አካል የሆኑትን ነገሮች ነገ ለሚመጣ ሰው እንግዳ ይሆናሉ ብለን ለማሰብ እና መዝግበን ለማስቀመጥ እድሉም ሆነ ምክንያቱ ቢኖረንም ይህን ለማድረግ ግን የተለየ ተነሣሽነት የለንም ። ለእኛ ራሱ ነገ በሚመጡት ሰዎች ጫማ ውስጥ ቆመን የራሳችንን ዘመን መመልከት ይሳነናል ። ታዲያ ምንም ለውጥ ይኖራል ብለው የማያስቡ ሰዎች ለእነርሱ 'ወተት ነጭ ነው' የማለት ያህል ተራ እና እውቅ የሆኑትን የእለት ተዕለት ህነቶች እና ሒደቶች በዝርዝር አለመመዝገባቸው ለምን ይገርመናል ?

እርግጥ ነው ፥ ልዩ ናቸው ተብለው ከተመዘገቡት ሒደቶችም ቢሆን የተለመደው እና የሚጠበቀው ነገር ምን እንደሆነ ፍንጮችን እናገኛለን ። መጥፎ ተብለው ከተመዘገቡት ነገሮች ደህና ተብለው የሚታሰቡት ነገሮች ምን እንደሆኑ ፣ ከተለመደው በተለየ መልኩ ጥሩ ናቸው ከተባሉት እና ምሳሌ ተደርገው ከሚጠቀሱት ነገሮች ደግሞ ማኅበረሰቡ ከራሱ ለመሻል በውስጡ የሚያደርገውን ትግል በጠቅላላው መረዳት እንችላለን ። ነገር ግን "ተራው" ሕይወት ይህን ይመስል ነበር ብሎ በትክክል ለመናገር የሚያበቃን አይሆንም ።

ስለዚህ በታሪካችን ውስጥ ጦርነት እና ረኃብ ፣ በሽታ እና ውድመት ጎልተው ብንመለከት ሊገርመንም ሆነ ፣ እነዚህን ነገሮች ሁነኛ የማኅበረሰባችን እና የታሪካችን መገለጫ አድርገን ልንመለከታቸው አይገባም ። ይልቁንም ከጤናማው ሰውነታችን ይልቅ ጠባሳ ያለበት አካል ተነጥሎ እንደሚጎላው ፣ ነገር ግን ያ መላውን ሰውነት ጠባሳ ነው እንደማያሰኘው ነው ። ምንም እንኳን ጤናማው ቆዳ ውብ ቢሆንም ፣ በመላው ሰውነት ላይ በመገኘቱ እና በመለመዱ ከእርሱ ውብነት ይልቅ ከእርሱ ውብነት ጋር ተነጻጽሮ የጠባሳው ጥፉነት ዐይንን እንደሚስበው ነው ።

እርግጥ ነው ጠባሳዎቹም ቢሆኑ ስለማኅበረሰቡ ይናገራሉ ። ያወቅናቸውን መልካም ነገሮች እና ልንደርስባቸው የተስማማንባቸውን መዳረሻዎች ዘንግተን በተቃራኒው ስለተጓዝነው ርቀት ፣ መንገዳችንን ስተን ስንባዝን ያጠፋነውን ጊዜ እና በዚያም የተነሣ የከፈልነውን ዋጋ ሁሉ እያስታወሱን እንደ ማኅበረ ሰብእ ወደ መንገዳችን እንድንመለስ ያስታውሱናል ፤ ወደ ንስሐ ይጠሩናል ።

ደግሞም እንደጠባሳዎቹ ሁሉ ዐይንን የሚስቡ ተለይተው የተዋቡ ወይም የተጌጡ የአካል ክፍሎችም ይኖራሉ ። ለምሳሌ በእኛ ዘንድ ለይተን የምናስባቸው ቅዱሳን ፣ ነገሥት ፣ አርበኞች ፣ ሕዝባዊ ጀብዶች እና ድሎች ወዘተርፈ አሉን ። እነዚህ ነገሮች ታዲያ በአንድ በኩል ማኅበረሰቡ ምንን እንደሚያከብር እና ወደ የት አቅጣጫ ለመድረስ እንደሚጣጣር ብቻ ሳይሆን ፣ በዚህ ጥረቱ ውስጥ አምጦ ፍሬዎች ማፍራቱን ፣ በእነዚህ ሰዎች እና ሁነቶች አማካይነት ሕልሞቹን ሥጋ ማልበሱን ፣ የሚጨበጡ እና የሚዳሰሱ ማድረጉን ፣ ከምናብነት ወደ እውነታነት መለወጡን የሚመሰክሩለት አይደሉምን ? ሕልሞቹ በሰማይ ያሉ ላሞች ሳይሆኑ የታዩ ፣ የተገለጡ ፣ መሆናቸውን የሚናገሩለት አይደሉምን ?

ዶስቶየቭስኪ እንደሚለው ፣ ከተለመደው ይልቅ ያልተለመደው ፣ ቅቡል ከሆነው ይልቅ የተነወረው እና

ተለይቶ የከበረው ስለሰው ልጅ እና ስለሚኖርበት ማኅበር የበለጠ ይናገራል ።[3]

ነገር ግን ማኅበረ ሰብዕ ቀስ በቀስ (ወይም በድንገት) ሲለዋወጥ እና የተለመደ የነበረው የተለየ ሲሆን ፣ ያን ጊዜ የቀድሞ ዘመን ጸሐፊዎች ትርጉም ያላገኙባቸው ነገሮች በድንገት አስገራሚ ሆነው ይታያሉ ። ተራ ሆኖ ለዘመናት የኖረው አስደማሚ ሆኖ ብቅ ይላል ። አንዳንድ ትውልዶች ደግሞ እንዲህ ያለውን መነዋወጥ በሕይወት ዘመናቸው ለማየት ይታደላሉ (ይረገማሉ ?) ። እንዲህ ካሉት ትውልዶች አባላት መካከት ጥቂቶቹ ደግሞ ያን ያዩትን መነዋወጥ ለመመዝገብ ችሎታውና ትጋቱ ይኖራቸዋል ።

ራስ እምሩና ተመስገን ገብሬ እንዲህ ካሉት ሰዎች መካከል የሚቆጠሩ ናቸው ። እነርሱ ተገርመው የመዘገቧቸው እና እኔ ከእነርሱ መጻሕፍት ውስጥ መርጬ የጠቀስኋቸው ነገሮች ሁልጊዜ ለኖረባቸው ሰው ምንም የሚያስደንቅ ነገር አይኖርባቸውም ። እነርሱም ቢሆኑ ቀድሞ ሲኖሩባቸው ለነገሮቹ የተለየ ግምት አልሰጧቸውም ። በኋላ ግን ነገሮች ሲለዋወጡ ወይም ወደሌላ ቦታ ሔደው ሲያጧቸው ነው እነዚያ ነገሮች መደነቅ ፣ ግርምት እና ቁዘማ የፈጠሩባቸው ። የተለመዱ የነበሩት ነገሮች በድንገት ብርቅ ሆነው ታዩዋቸው ። ተመስገን ገብሬ በልጅነቱ ዘመን እና ማስታወሻውን በሚጽፍበት ዘመን ያለውን ልዩነት እንዲህ ሲል ይገልጠዋል ።

> "በዚህ ባለሁበት ዘመን እና አባቴን በሕይወቴ ባወቅሁበት ዘመን መካከል ያለው ዘመኑ የሚያሳየው መለዋወጥ በኖኅ ዘመንና በኛ ዘመን የሆነውን የዘመን ርቀት ያህል ለማሳየት ይመስላል ። በእውነት ፥ በዚህ ዘመን የነበሩ አባቶቻችን የአፍሪካ መላእክት ነበሩ ። ለእሥረኛ እንኳን የቅዱሳን ዓይነት ይሉኝታ (ሞራል) ነበራቸው ። ሁሉም እንደ ርግብ የዋሃን ነበሩና እንደ ርግብ ደግሞ የዋሃን ነበሩ እንጂ ብልሃታቸው በልቡ እንደሚሳብ እባብ አልነበረም ። የዘመናቸውን በጎነት ከዚህ ከዘመናችን ጋር ስመለከተው እነርሱ መልካሙን ዘመን ኖረውት በመልካም ወደ ሌላው ዓለም ዘመቱ ።"[4]

ራስ እምሩም ቢሆኑ "የአውሮፓ ስብከት እስከገባበት ጊዜ ድረስ . . ." ሲሉ በወቅቱ እያዩት የነበረውን ለውጥ ይመሰክራሉ ። ይህ የጸሐፊዎቹ መደነቅ በራሱ ነገሮች የቀደመው አነዋወር መገለጫ ለመሆናቸው ምስክር ነው ።

ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ምናልባት በተወሰነ አካባቢ ብቻ ያሉ ቢሆኑ ወይም በብዙ መልኩ በተበላሸ ሥርዓት ውስጥ ቢገኙ እንኳን እንዴት በዚያ አካባቢ እና በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሊፈጠሩ እና ሊኖሩ ቻሉ? ብሎ ለመጠየቅ ዋጋ ያላቸው ይመስሉኛል ። ልክ ጦርነትን እና ረኃብን የተለመደው የታሪክ ሂደት መቋረጥ ሆነው ስለምናገኛቸው እንደምንመዘግባቸው እና እንደምንመረምራቸው ሁሉ ፥ እነዚህም ሁነቶች 'የተበላሸ' ብለን በምናስበው ታሪክ ውስጥ ልዩ ክስተቶች ሆነው ስለሚገኙ ለመመርመር የሚበቁ ይሆናሉ ። አንድ ሰውነት ጠባሳ ብቻ ሞልቶት ጥቂት ቦታዎች ላይ ብቻ ጤናማ ቢሆን እነዚያ ቦታዎች ጤናማ ሆነው መትረፋቸው የግድ አጋጣሚ ነው ማለት አይቻልም ። ምናልባት አንዳች ከጉዳት የጠበቃቸው እና ለሌላውም ሰውነት ሊጠቅም የሚችል ምስጢር ኖሮ ሊሆን ይችላል ። መመርመሩ ተገቢ ነው ።

ነገር ግን በጠቀስናቸው ብቻ ሳይሆን በዚያ ዘመንም ሆነ ከዚያ በፊትና በኋላ በተጻፉ ምንጮች ውስጥ እንዲህ ያሉ ትረካዎችን እናገኛለን ።[5] እንዲህ ዓይነት መንፈስ ያሏቸውን ልዩ ልዩ ትረካዎች ከተለያዩ ምንጮች ማግኘታችን ደግሞ ፥ ከአካባቢ አካባቢ ያለው ሁኔታ ቢለያይም ፥ በጠቅላላው ግን ማኅበረሰቡ የሚጋራቸው ትውፊቶች እና ዕሴቶች እንደነበሩት ያረጋጥልናል ። በመልክአ ምድራዊ ፣ በአስተዳደራዊ እና በሌሎችም ምክንያቶች ቋንቋ አንድ ሆኖ በተለያየ አካባቢዎች በተለያየ

[3] "What the majority calls almost fantastic and exceptional, for me sometimes constitutes the very essence of the real. The ordinariness of events and a routine view of them is not realism in my view, and even the opposite…" Frank, Joseph, *Dostoevsky: The Miraculous Years (1865-71)* (Prinston University Press, 1995) p. 351

[4] ተመስገን ገብሬ ፣ ሕይወቴ ፣ ገጽ 6

[5] በአሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ እና በሃያኛው ምዕት ዓመት መባቻ የተጻፉ የታሪክ መዛግብት እና የግለሰብ ማስታወሻዎች በተለይ ለዚህ ነገር ጥሩ ምንጮች ይሆናሉ ። እኔ ራሴ ያየኋቸው በተዘዋዋሪ መሆኑን አልክድም እንጂ በ18ኛው እና በአሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት ኢትዮጵያን የጎበኙ አውሮፓውያን ማስታወሻዎችም እንዲሁ ። እኔ በደንብ ለመመልከት ከቻልኋቸው መጻሕፍት መካከል (ጽሑፉ ውስጥ ከጠቀስኋቸው መጻሕፍት በተጨማሪ) የብላታ መርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስን መጻሕፍት ፣ የብላቴን ጌታ ኅሩይን 'የልቅሶ ዜማና ግጥም' ፣ የፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትን 'ኦቶባዮግራፊ' ፣ የሀዲስ ዓለማየሁን 'ትዝታ' ፣ የመንግሥቱ ለማን 'ደማሙ ብዕረኛ' ይነበቡ ዘንድ እመክራለሁ ።

አኳኋን እንደሚነገር ሁሉ ባህሉም በመሠረቱ አንድ ሆኖ ግን በልዩ ልዩ አካባቢ ልዩ ልዩ ገጽታ ይኖረዋል ። ታዲያ ይህ ልዩ ልዩ ገጽታ ያለው ባህል፣ ትውፊት ፣ አነዋወር ዐቢይ ምንጭ እና ማዕከል ቤተ ክርስቲያን መሆኗ እንዲህ ባሉት ግላዊ አስተውሎዎችና ትረካዎች ብቻ ሳይሆን ፥ ይሁነኝ ብለው የኅብረተሰቡን አነዋወር ባጠኑ ተመራማሪዎች ዘንድም ምስክር ያለው ሐቅ ነው ።

> "የአቢሲኒያ ማኅበረ ሰብእ እና ባህልበሃይማኖት የተወረሰ እና የተቀረጸ ነበር ። የገበሬው ዓለም በደብሩ ድንበር የተወሰነ ነበር ፤ የማኅበራዊ መስተጋብሩ ማእከልም ቤተ ክርስቲያን ነበረች ። ቀሳውስት በማኅበሩ ውስጥ ከሁሉም የላቀ ሚና እና ከበሬታ ነበራቸው ፤ ቁጥራቸውም በርካታ ነበር ። የሕዝቡ የኑሮ ፍሰት እጅግ ብዙ በዓላት እና አጿማትን በሚያካትተው የቤተ ክርስቲያን የቀን አቆጣጠር ነበር የሚወሰነው ። የመንግሥቱ ርእዮት እና ቅቡልነትም ከቤተ ክርስቲያን የተገኘ ነበር ። ሃይማኖትን ፣ ሀገርን እና ዘውድን በማይፈታ ቋጠሮ ፍጹም ከሆነ መነሻ እና ትንቢታዊ ከሆነ ዕጣ ፈንታ ጋር ያጣመረውን ትረካ ያስገኘችው ቤተ ክርስቲያን የሥርወ መንግሥቱ ምሰሶ ነበረች ።"[6]

ፕሮፌሰር ሌቪን ይህን እውነታ የገለጠበትን መንገድ ስንመለከት ደግሞ ክርስትናው ለማኅበረሰቡ አጥንት ለሰውነት የሆነውን ያህል እንደነበረ እንረዳለን ።

> "ሙስሊም ከሆኑት ጥቂት አማሮች በስተቀር ለሁሉም አማራ 'ክርስትና' እና 'አማራነት' ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው ። 'ክርስቲያን' ማለትም በኢትዮጵያ የነበረው ኦርቶዶክሳዊነት ብቻ ነው ። ለገበሬው 'ካቶሊክ' እና 'ፕሮቴስታንት' የሚሉት ቃላት 'ሙስሊም' ወይም 'አረመኔ' ከማለት የተለዩ አይደሉም ። በማኅበረሰቡ ዘንድ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን መሆን በሁለት መልኩ ልዩ የበላይነት መገለጫ ነው ። በአንድ በኩል የእውነተኛው ክርስትና ባለቤት መሆን እና ብቸኛው የእሥራኤል ወራሽ መሆን ነው ። በሌላ በኩል ፥ ጾምና ጸሎት በተለይ ኢትዮጵያዊ ጥበቦች ተደርገው ስለሚታዩ ፥ በእነዚህ ጥበቦች መካንን ያሳያል ። ይህ አይነቱ መረዳት ማኅበረሰቡ ክርስቲያን ያልሆኑትን ኢትዮጵያውያን በተወሰነ ደረጃ እንዲያገል አድርጎታል ። ዳግመኛም ክርስትናው ከባሕሉ ጋር ከመጣበቁ የተነሣ እነዚህን ክርስቲያን ባለመሆናቸው ዝቅ አድርገው የሚያይዋቸውን ሰዎች (ባህላቸው ከእነርሱ ልዩ በመሆኑ) ለማሳመን እና ወደ ክርስትና ለመመለስ መነሣሣት አይታይባቸውም ።"[7][8]

[6] "Abyssinian society and culture were pervaded and structured by religion. The world of the peasant was defined by the boundaries of his parish, and the church was the focus of social intercourse. The priest was easily the most important figure, and the ranks of the Abyssinian clergy were legion. The rhythm of rural life was determined by a church calendar that included innumerable holy and fasting days. Religion also provided the ideology and legitimacy of the state. Christianity was a pillar of the imperial dynasty, having provided it with a founding legend that joined faith, nation and throne in an indissoluble union with a mythical past and a prophetic future." ." John Markakis, *Ethiopia: The Last Two Frontiers* (James Currey, 2011), pp. 33-4

[7] በመጀመሪያ ይህን ጽሑፍ ስጽፍ እና ይህን ጥቅስ ስጠቅስ የሌቪን መጽሐፍ የሰሜን ኢትዮጵያን እና በተለይ ደግሞ እርሱ 'አማራ' ብሎ የጠራው እና አሁንም እንዲሁ የሚገለጠው ማኅበረ ሰብእ ላይ ያተኮረ ስለሆነ የጽሑፌ ሐሳብ ከዚህ አንጻር ሊተች እንደሚችል ባውቅም ማብራሪያ ለመስጠት አልፈለግሁም ነበር ። ምክንያቱም ትችቱ ተገቢ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ የአመለካከት ልዩነትን የሚያሳይ ስለሚመስለኝ ራሱን ችሎ በሌላ ጽሑፍ ወይም ውይይት ካልተስተናገደ ይህን ጽሑፍ ይጠልፈዋል ብዬ ስላመንሁ ነበር ። ነገር ግን ጽሑፉን አይተው የተቹልኝ ሰዎች ነገሩን ያላሰብሁበት መስሎ እንደተሰማቸው እና ጽሑፉ ላይ ጥላ ሊያጥላበት ይችላል ብለው እንዳሰቡ ስላየሁ ፥ በአጭሩም ቢሆን ሐሳቤን መግለጤ ጥሩ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብሁ ።

በቅድሚያ ይህን ምንባብ መጥቀሴ ምንም ችግር ያለው መስሎ አይሰማኝም ። ይልቁንም ችግር ሊኖረው ይችላል ተብሎ መታሰቡ ችግር ሆኖ ይታየኛል ። ችግር ሊኖረው ይችላል ተብሎ የሚታሰበው በመሀከላችን ሰፍኖ ባለ ግን መቀበል አለብን ብዬ የማላስበው አመለካከት የተነሣ ነው ። ይኸውም ክርስትናን የባህልን እና ማንነትን የሚቀርጽ እውነት እና የሕይወት መንገድ ሳይሆን የባህልእና የማንነት አንድ አካል ፣ የውግንና መገለጫ አድርገን ስለምንመለከተው ነው ። ክርስትናን በመጀመሪያው መንገድ ስንመለከተው ፣ ለየትኛውም ባህል የምንሰጠው ዋጋ ክርስቲያን ከሆነበት መጠን ጋር የተያያዘ ሲሆን በሁለተኛው መንገድ ስንመለከተው ግን ውጫዊ መገለጫ እንጂ ይዘትን እና ክብደትን የሚወስን መሆኑ ይቀራል ማለት ነው ። ስለዚህም ክርስቲያን የሆነን እና ያልሆነን ባህል ማነጻጸር አንድን ቀለም ከሌላ ቀለም ጋር እንደ ማነጻጸር ይሆናል ። ስም አለው - cultural relativism ይባላል ።
እኔ ጉዳዩን ለመመልከት የተነሣሁት በመጀመሪያው መንገድ ስለሆነ እና ክርስቲያን የሆነ ሰውም በዚሁ መንገድ መመልከት አለበት ብዬ ስለማስብ - ይህ ባህል እና አነዋወር ጉዳዬ የሆነው በክርስትና ከመቀረጹ የተነሣ ነው ። ክርስትና በሰሜን በኩል ወደ ሀገራችን መጥቶ እና ሰፍኖ ሳለ ክርስቲያናዊ የሆነን ባህል ፍለጋ ዘልዬ ሌላ ቦታ መሄድ አይጠበቅብኝም ። ምናልባት በኢትዮጵያ ክርስትና ሳይኖር

ታዲያ ከጥንት ጀምሮ ክርስትናው በዚህ መጠን ባህሉን እና አኗኗሩን ይቀርጸው እና ይወስነው ከነበረ እና ዛሬ ደግሞ ኅብረተሰባችን ደግሞ ይህን ያህል ከተለዋወጠ ፣ ቀድሞ የአዘቦት ሕይወት አካል የነበሩ ነገሮች ዛሬ ላይ ተረት እስኪመስሉን ድረስ ከሕይወታችን የራቁ ከሆኑ - የኅብረተሰቡ ለውጥ ስለዛሬ ክርስትናችን እና በማኅበረሰቡ ውስጥ ስላለው ሚና ምን ይናገራል ? ይህንን ጥያቄ ነው - ለመመለስ ሳይሆን - በሰፊው እና በአግባቡ ለማንሣት የምሞከረው ።

፱

ምናልባት የላይኛዎቹን ምሳሌዎች በማምጣት - ፍጹም ሰላማዊት ፣ ፍትሐዊት ፣ ክርስቲያናዊት ኢትዮጵያ የነበረች መሆኑን ለማስታወስ እየሞከርሁ እና ዛሬም ማድረግ ያለብን 200 ወይም 150 ዓመት ወደ ኋላ መመለስ ወይም ተቀምጠን ያን ዘመን መናፈቅ ነው ያልሁ እንዳልመሰለብኝ ተስፋ አደርጋለሁ ፤ አይደለምና ።

---

በሱዳን ወይም በኬንያ ብቻ ኖሮ ቢሆን እዚያ የተፈጠረውን ባህል ጉዳዩ አደርገው ነበር ይሆናል ። ቢያንስ ማድረግ ይኖርብኛል ብዬ አስባለሁ ። ዋናው ጉዳይ ባህሉ ወይም ቋንቋው ሳይሆን ክርስትናው ነው - ባህሉ እና ቋንቋው ለክርስትናው መሣሪያ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው ጉዳያችን የሚሆኑት ።

ሌላው ነጥብ ደግሞ በአንድ ሀገር ውስጥ ሁል ጊዜም ቢሆን አንድ አይነት ገንኖ የወጣ (dominant) ባህል የመኖሩ እውነታ ነው ። ምንም እንኳን በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎችም ክርስትና የቀረጻቸውን ባህሎች የምናገኝ ቢሆንም - የጉራጌን እና የጋሞን ባህሎች እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል - የሰሜኑ ክርስቲያን ማኅበረ ሰብእ ባህል ለረዥም ዘመናት የበላይ ሆኖ መኖሩን መካድ አይቻልም ፤ ተገቢም አይሆንም ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ያሉኝን ሐሳቦች ለሌላ ጊዜ ላቆያቸውና - ለዚህ ጽሑፍ ግን ይህን በአንድ ትልቅ ሀገረ መንግሥት ለረዥም ዘመናት የበላይ እና ገዢ ሆኖ የቆየን ክርስቲያናዊ ባህል አብነት ማድረግ መቻሌ እንደጠቀመኝ አምናለሁ ። ምክንያቱም ይህ ጉዳዩን ከብዙ ነገር አንጻር ለመመልከት እድል ይሰጣልና ። በሰዉ ማኅበራዊ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በአስተዳደራዊ ፣ ሕጋዊ ፣ የጦር እና ሌሎችም የማኅበረ ሰቡእ ገጾች ውስጥ ክርስትናው ምን ሚና እንደነበረው ለመመልከት ይቀናል ።

ሌላው ነጥብ የጠቀስሁት ምንባብ ይዘት ነው ። በምንባቡ ውስጥ አማራነት እና ክርስትና - በማኅበረሰቡ (ሙስሊም ከሆነው ክፍል በስተቀር) ያው እንደሆኑ ተደርገው እንደሚታሰቡ ተገልጧል ። ዳግመኛም አማሮች በክርስትናቸው ከመኩራታቸው የተነሣ ክርስቲያን ያልሆኑትን እንደሚንቁ እና ክርስትናቸው ደግሞ ከቋንቋቸው እና ከባሕላቸው ጋር ከመሰፋቱ የተነሣ ከዚያ ባህል ያልተገኙ ሰዎችን ወደ ማኅበራቸው ለመቀበል እንደሚቸገሩ ተገልጧል ። እነዚህ ነጥቦች ለትችት እና ለነቀፋ የሚጋብዙ ናቸው ። የጭቆና መገለጫ አድርጎ የሚመለከታቸው ሰውም አይጠፋም ። አንድም ‘ክርስቲያናዊ የሆነ ማኅበረ ሰብእ መገለጫ ናቸው ወይ ?’ የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ አይቀርም ።

“አማራነትን” ከክርስትና ጋር አንድ አድርገው መመልከታቸው በምንም ረገድ ችግር ሆኖ አይታየኝም ። ማኅበረሰቡ በስፋት ክርስቲያን ከመሆኑ የተነሣ እና ክርስትና የማኅበሩን አኗኗር በጥልቀት ከመቅረጹ አንጻር የሚገርመው ይህ ባይሆን ነበር ። ይህን ምንባብ መጥቀሴም ይህ ነጥብ የጽሑፌን ሐሳብ ስለሚደግፍልኝ ነው ። ዛሬ አንድ ሰው ዓረብ ወይም አፋር ወይም ሶማሊ ወይም ስልጤ ስለሆነ ሙስሊም ስለመሆኑ እርግጠኛ እንደምንሆነው እና ባይሆን እንደምንገረመው ነው ። የተለየ ነገር የለውም ። አንድ ማኅበረ ሰብእ በስፋት ክርስቲያን ከመሆኑ የተነሣ ክርስቲያን ያልሆነን ሰው የዚያ ማኅበረ ሰብእ አካል አድርጎ ለመቀበል አስቸጋሪ እንደሚሆነው ሁሉ ፥ ክርስቲያን ሆኖ ግን ከዚያ ማኅበረ ሰብእ መልክእ ፣ ቋንቋ እና አኗኗር ጋር የማይገጥም ሰውም እንዲሁ ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል ። ለምሳሌ በእኛ ባህል ጥዩፍ የሆኑ ምግቦችን የሚመገቡ ኦርቶዶክሳውያን ከሌሎች ሀገሮች ወደኛ ቢመጡ ፣ ያን ልማድ እስካልተዉ ድረስ ተቀባይነት የማግኘት እድል አይኖራቸውም ። በሰዎች በጠቅላላው የሚገኝ ፣ ወግ አጥባቂ በሆነው በእኛ ማኅበረ ሰብእ ደግሞ የሚበረታ ጠባይ ነው ።

ቀጥሎ ያሉት ሁለት ነጥቦች - ክርስቲያን ያልሆነውን የመናቅ እና ከሌላ ባህል የሚመጡ ሰዎችን ለመቀበል መቸገር ግን ከክርስትና አንጻር ተቃውሞ ሊነሣባቸው የሚገቡ ነጥቦች ናቸው ። ይህን ስል በዘመናችን ከመጣው ‘መቻቻል አለብን’ ወዘተርፈ የሚል ስብከት አንጻር ሳይሆን ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች በዋናነት ሊኖረን የሚገባው ወደ ክርስትናው ብርሃን እንዲመጡ የመጥራት ፍቅር እና ሐዘኔታ ስለሆነ ነው ። እኔም የጠቀስሁት በስምምነት ሳይሆን ከላይ ያለውን ጠቅሼ ይህን ብተወው ቁንጸላ ይሆንብኛል ብዬ ነው እንጂ የእኔን ሐሳብ ስለሚገልጥልኝ አይደለም ። በጽሑፌ ዝቅ ብዬ እንደማነሣው - ክርስቲያናዊ በሆነው ማኅበረ ሰብእ ውስጥም ቢሆን ከክርትስና የተቃረኑ ዝንባሌዎችን አናገኝም ማለት አይደለም ። በተጨማሪም ምንም እንኳን ይህን ዝንባሌ ከክርስትናው አስተምህሮ አንጻር ልንታገለው የሚገባ እና በተለይ ሐዋርያዊ ተልእኮ ላይ ያለብንን ድክመት የሚያሳይ ቢሆንም ግን እንዴት ሊፈጠር እና ሊያድግ እንደቻለ ማሰብ ፣ ማጥናት እና ማብራራት ያስፈልጋል ። ከራሱ ከኦርቶዶክሳዊነት ባህልን የመዋሃድ እና ከውህደቱ የተነሣ አንድ ተደርጎ የመታየት ጠባይ ጋር ፣ በሁሉም ማኅበረ ሰብእ ውስጥ ካለው መሠረታዊ የሚባሉ እምነቶችን እና ልማዶችን የማይጠብቅን ቡድንም ሆነ ግለሰብ የማግለል ጠባይዕ ጋር ፥ እንዲሁም በየጊዜው ከነበሩት ግጭቶች አንጻር በዝርዝር መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ። ይህን ዝርዝር ግን ለሌላ ጽሑፍ እናቆየው - ከያዝነው ጉዳይ ጠልቆ እንዳያስቀረን ።

8 “To all Amhara except a small minority who are Muslim, the name of their ethnic group is synonymous with "Christian." The term signifies Ethiopian Orthodox Christian; for the Amhara peasant, "Catholic" and "Protestant" are equivalent to "Muslim" and "pagan" as terms designating so many kinds of heathens. And being an Ethiopian Christian is to the Amhara a mark of superiority in at least two respects: it means belonging to a chosen people, heirs to the Jews and sole bearers of authentic Christianity; and it means being adept in praying and fasting, which to the Amhara are peculiarly Abyssinian arts. This orientation has motivated a certain amount of exclusionism vis-a-vis non-Christian Ethiopians. The latter are disdained because they are not Christian, while at the same time the particularistic cast of Abyssinian Christianity has made the Amhara somewhat reluctant to proselytize and admit non-Abyssinians to the fold.” Donald Levine, *Wax and Gold: Tradition and Innovation in Ethiopian Culture* (Chicago University Press, 1974), p. 78

ብዙ ያን ዘመን እንዳንናፍቀው የሚያደርጉን ምሳሌዎች ማምጣት እችላለሁ - ቀደም ብዬ በጎ በጎ ነገሮችን ያሳያሉ ያልኋቸውን ምንባቦች ካወጣሁባቸው መጻሕፍት ውስጥ ሳይቀር ። ግን ለለውጥ ያህል ወደ ሌላ ምንጭ ልሒድ ። የመንግሥቱ ለማ አባት ሊቁ አለቃ ለማ በአፄ ዮሐንስ ዘመን ለምን ትምህርት ቤት መግባት እንደፈለጉ እንዲህ ያጫውቱናል ፤

"የኢትዮጵያ ትዳር እኮ እንዲህ እንደ ዛሬ አልነበረም - ግብሩ ። ወታደር ይመራበታል ሕዝቡ ። በሰኔ አምስት መቶም እንደሆነ ስድስት መቶም እንደሆነ ሺህም እንደሆነ በያገሩ እንደ መጠን እንደ መጠኑ ይመራል ። ኻዲያ ፥ ሽማግሌ ይሰበሰብና ከጭቃ ሹሙ ጋራ 'እገሌ ባለንብረት ነው ፤ ይህን ያህል ይችላል ። እገሌ ድኃ ነው ፤ የለም ይህን ያህል ይበቃዋል . .' ይመከር ይመከርና ፥ ወታደር ይመራል - ከሰኔ ጀምሮ እስከ መስቀል ድረስ ።

እንግዴህ ያ ገበሬ የተመሩበት እሱ ሊያርስ ይሄዳል ፤ ወታደር ሚስቱን ይዞ ይውላል ። በዚያን ጊዜ ኸትግሬ እያረገዙ የወለዱ ብዙ ናቸው በኛ አገር እንኳ ። ለባላገሩ ጭንቅ ነው እንጂ ! ቄስ ምንም የለበት ፤ ዲያቆንም ያባቱን ቤት ኸግብር ኸምሪት ያድናል ባጤ ዮሐንስ ጊዜ ።

(ባጤ ዮሐንስ ጊዜ ባለቤቱ ወታደር ገባ ተመራ ኸቤትህ ሲሉት ጊዜ ተነሥቶ መጣ ። እገባለሁ ሲል ፤ 'እንዴ ተከናንቦ ይገባል ? ታጠቅ ! አደግድግ አሉት ወታደሮቹ ፤ ኸዚያ ግቢ ያለው አለቃቸው ነውና ። 'ተከናንቤ የገባሁብሽ ቤቴ ፥ ማሪኝ ! ማሪኝ !)

ባጤ ዮሐንስ ጊዜ ካህን ብቻ ነው ባለንብረት ፤ ማይም የሆነ ባለሥቃይ ነው ። ገባር ሆኜ መከራ አልቀበልም ብዬ ካላስተማራችሁኝ . . ."[9]

ዳግመኛም በክፉ ቀን ዘመን ስለሆነው ነገር እንዲህ ያወሳሉ ።

"ረሀቡን ያስነሣው የከብቱ ማለቅ ነው ። በምን ይታረስ ? መሬት ሳይታረስ እንዲሁ እንዳለ ቀረ ። ረሀቡ ያን ጊዜውን ከብቱ እንዳለቀ ተከተለ ፤ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ሰነበተ ።

ጅብ ጭርስ አደረገው ሰዉን ። . . . ሌሊት ወሰደኝ ! ወሰደኝ ! ወሰደኝ ! ሲል ያድራል ። . . . ማ ይወጣላ ጅብ ሊከለክል ? ሁሉም ደካማ ነው - ረሀብ ። ደሞ እሱን ቢወስደውስ ማን ያድነዋል ?

አንዲት ልጅ ወዛ ብላለች - ጋይንቴ ደስታ እሚባል ነበርና እሱ እየረዳዳት ። ተነሥታ ፍልውሃ ወረደች ። ብዙ ሰው የተቀመጠው እዚያ ነው ፥ ይህ ስደተኛው ሁሉ - ተቀበለና እዚያ አረደና በላት ።

ልጆቻቸውን ጥቃቅኖቹን እያረዱ የበሉ ሴቶች ብዙ ናቸው ። ሰው ቅጠል በላ ፤ ያልተበላ ቅጠል የለም ፤ ይኸ ቅጠል ቀረ እሚባለውን ነገር አላውቀውም ።"[10]

ረኃብ በእኛ ብቻ ያለ አይደለም ። ይህኛውን ረኃብ ልዩ የሚያደርገው ከዝናብ እጥረት ፣ ከድርቅ የመጣ አለመሆኑ ነው ። አለቃ እንደ ነገሩን ረኃብ የተከሰተው በከብት በሽታ ምክንያት ነው ። የሚታረስባቸው ከብቶች ስላለቁ ብቻ ነበር ዝናብ ባልጠፋባቸው ዓመታት ሰው ሰውን እስከመብላት የደረሰው ። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ረኃቡ በመጨረሻ እንዴት እንደተወገደ እንደሚከተለው ይነግሩናል ።

"በዓይነቱ ከብት እንጂ ዝናም አልጠፋም ። ዘዴ ተፈጥሮለት የሚሠራ እጅ ከተገኘ ችግሩ ሊወገድ ይችላል ። ስለዚህ በብዛት መቆፈሪያ ዶማ እየተሠራ ለሕዝብ ይታደል ጀመር ። ለአርዓያነትም አፄ ምኒልክ ራሱ እየወጣ ይቆፍር ጀመረ ። "እንደ ንጉሡ አጎንብሱ" እንደተባለው ሁሉም ይቆፍር ገባ ። ስለዚህ በ1883 ዓ.ም.

---

[9] *መንግሥቱ ለማ ፣ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ* (1959 ዓ.ም.) ፣ ገጽ 59

[10] *መንግሥቱ ለማ ፣ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ* ፣ ገጽ 143

እንደተባለው "ጭላንጭል" መታየት ጀመረ ፡፡
አዝመራም ብዙም ባይሆን በቂ ተመረተ ፡፡"[11]

እንዲህ ያለ ቀላል መፍትሔ በቅርብ ሳለ ያ ሁሉ ሰው ማለቁ እንዴት ያሳዝናል ፤ እንዴትስ ያስደንቃል ? ይህ መሆኑ አነዋወራችን ውስጥ ያለን አንዳች ውድቀት አያሳይም ? ታሪካችን አንዳንዶች እንደሚሉት ጨርሶ ጨለማም ባይሆን ፥ ብዙ የሚያሳዝን እና ፈጽሞ እንዲደገም የማንፈልገው ነገር የያዘ ነው ፡፡ ሰው ተርቦ ሰውን የሚበላባት ገነት አለችን ?

እንግዲህ በቀደመው ታሪካችን ፣ ባህላችን እና ትውፊታችን ብዙ ግሩም እና ከክርስትና አስተምህሮ የሚቀዱ ልማዶች እንደ ነበሩ ፣ እንዲሁ ደግሞ ብዙ አሳዛኝ እና አሰቃቂ ውጤት የኖራቸው ልማዶችም እንደ ነበሩ ካየን ስለዚያ ዘመን ድምዳሜያችን ምንድነው ሊሆን የሚገባው ? ይህን ጥያቄ መመለሳችን የግድ ነው ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ልብ ማለት የሚገቡን ነጥቦች አሉ ፤ ነገሩን በቅጡ ለመመልከት ያግዙን ዘንድ ፡፡

ቅድም ክርስትና የቀደመውን ባህላችንን በመሥራት ውስጥ ዐቢይ ሚና እንዳለው አንሥቻለሁ ፡፡ ነገር ግን ይህን ስንል ብቸኛው ሠሪ ክርስትና ነው እያልን እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን ፡፡ የክርስትና ተፈጥሮ በራሱ (በዚህ ዓለም) ተፈጥሯዊ ከሆነው የሰው ባሕርይ ጋር ትግል የሚገጥም እና እሱን ለመግራት የሚጥር እንደሆነ የታወቀ ነው ፡፡ ከመጀመሪያው ጀምሮ - ክርስትና በነበረባቸው ቦታዎች ሁሉ ይህ ትግል ነበረ ፡፡ በዚህ ትግል ውስጥ ደግሞ ክርስትናው ሰዎችን ጨርሶ ለመግራት የቻለባቸው ጊዜያት እጅግ ጥቂት ናቸው ፡፡ ከሐዋርያት መልእክታት ጀምሮ የአባቶች ትምህርቶች እና ጸሎቶቻችን እንደሚመሰክሩት ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ጨርሰው ለክርስትና ማስገዛት አልተቻላቸውም - የወደቀው ተፈጥሯቸው ገፊት አይሏል ፡፡ በኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ ውስጥ ንስሐ ዐቢይ ጉዳይ የመሆኑ ምክንያት እና ለቅዱሳን የሚሰጠው ታላቅ ክብርም ከዚህ እውነታ የመነጨ ነው ፡፡ ስለዚህ በሁሉም ማኅበረ ሰብእ ውስጥ የተወሰኑ ጎልተው የሚወጡ ዝንባሌዎች ይኖራሉ ፡፡ በእኛም ሀገር እንዲሁ ዓይነት ዝንባሌዎች ነበሩ ፣ አሉም ፡፡ ለምሳሌ ሌቪን ከጥል እና ግጭት ጋር በተያያዘ ያለውን ዝንባሌ እንዲህ ይገልጡታል ፡፡

"ገበሬው በአንድ ጊዜ የቁጣ እና የግጭት ዝንባሌውን በማነቃቃት እና በመቆጣጠር የተጠመደ ነው ፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ጠብን በተመለከተ ያለው (የካሕናትን እና የባሕታውያንን ፍጹም ሰላማዊነትንም ፥ የሽፍታውን እና የበቀለኛውን ጀግንነትም የማድነቅ) እርስ በእርሱ የሚጣረስ ልማድ ገበሬው በሕይወቱ የሚፈተንበት ዋናው የሞራል አጣብቂኝ ነው ፡፡ ተፈጥሮ ፣ ፈጣሪ እና ሌሎችም የሕይወት ጉዳዮች በብዛት ትኩረቱን የሚይዙት ቢሆንም ይህ በሰው ሕይወት የሚስተዋለው የኃይል እና የግጭት ዝንባሌ ግን የገበሬውን ተሞክሮ በበላይነት የሚቆጣጠር ይመስላል ፡፡ "[12]

ሩካቤን በተመለከተ የነበረውም ባህል እንዲሁ በስፋት ከክርስትናው አስተምህሮ በተቃራኒ እንደሆነ አስፍረዋል ፡፡

"በጎ የሚለውን ሕይወት በመሣል ውስጥ ለገበሬው አጣብቂኝ የሚሆኑበት ጉዳዮች ሩካቤን እና ግጭት ናቸው ፡፡ እነዚህ አጣብቂኞች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለው የክርስትና እና የአረመኔ ባህሎች መቀላቀል መገለጫዎች ይመስላሉ ፡፡ ከክርስትና የተነሣ ጋብቻ ቅዱስ ፣ ፍቺ የተጠላ ፣ ዝሙት ደግሞ ርኩስ እንደሆኑ ይታመናል ፡፡ ታዲያ ገበሬው እነዚህ እምነቶች በካህናቱ ሕይወት ውስጥ መገለጣቸውን እያከበረ ፣ እርሱ ራሱ ግን ከትዳሩ ውጪ በመሄዱ እና ሲያስፈልግም ፍቺ በመፈጸሙ እምብዛም ጸጸት አይታይበትም ፡፡ ምናልባት ይህ በእምነት እና በተግባር መካከል ያለን ክፍተት ያሳይ ይሆናል ፡፡ ነገር ግን ነገሩ እንደ ደንብ መታየቱ ጥንት ከክርስትና በፊት ከነበረ ብዙ ሚስቶች ማግባትን እና ዕቁባት

[11] *ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ፥ የአዲሱ ሥልጣኔ መስራች* (የተተየበ ግን ያልታተመ)

[12] "The Amhara peasant is simultaneously preoccupied with the stimulation and the control of aggressive behavior. The previously mentioned conflict of norms regarding violence is perhaps the chief area of moral conflict in his thinking about the good life. Though nature, God and other aspects of man's life occupy much of his attention from time to time, it appears the phenomenon of human aggression dominates the confrontation between the Amhara peasant and the objects of his experience." Levine, *Wax and Gold*, p. 85

> ማስቀመጥን ይፈቅድ ከነበረ ባህል የመጣ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማል ።”[13]

ስለዚህ ክርስትናው ባህልን ከመቅረጽ አንጻር ብዙ ተጋፊዎች እንዳሉት ግምት ውስጥ መክተት ይኖርብናል ።

ሌላው ጉዳይ ለለውጥ ያለው ፍርሀት እና ጥርጣሬ ወይም ወግ አጥባቂነት ነው ። ይህ የለውጥ ፍርሀት እና ወግ ማጥበቅ በራሱ መጥፎ አይደለም ብዬ አስባለሁ ። ክርስቲያናዊ ነውም ብዬ አስባለሁ ። አንዴ የተሰጠችውን ሃይማኖት እና አባቶቻችን የሠሩትን ሥርዓት ለመጠበቅ አስፈላጊ ዝንባሌ ነው ። በሰው ልጅ ታሪክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የቀደሙ ሰዎች የተሻለ እንደሚያውቁ እና እንደሚያስተውሉ ፣ ያለፉ ትውልዶችም የተሻለ ጥበበኞች እንደሆኑ ነበር የሚታመነው ። ሕይወት የረጋ እና የማይለወጥ ፣ ሲለወጥም እንኳን መለወጡ በማያስታውቅ መልኩ ስለነበረ አዲስ የሚመጣው ትውልድ ከሱ በፊት ከነበሩት የተለየ የሚያገኘው እና የሚያውቀው ብዙ ነገር አይኖርም ። ያለፈው ትውልድ ግን አዲሱ ትውልድ የሚያልፍባቸውን መንገዶች ሁሉ አስቀድሞ ያየ ፣ መከራዎቹንም ሁሉ ቀድሞ የተጋፈጠ ስለሆነ አዲሱን ትውልድ ለመምራት ብቁ መሆኑ አይጠረጠርም ።

ይልቁንም ዋናዎቹ የሕይወት እና የማንነት መሠረቶች ፥ የሃይማኖት ፣ የቤተሰብ እና የማኅበረ ሰብዕ ዕሴቶች ፥ እነዚህን ዕሴቶች የሚወክሉ ታሪካዊ ተምሳሌቶች (ቅዱሳን ፣ ነገሥት ፣ ሊቃውንት ፣ ጀግኖች ወዘተርፈ) ሁሉ ቀድመው የተገኙ ስለሆኑ እና አዲስ የሚመጣው ትውልድ ከእነዚያ መሠረቶች ስለሚርቅ ለእነዚያ መሠረቶች የሚቀርቡትን ትውልዶች ከእርሱ ይልቅ ለምንጩ የቀረቡ እና ያልተበረዘውን የሕይወት መንገድ ሊያሳዩት የሚችሉ ጠቢባን አድርጎ ይመለከታቸዋል ።

ከክርስቲያናዊ ትውፊት እና ልቡና አንጻር ካየነው ፣ ይህ አመለካከት ትክክል ነው ። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እና ካህናት ዋና ሥራ የተሰጣቸውን መስጠት ፣ የተቀበሉትን እውነት ማቀበል ነውና ። ይህ እውነት ደግሞ የተጻፈ ሕግ ብቻ ሳይሆን በኑሮ እና በድርጊት የሚገለጥ የአነዋወር ዘዬ ነውና ከመጻሕፍቱ በተጨማሪ የማኅበረሰቡን ኦርቶዶክሳዊ ሥሪት መጠበቅ የዚህ ተግባር ዐቢይ አካል ነው ። የተጻፉት ነገሮች እንኳን በሕይወት የሚገለጡበት መንገድ ከጠፋ እና የተጻፉበት ዓውድ ካልታወቀ ብዙ ሰው በብዙ መንገድ ሊተረጉማቸው ስለሚችል ፥ ይህ ነው የሚባል ትርጉም እንዳይኖራቸው ይሆናሉ ።

ስለ ዘመን ማለፍ ያለውም አመለካከት አሉታዊ ነው ። እንደ ወንዝ ሁሉ ከምንጩ ጠርቶ ፣ በፈሰሰ ቁጥር ግን የሚቆሸሽ እና የሚደፈርስ ተደርጎ ይታሰባል ። ደጉ ዘመን ወደኋላ የቀረ ፥ የሚመጣው ዘመን ደግሞ ክፉ መሆኑ ይታመናል ።

ይህ ወግ አጥባቂነታችን ግን ከመጠን በላይ የተለጠጠ መሆኑ አያጠራጥርም ። ቅድም ካልናቸው የሕይወት እና የማንነት መሠረቶች አሳልፈን ለሁሉም ዓይነት ልማዶች እናውለዋለን ። አስተራረሳችንን ፣ አለባበሳችንን ፣ አመጋገባችንን ፣ የግብር ሥርዓታችንን ፣ የፖለቲካ አሠራራችንን ሁሉ አንዳንዴ እስከ ጥቃቅኖቹ ይዘቶች ድረስ በዚያው ልክ እንመለከታቸዋለን ። አንዳንዴ ከክርስትናው አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጋጩ ልማዶች ሳይቀሩ በዚህ ልክ ሲጠበቁ እናገኛቸዋለን ።[14]

ቅድም ስለ ክፉ ቀን ረሐብ ሥርግው ሐብለ ሥላሴን ጠቅሰን ያወሳነው ነጥብ ለዚህ ጥሩ አስረጂ ይመስለኛል ። በከብት ከማረስ ጋር በእጅጉ ከመዛመዳችን የተነሣ በረኃብ ስናልቅ እንኳን እፊታችን የነበሩት ቀላል መፍትሔዎች

---

[13] “The chief areas of conflict within the Amhara peasant's conception of the good life are those of sex and aggression. These conflicts appear to reflect the mixture of Christian and pagan cultures in Abyssinian history. From Christianity come beliefs that marriage is sacred, divorce is not legitimate, and adultery is taboo. The Amhara peasant, while respecting the embodiment of these norms in the lives of priests, feels justified in having sexual relations outside marriage and in getting a divorce whenever the need arises. Perhaps it can be argued that this represents a conflict between norms and practice, but the legitimate tone of the non-Christian behavior suggests that it might well be considered an alternative norm, a carry-over from the ancient culture which legitimized polygamy.” .” Levine, *Wax and Gold,* p. 83

[14] “In addition to the feeling that innovation is ineffectual, the Amhara peasant tends to feel that is it immoral. Reverence for fathers and forefathers is, we observed, a key element in Amhara ethos. The patriarchal sentiment informs the Amhara’s defense not only of his land and his religion but of the procedures of daily living as well. It is not good to deviate from the familiar ways for doing things because they, too, have been handed down by “our fathers”; this is a phrase which interlards Amharic conversation.” Levine, *Wax and Gold,* p. 87

ሊታዩን አልቻሉም ። ነገር ግን በመጨረሻ ችግሩ የተፈታበት መንገድ ደግሞ ማኅበረሰቡ ለለውጥ ያለውን ጥላቻና ፍርሀት እንዳለ ሆኖ ከሚያምናቸው ምንጮች ፥ ማለትም ከቤተ ክርስቲያን እና ከመሪዎች ፥ ሲመጣ ግን አዲስን ነገር የመቀበል ዝንባሌ መኖሩን ከዚሁ ታሪክ መረዳት እንችላለን ። ሌቪንም ይህንኑ ልብ ብለዋል ።[15]

ስለዚህ ትውፊት ሁሉ ኦርቶዶክሳዊ ፣ ባህልና ልማድም ሁሉ ክርስቲያን ማኅበረ ሰብዕ ውስጥ ስለተገኘ ክርስቲያናዊ አለመሆኑን ልናሰምርበት ይገባል ። በመሆኑም የቀደመው ባህል እና ትውፊት መሠረታዊ ባሕርይው (ሥሪቱ) ኦርቶዶክሳዊ መሆኑ የታመነ ቢሆንም ፥ ነገር ግን ባህሉ ውስጥ ያለው ነገር በሙሉ ከኦርቶዶክሳዊነት ጋር የሚገናኝ አለመሆኑ እና አንዳንዴም ከኦርቶዶክሳዊነት ጋር የሚቃረን መሆኑም ሐቅ ነው ። ስለዚህ ከዚህ በኋላ በምናነሣቸው ነገሮች ሁሉ የሚከተለው ነጥብ ከአእምሮአችን መጥፋት የለበትም ።

የቀደመ ባህላችን እና የልቡናችን ሥሪት ኦርቶዶክሳዊ ነው ስንል ፥ የባህላችንም ሆነ የልቡናችን ሥሪት ፍጹም ኦርቶዶክሳዊ ነው እያልን አይደለም ። ከእሱ ጋር የሚቃረኑ ዝንባሌዎችን እና ልማዶችንም ጭምር የያዘ መሆኑንም አንዘነጋም ። ስለዚህም ጠቅላላው ባህል ከኦርቶዶክሳዊ ባህል ጋር ተመሳሳይ አይደለም ። በሁለቱ መሀል ግልጽ መስመር ማስመር እንኳን ቢያስቸግር ፥ ቢያንስ ከክርስትናው በግልጽ የራቁትን ነገሮች ኦርቶዶክሳዊ ሥሪት ካልነው ጋር ያለማቀላቀል ቅንነት ሊኖር ይገባል ።

ይህን ልዩነት ማጠየቅ ያስፈለገው ይህ ዐይነቱ የተሳሳተ አረዳድ ዋናውን ጥያቄአችንን እንዳንመልስ እንቅፋት ስለሚሆንብን ነው ። ባህላችን ችግሮች እና ጉድለቶች ካሉበት እና ባህላችን ኦርቶዶክሳዊ ከሆነ - የችግሮቹ እና የጉድለቶቹ ምንጭ ኦርቶዶክሳዊነት ራሱ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊወስድ ይችላል ። እንዲህ ዓይነት መረዳት ያላቸውም ሰዎች አሉ ። ይህ ሐሳብ ደግሞ በሁለት መንገድ ሊደገፍ ይችላል ። አንደኛው እንደተባለው የቀደመውን ባህል ሁሉ ኦርቶዶክሳዊ አድርጎ በመረዳት ሲሆን ፣ ሌላኛው ደግሞ ኦርቶዶክሳዊ መሠረት ያላቸውን ባህሎች እና ትውፊቶችን ራሳቸውን በመንቀፍ እና "ኋላቀር" አድርጎ በመቁጠር ነው ። ሁለተኛው መንገድ የተሳሳተም ቢሆን ግን ቀና ነው - ኦርቶዶክሳዊነትን የሚከሰው የራሱ በሆነ ነገር ስለሆነ ክሱን ለመከላከል ያመቻል ። የመጀመሪያው መንገድ ግን ስህተትም ጠማማም ሆኖ ግን አዋጭ ነው ። ምክንያቱም የባህሉን ችግር እና ጉድለት በሙሉ ለኦርቶዶክሳዊነት አሸክሞ ስለሆነ የሚከሰው ፥ ሸክሙን ተቀብሎ ክሱን መከላከል ስለማይቻል ነው ። ስለዚህ በመጀመሪያ የባህሉ ጓዝ በጠቅላላ ወደ ኦርቶዶክሳዊነት ተጠቃሎ እንዳይመጣ መከላከል ያስፈልጋል ፤ እውነቱ ያ ስለሆነ ። አንድም ይህ ክርክር ባይኖር ራሱ ፥ በፊትም ሆነ ዛሬ ባህሉን የበለጠ ኦርቶዶክሳዊ ለማድረግ ኦርቶዶክሳዊ ያልሆኑትን የባህሉን ክፍሎች መለየት ያስፈልጋል ። የተለጠጠ ወግ አጥባቂነታችን በዋናነት እንቅፋት የሆነብን ይህን እንዳናደርግ ይመስለኛል ።

ይህን ልዩነት በግልጽ ካስቀመጥን ፥ አሁን ቀድመን ያነሣነው ጥያቄ ላይ አንዳንድ ሐሳቦች እንስጥበት ። ምሳሌዎች አንሥተን እንዳየነው ፥ ታሪካችን አስደማሚ ክርስቲያናዊ ወጎችንም ፥ ብዙ አስከፊ እና አሰቃቂ ልማዶችንም የያዘ ነው ። በአኩሪ እና አስደሳች ሁነቶች የተሞላም ፥ በብዙ መከራ እና ሰቆቃ የታጨቀም ነው ። ስለዚህ እንዴት እንረዳው ? "የጨለማ ዘመን" ወይስ "ደጉ ዘመን" ? ኦርቶዶክሳዊነትስ ለዘመኑ ጨለማነት ወይም ደግነት ምን አበረከተ ?

## ፫

በመጀመሪያ ነገሮችን እጅግ በተቃለለ መንገድ ላለመመልከት እንጠንቀቅ ። ጉዳዩ ውስብስብ ነው ። የቀደመውን ታሪካችንን እና ባህላችንን በመናፈቅም ሆነ በማጥላላት በሕዝባዊውም ሆነ አካዳሚያዊ በሆነው ተዋሥኦ ፣ እንዲህ ካለ ነዳይ ምልከታ በመነሣት ትልልቅ ድምዳሜዎች ይቀመጣሉ ፤ መጻሕፍት ይጻፋሉ ፤ የፖለቲካ ድርጅቶች ይመሠረታሉ ፤ ሰዎች ይሞታሉ ፤ ሥርዓት ይሠራል ። ምናልባት በባዶ ሜዳ ክስ እያቀረብሁ እንዳይመስልብኝ ምሳሌዎች ላምጣ ።

ለምሳሌ የቀድሞውን የኢትዮጵያ ፕሬዚደንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን እንውሰድ ። ትግላችን የሚለውን መጽሐፋቸውን የሚጀምሩት ከእሳቸው ዘመነ መንግሥት በፊት ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ ለመተረክ በመሞከር ነው ። ሙከራው ደግሞ የተደረገው አንድ

[15] "The Amhara typically rely on legitimate authority figures to define appropriate responses to new situations, and regard the delegation of powers as a diminution of the status of such authorities. The peasant has thus refrained from initiating changes in the public domain because the prerogative of taking initiative is generally reserved to ecclesiastical and political authorities." Levine, *Wax and Gold*, p. 88

ምንጭ እንኳን ሳይጠቀስ እሳቸው ታሪክ ነው ብለው ያሰቡትን ሁሉ በመጻፍ ነው ። መነሻቸው የራሳቸው አስተያየት እንጂ ጥናት ስላልሆነ የጻፉትን ታሪክ እንደቁም ነገር መውሰድ ያስቸግራል ። በእርግጥ እሳቸውም ይህን የሚያጡት አይመስለኝም ። ነገር ግን ልብ ወለዱንም ቢሆን በተወሰነ ደረጃ እንደ ቁም ነገር ማየት የሚኖርብን ይህ የታሪክ አረዳድ 17 ዓመት ሀገር "የመራ" ስለሆነ ነው ። ምሳሌዎች ላምጣ ።

> "አፄ ቴዎድሮስ መላውን የሥልጣን ዘመናቸውን ያሳለፉት ከውስጥ ከፋፋይና ሥርዓት አልበኛ መሳፍንቶች ጋር በመቀጣቀጥ ነው ። ለነጻነት ፣ ለአንድነት ፣ ለጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት የመመሥረት ዓላማ ተግባራዊነት እየታገሉ የጉልተኛ መሳፍንቶችንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ካህናትን የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሠረት በማፈራረስ ማዕከላዊውን መንግሥት ፣ የመከላከያውን ተቋምና የሕዝቡን አስተዳደር በዘመናዊ ሥርዓት ለመገንባት በመጣር ላይ እንዳሉ በአካባቢው መሳፍንቶች ፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናቶችና በውጭ ተፃራሪ ኃይሎች የተቀነባበረ ጥቃትና ሴራ በአጭሩ ተቀጩ ።"[16]

> "በአንድ ንጉሠ ነገሥት በምትመራና በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ጥላ ስር በምትተዳደረው ጉልታዊት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የአስተዳደር ክልሎች ለማዕከላዊ መንግሥት የተወከለ ብሔራዊ የመከላከያ ሠራዊት ፣ ሕግ አስከባሪ ፖሊስ ፣ ዳኛና ፍርድ ቤት ወይም የሕግ እና የፍትሕ ተቋም ብሎ ነገር አልነበረም ። የየክልሎቹ ገዥ ጉልበተኞች የየራሳቸውን ክልሎች እንዳሻቸው የሚረግጡበት የየራሳቸው ልማዳዊ የአገዛዝ ዘይቤ ፣ የጥቅማቸው ፣ የሥልጣናቸውና የየግላቸው ፀጥታ አስከባሪ የሚባል ግን ዘራፊና ገፋፊ የገበሬ ፀር የሆነ የግል ሠራዊት ያላቸው ናቸው ። እንዳሻቸውና እንደልማዳቸው በሕዝቡ ሀብት ፣ ጉልበትና ሕይወት ጭምር የሚያዙና የሚፈርዱ የሚያስፈልጓቸውን ባለሥልጣኖች በዘር ሐረግ ላይ ተመሥርተው በሥጋ የሚዛመዷቸውን የሚሾሙም የሚሽሩም ናቸው ።

> "በሕዝቡ ላይ ምንም ዓይነት ግፍና በደል ቢፈጽሙ ተከሳሽነትና ተጠያቂነት የሌለባቸው ፣ የማይገሰጹና የማይከሰሱ ፣ የሁሉም ነገር ባለቤት ሆነው እንደመሰላቸው ለአገልጋዮቻቸው እርስትና ማደርያ መሬት እየሸነሸኑ የሚተክሉና ሲያስፈልጋቸውም የሚነቅሉ ፈላጭ ቆራጭ ፣ ገዥም ፣ ዳኛም ፣ ሕግም ናቸው ።"[17]

መቼም የጓድ ሊቀመንበር ድፍረትና ቆራጥነት አይጠረጠርም ። ቆራጥ ታሪክ አጻጻፋቸው ግን እንደ ቆራጥ አመራራቸው ሁሉ ወደ ውድቀት እና ግዞት እንጂ ወደ ሌላ አያመራም ። ጅብ የማያውቁት ሀገር ሔዶ እንዲሉ ፣ ከ16ኛው እስከ 19ኛው ምዕት ዓመት የነበሩ ነገሥታትን ፣ መሳፍንትን እና መኳንንትን በ20ኛው ምዕት ዓመት ስላልኖሩ የመውቀስ ድፍረት ሌላ ማን ሊኖረው ይችላል ? ኢትዮጵያ በነገሥታቱ ዘመን መከላከያ አልነበራትም ብሎ እየደመደመ ወዲያው ደግሞ ስለ ነጻነት ታሪኳ ሲተርክ የማይጋጭበት ሌላ ማን ሊኖር ይችላል ? ኢትዮጵያ ውስጥ ፥ ምንም እንኳን ፍርድ እና መፋረድ ዐቢይ ጊዜ ማሳለፊያ እና የሚደነቅ ጥበብ ቢሆንም ፥ የሕግ መጻሕፍት የነበሩን ቢሆንም ፥ ለዕለት ገበያ እንኳን ፍርድ ቤት የሚቆምበት ሀገር የነበረ ቢሆንም ፥ ሕግም ዳኛም አልነበረም ብሎ እውነቱን ፍርጥ ለማድረግ ሌላ ማን ሊደፍር ይችላል ? ስላላወቅን ርስት የማይነቀል የገበሬ ሀብት ፣ ጉልት ደግሞ ሹመት እስካለ የሚጸና ፣ ሽረት ሲመጣ የሚሔድ የመኳንንት ደምወዝ መሰለን እንጂ የተገላቢጦሽ መሆኑን ጓድ ሊቀ መንበር ባያስረዱን ምን ይውጠን ነበር ? ማስተዳደር ወንጀል መሆኑንስ ማን ነገረን እስከ ዛሬ ? ሊቀመንበር ባይገልጡልን ኖሮ አፄ ቴዎድሮስን ጲላጦስ እና ፈሪሳውያን እንደነበሩ የሰቀሏቸው መች አወቅን ? ተአምራቸው ተወርቶ ስለማያልቅ እንተወው እንጂ ጓድ ሊቀመንበር ወደ አልኖሩበት ዘመን ሔደው በዐይናቸው የተመለከቱትን ታሪክ ሲተርኩ ሀዲስ አለማየሁን ለማስናቅ ሁሉ ይቃጣቸዋል ።

እስቲ አለፍ ብለን የሌላውን "ምሁር" መጽሐፍ እንቃኝ ። ዶክተር ተስፋዬ መኮንን ቀድሞ የኢህአፓ አባል የነበሩና

---

[16] *መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ፣ ትግላችን ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ፥ ቅጽ 1* (ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት ፣ 2004) ፣ ገጽ 43

[17] *መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ፣ ትግላችን ቅጽ 1* ፣ ገጽ 46

እና በኋላ ማሌሪድ የተባለ ድርጅት መሥርተው ከደርግ ጋር አብረው የሠሩ እና ከደርግ ጋር አብሮ እንደሠራ እንደ ማንኛውም ሰው በኋላ ለወህኒ የተዳረጉ ሰው ናቸው ። ከረዥም የትምህርት እና የሥራ ቆይታቸው በኋላ በ1983 ባሳተሙት መጽሐፋቸው ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ከጻፏቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ።

> "ስለኢትዮጵያ ታሪክ ስናስብ ቀደም ሲል ከሚታወቀው ጥንታዊውና ፊውዳል ኢትዮጵያ ታሪክ ሌላ ደማቅ የሥልጣኔ ታሪክ የለንም ። መነሻውም መድረሻውም ይኸው ኋላቀር ታሪካችን ነው ።"[18]

> "የጥንቱን የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድ የመሰባሰብ እና የመጠጋጋት ታሪክ ልዩ የሚያደርገውና ተከትሎም ለመጣው ማዕከላዊ መንግሥት ምሥረታ ብቸኛውን ሚና የተጫወተው ከጥንት በእስልምና ሀይማኖት የመስፋፋት ግፊት ፣ አስከትሎም በመጣው የኦቶማን ቱርክና የፖርቱጋሎች የመስፋፋት ሙከራ ፣ በኋላ በኢጣልያ ፣ በእንግሊዝ ፣ በፈረንሳይ አቅኝዎች ከበባ የደረሰው ግፊት መሆኑ ምን ያጠያይቃል ?"[19]

> "ከጥንት ጀምሮ ዘልቆ ከመጣው የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ለአያንዳንዱ ወራሪ ኃይል የሞራል በትር በመሆን በማገልገል ብቻ ሳይሆን ለወረራውም ትክክለኝነት ቅባ ቅዱሷን ስትሰጥ የመጣችና የመንፈስ መሪ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ቴዎድሮስ ከጎናቸው አጡ ። የእሳቸው ትልቁ ሽንፈት ይህንን የሞራል በትርና የመንፈስ መሪ ለመጨበጥ አለመቻል ነበር ። የእብደታቸውም የፕሮፓጋንዳ ታሪክ የተሰበከው በቤተ ክርስቲያን መሆኑም ያለ ምክንያት አልነበረም ። የተመሠረተችበትና ተንሰራፍታ የያዘችው መሬት ተሸንሽና ለቋሚ ጦር ቀለብ ማስገኛ ሊሆን ሆነ . . . ቤተ ክርስቲያንም ከመሳፍንቱ ጋር ሁና ንጉሡን በማውገዝና ሕዝቡን ከስራቸው በማሸፈት እንዳይገዛ በመገዘት ጦርነቱን በእልህ ተያያዙት ።"[20]

እኚህ ደራሲ "ስለ ታሪክ ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖረን ግዴታ ነው ።" ሲሉ ይመክሩናል ። ከዚህ ምክራቸው እና እሳቸው ከጻፉት ታሪክ አንዱን መምረጥ ይኖርብናል ። ምክሩን መርጠናል ። መጽሐፉ ውስጥ ካሉት የአሽሟቃቂ ምንባቦች ቡፌ ከላይ የተጠቀሱትን ብቻ በማንሳት መወሰን ነበረብኝ እንጂ ድግሱስ ድል ያለ ነበር ። ግን ቢያንስ የኢትዮጵያን ታሪክ ተመልክቶ "ኋላቀር" ከሚል ሌላ ቃል የማይመጣለት ጸሐፊ ፣ በኢትዮጵያ "የሕዝቦች" አንድነት ከእስልምና እና ከኦቶማን ቱርክ መስፋፋት እንደሚቀድም ያላወቀ እና ስለ ሁለት ሺህ ዓመታት ታሪክ ሲያወራ ምንም ምንጭ ሳይጠቅስ እና አባባሉን በማስረጃ ሳይደግፍ "ብቸኛው" እና "ምን ያጠያይቃል" የሚሉ ቃላትን ለመጠቀም የማያፍር "ምሁር" ፣ ቤተ ክርስቲያንን የወራሪ (ወራሪው ማን እንደሆነ ሁሉ ሊገባኝ አልቻለም - ጣሊያን ይሆን ወይስ እንግሊዝ ወይስ ግብጽ) መሣሪያ ብቻ አድርጎ የሚመለከት ሰው ነው "ሰፋ ያለ ግንዛቤ" እንዲኖረን የሚመክረን ።

ለምሳሌ ያህል ይህን ጠቀስሁ እንጂ ታሪክን በተመለከተ የተጻፉ ወይም ታሪክን ለሚጽፉበት ጉዳይ እንደ መነሻ የሚጠቀሙ መጻሕፍት ላይ በስፋት የማስተውለው ችግር ነው ። ሌላው ቀርቶ 'ባለሙያ' (professional) የምንላቸው ታሪክ ጸሐፊዎች ሳይቀር የዚህ ችግር ሰለባ ናቸው ። ለምሳሌ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ (እሳቸው ራሳቸው የዶክተር ተስፋዬን ታሪክ አጻጻፍ ይተቻሉ) የተማሪው እንቅስቃሴ ለምን ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን አነብናቢ እንጂ የሀገሪቱን ሁኔታ አገናዝቦ መፍትሔ የሚያቀርብ ሊሆን አልቻለም የሚለውን ጥያቄ ሲመልሱ እንዲህ ይላሉ ።

> ". . .የተማሪው ንቅናቄ ቀኖናዊ መሆኑ ከቀደመው (የሀገሪቱ) ታሪክ የመነቀል ሳይሆን ከዚያው የመቀዳት ውጤት ሆኖ ነው የሚታየኝ ። ቀድሞ የነበረው ሃይማኖታዊ ግትርነት ነው ወደ ማርክሳዊ ግትርነት የተቀየረው ። ያው ዶግማዊነት ነው በሌላ መንገድ የቀጠለው ።"[21]

---

[18] ተስፋዬ መኮንን ፣ *ይድረስ ለባለታሪኩ* (2010) ፣ ገጽ 15

[19] ተስፋዬ መኮንን ፣ *ይድረስ ለባለታሪኩ* ፣ ገጽ 24

[20] ተስፋዬ መኮንን ፣ *ይድረስ ለባለታሪኩ* ፣ ገጽ 31-32

[21] "…I would tend to see in this canonical character of student radicalism not a negation of the past but its continuation. What occurred was to all intents and purposes a transmutation of the religious orthodoxy of the classical tradition… into a Marxist orthodoxy, or continuation of dogma by other means." Bahru Zewdie, *The Quest for Socialist Utopia: The*

ባሕሩ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሦስት ነገሮችን ተናግረዋል ። አንደኛው የተማሪውን እንቅስቃሴ ማርክሲስታዊ ግልብነት እና አነብናቢነት ነው (ይህን ነው ቀኖናዊ መሆን የሚሉት) ። ሁለተኛ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ባህል ሃይማኖታዊ ዝንባሌው እንዲሁ መሆኑን ነው ። ሦስተኛው ይህ የተማሪው ዝንባሌ የመጣው ከጥንቱ ባህል መሆኑን ነው ። አንደኛው አባባል በመጽሐፉ ውስጥ ብዙ ማስረጃ የቀረበበት ስለሆነ እንቀበለዋለን ። ሁለተኛው እና ሦስተኛው ድምዳሜዎች ግን ጸሐፊው ያለምንም ማሳያ ፣ ያለምንም ምንጭ እና ያለምንም ምርምር "ደርሰውባቸው" እንደ ዕውቀት ለኛ ሊያቀብሉን የሚሞክሯቸው ናቸው። ማርክሳዊነት በተራመደባቸው እና በተተገበረባቸው ሀገሮች ሁሉ እንዲህ ያለ ጠባይዕ የነበረው መሆኑ ለፕሮፌሰር ባሕሩ ይሠወራቸዋል ብዬ አላምንም ። ነገር ግን ይህን እውነታ ከቁጥርም ለማግባት አይሹም ።

ዝርዝር ጉዳዩ ራሱን ችሎ መመርመር ያለበት ስለሆነ ከዚህ በላይ አልልም እዚህ ጋ ። ግን አንድ የታሪክ ምሁር ጥንታዊውን እና ሰፊውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት እና ትውፊት ሳይመረምረው ፥ እሱን ተቃርኖ በተነሣ እና ርእዮታዊ መሠረቱ ባዕድ በሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ ለነበረ ትልቅ ጉድለት ፥ ያውም ደግሞ ከላይ እንደጠቀስሁት ይህ ርእዮት በሌሎችም ቦታዎች በተመሳሳይ ችግሮች መጠቃቱ የታወቀ ሆኖ ሳለ ፥ ምንም ማስረጃ ሳያቀርብ ተጠያቂ ማድረጉ ነገሮችን አቃልሎ የመመልከቱ ችግር ምን ያህል ሥር የሰደደ እንደሆነ የሚያሳይ ነው ።

እርግጥ ነው ይህ ዝንባሌ እጅግ የሚፈትን ነው ። ስንፍናን እና ችኮላን ለመሸፈን ያመቻል ። ቀድመን ወደ ደረስንበት ዝንባሌ ለመንደርደርም ይቀናል ። ቀድሞ የፈጸሚቸውን ድርጊቶች እና የወሰዷቸውን እርምጃዎችም ለመከላከል ይቀላል ። ነገር ግን ይህ መንገድ ምንም ያህል ቢሰፉ እና ቢመች የትም አያደርሰንም ። ሌላው ቀርቶ መነጋገር እንኳን እንዳንችል ነው የሚያደርገን ።

ታሪካዊ ሁነቶችንም ሆነ ሰዎችን በተመለከተ አንዳች ድምዳሜ ላይ መድረሳችን የሚቀር ሆኖ አይደለም ። 'ሁሉም ወቅት እና ሁሉም ሰው በጎ እና መጥፎ ጎን አለውና ይህ ከዚያ ይሻላል ማለት አይቻልም' ብለን ማለፍም በራሱ ግልብነት እና ስንፍና ነው ። ምናልባትም

Ethiopian Student Movement (James Currey and Addis Ababa University Press ,2014), p. 138

ይህኛው አካሔድ በችኮላ ከሚወሰደው ውሳኔ የከፋ ነው ።

ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ መከተል ያሉብን ሂደቶች አሉ ። በመጀመሪያ ታሪክን ስንመለከት ምንን ፍለጋ እንደሆነ ማወቅ አለብን - አስፈላጊ ፣ ወሳኝ ፣ ክብደት ያላቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው ? ስለዚህ የኛ ርእዮት እንዴት ያለ እንደሆነ መበየን ይኖርብናል ። ምን ላይ ቆመን ነው ነገሮችን የምንመለከተው ? ጥሩ ወይም መጥፎ ናቸው ብለን የምናስባቸውን ነገሮችንስ ከምን ተነሥተን ነው የምንወስነው ? ርእዮታችን ምን ምን ዕሴቶችን በውስጡ ይይዛል ? ከእነዚህስ ዕሴቶች በመሠረታዊነት ለእኛ ወሳኝ እና መሠረታዊ ናቸው ብለን የምናስባቸው የትኞቹ ናቸው ? በዚህ መነጽር ነው ከምናነበው ታሪክ ውስጥ ለየትኞቹ ሁነቶች እና ሰዎች ዋጋ መስጠት እንዳለብን የምንለየው ።

ከዚያ ደግሞ በምናጠናው ወቅት የምናጠናው ኅብረተሰብ ዓለምን እና ራሱን በምን ዓይነት መነጽር ይመለከት እንደነበረም ማወቅ ይጠበቅብናል ። አለዚያ የምናጠናቸውን ሰዎችም ሆነ ሁነቶች በዐውዳቸው መረዳት አንችልም ። ይልቁንም የእኛን መነጽር ብቻ አጥልቀን የእነሱን መረዳት እና አመክንዮ ሳንገነዘብ የሚኖረን ንባብም ሆነ ከንባባችን ተነሥተን የምናደርገው አቅርቦት የሰዎቹንም ሆነ የሁነቶቹን ባሕርይ ያልተረዳ ስለሆነ ምንም ካለመረዳት የተሻለ አይደለም ። እንዲያውም ምንም አለመረዳት ሊሻል ይችላል ።

የራሳችንን ርእዮተ ዓለም ብቻ ይዘን ያለፈውን ማኅበረ ሰብእ ማሞገስም ማኮሰስም እግር ኳስን በቅርጫት ኳስ ሕግ ለመዳኘት እንደ መሞከር ይሆናል ። ትርጉም ሊሰጥ አይችልም ። በጣም ፕሮፌሽናል የሆኑት ተጫዋቾች እጅግ ቀሽሞች ይመስሉናል ። ጥቂት የማገናዘብ አቅም እና ፍላጎት ካለን ፥ ካሰብነው ሌላ ነገር እየተከናወነ እንደሆነ መረዳት አያቅተንም ። ግን ብዙ ጊዜ በራሳችን ከልክ በላይ በመተማመናችን እና እኛ ከምንሄደው ሌላ መንገድ ፣ እኛ ከምናውቀው ሌላ ጨዋታ ፣ እኛ ከወሰንነው ሌላ ግብ ያለ ስለማይመስለን ፣ እግር ኳስ ተጫዋቾቹ ቀሽም ናቸው ብሎ መደምደሙ ይቀለናል ።

የነገሩን ምንነት አጣርተን ጨዋታው የተለየ መሆኑን ከተረዳን በኋላ "አይ ቅርጫት ኳስ የተሻለ ጨዋታ ነው" ብሎ መደምደም ይቻላል ። ይህ ቢያንስ ለንግግርም ፣ ለሙከራም ፣ ለክርክርም የሚመች አቋም ነው ። የሆነ ሆኖ ምሳሌ ምስጢር አይጠነቅቅምና ጨዋታ የግል

ምርጫ እና የመዝናናት ጉዳይ እንደሆነ ሁሉ ዋናው ጉዳያችንንም በዚህ መንገድ ተረድቼው እንደሆነ እንዳይወሰድብኝ ።

በቀደመው ዘመን የኖሩ ሰዎች ከእኛ የተለየ ምርጫ እና መረዳት በኖራቸው ጊዜ ፣ የእኛን ያህል ዕውቀት እና መረዳት ስለሌላቸው ነው ብሎ ማሰብም ሌላው ፈተና ነው ። እውነት ነው በአንዳንድ ጉዳዮች እና ከእነሱ የተሻለ ዕውቀት እና መረዳት ይኖረን ይሆናል ። ነገር ግን በብዙ ነገሮች ፥ በተለይ ደግሞ መሠረታዊ በሆኑ የሕይወት ምርጫዎች እና ልማዶች ቀድመን የበላይነት እንዳለን ማሰቡ ዕቡይነት ነው ። ነገር ግን ይህ ዓይነቱ አካሄድ በዘመናዊው የትምህርት ሥርዓት በጣም የተለመደ ሆኗል ። እንዳስተዋልሁት ከሆነ ብዙ ‘አሉ’ የተባሉ ምሁራን ፥ በተለይ የበለጠ ክብር ባገኙ ቁጥር ፥ ይህን የማድረግ ዝንባሌያቸው እየጨመረ ይመጣል ።

በመጨረሻ ድምዳሜ ላይ ስንደርስ ግን ፥ ማለትም ያ የምናጠናው ዘመን ለእኛ ስላለው ጠቃሚነት ፣ ትምህርት ፣ ልንመስለው ወይም ልንሸሸው የምንፈልግ ስለመሆኑ ስንወስን ፥ ከራሳችን ርእዮት አንጻር ነው ልንወስን የምንችለው ። ርእዮታችን ከሚያቅፋቸው ዕሴቶች ደግሞ የተወሰኑት ከሌሎቹ ይልቅ መሠረታዊ መሆናቸው የግድ ነው ። ነገር ግን ምንም እንኳን ዋናው ፍርድ እነዚህ ዕሴቶች ላይ ቢመሠረትም ፥ ከዚያ በዘለል ያሉ ዕሴቶችን እና ሌሎች ጉዳዮችንም መመልከት አስፈላጊ ነው ። ለምሳሌ አንድ የማኅበረ ሰብእ ውቅር በመሠረታዊነት (ከእኛ ዕሴቶች አንጻር) የተዛባ እና ሊመስሉት የማይገባ ነው ብለን ብንደመድም - ነገር ግን እኛ ትክክለኛ መሠረት አለው ብለን የምናስበው ውቅር ላይ ተወስዶ ሊገባ እና ሊጠቅም የሚችሉ ነገሮች ልናገኝበት እንችላለን ። በተመሳሳይ ጥሩ መሠረት ያለውም ውቅር ፥ ውቅሩ ሳይጎዳ ሊወገዱ የሚችሉ ረብሕ የሌላቸው ፣ ምናልባትም ባሉበት ከተተዉ የውቅሩን ህልውና አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ አካላት ሊኖሩት ይችላሉ ።

ነገሩን እንዲህ ውስብስብነቱን በሚመጥን ደረጃ ስናጤነው ልዩነቶቻችንን በደንብ ለመረዳት እና አግባብ ያለው ተዋሥኦ ለማካሔድ ይመቻል ። ታሪክም ድምፅ የሌላቸው ተዋንያን ነጭ እና ጥቁር ብቻ ለብሰው የሚራወጡበት ሳይሆን ፥ ብዙ መልኮች እና ብዙ ቀለሞች የሚታዩበት ፥ የድጋፍ እና የተቃውሞ ድምፆችን ብቻ ከማስተናገድ የሚሻገር ልዩ ልዩ ሐሳቦችን እና ስሜቶችን የሚያጭር ግሩም መድረክ ይሆናል ። ሊሆንም ይገባል ። ሕይወት እንዲያ ናትና ፥ ታሪክ ደግሞ ሕይወት ነውና ።

## ፩

አንዳንዴ ብያኔዎቻችን ከመለያየታቸው የተነሣ ሳንግባባ የተግባባንባቸው የሚመስሉን ጉዳዮች አሉ ። ከእነዚህ ጉዳዮች አንዱ እና እዚህ ጋ ላነሣው የምወደው የታላቅነት ፅንሰ ሐሳብ ነው ። ብዙ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያን የሚያጠኑ ሰዎች ‘ታላቅ ሀገር’ የነበረች መሆኗን ያምናሉ ። ይህ አባባል አንድ የሚያመለክተው ነገር አለ ፤ የተባለው ታላቅነት ቀድሞ የነበረን ፥ አሁን ግን የሌለን ፣ ያጣነው ነው ማለት ነው ። ስለዚህ መጠየቅ አለብን ፤ አሁን ያጣነው ፥ በነበረን ጊዜ ግን ታላቅ ያደረገን ያ ነገር ምንድን ነበር ? የተለያዩ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ የተለያየ መልስ ነው ያላቸው ።

(እርግጥ ነው ይህ ታላቅነት ጨርሶ የማይታያቸውም ሰዎች አይጠፉም ፥ እንደ ጓድ ተስፋዬ መኮንን ለምሳሌ ። ነገር ግን እነሱን እና የነሱን አመክንዮ ለጊዜው ወደ ጎን እንተዋቸው (ዋጋ ስለሌላቸው ሳይሆን ቦታው ስላልሆነ) እና ‘ታላቅነቱ’ በሚታያቸው ሰዎች መካከል ያለውን የአመክንዮ ልዩነት ማስታረቅም ባይሆንልን ለመመርመር እንሞክር ።)

ጉዳዩን ላነሣው የፈለግሁት ቀድመን ያነሣነውን ጥያቄ ለመመለስ ያስችለናል ብዬ ስለማስብ ነው ። ‘የቀደመውን ዘመን እንዴት ነው የምንመለከተው ? እንደ መሠረት ልንጠቀምበት የምንችለው ታሪክ ነው ? ወይስ ምናልባት አንዳንድ ነገሮችን ለጌጥ ያህል ወስደን ወደ ጎን የምንተወው ነው ?’ ‘የጨለማ ዘመን ነበር ? ወይስ ደግ ዘመን ?’ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይህን ጉዳይ ማጥራት አለብን ። ምክንያቱም ከላይ እንዳልነው ያለፈው ዘመን ዛሬ ያለውን ሚና የምንወስነው በርእዮታችን ላይ ተመሥርተን ነው ። ይህ የታላቅነት ፅንሰ ሐሳብ ደግሞ ርእዮታችንን ፥ ይልቁንም ያሉንን የርእዮት ልዩነቶች ፥ በደንብ ሊያሳይ የሚችል አንኳር ጉዳይ ነው ።

እኔ እዚህ ጉዳይ ላይ ያሉት መረዳቶች በሦስት ሊከፈሉ የሚችሉ ይመስለኛል ፤ ታሪካችን የኋላቀርነት ብቻ ነው የሚለው መረዳት ሲቀር ።

የመጀመሪያው የታላቅነት መረዳት ኢትዮጵያውያን ለሌሎች ሳንገዛ ፣ ጠላቶቻችንን ሁሉ በጦር ሜዳ ድባቅ እየመታን ፣ ነጻነታችንን ጠብቀን ከጥንት እስከ አሁን በመዝለቃችን የሚገለጥ ነው የሚለው ነው ። በእኔ ንባብ መሠረት ፥ ይህ በዋናነት በንጉሡ ዘመን በነበረው

“ዘመናዊ” የትምህርት ሥርዓት በኩል ተዋውቆ ፣ በኋላ ደግሞ በደርግ ዘመን የሀገሪቱን ማንነት እና የአንድነቷን ምክንያት ከዘውዱ እና ፊውዳላዊ ከተባለው ሥርዓት ለማላቀቅ እንዲሁም ከኦርቶዶክሳዊ ይልቅ secular በሆነ ትረካ ላይ ለመመሥረት ጥረት ሲደረግ ይበልጥ እየዳበረ እና እየሠረጸ የሄደ መረዳት ነው ።

> “ኢትዮጵያ የጥንት ገናና ሥልጣኔ ባለቤት የሆነች እና ለብዙ ሺህ ዓመታት ሳይቋረጥ የቆየ ነጻ መንግሥት ያላት ሀገር ናት ።
>
> “የኢትዮጵያ መንግሥት በሐውርታዊ ሆኖ የኖረ ነው ። የአገሪቱ ብሔረሰቦችና ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች በባህል መወራረስ ፡ በፈለሳ ፡ በንግድና በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ፥ በሰላምና በጦርነት ጊዜ ተሣሥረው የኖሩ ናቸው ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ረጅም የነጻነት ታሪክ የብሔረሰቦቿ የጋራ ህልውናና የጋራ የትግል ታሪክ ነው ።
>
> “ኢትዮጵያ የአፍሪካ ፡ የእስያና የአውሮፓ አህጉሮች መገናኛ በሆነ ስትራቴጂያዊ አካባቢ የምትገኝ ፥ የታላላቅ ወንዞች መነሻና ለም አገር በመሆኗ ባዕዳን በወረራ ሊይዟትና ሊከፋፍሏት ሞክረዋል ። በተለይም ካፒታሊዝም በምዕራብ አውሮፓ ካቆጠቆጠበት ከ፲፮ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ቅኝ ገዥዎች በቁጥጥራቸው ሥር ሊያደርጓት ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገዋል ። ይሁን እንጂ ወራሪዎች እኛ ቅኝ ገዥዎች በየዘመኑ የሠነዘሩትን ጥቃትና አገሪቱን ለመያዝ ያደረጉትን ሙከራ ሁሉ ሕዝቡ በቆራጥነት እየመከተ ድል ሲያደርግ ኖሯል ። ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ደረጃ በተሸጋገረበትና ኢምፔሪያሊስቶች ዓለምን ለመቀራመት በተነሣሡበት ወቅትም አልተበገረችም ። ይልቁንም በ፲፰፻፹፰ በጊዜው ዘመናዊ በነበረው የቅኝ ገዥ ጦር ላይ የተቀዳጀችው ታላቁ የዓድዋ ድል በዓለም ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ልዩ የነጻነት ተጋድሎን ክብርና አኩሪ ታሪክ አጎናጽፏታል ። በአርበኞቿ የአምስቱ ዓመት ትግልና መስዋዕትነትም በፋሺዝም ወረራ ላይ ድልን በመቀዳጀት በታሪክ ተረጋግጦ የቆየውን የነጻነት ዓርማዋን ከማውለብለብ የሚገታት ኃይል አለመኖሩን እንደገና አስመስክራለች ።
>
> “የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጠላት የሚሠነዘርበትን ጥቃት እየመከተና ተደጋጋሚ ድሎችን እየተቀዳጀ አልደፈር ባይነቱንና ለነጻነት ቀናኢነቱን እያረጋገጠ አገሩን አስከብሮ ኖሯል ።
>
> “በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ በዚህ የረጅም ዘመን ታሪኩ በልዩ ልዩ ማኀበረ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች ውስጥ የተጓዘ ሲሆን በዚሁ ሂደት ላይ መራራ የመደብ ጭቆናና የብዝበዛ ጊዜ አሳልፏል ። በተለይም በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ የነበረው ግንኙነት ገበሬውን አስከፊ በሆነ የጭቆና ቀንበር ሥር ጥሎት እንደነበር ይታወቃል ። ፊውዳሎች በየጊዜው በመካከላቸው በሚያነሡት ግጭት እና ጦርነትም ሕዝቡ ሲማገድ ፥ የጉልበቱ ውጤት የሆነውን ምርት በልዩ ልዩ መንገድ ሲቀማ ፥ ረሃብ ፥ በሽታና ዕልቂት ሲፈራረቁበት ኖሯል ።”[22]

ይህ መረዳት ዛሬም ቢሆን በብዙ ሰዎች ዘንድ ያለ ነው ። በመንግሥት ባይደገፍም በተለይ በሥነ ጽሑፍ እና በሙዚቃ ሥራዎች ውስጥ የሚታይ ነው ። የዚህ መረዳት ዋናው ችግር ወይም ጉድለት ብዬ የማስበው ሁለት ዋና ዋና ጥያቄዎችን የማያነሣ መሆኑ ነው ። አንደኛው የእነዚህ ድሎች እና የጀግንነት ሥራዎች ዓላማ ምንድነው የሚለው ነው ። ለእነዚህ ድሎች የተከፈለው ዋጋ ለምን ተከፈለ ? እውነት ነው ነጻነታችን ተጠብቋል ፤ ግን ነጻነታችንስ ለምንድነው ? ከምንስ ነው ?

ቀደም ብለን ከጠቀስናቸው ታሪኮች እንደምንረዳው እና ሕገ መንግሥቱም እንደሚያሰምርበት - ሕዝቡ ቀላል ኑሮ የሚኖር አልነበረም ። እነዚህ ድሎች ደግሞ የተገኙት ፥ ይህ ኑሮ የከበደበት ሕዝብ በነገሥት ፣ በመሳፍንት እና በመኳንንት እየተመራ በከፈለው መስዋዕትነት ነው ። ከነበረው ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑት መሪዎችስ ለራሳቸው ሲሉ ይዘምታሉ ፣ ይሞታሉ ። ተራው ሕዝብ ግን ለምን ብሎ ቤቱን እና እርሻውን ትቶ ፣ በረኃብ እና በጥም ለወራት እየተሠቃየ አንዲት ሕይወቱን ለመስጠት ይዘምታል ? ምናልባት እንደ አንዳንዶች አባባል “ከባዕድ ጨቋኝ የሀገሬ ጨቋኝ ይሻለኛል” ብሎ ነውን ?

[22] *የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት* (1980) ፣ ገጽ 6-7
*ቃለአብ ታደሰ ፣ ሕገ መንግሥት በኢትዮጵያ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኤፌዲሪ ፣* (ሜጋ አሳታሚ እና ማከፋፈያ ፣ 2011) ፣ 229

ይዋጥላችኋል ? እኔ ይህ ዓይነቱ "ትንታኔ" በንቀት የተሞላ ሆኖ ነው የሚታየኝ ። ቅድም ያነሣነው የተቃለለ መረዳት ማሳያ ነው ። የቀደሙን ሰዎች እንደኛ "ዘመናዊ" ዕውቀት ባይኖራቸው እንኳን ፥ መጨቆናቸውን እንኳን በቅጡ የማይረዱ ናቸው ? በጣሊያን ቅኝ ገዢዎች እና በኢትዮጵያ ነገሥት እና መሳፍንት መካከል ያለው ልዩነት የውስጥ እና የውጭ መሆናቸው ነው ?

ተራው ሕዝብ ፥ ገበሬው ሥርዓቱን የኔ አይለውም ? ሥርዓቱስ የኢኮኖሚያዊ ጭቆና እና የሥልጣን ሽሚያ መሣሪያ እንጂ ሌሎች ገጾች ያልነበሩት ነው ? ቀድሞስ ዋናው ቁም ነገር ሀብቱ እና ሥልጣኑ ነበር ?

በኢትዮጵያ ታሪክ በጣም ጉጉት ከሚያጭሩብኝ እና በቅጡ አልተወሱም ፣ በታሪክ ተዋሥኦው ውስጥ በቂ ቦታ አልተሰጣቸውም ፣ በሕዝቡም አእምሮ ውስጥ እንደሚገባ አልተቀረጹም ብዬ ከማስባቸው ምዕራፎች መካከል በሱስንዮስ ዘመን የነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት ነው ። ምናልባትም በኢትዮጵያ ታሪክ አብዮት የሚባል ስም የሚገባው ሁነት ካለ ይህ ይመስለኛል ።

ይህ አጋጣሚ "አይጠየቄ እና አይከሰሴ" ስለመሆኑ ደጋግመን የምንሰማው ዘውድ ፣ የሀገሪቱን ሃይማኖት ለመለወጥ በሞከረ ጊዜ እጅግ ከባድ ተቃውሞ እና አመፅ ገጥሞት ለአሥር ዓመታት የእርስ በእርስ ጦርነት የተካሔደበት ነው ። ያም ጦርነት የተጠናቀቀው አፄ ሱስንዮስ ዙፋናቸውን ለቅቀው የቀደመው ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት እንዲመለስ ለማወጅ ሲገደዱ ነው ።[23]

ሕገ መንግሥቱ እንደሚለው "ፊውዳሎች በየጊዜው በመካከላቸው በሚያነሡት ግጭት እና ጦርነት ሲማገድ ፥ የጉልበቱ ውጤት የሆነውን ምርት በልዩ ልዩ መንገድ ሲቀማ ፥ ረኃብ ፥ በሽታና እልቂት ሲፈራረቁበት" የኖረው ሕዝብ በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ እምቢ ሳይል ፣ ሳይነሣ ፣ ሥርዓቱን ሳይገረስስ የቀረው ለምንድነው ? (የ1966ቱም ዓብዮት ቢሆን የገበሬ ወይም የብዙኃን አብዮት እንዳልሆነ ልብ ይሏል።)

ቅኝ ገዢን ተባብሮ ድል የመታ ግን ደግሞ የራሱ ንጉሥ ነገሥትም ሥርዓቱን እና ሃይማኖቱን ሊለውጡበት በሞከሩ ጊዜ መንበር እስከማስለቀቅ የተነሣባቸው ሕዝብ ፣ የሕይወቱ ብቸኛ ወይም ዋና ይዘት ጭቆና እንዳልሆነ ግልጽ ይመስለኛል ። የነበረው ሥርዓት ብዙ ኢፍትሐዊ ገጾች እንደነበሩት ባይካድም ፥ ሕዝቡ የኔ ብሎ የተቀበላቸው እና ለዘመናት የጠበቃቸው ፣ ለመጠበቃቸውም ብዙ ዋጋ የከፈለላቸው ነገሮች በዚያው ሥርዓት ውስጥ እንደነበሩም አለማየት አይቻልም ። ስለዚህ ለታላቅነት ምንጭ ተደርጎ የተጠቀሰው ድል አድራጊነት እና አልበገር ባይነት ፣ የተጠበቀው ነጻነት እና የተከፈለው ዋጋ ከተከፈለለት ነገር ተለይቶ ትርጉም ሊኖረው ይችላል ? የድሉን ዓላማ ረስተን ስለ ድሉ ብቻ መኩራት አንድን ነገር ለመግዛት ውድ ዋጋ ከከፈልን በኋላ የገዛነውን ንብረት ሜዳ ላይ ጥለን ዋጋ ስለመክፈላችን መኩራት አይሆንብንም ?

ምናልባት ድሉ ብቻውን የሚያኮራ ቢሆን እንኳን ፣ እኛ የመኩራት ወይም ድሉን የእኛ ብለን የመጥራት መብት ያለን አይመስለኝም ። ምክንያቱም ድሎቹን ያስገኙት አባቶቻችን እንጂ እኛ አይደለንምና ። አባቶቻችን ዋጋ የከፈሉለትን ዓላማ የጠበቅን እና ይዘን የተገኘን ፣ የተጋራናቸው ቢሆን የእነሱ ድል ከእኛ ጋር የሚገናኝበት መስመር ይኖረዋል ። ነገር ግን እነሱ ለመጠበቅ እና ለእኛ ለማቆየት ዋጋ የከፈሉለትን ነገር መጠበቅ ሳንችል ወይም ሳንፈልግ ቀርተን ከተውነው በኋላ ስለ ድላቸው ማውራት ምን ትርጉም ይኖረዋል ?

ሌላው ነጥብ ይህ ድል እና ጀግንነት ለምን ከእኛ ዘንድ ተገኘ የሚለው ነው ። በተፈጥሮ እና በዘር ከሌሎች ስለምንሻል ነው ? ወይስ በቴክኖሎጂ ከጠላቶቻችን ልቀን ስለተገኘን ነው ? ወይስ "የታሪክ አጋጣሚ" ነው ?

በእኛ ታሪክ እንደሆነው ሁሉ አንድ ማኅበረ ሰብእ ሥርዓት ሠርቶ ፣ ባህል አዳብሮ ፣ በዙሪያው ያለው ዓለም በብዙ መልኩ ሲለወጥ እና ሲገለባበጥ በዚህ ሁሉ ወጀብ ጨርሶ ሳይናወጥ እና ሳይፈርስ ህልውናውን ጠብቆ ለረዥም ዘመናት ለመጽናት ጥሩ መሠረት እና ጥብቅ ሥሪት ያስፈልገዋል ። በተለይ ደግሞ ከላይ እንደተስማማነው የማኅበረሰቡ ሥርዓት ራሱ በውስጡ ትልልቅ ችግሮች ያሉበት ሲሆን ደግሞ እነዚህ በመዋቅሩ ውስጥ ያሉት ስንጥቆች እና ችግሮች ከውስጥ ሳያፈርሱት ሊቆዩ የሚችሉት እነዚህን ውስጣዊ ችግሮች ሳይቀር ተቋቁመው ማኅበረሰቡን በቆመበት ሊያስቀጥሉ የሚችሉ ጠንካራ መሠረት እና ጽኑዕ ዐምዶች ያሉት እንደሆነ ነው ። በዚህ መሠረት ፥ የኢትዮጵያ ማህበረ ሰብእ ምን ያህል በችግሮች እና በኢፍትሐዊ አሠራሮች ተተብትቦ እንደኖረ

---

[23] Mordecai Abir, *Ethiopia and the Red Sea, The Rise and Decline of the Solomonic Dynasty and Muslim–European Rivalry in the Region* (Frank Cass and Co. Ltd., 1980) p. 211-226

ስንናገር ፣ ይህ ማኅበረ ሰብእ ለረዥም ጊዜ ህልውናውን እና ማንነቱን ጠብቆ መቆየት መቻሉ ሀቅ ስለሆነ ፥ በማኅበረሰቡ ውስጥ የነበረውን በደል የሚሻገሩ በጎ ኅብረተሰባዊ ግንኙነቶች ፣ የነበሩትን መጥፎ ልማዶች የሚያርቁ ወይም ተጽዕኖአቸውን የሚገድቡ ዕሴቶች ፣ ከረኃቡ እና ከሰቆቃው ሁሉ የሚያጽናና እና የሚያበረታ የሕይወት ትርጉም በማኅበረሰቡ ውስጥ የነበሩ መሆኑንም ነው እየተናገርን ያለነው ።

ስለዚህ አልበገር ባይነቱ እና ድል አድራጊነቱ የኅብረታዊ አነዋወሩ ፣ የዕሴቶቹ እና የማንነት መረዳቱ ውጤቶች መሆናቸውን ማወቅ ይኖርብናል ። ስለዚህ በድል መኩራታችን እንዲህ ለድሎቻችን ምንጮች የሆኑትን መሠረቶች የጨመረ ካልሆነ ትርጉም አይኖረውም ።

ሌላኛው የታላቅነት መረዳት በልዩ ልዩ ዘመን እና አጋጣሚዎች የተሠሩ ሕንፃዎች ፣ ሐውልቶች ፣ ለዘመኑ ሥልጡን የነበሩ የጽሑፍ ፣ የእርሻ ፣ የፖለቲካ ፣ የዲፕሎማሲ እና ሌሎች ጥበቦች የነበሩን እና ያሉን በመሆኑ ይገለጣል የሚል ነው ። የአክሱም ሐውልት ፣ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ፣ የጎንደር ቤተ መንግሥት ፣ የሐረር ግንብ ፣ የኮንሶ እርከን ወዘተርፈ ስለሀገራችን ታላቅነት ስናስብ እና ስንናገር ቀድመው ወደ አእምሮኣችን የሚመጡ ነገሮች ናቸው ። አንዳንዴ በፉክክር መንፈስ ሆነን አሁን "ታላላቅ" ከሆኑት ሀገራት ቀድመን ስለፈጸምናቸው እና ከእነሱ ፈጥነን ስለተቀበልናቸው ነገሮች የምንኮራበት ጊዜ አለ ። ከአፍሪካ ቀዳሚ እና ብቸኛ መሆን የዘወትር መኩራሪያችን እና ጸሎታችን ነው ።

አንዳንዶቹ ነገሮች ፣ እውነት ነው የሚያስደንቁ ናቸው ፥ ጥርጥር የለውም ። አንዳንዶቹ ደግሞ አይደሉም - በተለይ በፉክክር መንፈስ የሚጠቀሱቱ ። ነገር ግን ቀደም ብለን ባነሣነው መረዳት መሠረት ፥ እነዚህም ነገሮች የጥቂቶች መጠቀሚያ ሆነው የተራው ሕዝብ ሕይወት ግን በሚባለው መጠን ጨለማ ከነበረ ፥ የእነዚህ ነገሮች ዋጋ ምን ይሆናል ? ወዲያውስ አንዳንዶቹ ነገሮች በተራው ሕዝብ ጭቆና እና ብዝበዛ ለነገሥቱ ፣ ለመሳፍንቱ እና ለመኳንንቱ የተገኙ ፍሬዎች ናቸው ሊባልስ አይችልም ? የሚሉም ይኖራሉ ። ያን ጭቆና እና ብዝበዛ ከእነዚህ አኩሪ ሥራዎች ጎን ብንመዝናቸው የቱ ሚዛን ይደፋል ?

እንደ ሕገ መንግሥቱ ነገረ ጭቆናን የሰው ልጅ ታሪክ ዐቢይ ጉዳይ አድርጎ ለሚነሣ አካል ፣ ያልናቸው ሥራዎች ሁሉ ዋጋ እንደማይኖራቸው ግልጽ ነው ። እንዲያውም የጭቆና ሐውልቶች ተደርገው ሊቆጠሩም ይችላሉ ። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ልንኮራባቸው እንድንችል ከጭቆና ይልቅ የሚወክሉት መልካም ነገር ሊኖር ይገባል ። "የገዢው መደብ" ጥጋብ እንደሠራቸው የባቢሎን ግንቦች ሳይሆን መላው ሕዝቡ የኔ የሚላቸው እና በጎ የሆኑትን የሕይወቱን ገጾች የሚወክሉለት ፥ መወከል ብቻም ሳይሆን የሚያገለግሉት ፥ ሕይወቱ ላይ ዕሴት የሚጨምሩለት ክንውኖች መሆን አለባቸው ።

ስለዚህ የዚህ መረዳት ችግር ፥ ልክ እንደ ድሎቻችን ሁሉ ከብዙዎቹ የታላቅነት መገለጫ አድርገን ከምንወስዳቸው ሥራዎች ጀርባ ያለውን ምክንያት ያልመረመረ እና ለዚያ ዋጋ ያልሠጠ አረዳድ መሆኑ ነው ። የላሊበላን ሕንጻት ከሕንጻው ውበት አንጻር ብቻ የምናደንቀው ከሆነ የሠሩትን ሰዎች አእምሮ አልተረዳነውም ማለት ነው ። ይልቁንም መረዳት ያለብን ተማሪው ከአባቱ እና እናቱ ቤት ጠፍቶ (ምናልባትም ጨርሶ ላይመለስ) መንገዱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጥቶ ፥ ረኃቡን እና ጥሙን ፣ መታረዙን እና ሌላውን ሁሉ ሥቃይ ችሎ 20 እና 30 ዓመታትን በየሀገሩ እየዞረ እንደመማሩ ፥ ገበሬው ከምርቱ መሃል ተጠንቅቆ ለቁርባን የሚሆነውን ስንዴ መርጦ ፥ ተርቦም እንኳን ቢሆን ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደማምጣቱ ፥ መነኮሳቱ እና ሊቃውንቱ ቆዳ ሰብስበው ፣ ብራና ፍቀው ፣ ቀለም በጥብጠው ፣ ረዥም ጊዜ ደክመው ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደመገልበጣቸው ፥ ክህነትን ያመጡ ዘንድ ተልዕኮ ተቀብለው አገር አቆራርጠው እንደመሔዳቸው ፥ አንዳንዴም ጳጳስ በሀገር ሲጠፋ ግብጽ እና ኢየሩሳሌም ድረስ እንደመጓዛቸው ፥ ይህንም ሲያደርጉ ብዙዎቹ መንገድ ላይ እንደመሞታቸው ወዘተርፈ ነው ። ይህም የአልዓዛር እኅት ማርያም ውዱን ሽቱ በጌታችን ራስ ላይ እንዳፈሰሰችው ፥ ያች መበለትም ያለቻትን ሁለት ዲናር ወደ ሙዳየ ምጽዋቱ እንደጨመረችው ያለ ፥ ያለን ሁሉ ከእግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ እና ከተሰጠን ደግሞ ምርጡን ለእርሱ መልሰን የመስጠት ፣ በሕይወታችን ቤተ ክርስቲያንን ፣ ክርስቶስን ማእከል የማድረግ ፍቅር ነው ። ክፉ ዘመን ሲመጣም ልክ የጥንት ሰማዕታትን መስለው ፣ በግራኝ ዘመንም ሆነ በሱስንዮስ ዘመን ሕይወታቸውን ጭምር መስዋዕት አድርገው የማቀረባቸው ፍቅር ነው ። ይህ ፍቅር ነው ድል ካደረግናቸው ጦርነቶች ፣ ከላሊበላ ሕንጻት ፣ ወይም ከሥነ ጽሑፋችን ፣ ወይም ዛሬ "ቅርስ" ወይም "የቱሪዝም መስሕብ" ብለን ከምንጠራቸው የአባቶች ሥራዎች ጀርባ ያለው ዐቢይ ምስጢር ። ልናከብረው እና ልንጠብቀው የሚገባንም ይህን መሰጠት

ነው እንጂ ዛሬ ለዐይናችን ጎልተው የታዩንን “ቅርሶች” አይደለም ። ቅድም ያልኳቸው ምሳሌዎች በሙሉ በዚህ ዕይታ አንጻር ከላሊበላ ምናልባት ቢበልጡ እንጂ የሚያንሱ አይደሉም ፥ ከሙላት ላይ ሳይሆን ከእጦት ላይ ተሰጥተዋልና ።

## ፭

ሌላው በተለይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስፋት የሚነገረው የታላቅነት መገለጫ ከክብረ ነገሥት ትረካ በመነሣት ፥ ኢትዮጵያ እሥራኤልን ተክታ የእግዚአብሔር ሀገር እንደሆነች ያለው እምነት ነው ። የክብረ ነገሥት ትረካ እና ከዚያ በመነሣት የሚነገሩ ሌሎች ታሪኮች በራሳቸው ሰፊ ውይይት የሚፈልጉ ናቸው ። ግን ከዚህ በመነሣት አለን ስለምንለው መመረጥ እና ታላቅነት ጥቂት ሐሳቦች ላንሣ ።

ምንም እንኳን ከክርስትና አስተምህሮ አንጻር የቃል ኪዳኑ ታቦት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣቷ ኢትዮጵያ እሥራኤልን ተክታ ሀገረ እግዚአብሔር ሆናለች ፤ ኢትዮያውያንም እሥራኤል ዘነፍስ ሆነዋል የሚለው ትረካ እና አረዳድ በደረቁ ከወሰድነው ፥ በተለይ ከነገረ ድኅነት አንጻር ፥ ትክክል ባይሆንም ፥ ግን ጠለቅ ብለን ብንመረምረው ቁም ነገር የያዘ ሆኖ እንደምናገኘው አስባለሁ ።

ይህ የተመረጠ ሀገር እና ሕዝብ የመሆን ነገር በክርስትናው ውስጥ በእኛ ዘንድ ብቻ ሳይሆን ከአምስተኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ በቢዛንታይን ፣ በሮም ፣ በሩሲያ ፣ በአሜሪካ ሳይቀር በተለያየ ቅርጽ የምናገኘው ነው ። አመክንዮውም ልዩ ልዩ ነው ። በእኛ ዘንድ ይህን ለመደገፍ የቀረበው ታሪክ ፥ ታሪካዊ እውነታነቱን ለጊዜው ወደ ጎን ትተን ፥ ከእሥራኤል ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ። የኢትዮጵያን የመንግሥት ታሪክ የዳዊት እና የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት ታሪክ ቅጥያ አድርጎ የሚያቀርብ ነው ። ይህ ግንኙነት - ሕዝባዊ ጉዟችንን እንዴት እንደምንመለከት እና እርምጃችንን እንዴት እንደምንለካ ነጋሪ ነው ።

የእሥራኤልን ሕዝብ እና መንግሥት የተለዩ የሚያደርጋቸው የግዛታቸው ስፋት ፣ የሠራዊታቸው ብዛት ፣ የደረሱበት ቴክኖሎጂ ርቀት ፣ የሕንጻዎቻቸው ማማር እና ግዝፈት አልነበረም ። በዚህ ሁሉ ከእነሱ በፊትም በኋላም ከእነሱ የላቁ ሕዝቦች እና ሀገሮች ነበሩ ። ይልቁንም እነሱን የተለዩ ያደረጋቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ነው ። መውጣት እና መግባታቸው ፣ መራብ እና መጥገባቸው ፣ ድል መንሣት እና መነሣታቸው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በነበራቸው ግንኙነት በኩል የሚታይ ነበር ። ምናልባትም ከስማቸው በመነሣት ለመበየን ብንሞክር ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ያዕቆብ ከመልአኩ ጋር ያደረገውን ትግል ይመስላል ። ከሕግ መውጣታቸው እና እርሱን ማሳዘናቸው አልቀረም ፥ ግን ከእርሱ ርቀው መኖርንም አልፈቀዱም ፤ ሳይባርካቸው ሊለቁት አልወደዱም ። የታላቅነታቸው መዳረሻ ለእግዚአብሔር ፈጽሞ በመታዘዝ የእሱ መሣሪያ መሆን ነበር ። ስለዚህም ታላላቅ ሥራዎቻቸውን ሁሉ ለራሳቸው አይሰጡም ፤ በእነሱ ውስጥ እሱ እንደሠራው ይረዳሉ እንጂ ። ይህንም ከሚከተለው መዝሙር መረዳት እንችላለን ።

> ታላላቅ ነገሥታትን የመታ ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> ብርቱዎችንም ነገሥታት የገደለ ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> የባሳንን ንጉሥ አግን ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> ምድራቸውን ርስት አድርጎ የሰጠ ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> ለባሪያው ለእሥራኤል ርስት ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> እኛን በመዋረዳችን አስቦናልና ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> ከጠላቶቻችንም እጅ አድኖናልና ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> ለሥጋ ሁሉ ምግብን የሚሰጥ ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ፣
> የሰማይን አምላክ አመስግኑ ፡ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ። (መዝ. 135 ፥ 17-26)

ከዚህ መዝሙር እንደምንረዳው እሥራኤላውያን የግል ኑሯቸውን ብቻ ሳይሆን ኅብረታዊ ሕይወታቸውን እና ዕጣ ፈንታቸውን ጭምር ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት መሠረት ነው የሚበይኑት እና የሚረዱት ። ሩሲያዊው ካህን እና የፍልስፍና እንዲሁም የነገረ መለኮት ምሁር ጆርጅስ ፍሎሮቭስኪ ለእሥራኤል የተሰጣቸው ሕግ ሁለንተናዊ መሆኑን እንዲህ ያስረዳሉ ።

> “(ለእሥራኤል የተሰጠው ሕግ) መላውን የሕዝቡን ሕይወት ‘መንፈሳዊውንም’ ፣

> ‘ዓለማዊውንም’ ያቀፈ እና የሚገዛ ነበር ። ምክንያቱም የሰው ልጅ አነዋወር ሙሉ በሙሉ በመለኮታዊ ፈቃድ መመራት ነበረበትና ። ደግሞም ነገሩን በጥልቀት እናጢነው ከተባለ ‘ዓለማዊ’ እና ‘መንፈሳዊ’ የሚለው ክፍፍል ጥልቅ ምርምርን ሊቋቋም የማይችል (ግልብ) ነው ።”[24]

የእኛም አባቶች መረዳት ይህ ይመስለኛል ። የታላቅነት መለኪያቸው በፍጹም ቁስ አካላዊ አልነበረም ። በጦርነት የተገኘ ድል እና ሽንፈት ፣ የዝናብ መምጣት እና መቅረት ፣ ከእርሻ የተገኘ ምርት ፣ የተሠሩ ሕንጻዎች እና ሐውልቶች ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እና ውዴታ አንጻር ነው የሚታዩት ። በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት የሚፈጠሩ ፥ ጥቃቅንም ይሁኑ ግዙፍ ፥ ሁነቶችም እንዲሁ ።

በእርግጥ ምድራዊ ሁነቶችን ሁሉ ከሰማያዊ ፈቃድ እና ውዴታ አንጻር መመልከቱ ከመጠን ያለፈ ነበር ብዬ አስባለሁ ። ይህም የሚሆነው መሠረታዊ ሐሳቡ ላይ ችግር ስላለበት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና ውዴታ መጋፋትን ከመፍራት የተነሣ ፈቃዱን መተላለፍ ይሆናል ብለው የሚያስቡትን ድንበር በእጅጉ አጥብበው ስለሚያሰምሩት ይመስለኛል ። (ዶናልድ ሌቪን ‘innovation (ፈጠራ ፣ ምርምር ወይም ግኝት) እንደ ኃጢአት ይታያል’ ያሉትን እናስታውስ ።)

በተጨማሪም ከላይ ያነሣነውን ራስን ባዶ አድርጎ ለእግዚአብሔር የመስጠት ፍቅር በብዙ መንገድ ኀብረቱ መካከል ሕይወት ዘርቶ ሲሠራ እንመለከተዋለን ፤ ከላይ የጠቀስናቸውን ምሳሌዎች አልረሳችሁም ብዬ አልደግማቸውም ። ግን ሕይወት ዋጋዋን ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ቁርኝት እና የእርሱን ፈቃድ በመፈጸም ውስጥ ታገኝ የነበረ መሆኗ በዚህም ይገለጣል ።

ሌላው ወሳኝ ነጥብ የሚመስለኝ ፥ ያለፍንበት ታሪክ ይህን መረዳት እንዴት እንዳጠናከረው ነው ። እሥራኤላውያን በብቸኝነት ሕግን እና የተስፋውን ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር የተቀበሉ በመሆናቸው ፥ እነርሱ ከሌሎች ሕዝቦች ተለይተው መቀደሳቸውን ያምናሉ ። “ያልተገረዘ” ሁሉ የረከሰ ነው ።

ከላይ እንዳነሣሁት ይህን መሰል አረዳድ በክርስትናው የሚሆን አይደለም ። ያ የእሥራኤላውያን ኀብረት በሐዲስ ኪዳን ምድራዊ በሆነ ዝምድና በተዛመደ ሌላ ሕዝብ የተተካ አይደለም ። የተጠመቁ ሁሉ በተሰበሰቡባት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንጂ ። ስለሆነም ኢትዮጵያ እሥራኤል በነበረችበት መንገድ “የተቀደሰች” ልትሆን አትችልም ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ከኖራት ጀምሮ ለረዥም ዘመን በውስጧ እና በዙሪያዋ የሆነውን ታሪክ ስንመለከት ፥ እሥራኤላውያን በጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ተከበው በመኖራቸው ሕጉን እና ቃል ኪዳኑን የማቆየት ግዴታ እንዳለባቸው ያስቡ እንደነበረ ሁሉ ፥ አባቶቻችንም ይህ ዓይነት ግዴታ እንዳለባቸው ነበር መረዳታቸው ።

ከአራተኛው እና ከአምስተኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ፥ በተለይ ደግሞ ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ፥ ክርስትና የተንሠራፋበት የቢዛንታይን መንግሥት ወደ ኑፋቄ ሲገባ እና እውነተኛው እምነት በኢትዮጵያ እና በተወሰኑ አካባቢዎች ሲወሰን ፥ ከዚያ በኋላ ደግሞ በሰባተኛው ምዕት ዓመት በእስልምና መስፋፋት የተነሣ ፥ ትክክለኛው ክርስትና ቀርቶ ፍንጩ እንኳን በዙሪያዋ ካሉት አካባቢዎች ሲጠፋ ወይም ጥቂት ቁጥር ባላቸው ሰዎች ተወስኖ ሲቀር ፥ ኢትዮጵያውያን ነገሥት እና ሊቃውንት ይህን እውነት ጠብቆ የማቆየቱን ተልዕኮ ለመውሰድ ተገደዱ ።

እውነት ነው ከእሥራኤል ውጪ እግዚአብሔር እንደ ኢዮብ ያሉ ጻድቃንን እንዳገኘ ሁሉ ፥ ከኢትዮጵያ ውጪ ክርስቲያኖች አልነበሩም ወይም ክርስቲያን መሆን አይቻልም ማለት አይደለም ። ነገር ግን እሥራኤላውያን በብዙ በደል ውስጥ ሲያልፉ እና ነቢያትን ሲያሳድዱ እንኳን ለሙሴ በተሰጠው ሕግ አማካይነት የተገለጠው እውነት በኀብረታዊ መልኩ በሌላ ቦታ እንደሌለ ሆኖ ራሱን የገለጠው በእሥራኤል መካከል እንደሆነ ሁሉ ፣ ኦርቶዶክሳዊነትም ያለ መሳደድ እና ያለ መሳቀቅ ፣ ነጻ በሆነ ኀብረት ውስጥ በምልአት የተጠበቀው በኢትዮጵያ እንደሆነ ነበር የአባቶቻችን እምነት ። በሌሎች ቦታዎች ሰው ክርስቲያን ለመሆን ከወንዙ ፍሰት በተቃራኒ መዋኘት

[24] “(The law given to Israel) embraced the whole life of the people, the ‘temporal’ as well as the ‘spiritual’, precisely because the whole life of human existence had to be regulated by the divine precepts. And the division of life into the “temporal” and “spiritual” departments is, stricltly speaking, precarious.” Georges Florovsky, “Revelation and Interpretation” in *Bible, Church, Tradition: An Eastern Orthodox View* (Nordland Publishing Company, 1972), pp. 32-3

ሲኖርበት ፥ እዚህ ግን የወንዙ ፍሰት በራሱ ክርስቲያን እንዲሆን የሚገፋው ነው ። ይህ ነው አባቶቻችን ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር እንደሆነች እንዲያስቡ ያደረጋቸው ። ይህም ነው እንዲህ ያለውን ኅብረት ጠብቀው ለማቆየት ተልእኮ እንዲወስዱ ያደረጋቸው ።

ስለዚህ የታላቅነቱ መረዳት - ይህን ተልዕኮ በመቀበል እና በመወጣት የሚገለጥ ነው ። ሌላው "የሥልጣኔ" ሁኔታ ከዚህ ተልዕኮ ጋር ሲነጻጸር የገለባ ያህልም ዋጋ ሊሰጠው አይችልም ። ቀድሞም አባቶቻችን ቁሳዊ ብልጽግናን እንደ በጎ የሚመለከቱት አይደለም ።

የዚህ ተልዕኮ ትርጉሙ ምንድነው ? የአቅጣጫ ፣ የግብ ጉዳይ ነው ። እንደ ማኅበር ፥ ኢትዮጵያውያን የእግዚአብሔርን ሕግ እና ፈቃድ ፈጽመው ይጠብቃሉ ማለት አይደለም ። ነገር ግን እሱን ግባቸውን አድርገዋልና ጉዟቸው ወደ ትክክለኛው መዳረሻ የሚደረግ ፥ የተከተሉትም መንገድ በመሠረቱ ርቱዕ ነው ማለት ነው እንጂ ። ስለ መዳረሻቸው ግራ የተጋቡ አይደሉም ፤ ወይም መዳረሻቸውን ከራሳቸው ፍላጎት አንጻር የወሰኑ አይደሉም ።

ስለዚህ ጥንታዊ የሆነው የታላቅነት መረዳት "ዘመናዊ" ከሆነው የታላቅነት መረዳት ፥ ማለትም ቀደም ሲል ካየናቸው በድሎቻችን ፣ ወይም በፖለቲካዊ ፣ ዲፕሎማሲያዊ ፣ ኪነ ሕንጻዊ እና ሌሎች ቁሳዊ ስኬቶች ከሚገለጡ የታላቅነት ብያኔዎች ፥ በጣም የተለየ ነው ።

አስቀድሜ እንዳልሁት 'እንደ ማኅበረ ሰብእ ለረዥም ዘመን ያደረግነው ጉዞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና ውዴታ መዳረሻ ያደረገ ነው' ስል ፥ ፍጹም ክርስቲያናዊ ማኅበረ ሰብእ ነበር ለማለት አይደለም ። በተለይ በሁለት ምክንያቶች ብዙ ችግር የነበረበት ማኅበረ ሰብእ ነበር ።

አንደኛ ክርስቲያናዊ ዕሴቶች ራሳቸው በምልዓት እና በሚዛን ዋጋ ተሰጥቷቸው ነበር ለማለት አንችልም ። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ መንሥኤዎች ይኖራሉ ። በጽሑፋችን የመጀመሪያ ክፍሎች እንዳነሣነው ፥ ባህላችን 'ክርስቲያናዊ ነው' ስንል 'ክርስቲያናዊ ብቻ ነው' እያልን አይደለምና ፥ ሌሎችም ባህሉን የሚቀርጹ ነገሮች አሉና ። በዚያ ላይ ዋጋ የተሠጣቸውም ዕሴቶች ራሳቸው ሁልጊዜ ይጠበቁ ነበር ማለት አይደለም ። ይልቁንም በእሥራኤላውያን ታሪክ የምናየው ያልተቋረጠ መውደቅና መነሣት በእኛም ታሪክ ውስጥ የሚታይ ነው ። ቁም ነገሩ ሕጉ ከፊታቸው አለመጥፋቱ ፥ መስፈርትነቱ አለመቅረቱ ነው ። የጽድቅን ጽድቅነት እና የኃጢአትን ኃጢአትነት በተመለከተ ግራ አለመጋባታቸው ፥ ብዥታ ያልነበኛቸው መሆኑ ነው ። እሥራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ ጀምሮ በየጊዜው ጥፋት እየሠሩ ቅጣት ደርሶባቸዋል ። ነገር ግን እግዚአብሔርን ጨርሰው ያስቆጡት ሌሎች አማልክትን ባመለኩ ጊዜ ነበር ። ቅዱስ ዳዊት ራሱ ኦርዮ ላይ በሠራው በደልም ሆነ ሕዝቡን በመቁጠሩ ቅጣትን እና መቅሰፍትን ተቀብሏል ። ግን እንደ ሰሎሞን እና ከሱ በኋላ እንደመጡት ነገሥት እግዚአብሔር ፈጽሞ ያልተቀጣበት ወደ ሌሎች አማልክት ፊቱን በማንኛውም ጊዜ አላዞረም ነበርና ነው ።

ሁለተኛ ደግሞ ፥ ቀደም ሲል እንዳነሣነው ፥ በጣም ብዙ ገደቦችን ሳያስፈልግ ራሱ ላይ ፥ ዕሴቶቹን የማይነኩበት ነገሮች ላይ ሳይቀር ፥ ከመጣሉ የተነሣ ብዙ ማስቀረት ይቻል የነበረ ሥቃይ እና መከራ መድረሱ ነው ። እንዲህ ያለውን ሥቃይና መከራ መግቢያችን ላይ ስላነሣን እዚህ ጋ በድጋሚ ዝርዝር እና ምሳሌ የማቅረቡ ጥቅም አይታየኝም ።

(በተለይ አንዳንድ ዕውቀቶችን እና ግኝቶችን በተመለከተ ከምዕራባውያን የምንማረው ብዙ ነገር እንዳለ አስባለሁ ። ነገር ግን ይህ ከእነሱ አጠቃላይ ትክክለኝነት የተነሣ ሳይሆን ፥ መሳሳታቸው እና ከመንገድ መውጣታቸው ፥ ከዋናው መዳረሻ ውጪ ስላሉት እና እኛ ደግሞ በመንገዳችን ላይ ዞር ዞር ብለን ራሱ መመልከት ባለመፈለጋችን ምክንያት ሳናያቸው ስለቀረናቸው ነገሮች ከእኛ የተሻለ መረዳት እንዲኖራቸው ስላደረገ ይመስለኛል ። ያ ማለት ግን መዳረሻችንን እስከሚያስረሱን ድረስ በእነዚህ ነገሮች ልንማረክ ይገባል ማለት አይደለም ። ይልቁንም ለመንገዳችን የሚጠቅሙን ወይም ቢያንስ የማያሰናክሉን ሆነን ካገኘናቸው ድረስ ልንይዛቸው እንችላለን ። ከመንገዳችን የሚያዘናጉን ከሆኑ ግን ከመተው ውጪ አማራጭ አይኖረንም ። የመኳዛችን ምክንያት መዳረሻችን ነውና ።)

ግን እነዚህን ሁለት ዋና ዋና ችግሮች ስናነሣ ፥ ቀድመን ነገራችንን የመሠረትንበትን ጉዳይ መጣል የለብንም ፤ እንደ ማኅበረ ሰብእ እየሄድን ያለንበት አቅጣጫ እና እንደ መዳረሻ ከፊታችን ያኖርነው ግብ ። የአንድ ማኅበረ ሰብእ ግብ የታላቅነቱ መለኪያ ከሆነ ፥ ይህ ግብ ሳይኖረው ከላይ የጠቀስናቸው እና ሌሎችም ችግሮች ከሌሉበት ማኅበረ ሰብእ ይልቅ (ሊኖር ከቻለ ፣ አይችልም እንጂ) ይህን ግብ ይዞ ግን እንዲህ ዓይነት ችግሮች ያሉበት ማኅበረ ሰብእ የተሻለ ነው ማለት ይሆናል ። "ታላቅነት" ስንል የጸና

የኀልዮ መሠረት ያለው ፣ ባዶ ውግንና ላይ ያልተንጠለጠለ የታላቅነት ብያኔን ማለታችን ከሆነ ይህ መረዳት ብቻ ይመስለኛል ሊያግባባን የሚችለው ። ይህ ብያኔ የማይዋጥልን ከሆነ ደግሞ ወይ ሌላ ዓይነት ብያኔ ማምጣት አለብን ወይ ደግሞ ታሪካችን ፣ ምንም ያህል መልካም ነገሮች በውስጡ ቢኖሩ ፣ በመሠረቱ ግን የጨለማ ነው ብለን መደምደም ይኖርብናል ። ከኦርቶዶክሳዊ ዕይታ አንጻር (ቅድም እንዳልሁት በተለይ ውስጡ ያሉትን ትረካዎች ለጊዜው ወደ ጎን ትተን) ይህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሠረት ያደረገ ማኅበረሰባዊ ግብ ትክክል እንደሆነ አምናለሁ ። ይህን ማመኔ ደግሞ የግል አስተያየቴ እና ምርጫዬ ስለሆነ ሳይሆን ኦርቶዶክሳዊው አስተምህሮ በተረዳሁት መጠን ይህን ስለሚነግረኝ ነው ።

እንግዲያስ እንደ ኦርቶዶክሳውያን ይህን የአባቶችን ግብ እና መዳረሻ የወረስን የመሆን ወይም ያለመሆናችን ጉዳይ ዋና ነገር ነው - ‘የአባቶች ስለሆነ’ ሳይሆን ትክክል ስለሆነ ። ያለዚህ ግብ ኦርቶዶክሳውያን ሆነን መቀጠል አንችልምና ።

## ፮

በመጀመሪያ ወደ አነሣነው ጥያቄ እንመለስ ። በፍጥነት ወደ ምዕራብ የሚገሰግስ ረዥም ባቡር ላይ ተሳፍራችሁ ፥ በቻላችሁት ፍጥነት ወደ ምሥራቅ ብትሮጡ የት ትደርሳላችሁ ?

የዘመናችን ክርስትና እንዲህ ዓይነት ጉዞ ይመስለኛል ። ጉዞው ከአባቶቻችን የወረስነው ነው ። እኛም እየተጓዝን ያለነው የእነሱን ጉዞ ነው (እንላለን) ። መዳረሻችንም ተመሳሳይ ነው (እንላለን) ። ልዩነቱ ፥ እነሱ በእግራቸው መሬት ላይ የተጓዙትን ጉዞ እኛ በእግራችን ባቡር ላይ ወጥተን ነው እየቀጠልነው ነው ያለነው ፥ በተቃራኒ አቅጣጫ ወደ ሌላ መዳረሻ እየተጓዘ ያለ ባቡር ላይ ። እርግጥ ነው ፥ ፊታችንን እና እግራችን ወዴት መዞር እንዳለበት ማወቃችን በራሱ ትልቅ ነገር ነው ። ነገር ግን ባቡር ላይ መሣፈራችንን ካላስታወስን የእግራችን ሩጫ ፋይዳ አይኖረውም ። ጉዞው የእነሱ ጉዞ ፥ መዳረሻውም የእነሱ መዳረሻ ሊሆን አይችልም ።

ባቡር ላይ መሳፈራችንን መርሳት ስል እያጋነንሁ አይደለም ። በዙሪያችን ያለው ማኅበራዊ ሥሪት ፣ ባህልእና መንግሥታዊ የአስተዳደር ፣ የኢኮኖሚ ፣ የሕግ ፣ የሚዲያ መዋቅር እንዲሁም በዚህ መዋቅር አማካይነት የሚተገበሩ ፖሊሲዎች ሕይወታችን ላይ ፣ ክርስትናችን ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳላቸው በተገቢው ልክ ያስተዋልን አይመስለኝም ። ተጽዕኖ ወይም ጫና ብቻ አይደለም - የወሳኝነት ጭምር ሚና ነው ያላቸው ።

ለምንድነው የማናስተውለው ከተባለ ፥ ከባቡሩ ትልቅነት የተነሣ ባቡሩን ራሱን አንመለከተውም ። ምናልባትም ከባቡር ይልቅ የምድራችንን ዙረት እና ሹረት የመሰለ ነው እንቅስቃሴው ፤ መጠኑም እንዲሁ እንደ መሬት የገዘፈ ነው ። እናም ከመፍጠኑ የተነሣ የቆመ ፥ ከመግዘፉም የተነሳ የረጋ የመሰለን ባቡር ላይ ተሳፍረናልና መሄዳችንን አላስተዋልንም ።

አናስተውለውም ማለቴ እንደ ቤተ ክርስቲያን ፣ እንደ ክርስቲያን ማኅበረ ሰብእ ዋና ጉዳያችን ብለን ከምንይዛቸው ነገሮች መካከል ስለማልመለከተው ነው ። ስናስተውለው እንኳን ወይ ነገሩ ምን ያህል ርቀት እንደሚወስደን ባለመረዳት ፥ አሊያም ውሃ ከላይ ወደ ታች እንደሚፈስስ ሁሉ ይህም ጉዞ ተፈጥሯዊ እና ሊቀር የማይችል እንደሆነ በማሰብ ፥ ነገሩን በስፋት እና አሳሳቢ በሆነበት ልክ ጉዳያችን አላደረግነውም ።

ሁኔታችን ግርምቢጥ ነው ። በአንድ በኩል ከላይ በቁንጽል ምንባቦች አጋዥነት ለመቃኘት ከሞከርነው ጥንታዊ ዓለም ርቀን መኖራችንን እናውቃለን ። አካላዊ እና ቁሳዊ ሁኔታችን እንደተሻሻለ እናስባለን ። እንዲሁም እንደ ማኅበረ ሰብእ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፍልስፍናችን እና አደረጃጀታችን እንደተለወጠም አናጣውም ።

በክርስትናችን በኩል ግን ልክ አባቶቻችን ይኖሩ በነበረበት ዘመን እንደምንኖር ነው አኳኋናችን ። ። ከአባቶቻችን በተለየ ዓለም እንደመኖራችን ክርስትናችን ሌሎች ፈተናዎች የገጠሙት መሆኑን የተረዳን አይመስልም ። ቁሳዊ ሁኔታችን መለወጡም ሆነ አስተሳሰባችን እና አደረጃጀታችን “መሠልጠኑ” ከክርስትናችን ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው ነው የምናስበው ። ማኅበራዊ ዓውዱ ፈጽሞ መለወጡ ለክርስቲያኖች የቤት ሥራ የሰጠን መሆኑን የተገነዘብን አይመስልም ።

ይልቁንም ክርስትናችንን ኅብረታዊ ሳይሆን ግላዊ አድርገን በመረዳት ፥ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን መላውን የሕይወታችንን ክፍል የመቀደስ እና የማደስ ሚና ያላት ሳይሆን በተወሰነ ጊዜ ፣ ቦታ እና በተወሰኑ የሕይወታችን ክፍሎች ላይ ብቻ ሚና ያላት አድርገን በመገደብ ፥ አንድም ቤተ ክርስቲያንን በራሷ መዳረሻ ሳይሆን እኛ ወደ

ፈለግንበት ቦታ መድረሻ መንገድ አድርገን በመመልከት ፥ አንዳንዴም እሷ የፍጹሙ ባለቤት እውነታ ሆና የምትገሥጸን እና የምትወቅሰን ሳትሆን እኛ በሠለጠነ አመለካከታችን የምንተቻት እና የምንገሥጻት እና የምናርማት አድርገን በማሰብ መጋፈጥ ያሉብንን ጥያቄዎች እንሸሻቸዋለን ።

ግን መጋፈጥ ያሉብን ብዙ ጥያቄዎች አሉ ። ለምሳሌ ፦ ሥሪቱ ኦርቶዶክሳዊ ስለ መሆኑ በተስማማንበት የጥንት ዓለም ውስጥ እንደማንኖር ገብቶን ከሆነ ፣ አሁን የምንኖርበት ዓለም ሥሪቱ እንዴት ያለ እንደሆነ መጠየቅ ግዴታችን አይሆንም ? በቀደመው እና በእኛ ዘመን መካከል ያለው ልዩነት እንዴት እንደተፈጠረስ ? የዛሬው ዘመን አነዋወርና ኦርቶዶክሳዊነት ያላቸው ግንኙነት ምንድነው ? የዛሬው ባህል እና አነዋወር ምን ያህል በኦርቶዶክሳዊነት የተቀረጸ ነው ? ወይም ቢያንስ ከኦርቶዶክሳዊነት ጋር ስምምነት ያለው ነው ወይስ (በረዥም የጊዜ ሂደት) የሚጠፋፉ ናቸው ? ባህሉ ከኦርቶዶክሳዊነት ተጽዕኖ የራቀ ከሆነ እና ሁለቱ የሚቃረኑ ከሆነ ደግሞ ፥ ለምን እንዲህ ሆነ ? ኦርቶዶክሳውያን በበዙበት እና ለረዥም ዘመን ኦርቶዶክሳዊ ባህል ተገንብቶ የነበረበት ሀገር ላይ እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል ? ኦርቶዶክሳዊነት እና አነዋወራችን ያላቸው ግንኙነት ከተለወጠ ፥ ኦርቶዶክሳዊነት በምእመኑ ሕይወት ውስጥ ያለው ቦታም ጥንት ከነበረበት ተለውጧል ማለት ነው ?

ብዙ እና ከባባድ ጥያቄዎችን መመለስ አለብን ። ሁሉንም በዚህ ጽሑፍ መመለስ ቀርቶ በአግባቡ ማንሣት እንኳን ስለማይቻለኝ በይደር አቆያቸዋለሁ ። ነገር ግን ወደሚቀጥለው ለሐሳባችን (እና ምናልባትም ለሌላ ጽሑፍ) መንደርደሪያ እንዲሆነን አንድ ጥያቄ አንሥቼ ይህን ጽሑፍ ላብቃ ።

ከላይ ስለ ታላቅነት በጻፍሁበት ክፍል የአባቶቻችን ታላቅነት በቁስ አካላዊ ብልጽግና ወይም በወታደራዊ ድሎች ወዘተርፈ የሚገለጥ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ግንኙነት እና በሁሉም የሕይወታቸው ዘርፎች እንደ ግለሰብ (ብቻ) ሳይሆን እንደ ማኅበር ራሳቸውን ለእሱ ፈቃድ ማስገዛትን ዓላማ ፣ ግብ ፣ መዳረሻ ማድረጋቸው መሆኑን ገልጫለሁ ። እኛ ግን ይህን ግባቸውን ፥ እንደ ማኅበር አልወረስንም ባይ ነኝ ። በባቡር ለመመሰል እንደሞከርሁት ሌላ ጉዞ ነው እያደረግን ያለነው ። ይህ እውነታ በብዙ መንገድ የሚታይ ፣ የተገለጠ መሆኑ ቢሰማኝም ግን ይህ አባባሌ የማይዋጥላቸው ሰዎች ቢኖሩም አልገረምም ። ስለዚህ መዳረሻችን መለወጡን እና እንዴት ከቀድሞው መዳረሻችን እንደሚለይ በጥቂቱ ለማሳየት እሞክራለሁ ። ለመሆኑ የት ነው ይህ አዲሱ መዳረሻችን ? እስቲ መልሱን ፍለጋ ወደ ሕገ መንግሥታችን እንሂድ ። የሀገር ፣ የማኅበረ ሰብእ አቅጣጫ የሀገሪቱ የበላይ በሆነው ሕግ ካልተወሰነ በምን ይወሰናል ?

> "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች ፥ ብሔረሰቦች ፥ ሕዝቦች ፦
>
> በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም ፥ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ፥ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን ፥ የራሳችንን እድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን ፥ በነጻ ፍላጎታችን ፥ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረ ሰብዕ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሣት ፤
>
> ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ፥ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሠረታዊ መብቶች መከበራቸው ፥ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ ፥ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን በመሆኑ . . ."[25]

እያለ ይቀጥላል ። የሕገ መንግሥቱ መግቢያ ዓላማ ብሎ ያስቀመጠው ሰላምን ፣ ዲሞክራሲን ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገትን ፣ ነው ። ከዚህ መሀል ማኅበራዊ እድገት የሚለው ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም ፥ ሌላው ግን በድፍኑ ለመረዳት አያዳግትም ። ማኅበረሰቡ መሆን የፈለገው ፥ ሰላማዊ ፣ ዲሞክራሲያዊ እና በኢኮኖሚ ያደገ መሆንን ነው ። ከእነዚህ ውስጥ ሰላም ፥ ሰላምን የአካላዊ ደህንነት መጠበቅ አድርገን እንመልከተውና ፥ ተፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ ስላልሆነ ወደ ጎን እንተወው ። ስለዚህ የተቀሩት ሁለቱ ላይ እናተኩር - ዲሞክራሲ እና የኢኮኖሚ እድገት ። ከዚህ ሌላ ለተፈላጊዎቹ ነገሮች መገኘት አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ነገሮች የግለሰብ እና የብሔሮች መብቶች

---

[25] *ነጋሪት ጋዜጣ ፣ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት* ፣ (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፣ 1987) ፣ ገጽ 2

መከበር ፣ የፆታ እኩልነት እና የባሕሎችና የሃይማኖቶች እኩልነት ናቸው ።

ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደመሆኑ (ሥራ ላይ በሚውልበት ልክ) እነዚህ ግቦች የማኅበረሰባችን መዳረሻዎች ናቸው ። የሚወጡ ሕጎች ፣ የሚቋቋሙ መሥሪያ ቤቶች ፣ የሚቀረጹ ፖሊሲዎች ፣ የሚሰበሰብ ግብር ሁሉ ፣ የሚቀጠሩም ሠራተኞች ሁሉ እነዚህን ግቦች ማሳካት ነው ዓላማቸው ። እኛም ሆንን ልጆቻችን ከሕፃንነታቸው አንሥቶ ከ14 እስከ 20 የሚሆኑ ዓመታትን ትምህርት ቤት ውስጥ ስናሳልፍ ፥ ዓላማው የእነዚህን ግቦች ምንነት እና አስፈላጊነት ተገንዝበን ፥ ለመሳካታቸው አስተዋጽዖ ልናደርግ የምንችልበትን ክህሎት አግኝተን ፣ በመረዳታችን እና በክህሎታችን ልክ እነዚህን ግቦች እናገለግል ዘንድ ነው ። ይህ ማለት ግቦቹ በተፈለገው ልክ ተቀባይነት አግኝተዋል ፣ ወይም ወደ ግቦቹ ለማድረስ የተዘረጉት መንገዶች በጥሩ ሁኔታ ተተልመዋል ፣ ተገንብተዋል ማለት አይደለም ። ግን ዓላማው ያ ነው ።

ሕገ መንግሥቱ ከዚህ ከጠቀስሁት መግቢያ ጀምሮ ብዙ ኢትዮጵያውያን የማይስማሙባቸው ነገሮችን የያዘ ቢሆንም ፥ በጠቅላላው ግን “ዘመናውያን” የሚባሉትን የሰው ልጅ ግቦች የያዘ ነው ። ሕገ መንግሥቱ ለብሔሮች በሰጠው እስከ መገንጠል ድረስ የሚሔድ ሉዓላዊነት ፣ መሬትንም እንዲሁ የግለሰቦች ከማድረግ ይልቅ የሕዝብ (በተግባር የመንግሥት) በማድረጉ በስፋት የሚተች ቢሆንም ፥ ሌሎቹ ያስቀመጣቸው ግቦች ፥ ዲሞክራሲ ፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ የግለሰቦች መብቶች መከበር ፣ የጾታ እኩልነት ፣ የብሔሮች እና የሃይማኖቶች እኩልነት ወዘተርፈ ፥ ሲተቹ ሰምቼ አላውቅም ። ፖለቲካዊም ሆነ ማኅበራዊ በሆኑ ተዋሥኦዎች ውስጥ በጠቅላላው የሚደገፉ ሐሳቦች ናቸው ። ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ቢሆኑ ከላይ የጠቀስኋቸውን የልዩነት ነጥቦች ያነሡ ይሆናል እንጂ ወይም ሕገ መንግሥቱ በአግባቡ ሥራ ላይ አልዋለም የሚል ቅሬታ ይኖራቸዋል እንጂ እነዚህን ሐሳቦች ተቀብለው ከመድገም እና እኛ የተሻለ እናሳካቸዋለን ከማለት ሌላ የሚቃወሟቸው አይደሉም ።

ነገር ግን በዚህች ሀገር ውስጥ እንደሚኖር የክርስቲያን ማኅበር ፣ በእውኑ ኦርቶዶክሳውያን እነዚህን ዕሴቶች መቀበል እንችላለን ? እነዚህን ዕሴቶች ከሁሉም ሌሎች ዕሴቶች በላይ ሰቅለን የማኅበረ ሰብአችን መዳረሻ እንዲሆኑ ልንፈቅድ እንችላለን ? እኛ በሥራችን እና በግብራችን ልናገለግላቸው ፣ ልጆቻችንም እንዲማሯቸውና እንዲቀረጹባቸው መፍቀድ እንችላለን ? ያን ብናደርግ (ስናደርግ) ክርስትናችን ካስቀመጠልን መዳረሻ ፈቀቅ ለማለት አንገደድም ? እነዚህን ግቦች በጥሩ ሁኔታ አሳክተዋል በሚባሉት ሀገሮች ውስጥ እንዳለው ያለ ማኅበረ ሰብእ በእኛ ዘንድ እንዲኖር እንፈቅዳለን ? በእነርሱ ዘንድ እንደሆነው እነዚህ ግቦች የበለጠ በተሳኩ ቁጥር ክርስትና (ኑፋቄም እንኳን ቢሆን) እየከሰመ መምጣቱ የሥልጣኔው ተፈጥሯዊ ባሕርይ ከሆነ ፥ እኛም በተመሳሳይ መንገድ ለመሔድ እንወዳለን ?

መልሱን ለሐሳባችን እና ለሌላ ጽሑፍ ላቆየው ።[26]

[26] (ምናልባት ስለ ታሪክ እና ስለ ታላቅነት ያነሣኋቸው ነጥቦች ከሀገር እና ከመንግሥት ጋር ስለሚያያዙ እንዲሁም አሁን ሕገ መንግሥቱን ስለ ጠቀስሁ ክርስቲያናዊ መንግሥት ከሌለን ክርስቲያኖች ሆነን ልንኖር አንችልም እያልሁ ሊመስል እንደሚችል እገነዘባለሁ ። ግን አይደለም ። ይህን የምለው ግን መንግሥትና ሃይማኖት አንዱ በአንዱ ጣልቃ አይገባም የሚለውን መርህ (secularism) ስለምቀበል አይደለም ። ፈጽሞ ። የሰው ልጅ ራሱን ከዋሻቸው ውሸቶች ትልቁ ይህ ሳይሆን አይቀርም ብዬ አስባለሁ ። ለዚያ ካደረሰን በሌላ ጽሑፍ ለማሳየት እንደምሞክረው “በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ አልገባም” የሚለው መንግሥት በብዙ መንገድ ራሱን የሰዉ እምነቶች ላይ መጫኑ እና ክርስቲያኖችም ሆኑ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የሚናዘዟቸውን እምነቶች መኖር የሚፈቀድላቸው መንግሥት በሕግ ያሰመረውን መንገድ እስካልተላለፉ ድረስ ብቻ መሆኑ ሐቅ ነው ። ይህም በእኛም ሆኑ በሌሎች ሀገራት ቤተ ክርስቲያንን የሥልጣን መሣሪያ ለማድረግ የሚደረገው ሥውር እጅ መጠምዘዝ እና ግልጽ ጣልቃ ገብነት ባይኖር ብለን አስበን ነው ፤ ከመርሑ በግልጽ የተቃረነ ስለሆነ ማለት ነው ። በመንግሥት እና በቤተ ክርስቲያን መካከል በግልጽ የተሠመረ ድንበር ኖሮ ሁለቱም ያን ድንበር ሳያቋርጡ ግን ደግሞ ህልውናቸውም ምንም ያህል ሳይሸራረፍ ይኖራሉ የሚለው እሳቤ ቅዠት ነው ።
ይልቁንም ይህን የምለው ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና ታሪክ ጋር የሚጋጭ ስለሚሆን ነው ። ክርስትና አረመኔ በነበረው የሮም ሀገረ ንጉሥ ውስጥ መጀመሩን እና ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል በስደት እና በሰማዕትነት መኖሩን አልዘነጋም ። የግብጽ ክርስቲያኖችም ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ በሙስሊም መንግሥት ሥር መተዳደራቸውንም እንዲሁ ። የክርስቲያኖች ተልዕኮ በምንም ሁኔታ ውስጥ ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ መኖር ነው እንጂ ምድራዊ የበላይነትን ማስፈን እና ማስጠበቅ አይደለም ። እንዲያውም አንዳንዴ ክርስቲያን ያልሆኑ መንግሥታት ቤተ ክርስቲያን ላይ ከሚያደርሱት ጥፋት ክርስቲያን ነን ባይ መንግሥታት የሚያደርሱት ጥፋት በእጅጉ ይልቃል ። ከውጭ በአዋጅ የመጣውን ያዩታል ፣ ይጋፈጡታል ። ከውስጥ ሆኖ የሚፈልገውን ሁሉ በክርስትና ስም የሚያደርገው ግን የበለጠ ይፈትናል ።
በዘመናችን ደግሞ ከዚህም በላይ ፈተና የሆነብን “በእግራችሁ ወደ ፈለጋችሁት ሒዱ ፣ የተሳፈራችሁበትን ባቡር ግን እኔ ወደምፈልገው እነዳዋለሁ ፥ እናንተን አይመለከታችሁም ።” የሚለን “ዘመናዊ” ሥርዓተ መንግሥት ነው ።

## አማርኛ ምንጮች

መንግሥቱ ለማ ፣ *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ* (1959)

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ፣ *ትግላችን ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ የትግል ታሪክ ፥ ቅጽ 1* (ፀሐይ አሳታሚ ድርጅት ፣ 2004)

*ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ፣ ዳግማዊ ምኒልክ ፥ የአዲሱ ሥልጣኔ መስራች* (ያልታተመ ረቂቅ)

ቃለአብ ታደሰ ፣ *ሕገ መንግሥት በኢትዮጵያ ከፍትሐ ነገሥት እስከ ኤፌዴሪ ፣ (ሜጋ አሳታሚ እና ማከፋፈያ ፣ 2011)*

ተመስገን ገብሬ ፣ *ሕይወቴ* (2001)

ተስፋዬ መኮንን ፣ *ይድረስ ለባለታሪኩ* (2010)

*የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯* ፣ (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 1987)

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት* (1980)

እምሩ ኃይለ ሥላሴ (ልዑል ራስ) ፣ *ካየሁት ከማስታውሰው* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ፣ 2008)

## እንግሊዝኛ ምንጮች

Frank, Joseph, *Dostoevsky: The Miraculous Years (1865-71)* (Prinston University Press, 1995)

Markakis, John. *Ethiopia: The Last Two Frontiers* (James Currey, 2011)

Levine, Donald. *Wax and Gold: Tradition and Innovation in Ethiopian Culture* (Chicago University Press, 1974),

Bahru Zewdie, *The Quest for Socialist Utopia: The Ethiopian Student Movement* (James Currey and Addis Ababa University Press, 2014),

Abir, Mordecai. *Ethiopia and the Red Sea: The Rise and Decline of the Solomonic Dynasty and Muslim– European Rivalry in the Region* (Frank Cass and Co. Ltd., 1980)

Florovsky, Georges. “Revelation and Interpretation” *Bible, Church, Tradition: An Eastern Orthodox View*, (Nordland Publishing Company, 1972)

ኤማሁስ ፕሬስ

EMMAUS PRESS